የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

# መጽሐፈ አርጋኖን

## የእመቤታችን ምስጋና

(በአማርኛ)




## የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ድርሰት

(በ14ኛው ክፍለ ዘመን የተደረሰ)

www.ethiopianorthodox.org

# አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና
## ዘሰኑይ
## ክፍል ፩

፩. ባለመለየት ሶስት ፣ በተዋህዶ በአኗኗር (ባነዋወር) አንድ በመለኮት ትክክል ከሰውና ከመላእክትም ዘንድ አንድ ስግደት በሚሰገድለት በእግዚአብሔር ስም አምነን ይህንን አርጋኖን የሚባል የምስጋና መጽሐፍ እንጽፋለን፡፡

፪. ይኸውም የምስጋና መሰንቆ የቅዳሴም እንዚራ፡፡ አምላክን የወለደች በዕብራይስጥ (ማሪሃም) የተባለች መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን የምታሰጥ የእመቤታችን የማርያምን ድንግልናዋን የማድነቅ መጽሐፍን እንጽፋለን፡፡

፫. ክብሯንና ገናንነቷንም የመናገር ስሟንም የማክበር ቅድስናዋንም የማመስገን ለንግሥትነቷም መገዛት እንዲገባ የሚናገር መጽሐፍን እንጽፋለን፡፡

፬. አምላክን የወለደች እመቤታችን ይኽችውም የወርቅ መሰላልናት ከሚያሰጥመውም ባሕር ማዕበል ሞገድ የተነሣ የማትነቀንቅ፡፡

፭. መልኅቆቿም በሦስቱ ሥላሴ የተሸረቡ ገመዶች ናቸው አይቈረጡም (ይኽውም) ይኽችውም ደግሞ ከነፋሳት ኃይል የተነሣ የማትነቀንቅ በጭንጫ ላይ ያለች የዕንቁ ባሕርይ ምሰሶ ናት፡፡ እርሷንም የተጠጋ መውደቅ መሰናከል የለበትም፡፡

፮. አቤቱ የልቡናየን ደጅ ክፈት መንፈሳዊው ርግብ መንፈስ ቅዱስ በየዋህነቷ በርግብ ስለ ተመሰለችው የእመቤታችንን ምስጋና ኃይለ ቃሉን ያሳስበኝ ዘንድ እንዲገባ፡፡

፯. አቤቱ የጆሮየንም መስኮት ክፈት ከመንፈስ ቅዱስ እንደበት የሚሰማውን የድንግልን የምስጋናዋን ሹክሹክታ ያደምፅ ዘንድ፡፡

፰. አቤቱ ሆይ ያይኔን ጽጋግ ግለጽ የብርሃን እናቱ የምትሆን የእመቤታችንን ምስጋና ምሥጢሩን አመለከት ዘንድ፡፡

፱. ዳግመኛም እንደበቴን ክፈት አቤቱ ለእግዚአብሔር እናት እመቤታችን ለድንግልናዋ ምስጋና፡፡

፲. የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ያቃጠለውን የኦሪትንና የነቢያትን መጻሕፍት ቃል አጽፎ እስኪጨርስ ድረስ ዓርባ ቀን ሙሉ ሳይሰወርበት የዕዝራን እንደበት የገለጽህ ሆይ እኔንም ደግሞ እንደሱ እርዳኝ፡፡ የአብ ሙሽራ የምትሆን የእመቤታችንን ምስጋና ለመጻፍ እንድጀምር ዕዝ ፣ ፯ ፣፯፡፡

፲፩. ጀምሮ ከመተው አድነኝ አቤቱ እርሱንም ለመፈጸም አሰልጥነኝ ከንፈሮቼንም እንደ በገና አድርጋቸው ለሚሰሙት ያማረውን የተወደደውን ምሥጢር እንዲናገሩ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይቃኛቸው፡፡

፲፪. አንደበቴን እንደ መሰንቆ አድርገው በጎውንም ያማረውን የተወደደውን ዘፈን እንዲያቀነቅን የመንፈስ ቅዱስ ድኅነ ይደርድረው የሚያዳምጡትም እርሱን በመስማት ፈጽመው ደስ ይሰኙ፡፡

፲፫. ሐሳባቸውም ወደታች ያይደለ ወደላይ ይመሰጥ ጽድቅንም ያስቡ፡፡ ኃጢአትን ያይደለ ጽድቅን

www.ethiopianorthodox.org

ያስቡ ርኩሰትን ያይደለ ንጽሕናን ያስቡ፡፡

፲፬. የዋህነትንም ያስቡ፡፡ ሽንገላን ያይደለ፡፡ ትሕትናንም ያስቡ፡፡ ትዕቢትን ያይደለ ፍቅርንም ያስቡ፡፡ ቅንዓትን ያይደለ፡፡

፲፭. ልባምነትንም ያስቡ፡፡ ስንፍናን ያይደለ፡፡ ክብርንም ያስቡ፡፡ ጉስቁልናን ያይደለ፡፡ የሰማዩን ያስቡ፡፡ የምድሩን ያይደለ፡፡ የማያረጀውን ያስቡ፡፡ የሚያረጀውን ያይደለ፡፡ የማይጠፋውን ያስቡ፡፡ የሚጠፋውን ያይደለ፡፡

፲፮. ይህንንም መጽሐፍ የሚያነብ ሁሉ አንደበቱ በመንፈስ ቅዱስ ጨውነት የተጣፈጠ ከማርም ወለላና ከሦከር ምንጭ ይልቅ የጣፈጠ ይሁን፡፡

፲፯. በዚች ጸሎት የሚጸልይ ሁሉ የሕይወት እሳትን በሚዳስስ እጅሽ በረከት የተባረከ ይሁን፡፡ የመንፈስ ቅዱስ መዓዛም በተዋሀደው አንደበትሽ የተመረቀ ይሁን፡፡

፲፰. ዓምንም ሁሉ በያዙ በሥላሴ እጅ የተባረከ ይሁን፡፡ ጸሎቱም ነገር በማብዛት የሚሰማቸው እንደሚመስላቸው እንደ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ጸሎት አይሁን፡፡ ማቴዎስ ፣ ፮ ፣ ፯ ፣ ፳፫ ፣ - ፲፬፡፡

፲፱. ባባቱ ጆሮ በለኆሳስ እንደሚናገር እንደተወደደ እንዳንድ ልጅ ነገር ይሁን እንጂ፡፡ አባቱም የልጁን ነገር በደስታ ለመቀበል ጸጥ ብሎ እንደሚሰማው፡፡ እንደሚያዳምጠውም፡፡ እንዲሁ ደግሞ የሁሉ ጌታ እግዚአብሔር በዚች ጸሎት የሚጸልየውን ሰው ልመናውን ይስማ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፪</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ እመቤታችን የተመረፅሽ ድንግል ማርያም ሆይ ፣ አንቺም ደግሞ ዐመፀኛው በደለኛው ኀጥኡ እኔ በዚች ጸሎት በጸለይሁ ጊዜ ወደ አንደበቴ ነገር ጆሮሽን ዘንበል አድርገሽ ስሚ፡፡ ሰምተሽም ቸል አትበይ፡፡ በብሩህ ልቦና በንጹሕ አሳብ ያንደበቴን ነገር ተቀበዬው እንጂ፡፡

፪. ስለኃጢአቴም ብዛት የከንፈሮቼን ድካም እንደ ተናቀ ምናምን ነገር አታድርጊው፡፡

፫. እመቤቴ ሆይ ወርቅና ብር የማቀርብልሽ አይደለም፡፡ የሚያበራውን ዕንቁም የማቀርብልሽ አይደለም፡፡ ያማረውን የተወደደውን ምስጋና ለገናንነትሽ የሚቀርበውን ንጹሑን ውዳሴ ነው እንጂ፡፡

፬. ንግሥት ሆይ የከበረውን ልብስ በፍታውን ነጭ ሐሩን የወርቅ የዕንቁ ጌጥ ፈርጥ ያለበትን ብሩሁን ልብስ የማቀርብልሽ አይደለም፡፡ በወርቅና በዕንቁ ስለተሠራው ክቡር ልብስሽ ነፍሴንና ሥጋየን በፊሽ እዘረጋለሁ እንጂ፡፡

፭. የታላቁ ሊቀ ካህናት እናት ሆይ ኃጢአቴን ላንቺ እናዘዛለሁ ከዚህ ዓለም መቅሠፍት ከምድራዊም ጥፋት መሸሻ አንቺን አገኘሁ፡፡

፮. በኃይል ከሚነጥቁ በቅሚያም ከሚገሉ ከዓረብ አንበሶች መሸሻ አንችን አገኘሁ አውሮቹን ይነጥቃሉ ለጠቦቶቹም አይራሩም፡፡ አሮጊቶቹንም አይምሩም ሁልጊዜም ለመዋጥ አፋቸው የተለቀቀ ነው፡፡

፯. ለነገም ከማያሳድሩ ከዓረብ ተኩላት መሸሻ አንችን አገኘሁ፡፡ አውራውን ይነጥቃሉ ጠቦቲቱን አያስቀሩም ለእናቲቱም አይራሩም ለጠቦቱም አያዝኑም፡፡

፱. ከሰይፍ ስለት ከጦር ሐፎት ከፀብ ክርክርም ሁሉ ከፀብም መሣሪያ ሁሉ መሸሻ አንቺን አገኘሁ ከፀላቶቼም እጅ መሸሻ ሰውነቴንም ከሚጠሏት ሁሉ እጅ መሸሻ አንቺን አገኘሁ፡፡

፲. በስምሽ ያመነውን ማን ያስፈራዋል፡፡ በልጅሽስ ያመነውን ማን ያስፈራዋል፡፡ ያንበሳም ጩኸት እንደ ውሻ ጩኸት ይመስለዋል፡፡ የነብሮቹም ኃይል እንደ ድመት ድካም ነው፡፡

፲፩. ፈረስም ቢሮጥ አይደርስበትም ጦርም ቢወረወር አያገኘውም የፍላጻም ሐፎት አይቈነጥጠውም በደንጊያም መወገር ነፋስ እንደሚበትነው ትቢያ ይመስለዋል፡፡

፲፪. የፈሳሽ ውሀም ማዕበል ሞገድ አይበረታታበትም የነፋሳትም ኃይል አያነዋውጠውም የሰውም አንደበት ክፉ ሊያደርግበት አይችልም፡፡ ያመፀኛ ከንፈርም አይጐዳውም በተዋቀሰው ጊዜ ልጅሽ ድል አያስነሣውምና፡፡

፲፫. ይህንንም ሁሉ ዐውቄ ለመረዳቴ አንችን (እሻሁ) ባንችም በልጅሽም በኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ፈጽሜ ደስ ተሰኘሁ፡፡

፲፬. ፍርቅሽም በሰውነቴ አዳራሽነት ፈጽሞ ተዘረጋ እጅግም ከፍ ከፍ አለ በዛም፡፡ እንደ ወንዝ ፈሳሽም መላኝ እንደ ግዮን ወንዝ በክረምት ጊዜ እንደ ጤግሮስም ፈሳሽ ባዝመራ ጊዜ፡፡ እንደ ኤፍራጥስም ወንዝ በሸት ጊዜ፡፡ እንደ ኤፌሶንም ፈሳሽ በጮርቃ (እንጭጭ) ጊዜ፡፡

፲፭. ጉምም በምድር ላይ እንዲጐተት ደመናም በአየር ላይ እንዲረብ እንዲሁ በኔ ዘንድ ሆነ፡፡

## ምዕራፍ ፫ ክፍል ፪

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ እንቺም በተድላ በደስታዬ ጊዜ ሽልማት ሆንሽኝ፡፡ በኃሤትም ጊዜ ክብ ዘውዴ ሐቲም ቀለበቴ ነሽ፡፡

፪. በሐሳቤም ሁሉ አንቺን አደንቃለሁ፡፡ እንዲህም እላለሁ፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ምን ያህል ጸጋ ክብር ሰጠ፡፡

፫. እግዚአብሔር ከሰው ልጅ የማይተባበሩ ሥስት ልደታትን ተወለደ፡፡ እኔም ዐውቄ አደነቅሁ፡፡ ባራተኛው እንጂ የበጎ ዕረፍት አላገኘሁም፡፡

፬. አዳም ከሕቱም ምድር የተወለደ በተፈጥሮ ነው፡፡ እኔን ግን የጠቀመኝ የለም፡፡ ሔዋንም ከአዳም ግራ ጐን ተወለደች እርሷም በተፈጥሮ ነው፡፡ ለኔ ግን የጠቀመችኝ የለም፡፡

፭. ቃየልም እንደ ሰው ሁሉ በዘር በሩካቤ ተወለደ የጠቀመኝ የረባኝ የለም፡፡ ስንኳን እኔን እራሱንም አልጠቀመም፡፡ እሊህ ሦስቱ ልደታትም ለማንም ለማን አይረቡም አይጠቅሙም፡፡

፮. ክርስቶስ ግን ያለዘር ያለሩካቤ ከድንግል ተወለደ ለሁሉ የሚረባ የሚጠቅም ሆነ፡፡

፯. ለዚህ ልደት መስገድ መገዛት ይገባል፡፡ ክብር ምስጋና ለዚህ ልደት ይገባል ጌትነትና ገናንነት ኀያልነት ፣ አዚዝነት ፣ እልልታ ፣ ግርግታ ለዚህ ልደት ይገባል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፰. ይህ ጥበብ ፍልስፍና ዕጹብ ድንቅ ነው፡፡ ለዚህ አንክሮ ይገባል ይህም የሥጋዊ ምሥጢር ምን ይረቅ ምን ይጠልቅ፡፡ ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡ ይህም ሰው መሆን ሥጋ መልበስ እጅግ ዕፁብ ድንቅ ነው፡፡

፱. የሐዋን ደኅንነቷ እመቤታችን ሆይ የድንግልናሽ ኃይል እጅግ የሚያስደንቅ ዕጹብ ነው፡፡

፲. የአዳምን መርግመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ያጠፋሽለት እመቤታችን ሆይ የማይመረመር ረቂቅ ምሥጢር ባንቺ ተደረገ፡፡

፲፩. እሳትና ውሀም ባንድነት ተስማምተው መኖራቸው እጅግ ድንቅ ነው የሚያስራውንም ያንበሳ ደቦል ፀዓዳ በግዕት በክንዷ እጅግ ድንቅ ነው፡፡

፲፪. ከድንግልም ብላቴና ጡቶች ወተት መፍሰስ እጅግ ድንቅ ነው፡፡ በበረትም ለድኆች ልጅ የሰማይ ሠራዊት መስገድ እጅግ ድንቅ ነው፡፡

፲፫. ዓለምን ሁሉ የመላ አምላክም ከበረት ተጥሎ በጨርቅ ተጠቅሎመገኘቱ እጅግ ድንቅ ነው፡፡ በረት ከጽርሐ አርያም ቁመት ረዘመ ከሰማይም ዳርቻ ሰፋ፡፡

፲፬. ሕዝቅኤል ካየው ሠረገላ ዳንኤልም ካየው ኪሩባዊ ዙፋን በረት በለጠ፡፡ ይኽውም አደፍ ጉድፍ ሳይኖርበት ንጽሕት የወለደችው ንጹሕ በግ ነው፡፡ በረት ለንጹሑ መሥዋዕት ሽታ መሰብሰቢያ ሆነ፡፡

፲፭. ሰማይና ምድር የማይወስኑትን በረት ቻለው ወሰነውም፡፡ በረት የተመሰገነ ነው፡፡ የኃያላን ጌታ በውስጡ ተገኝቷልና፡፡

## <u>ምዕራፍ ፬</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለች እመቤታችን የተመረፀች ድንግል የሰማዩን ሠራዊት አሰገደቻቸው፡፡ የዓለም ጌጽ ሽልማት የሁሉ አባት የሚሆን መላእክትን የፈጠረ ጌታ ከርሷ ተወልዷልና፡፡

፪. በረት ተመሰገነ ምድርን በውሃ ላይ ያጸናት እርሱ ስለተጠጋባት ድንግልም የመላእክትን አለቆች ገዛቻቸው በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ እሱ በማኅፀኗ ስላደረ፡፡

፫. በረት ኪሩቤል እንደሚሸከሙት ዙፋን ሆነ ስፍራውም እንደ ጽርሐ አርያም ድንግል እንደ አብ ሆነች አንድ ልጅም በጎል ተጥሎ በጨርቅ ተጠቅሎ ተገኘ፡፡

፬. ዮሴፍና ሰሎሜ በወዲህና በወዲያ ላምና አህያም በወዲህና በወዲያ በበረቱ ጐንና ጐን ባራቱ ማዕዘን በዙፋኑ ቀኝና ግራ በጐንና በጐኑ አራቱ እንስሶች እንዳሉ፡፡

፭. የሰማይ ሥርዓት በምድር ላይ ተሠራ፡፡ ቤተ ልሔም ሰማይን መሰለች ስለ ፀሐይም በቅዱሳን ላይ የሚያበራ ለዘወትርም ጨለማ የማይቃወመው ኅልፈት ጥፋትም የሌለበት ዕውነተኛ ፀሐይ በውስጧ ተገኘ፡፡

፮. የብርሃኑም ክበብ መምላትና መጉደልን ስለሚያፈራርቅ በጨረቃ ፈንታ በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለች የድንግልናዋም ምስጋና በሁሉ የመላ ነው፡፡ ለዘወትርም የማይጐድል እመቤታችን የተመረፀች ድንግል ማርያም ተገኘች ስለ ከዋክብትም መላእክተ ብርሃን ታዩ፡፡

፯. ወደዚህ ማኅበር አንድነት እኖር ዘንድ ማን በከፈለኝ ከመላእክት ጋር እንዳመሰግን ከዋላጅቱም ጋር እንዳደንቅ ከእርኛችም ጋር እንዳገለግል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፰. በረቱንም  እጅ እነሣ ዘንድ ማን በከፈለኝ የሙታን ሕይወት የኃጥአንም ንጸሕና የቅቡፃን ተስፋ የተጨነቁትንም የሚያድን ጌታ ወደተቀመጠበት፡፡

፱. የዓለም ሁሉ መድኃኒት የምትሆን ብላቴና እግሯ የተመላለሰበቱን ምድር እስም ዘንድ ማን በከፈለኝ፡፡

፲. ይቅርታን የምታሰጥ ብላቴና ጥላዋ ይነካኝ ዘንድ ማን በከፈለኝ፡፡ የብርሃን ልጅ ወደ ሄደችበት እከተላት ዘንድ ማን በከፈለኝ የእግሯንም ጫማ እሸከም ዘንድ ማን በከፈለኝ፡፡

፲፩. አሁንም ያን ጊዜ በዕብራይስጥ ማሪሃም ከተባለች ከተመረጠች ድንግል ማርያም ጋራ ያን ጊዜ ካሉት አላንስም ሀሳቤን ከዚያ እንዳለሁ አድርጌ አለሁና፡፡

፲፪. በስጋ አልነበርሁም በመንፈስ ግን አለሁ፡፡ ባነዋወር አልነበርሁም በሃይማኖት ግን አለሁ በገጽ አልነበርሁም በማመን ግን አለሁ፡፡

፲፫. ሳልኖር እራሴን እንዳለሁ ያረደረግሁ እኔ የተመሰገንሁ ነኝ ጌታችን በወንጌል እንደተናገረ እንዲህ ሲል ሳያዩኝ የሚያምኑብኝ ግን የተመሰገኑ ናቸው፡፡

፲፬. እኔ ባሪያህ ስለሃይማኖቴ የተመሰገንሁ ነኝ፡፡ ስለ ዕውነቴ አይደለም ስለ መረዳቴም የተመሰገንሁ ነኝ፡፡ ስለ ንጽህናዬም አይደለም በእግዚአብሔር ስም ስለ አመንኩ የተመሰገንሁ ነኝ፡፡ በናቱም ጸሎት ስለ አመንሁ ንዑድ ክቡር ነኝ፡፡

## ምዕራፍ ፭ (ክፍል ፩)

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ እመቤቴ የተመረፅሽ ድንግል ማርያም ሆይ የጸሎትሽ ረዳትነት ጋሻ ጦር ይሆነኝ ዘንድ ወደአንቺ እማልዳለሁ፡፡

፪. የልጅሽ የልዑል ክንዱ ኃይል ለማዳን ይውረድ ተራሮችን የሚፈትታቸው ኃይል በረድኤት ወደኔ ይምጣ፡፡ ጠላቶቼን ይገለብጣቸው ዘንድ፡፡

፫. ሰማዩን እንደ ክርታስ የሚጠቀልለው ኃይል በረድኤት ወደኔ ይምጣ የሚጠላኝን ያስጨንቀው ዘንድ ምድርን የሚያነዋውጥ ባሕርንም የሚዳስስ ኃይል ይምጣ ጸላቶቼን ይዋጋቸው ዘንድ፡፡

፬. በሌጌዎን አጋንንት የሪያዎቹን መንጋ ያሰጠመ ኃይል ይምጣ ሰውነቴን የሚከራከሯትን ያሰጥማቸው ዘንድ፡፡ ጉሙንም እንደ አመድ የሚበትነው ኃይል የኔን ፀብ ክርክር የሚወዱትን ይበትናቸው ዘንድ፡፡

፭. የሚመርቁኝ የተመረቁ ይሁኑ፡፡ የሚረግሙኝ ግን ይረገሙ በልጅሽ አንደበት ሰይፋቸው ወደልባቸው ይመለስ ቀስታቸውም ይሰበር ይሰባበር፡፡

፮. ድካማቸውም ወደ ራሳቸው ይግባ ዓመፃቸውም በራሳቸው ላይ ይውረድ የሚከቡኝን ራስ የከንፈራቸው ድካም ይክደናቸው፡፡ የእሳትም ፍም በላያቸው ይውደቅባቸው እንዳይነሱም  መቆምም እንዳይችሉ በመከራ ይጣላቸው፡፡ መዝሙር ፻፵ ፣፱ ፣፲፡፡

፯. እንደ ምድያምና እንደ ሲሳራ እንደ ኢያቢስም  በቂሶን ወንዝ አጠገብ  እንዳደረግህ እንዲሁ አድርግባቸው በአንዶር እንደ ጠፉት፡፡ የእርሻም ፋንድያ እንደሆኑት፡፡ አለቆቻቸውን እንደ  ሄሬብና እንደ ዜብ፡፡ ታላላቆቻቸውን እንደ ዛብሂልና እንደ ስልማና አድርጋቸው፡፡ የእግዚአብሔርን ማደሪያ እንወርሳለን እንዳልት አምላኬ እንደ ትቢያ በነፋስ ፊትም  እንደገለባ  አድርጋቸው፡፡ በዱርም

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

እንደሚቃጠል እሳት ተራሮችን እንደሚያነድ ነበልባል፡፡ እንዲሁም በዓውሎ ነፋስህ አሳዳቸው በቁጣህም አስደንግፃቸው፡፡ ፊታቸውንም ኃፍረት ጉስልና ምላው፡፡ አቤቱ ስምህን ያውቁ ዘንድ ይፈሩ ለዘለዓለምም ይታወኩ ይደነግጹና ይጥፉ፡፡ መዝሙር ፹፫ ፣ ፱ - ፲፯ ፡፡

፱. ማዕዳቸው በፊታቸው ወጥመድ ትሁንባቸው ደኅንነታቸውም ለአሽክላ፡፡ ዓይኖቻቸውም እንዳያዩ ይጨልሙ፡፡ ወገባቸውም ሁልጊዜ ይናወጥ በላያቸውም መዓትህን አፍስስ የቁጣህም ትኩሳት ይያዛቸው አገራቸውም ምድረ በዳ ትሁን በቤታቸውም የሚኖር አይገኝ፡፡ ከተሞቻቸውም በእሳት ይቃጠሉ በኃጢአታቸውም ላይ ኃጢአት ጨምርባቸው፡፡ ወደ ጽድቅህም አይግቡ፡፡ ከሕያዋን መጽሐፍ ይደምሰሱ፡፡ ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ፡፡ መዝሙር ፷፱ ፣ ፳፪ - ፳፰፡፡

፲. ግፍ የሚያደርጉትን አትማራቸው፡፡ ማታ ይመለሱ፡፡ እንደ ውሾችም ያንጐራጉሩ፡፡ ባገርም ይዙሩ፡፡ አምላኬ በፀለቶቼ ደስ ያሰኘኛል፡፡ ሕግህን እንዳይረሱ አትግደላቸው፡፡ አቤቱ በኃይልህ አቅበዝብዛቸው፡፡ አዋርዳቸው፡፡ አንተ ጋሻችን ስለ አፋቸው ኃጢአት ስለ ከንፈራቸውም ነገር መርግምንና ሐሰትን ስለ ተናገሩ በትዕቢታቸው ይፀመዱ በቁጣህ አጥፋቸው ከንቱም እንዲሆኑ አጥፋቸው፡፡ መዝሙር ፶፱ ፣ ፭ -፲፫ ፡፡

፲፩. ኃጢአተኛውን በላያቸው አቁምባቸው በቀኛቸውም ሰይጣን ይቁም፡፡ መዝሙር ፻፱ ፣ ፮ ፡፡

፲፪. በተሟገቱም ጊዜ ተረትተው ይውጡ ጽሎታቸውም ኃጢአት ትሁንባቸው፡፡ (ቁጥር ፯ ፡፡)

፲፫. ዘመናቸውም ጥቂት ይሁን ሹመታቸውንም ሌላ ይውሰዳት፡ (ቁጥር ፰ ፡፡ )

፲፬. ልጆቻቸውም አባት እናት የሌላቸው ይሁኑ፡፡ ሚስቶቻቸውም መበለታት ይሁኑ፡፡ (ቁጥር ፱ ፡፡)

፲፭. ልጆቻቸውም ተቅበዝብዘው ይዙሩ ይለምኑ፡፡ ከቤታቸውም መፈታት የተነሣ ተሰደው እንጀራ ይፈልጉ ቁጥር ፲ ፡፡

፲፮. ባለእዳም ያለውን ሁሉ ይበርብረው፡፡ የደክመበትንም ገንዘቡን ሌሎች ይውሰዱት፡፡ (ቁጥር ፲፩ ፡፡)

፲፯. ከዚያም ወዲያ ምሕረት የሚያደርግለት ሰው አያግኝ፡፡ ለተጣሉትም ልጆቹ ማንም አይራራላቸው ፡፡ (ቁጥር ፲፪ ፡፡)

፲፰. ልጆቹ ይነቀሉ፡፡ ይቆረጡም በሁለተኛውም ትውልድ ስማቸው ይደምሰስ፡፡ (ቁጥር ፲፫ ፡፡)

፲፱. ያባቶቻቸውም ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ትታሰብ፡፡ የናቶቻቸውም ኃጢአት አትጥፋ፡፡ (ቁጥር ፲፬ ፡፡)

፳. በእግዚአብሔር ፊት ሁል ጊዜ ትኑር መታሰባቸውም ከምድር ይጥፋ፡፡ (ቁጥር ፲፭ ፡፡)

፳፩. መርገምን ወደ‌ልና ትምጣበት፡፡ በረከትንም አልወደደምና ከርሱ ትራቅ፡፡ (ቁጥር ፲፮ ፡፡)

፳፪. መርገምን እንደ ልብስ ይል በሱ፡፡ እንደ ውሀም ወደ ውስጣቸው ትግባ፡፡ እንደ ዘይትም ወደ አጥንታቸው፡፡ (ቁጥር ፲፯ ፡፡)

፳፫. እንደሚለብሰው ልብስ ዘወትር እንደሚታጠቀውም ድግ ትሁንበት፡፡ (ቁጥር ፲፱ ፡፡)

www.ethiopianorthodox.org

፳፬. ለጸላቶቼና በነፍሴ ላይ ክፉ ለሚናገሩት ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋቸው ይህ ይሁን፡፡ (ቁጥር ፳ ፡፡)

፳፭. ቁም አቤቱ በቁጣህ በጻለቶቼም ላይ  በመዓት ከፍ ከፍ በል፡፡

፳፮. አቤቱ የሚጣሉኝን ተጣላቸው የሚዋጉኝንም ተዋጋቸው፡፡

፳፯. ጋሻና ጦር ያዝ እኔንም ለመዳት ተነሣ፡፡ (ቁጥር ፪ ፡፡)

፳፰. ጦርህንም  ነቅንቅ፡፡ ያሳዳጆቼንም መንገድ ዝጋባቸው፡፡ ነፍሴንም እኔ ረዳትሽ ነኝ በላት፡፡ (ቁ.፫ ፡፡)

፳፱. ነፈሴንም የሚሹ ሁሉ ይፈሩ ይጐሳቈሉም፡፡ ለክፋቴም የሚያስቡ ወደ ኋላቸው ይመለሱ ይፈሩም ቁ ፬ ፡፡

፴. በነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ ይሁኑ የእግዚአብሔርም መልአክ ያባራቸው፡፡ (ቁ ፭ ፡፡)

፴፩. መንገዳቸው ጨለማና ድጥ ይሁን፡፡  የእግዚአብሔርም መልአክ ያሳዳቸው፡፡ (ቁ ፮ ፡፡)

፴፪. በድንገት ሞት ትምጣባቸው እርሳቸውም የሰወሯት አሽክላ ትያዛቸው፡፡ ለጥፋታቸውም ይውደቁባት፡፡ (ቁጥር ፰ ፡፡)

፴፫. ነፍሴ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይበላት በማዳኑም ሐሤት ታድርግ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፮  ክፍል  ፬</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለሽ የተመረፅሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ አንቺም ደግሞ  በጸላቶቼ አንገት የብረት ዛንጅር አግቢባቸው፡፡

፪. የመለከታቸውንም ድምፅ አክብጅው ደንቆሮም አድርጊው፡፡ እርሳቸውንም በቀፎ በቅርጫት  በእግር ብረት እሠሪያቸው፡፡

፫. በእግራቸው ወጽመድ በከንፈራቸው ልጓም ባፍንጫቸው ጉንፋን (ፋሮ) ላኪባቸው፡፡

፬. ሊሄዱበትም ወደ አልፈቀዱት መንገድ መልሻቸው፡፡ በልቡናቸውም ፍርሃትን መንቀጥቀጥን አሳድሪባቸው መሸበርንና መንቀጥቀጥንም ጨምሪባቸው እንደ  ሴቶች ይሁኑ፡፡

፭. ከጽኑ ነፋስ ኃይል የተነሣ ዛፍ ሲንቀሳቀስ ቅጠሉ እንዲረግፍ እንዲበተን እንዲሁ ይሁኑ ባባር በቸነፈር እህልን  በማጣት ቅሠፊያቸው፡፡

፮. በሜዳ ሰይፍ ልጆቻቸውን ያጥፋቸው  በቤታቸውም  ውስጥ  ፍርሃት ያስጨንቃቸው፡፡ ዘዳግም ፴፪ ፣ ፳፭ ፡፡

፯. እሳት በረድ ረሀብ ቸነፈር ይፍጃቸው፡፡ ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር የመዓቱ ጽዋ በጸላቶቼ ላይ ይውረድ  ዕድል ፈንታቸው ጽዋ ተርታቸው ይሁን፡፡

፰. የኔ ግን የባሪያሽ እድል ፈንታየ ጽዋ ተርታየ ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ይቅርታ  ከእስራኤልም አምላክ ዘንድ  ፍቅር  ሰላም ይሁን፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፱. ሁል ጊዜም ይጠብቀኝ ዘንድ ልጅሽን አደራ በይልኝ፡፡ በየሰዓቱም በየጊዜውም ሁሉ ከኔ ጋራ ይሁን ስወጣ ስገባ ስቀመጥ ስነሣ የማይተኙ ዓይኖቹ የማያንቀላፉ ሽፋሽፍቶቹ በረድኤት ይጠብቁኝ፡፡

፲. የፀናች ቀኙ ከፍ ያለች ክንዱ ከመሰናክል ትጠብቀኝ ያውም ከኃይል ጋራ፡፡

፲፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ ሕሙማን የሚያርፉብሽ ዕንጨት ሆይ፡፡

፲፪. ፈጽሞ እግዚአብሔር እንደባረከው እንደ ምድረ በዳ ዕንጨት መዓዛ የፍቅር መዓዛሽ ሸተተኝ ልቡናየንም መሠጠው፡፡

፲፫. የተባረክሽ የሕይወት እንጨት ሆይ የፍቅርሽ ሽታ ከሃይማኖት አበባ የተገኘ የሽቱ ፍሬን እንደ ተመላ የገነት ዕንጨት መዓዛ ሸተተኝ፡፡

፲፬. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ ቡርክት የመድኃኒት ዕንጨት ሆይ የፍቅርሽ መዓዛ በቤተ መቅደስ እንደሚታጠን ዕጣን ሽታ ሸተተኝ፡፡ ለፍንጫም ደስ እንደሚያሰኘው ፡፡ ለሸተተውም እንደሚያምረው፡፡

## <u>ምዕራፍ ፯ ክፍል ፫</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ እነሆ የፍቅርሽ መንፈስ አነሣሣኝ፡፡ በዕንጨቶች እመስልሽ ዘንድ፡፡

፪. በእንኮይ ዕንጨት እመስልሻለሁ ወድጄ ከጥላሽ አርፌአለሁና፡፡

፫. የጎቱም ድንግልናሽም አበባ ለፍንጫዬ ሸተተው፡፡ የንጽሕናሽ ፍሬም ለጉሮሮየ ጣመው ፡፡ ከናቱ ከልያ እርሻ ሮቤል እንዳገባው እንኮይ ዋጋ (ዘፍጥ ፣ ፴፬ ፡፡)

፬. የያዕቆብ ልጅ ይሳኮር ተጸነሰ፡፡ የሥሳኮር ስሙ ግን ትርጓሜው የእንኮይ ዋጋ ማለት ነው፡፡

፭. እንዲሁም ሊቶስጥራ በሚባል ስፍራ እይሁድ በጠመቁት በማኀፀንሽ ፍሬ ደም ዋጋ ጌታችን መድኃኒታችን ልጅሽ ከተሞሸረባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሃይምናን ተፀነሱ፡፡

፮. እንግዲህ ደግሞ የዘይት ዕንጨት እልሻለሁ ያቋቋምሽ ደም ግባት አማረኝ ካንቺ የፈሰሰው በለሳን ቅቤም የፊቴ መቀቢያ ሆነ፡፡

፯. የበለስ ዕንጨት ብዬ እጠራሻለሁ አዳም ሰፍቶ መከለያ አድርጐ ዕርቃኑን ስለሠወረበት የበለስ ቅጠል እንዲሁ እኔም ከልጅሽ ጐን ከፈሰሰው ጥምቀት ውሀ ሙሽርነትን ተከደንሁ፡፡ (ዘፍጥ ፫-፯ ፡፡)

፰. የነቢዩም የኤርምያስ ደቀ መዝሙር ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ስለ ለቀመው የበለስ ቅንጣት፡፡

፱. ከመሶብ ውስጥ አኖረው፡፡ ጥቂትም ፈቀቅ ብሎ ከዕንጨት ጥላ ስር ፷፮ ዓመት ተኛ ቢነቃም ዛሬውን ተኝቶ ዛሬውን የነቃ መሰለው፡፡

፲. ሙዳዩንም ከፈተ የበለሱንም ቅንጣት አየ፡፡ ደሙም ሲንጸፈጸፍ አገኘው ከባሮክም ዘንድ በደረሰ

ጊዜ በንስር አንገት አድርጎ ከመልእክት መጽሐፍ ጋራ ወደ ነቢዩ ኤርምያስ ዘንድ ላከው ተማርከው በባቢሎን ለሚኖሩ ሕሙማን ፈውስ መድኃኒት ሊሆን፡፡

፲፩. እንዲሁም በድንግልናሽ ወተት ያደገው የሆድሽ ፍሬ ደም ሲንጸፈጸፍ ተገኘ፡፡ በሲኦል ለነበሩ ለጽዮን ምርኮ ቁስለኞች ፈውስ መድኃኒት ሊሆን ተሰጠ፡፡

፲፪. የሎሚ ዕንጨት ብየ እጠራሻለሁ፡፡ ሎሚ ያማረ የተወደደ አበባ ያብባል መልካሙን ፍሬ ያፈራል፡፡ በጎ በጎ ይሸታል፡፡

፲፫. የክህነት ዕፃ እንደወጣበትም ደረቅ በትር ሳይተከል በቤተ መቅደስ ለምልሞ አፅቅ አውጥቶ አብቦ ተገኘ፡፡ ሽታው ያማረ የተወደደውን ሎሚ አፈራ፡፡ ( ዘኍልቁ ፲፯ ፣ ፰ ፡፡)

፲፬. እንዲሁም አንቺ በቤተ መቅደስ ዐሥራ ሁለት ዓመት ተቀመጥሽ፡፡

፲፭. ያለዘርና ያለሩካቤም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፀነሽው ፡፡ (ማቴዎስ ፩ ፣ ፲፰ ፡፡)

፲፮. በሱፍ ዕንጨት እመስልሻለሁ የሱፍ አበባ በሾህ የተከበበ ነው፡፡ አንቺም ከዳዊት ሐረግ የተገኘሽ ንጽሕት አበባ የዳዊት ግንድ አጽቅ ስትሆኚ አንገተ ደንዳና በሚሆኑ በእስራኤል ቆነጃጅት መሐከል እንደነበርሽ፡፡ እርሳቸውም ነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት የተናገረባቸው እንዲህ ሲል፡፡

፲፯. በጉስቁልናቸው የሚመኩ አንገታቸውን የሚያደነድኑ በዓይኖቻቸው የሚጠቃቀሱ፡፡ የልብሳቸውን ዘርፍ የሚጐትቱ፡፡ የሚዘፍኑትን የጽዮንን ልጆች ቈነጃጅት አለቆች እገዚአብሔር ያዋርዳቸዋል፡፡ ያጐሳቊላቸዋል ብሎ፡፡ (ኢሳይ ፫ ፣ ፲፮ ፣ ፲፯፡፡)

፲፰. እንግዲህ ደግሞ የወይን ሐረግ ብዬ እጠራሻለሁ የሆድሽ ፍሬ ያማረ የተወደደ ነውና፡፡ የድንግልናሽ ፍሬ የደሙ ጥማቂ ያማረ የተወደደ ሆነ፡፡

፲፱. በእንጆሪ በጅብራ በደደሆ እመስልሻለሁ፡፡ የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ለሙሴ በርሱ ላይ ሆኖ ታይቶታልና፡፡ ከፈርዖንም ባርነት ነፃ መውጣት ያስተምራቸው ዘንድ ወደ እስራኤል ልጆች ላከው፡፡ (ዘፍጥረት ፫ ፣ ፪ ፣ ፮ - ፯ ፡፡)

፳. ካንቺ የተገኘ የልዑል እግዚአብሔር አካላዊ ቃል ግን ሐዋርያትን ወደ ዓለም ሁሉ ዳርቻ ላከቸው፡፡ ከሰይጣን ባርነት ነፃ መውጣትን ያስተምሩ ዘንድ፡፡

## ምዕራፍ ፰ ክፍል ፬

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃማ የተባልሽ ድንግል እመቤቴ ቅድስት ማርያም ሆይ በከበሩ ድንጋዮች ደግሞ እመስልሽ ዘንድ ልቡናዬን አነሳሳው፡፡

፪. መረግድ የሚባል ዕንቁ ድንጋይ ነሽ፡፡ ኅብራቸውም ከተራራ በረድ በሚነፃ በጳዴሬና በኤሞዳ እመስልሻለሁ፡፡ ይኸውም ምሳሌ ለንጽሕናሽ ነው፡፡

፫. የጳዝዮን ደንጊያ ነሽ የሰንፔር የሶምና የክርስቲሎቤ ደንጊያ ነሽ፡፡ ይኸውም ምሳሌ ላይን ደስ ለሚያሰኘው ደም ግባትሽ መጠራት ነው፡፡

፬. አሜቴስጢኖስ ደንጊያ አንቺ ነሽ፡፡ ኢያሰጲድ ሰርዲኖን ደንጊያ ነሽ፡፡ ይኸውም ምሳሌ አደፍ

ጉድፍ ለሌለበት ኅቱም ድንግልናሽ ነው፡፡

፭. ዕንቁ ባሕርይ ደንጊያ  አንቺ ነሽ፡፡ በወርቅ የተጌጠም ያክንት ድንጋይ አንቺ ነሽ፡፡ ይኸውም ምሳሌ ጥፋት ክፋት ለማያገኘው ቅድስናሽ ጌጥ ነው፡፡

፮. አልመቅሊጦስ  ደንጊያ  አንች ነሽ፡፡  እርሱም ከርኩሰት  የሚያነጻ ነው፡፡  የዓለም ርኩሰት  ባንቺ ነጽቷልና ዝገቱም  ባንቺ ታድሷልና፡፡

፯. የደወል ደንጊያ የቤተ   መቅደስ ቃጭል አንቺ ነሽ   እርሱም በተመታ ጊዜ ለሚሰማው   ያማረ የተወደደ ነው፡፡    በሕማም ጊዜ ቢመታ በምጥ የተያዘችው ሴት ልቡናዋ ወደርሱ ይመሰጣል፡፡ ብላቴናውንም እስክትወልድ  ድረስ  ሕማም አይሰማትም  ሕመሟንም አታውቀውም፡፡

፰. እንዲሁም ሰማዕታት የቅድስናሽን ወሬ በመስማት የልጅሽንም ወሬ ለቤዛ ዓለም   መሰቀሉንም ከመስማት የተነሣ በሰማዕትነት የሚያገኛቸውን መከራ እሳቱን ስለቱን   አያውቁትም   የሰማዕትነት ዋጋቸውን   እስኪቀበሉ ድረስ፡፡

፱. ብረትን ሁሉ   የሚያቀልጥ የአድማስ ደንጊያ አንች ነሽ፡፡ በመውለድ ያልተለወጠ   የማኅተመ ድንግልናሽ ኃይል እንደ አድማስ ደንጊያ ጽኑ ነውና በልጅሽ በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል የኃጢአቴን ሰንሰለትና የእስራቴን እግር ብረት አቅልጠሽ አጥፍተሻቸዋልና፡፡

፲. ከልጅሽ ከወዳጅሽ አንደበት  የሃይማኖት  አለት ተብሎ ጴጥሮስ የተጠራባት  አለት ደንጊያ   አንች ነሽ፡፡

፲፩. የሐዋርያት ጉባዔ የምትሆን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ባንቺ ተመሠረተች የንጉሱም  ሙሽራ ባንቺ ተጌፀች ፡፡  የበኩር ልጅሽ አጬኛ  ባንቺ  ተጋረደለት፡፡

፲፪. ባንቺም በወርቅ ደንጊያ ተመሠረተች፡፡ በሚያንፀበርቀውም ዕንቁ ደንጊያ ባንቺ ተሠራች፡፡

፲፫. ባንቺም ምሰሶች ቆሙ ሕንፃዋ ባንቺ ፀና ግድግዳዋም ባንቺ ተሠራ፡፡ ጠፈርዋም ባንች ተጠፈረ፡፡ ዋልታዋም ባንቺ ተዋቀረ፡፡  ጭምጭሞዋም ባንቺ ተጨመጨመ፡፡

፲፬. ደጆቿች ባንቺ ተከፈቱ፡፡ መቃን መድረኳም በልጅሽ ደም ተረጨ፡፡

፲፭. ባንድ ልጅሽ መስቀል ያፈራችው ስፍራ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች   ከርኩሰቷም በሆድሽ ፍሬ  ደም  የነጻችው፡፡

፲፮. ያዘነች ስትሆን በልጅሽ በወዳጅሽ ትንሣኤ የተጽናናችው፡፡ የተዋረደች ስትሆን  በድንግልናሽ ቡቃያ መውጣት  ከፍ ከፍ  ያለችው  ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች፡፡

፲፯. በዕለተ ዓርብ ከልጅሽ ቀኝ በፈሰሰው ውሀ ተጠምቃ የውግታቱን ደም ተቀብታ ቅድስት ቤተክርስቲያን  ታመሰግንሻለች፡፡

፲፰. የልዑል እግዚአብሔር በግ የተባለ ልጅሽ ዐማኑኤል የተሞሸረባት መርዓዊ ሰማያዊ   የተባለባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች፡፡ (ዮሐንስ ፩ ፣ ፳፱ ) (ኢሳይያስ ፶፫ ፣ ፯ ፡፡)

፲፱. ከወለድሽው ጋራ አንድ  አም ሳል ከሳደግሽውም ጋራ  አንድ  አካል የሆነችው የተባለችው  ቅድስት ቤተ ክርስቲያን  ባንደበቷ አቀንቅና በከንፈሯም እልል ብላ ታመሰግንሻለች፡፡

፳. በእጅዋ አጨብጭባ በእግሯ አሸብሽባ ቅድስት ቤተክርስቲያን ታመሰግንሻለች፡፡ ባንቺም ደስ ትሰኛለች ከእግርሽም በታች ይሰገዱ ዘንድ ልጆቿን ትጠራለች፡፡

፳፩. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግንሻለች፡፡ የአሕዛብም ልጅ ለእስራኤል ልጅ ላንቺ ትሰግዳለች፡፡ በልጅሽ ለጋስነት በሀብቱም ብዛት ፳ኤላዊት ተብላለችና እርሱ ልዕልናውን በትሕትናዋ ስለጨመረ፡፡

፳፪. ትሕትናዋንም በልዕልናው ጨመረ፡፡ የርሷንም ሞት ወስዶ የርሱን ሕይወት ሰጣት ስለ ርሷም ፍቅር ከላይ ወደ ታች ወረደ ከኃጢአትም በቀር እንደኛ መሆንን አላፈረም፡፡

፳፫. ደከመ ወዛ ተራበ ተጠማ ተሰቀለ ታመመ የርኩሳን አይሁድንም ምራቅ ተቀበለ፡፡
ሞትንም በሥጋ ተቀበለ፡፡ ይህንን ሁሉም ስለ እርሷ አደረገ፡፡

፳፬. በትንሣኤውም የዘለዓለም ሕይወትን ከፈላት በዕርገቱም ከፍ ከፍ አደረጋት ወደርሱም አንድ አካል አንድ አምሳል አድርጎ ወዳባቱ ደግሞ ወደ ልዑል እግዚአብሔር መባ አቀረባት፡፡

፳፭. ስለዚህም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታመሰግናለች፡፡ በልቡናዋ ስላደረው ስለ ልጅሽ ፍቅር በፍቅር እየነደደች ትሰግድልሻለች፡፡ የስሙ አጠራርም ለዘወትር ካንደበቷ አይቋረጥም፡፡

፳፮. ድንግል ሆይ ርኩሰት የሌለብሽ ንጽሕት ሆይ ድንግል ሆይ የተመሰገንሽ ቡርክት ሆይ የተመረጥሽ ቅድስት ሆይ ድንግል የድንግልናሽ ምስጋና በሁሉ መላ፡፡

፳፯. ውዳሴሽም በዓለም ዳርቻ ሁሉ ሰፈፈ የውቅያኖስ ባሕር በመደቡ የተወሰነ ነው፡፡ የሐኖስም ባሕር እንደ መጠኑ ልክ አለው፡፡

፳፰. ያንቺ ምስጋና ግን ልክ ወሰን ስፍር ቁጥር ማለቂያ የለውም፡፡ አእምሮ ሊወስነው አንደበት ተናግሮ ሊፈጽመው አይችልም፡፡

## ምዕራፍ ፬ (ክፍል ፯)

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ ሁሉ ላንቺ ሆነ ሁሉም ስላንቺ ተፈጠረ፡፡

፪. አዳም ከኅቱም ምድር ተፈጠረ አንቺን ያፈራ ዘንድ ነው፡፡ ሔዋንም ከአዳም ከግራ ጎኑ ተፈጠረች አንቺን ትወልድ ዘንድ (ዘፍጥረት ፩ ፥ ፳፯፡፡)

፫. ምድርም ተፈጠረች አዳምን አባትሽን ታስገኝ ዘንድ፡፡ ለምግቡም ቡቃያውን ታወጣ ዘንድ ሰማይም ስለርሱ ተሰቀለ (ዘፍጥረት ፩ ፥ ፩ ፥ ፲፩ ፡፡)

፬. ፀሐይና ጨረቃም ከዋክብትም እንዲያበሩለት በመውጣትና በመግባታቸው የዘመኑ ቁጥር እንዲታወቅ ተፈጠረ፡፡ (ዘፍጥረት ፩ ፥ ፲፬ ፥ ፲፮ ፡፡)

፭. ደመናትም ቡቃያውን ለማሳደግ ዝናም እንዲያዘንሙ ተዘረጉ እንጨቶችም ለግዳጁ ሊሆኑ ነፋሳትም እሸቱን ለማብስግዝናም እንዲያዘንሙ ተዘረጉ እንጨቶችም ለግዳጁ ሊሆኑ ነፋሳትም እሸቱን ለማብሰል እንዲነፍሱ መላእክትም እንዲያገለግሉት ተፈጠረ፡፡ (መዝሙር ፻፬ ፥ ፬) (ዘፍጥረት ፪ ፮ ፯ ፡፡)

www.ethiopianorthodox.org

፮. ጳውሎስ እንደ ተናገረ እንዲህ ሲል የዚህንስ ዓለም ተውትና መላእክትን ስንኳን እንድንገዛ አታውቁምን፡፡

፯. ዳግመኛም እንዲህ አለ ነገር ግን ሕይወትን ስለሚወርሱ ጻድቃን ተፈጠሩ፡፡

፰. ድንግል ሆይ ክብርሽን ገናንነትሽን ለመናገር የሚቻለው ማነው ምስጋናሽን ለመናገር ማን ይችላል፡፡ ከፍጡራንም ወገን ሁሉ አንቺን የሚመስል የለም፡፡

፱. በሁሉ ላይ አለቃ ሆንሽ ሁሉንም ገዛሽ ከሰማይ በላይ ከፍ ከፍ አልሽ፡፡ ከኢዮርም ነጠቅ ያልሽ ሆንሽ፡፡

፲. ሰማዮች የሰየዮችም ሰማይ ያመሰግኑሻል፡፡ የፈጣሪያቸውን እናት ሆነሻልና፡፡

፲፩. መላእክት የመላእክት አለቆች ያመሰግኑሻል፡፡ የፈጠራቸውን ወልደሸዋልና፡፡

፲፪. ሰውና እንስሳ ሥጋም የለበሰ ፍጥረት ሁሉ ያደንቁሻል፡፡ ያመሰግኑሻል፡፡ በዝናም አብቅሎ በፀሐይ አበስሎ የሚመግባቸው እርሱን በድንግልናሽ ወተት አሳድገሽዋልና፡፡

፲፫. ምድርም ተራሮችም በላይዋም የተፈጠሩ ኮረብቶች ሁሉ ላንቺ ይገዛሉ ፡፡ ያጸናቸው እሱን በጉልበትሽ ላይ አቅፈሽ ይዘሽዋልና፡፡

፲፬. ወንዞች ባሕርም ፈሳሽም ውሆች ሁሉ ገናንነትሽን ይናገራሉ፡፡ ቁመታቸውን ጥልቅ ያደረገ ስፋታቸውንም ያሰፋ እሱን በጸባብ ሆድሽ ወስነሽዋልና፡፡

፲፭. እሳት የእሳት ነበልባል ላህቡም መባርቅትም ክብርሽን ይናገራሉ፡፡ ተፈጥሯቸው ከእሳት የሚሆን መላእክት ከግርማው የተነሣ የሚንቀጠቀጡለትን መባርቅትም ከቃሉ መውጣት የሚገለባበጡለት እርሱን በእጆችሽ ዳሰሽዋልና፡፡

፲፮. ኪሩቤል ሱራፌል ይሰግዱልሻል፡፡ በላያቸው የሚቀመጥ እርሱን በጀርባሽ አዝለሽዋልና፡፡ (መዝሙር ፲፰ ፣ ፲)

፲፯. የዕውነተኛ ፀሐይ እናት ሆይ ላንቺ እገዛለሁ፡፡ ፍጥረት ሁሉ ላንቺ ይገዛልና፡፡ የልጅሽ ስም በሁሉ ከተነገረ ዘንድ ያንቺ ስም ከዚያ ይነገራልና፡፡

፲፰. የልጅሽ መለኮትነት በሁሉ ገዥ ከሆነ ዘንድ ክብርሽ ገናንነትሽ ከዚያ ይነገራል፡፡ (መዝሙር ፹፫ ፣ ፳፪፡፡)

፲፱. አንድ ልጅሽ ወደ ሰማይ ባረገና በባሕርይ አባቱ በስተቀኝ በተቀመጠ ጊዜ ካንቺ የነሣው ትስብእት ከመለኮት ጋራ አንድ ሁኖ ከዚያ አለ፡፡ (ማርቆስ ፲፮ ፣ ፲፱) (የሐዋርያት ሥራ ፩ ፣፪)

፳. እግዚአብሔር ዕፁብ ድንቅን አደረገ አዳምን በፈጠረው ጊዜ ከራቱ ባሕርያት አከናውኖ በሠራው ጊዜ አራቱ ባሕርያት አንዱ ከሁለቱ ሶስተኛው ከአራተኛው እንዳይቸጋገሩ እርስ በርሳቸውም እምቢ እንዳይባባሉ ባሕርያትን አስማማ፡፡

፳፩. ዕርጥቡን ከደረቁ ጋራ ጨመረ ሙቀት ያለውንም ባሕርይ ከቁሪሩ ባሕርይ የሚታየውንም ከማይታየው ጋራ፡፡ የሚዳሰሰውንም ከማይዳሰሰው ጋራ አስማማ፡፡

፳፪. ከሚዳሰሰው ሦስት ከማይዳሰ ሰው ሁለት አደረገ ከደረቁ ሶስት ከርጥቡ አንድ ከቆሪሩ ሦስት ሙቀትም ካለው አንድ አደረገ፡፡

፳፫. ሠሪውም ቤቱ ጸንቶ የሚኖርበትን ምክንያት አወቀ የቤቱንም ማዕዘን ባራቱ ባሕርያት መሠረተ፡፡

፳፬. ዳግመኛም የርሱ ትንፋሽ የሕይወቱም መንፈስ ከልተዋሐደው በቀር ሽክላው መንቀሳቀስ መናገርም እንዳይችል ባወቀ ጊዜ የሕይወት መንፈስን በንፍሐት አሳደረበት፡፡ የሚንቀሳቀስ የሚናገር አደረገው፡፡ (ዘፍጥረት ፪ ፣፯ ፡፡)

፳፭. ቅድስት ኦሪት እንደተናገረች እንዲህ ስትል በአዳም አፍንጫ የሕይወት ትንፋሽ እፍ አለበት ሰውም ሕይወት ያለበት ነፍስ ሆነ፡፡ (ዘፍጥ ፪ ፣፯ ፡፡)

፳፮. ስለዚህም ነፍስ ከሥጋ ጋር አትሞትም ከእግዚአብሔር እንደበት ወጥታ ከሥጋዋ ጋር ትዋሀዳለችና፡፡ ጌታ በቅዱስ ወንጌል እንደተናገረ እንዲህ ሲል ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍሯቸው፡፡ ነፍሳችሁን ሊገድሉ አይችሉምና (ማቴዎስ ፲ ፣፳፰ ፡፡)

፳፯. ነፍስ አትግደል ያለው ግን ስለ ደመ ነፍስ ነው በሰው ሁለት ነፍሳት አሉና፡፡ አንዲቱ የሕይወት መንፈስ ናት እርሷም ከእግዚአብሔር አንደበት የወጣች ይህችም ከሥጋ ባሕርይ አቅቆጠርም አትሞትም፡፡

፳፰. አንዲቱ ደግሞ ደመ ነፍስ ናት እርሷ ግን ከሥጋ ባሕርይ ናትና ትሞታለች ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡፡ ከደመ ነፍስ ያልተለየውን ሥጋ አትብሉ፡፡

፳፱. የእግዚአብሔር የቤቱ ምሰሶ ግን የሕይወት መንፈስ ነው፡፡ እንግዲህ የሕይወት መንፈስ ከተለየው ወዲያ ሥጋ በድን ይሆናል፡፡

፴. ስለዚህ ኦሪት በድንን አረከሰች የሕይወት መንፈስ ከሱ ተለይቷልና በኛ ዘንድ ግን የክርስቲያን በድን ንጹሕ ነው፡፡ ሥጋው ከመለኮት ስጋና ደም የተዋሀደ ነውና፡፡ በጥምቀትም ያገኘው ጸጋ ከርሱ አይለይም፡፡

፴፩. ስለ ድንግል ልጅም ሥጋ ዳዊት እንዲህ አለ ወንድማቸውን እንደ ርኩስ በድን ጣሉ፡፡ (መዝሙር ፴፰ ፣፳፩፡፡)

፴፪. እንዲህ ማለት ቅዱስ እንደ ሆነ አላውቁትም ማለት ነው፡፡ የአይሁድ ወገኖች በእናቱ በኩል ዘመዶቹ ናቸውና በድን ማርከስም በሕጋቸው ልማዳቸው ነውና፡፡

፴፫. የእግዚአብሔር ጥበቡ ዕፀብ ድንቅ ነው፡፡ አዳምና ሔዋንን በመልኩ በምሳሌው ፈጠራቸው፡፡ ( ዘፍጥረት ፩ ፣፳፯፡፡)

፴፬. በወደደ ጊዜ ደግሞ በዘራቸው ልጅ ማኅፀን ተሠወረ፡፡ ከሠራው ቤት አደረ ወደ አነጸውም ገባ ሥጋዊ ደማዊ ባሕርይን ባሕርይ አደረገ፡፡ ሥጋዊ ደማዊ ፈቃድ አላገኘውም፡፡

፴፭. ተራበ አልቀማም ተጠማ ስልት ቀጠና አላገኘውም፡፡ ደከመ ከሰው ማንንም ረዳት አልሻም፡፡ በፈረስና በሠረገላም የሚረዳው ሊኖር አልፈለገም፡፡ (ማቴ ፳፮፡፡)

፴፮. ተሰደበ አልተቀየመም፡፡ ተሰቀለ ታመመ ለሰቀሉት ሥርየት ለመነ፡፡ እንዲህ ሲል አባቴ ሆይ ዕዳ

በደል አታድርግባቸው ያለዕውቀት ይሠራሉና፡፡ (ማቴዎስ ፳፫ ፣ ፵፱ ፣ ፶፪፡፡)

፵፯. ሰይጣን በርሱ ላይ ምንምን ምክንያት አላገኘም ስለዚህ ዳዊት እንዲህ አለ ከባለ ቀንድና ሰኰናው ከተሰነጠቀ በሬ ከወይፈንም ይልቅ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘዋለሁ፡፡ (መዝሙር ፷፱ ፣ ፵፩ ፡፡)

፵፰. የእግዚአብሔርን ልጅ ላም ብሎ ጠራው፡፡ የተመረጠችውን ድንግል ደግሞ ጥጃ አላት ቀንድና ጽፍር ያላበቀለ ማለቱ ግን በእጆቹ ቅሚያ በራሱ የኃጢአት ጽኑ ሸክም ስላልኖረበት ነው፡፡ (ዮሐንስ ፲፰ ፣ ፳፱ ፡፡)

፵፱. የንጽሕት እምቦሳ ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስ በውነት ንጹሕ የተወደደ መሥዋዕት ነው፡፡

፶. ለመታረድ የማያቋርፅ እርዱ የማያልቅ ንጹሕ ላህም ዕውነተኛ መሥዋዕት ነው፡፡ የሚበሉትንም የሚቀድሳቸው የሚቀበሉትንም የተመሰገኑ የሚያደርጋቸው እርሱ እውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነው፡፡

፶፩. በእስራኤል እጅ የተሠዋ እርሱ ዕውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነው በአይሁዳዊ እጅ የተሠዋ እርሱ ዕውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነው፡፡

፶፪. በወጉት ፊት በቀንዱ የማይበረታታ ላም በሚሸልቱትም ፊት የሚይናገረው በግ ዕውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነው፡፡ (ኢሳይያስ ፶፫ ፣ ፯ ፡፡)

፶፫. ሥጋውን የበላ አይሞትም ደሙንም የጠጣ አይጐዳም በዕውነት ንጹሕ መሥዋዕት ነው፡፡ (ዮሐ ፮ ፣ ፶፫ ፣ ፶፱ ፡፡)

፶፬. በፈቃዱ የታመመ ወይም የሞተ እርሱ ንጹሕ መሥዋዕት ነው፡፡

፶፭. ዘወትር የሚሠዋው ዘወትርም ሕያው ሁኖ የሚኖረው የጐኑ መዳሰስም የማያልቀው እርሱ የዕውነት መሥዋዕት ነው፡፡

፶፮. ይህንን እሳት ያለ ጉጠት ሳይፈራ የሚዳስስ ካህን እንደምን ያለ ነው ለዚህ ለመዳሰሱ አንክሮ ይገባል፡፡

፶፯. በመሠዊያ ላይ ይህንን ኅብስቱን የሚፈትተው ካህን እንደምን ያለ ነው፡፡ ለዚህ ለመፍተቱ አንክሮ ይገባል፡፡ ብላቴናውን ባባቱ ፊት በናቱ ራስ ላይ አኑሮ የሚሠዋ ይመስላል፡፡

፶፰. የምሥጢሩን ወይን በጽዋው የሚያዘጋጀው ካህን እንደምን ያለ ነው፡፡ ለዚህ ለማዘጋጀቱ አንክሮ ይገባል ነው፡፡ ለዚህ ለማዘጋጀቱ አንክሮ ይገባል፡፡ የልጁን ደም ባባቱ ፊት ደሙም በናቱ ራስ ላይ ሲንጸፈጸፍ የሚቀዳ ይመስላል፡፡

፶፱. ሙሽራውን ያለ ወቅለምት የሚሠዋ ሙሽራይቱን የሙሽራውን ሥጋ እንድትበላ የሚጠራት ልጆቿንም ባባታቸው ሥጋ የሚያሳድጋቸው ይህ ካህን እንደምን ነው ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡

፷. የእግዚአብሔርን በግ ለመሥዋዕት ጣቶቹ ወቅለምት የሆኑለት ይህ ካህን እንደምን ያለ ነው፡፡ ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡

፷፩. እንደበቱም መናፍቃንን ከምዕመናን ለመለየት ሰይፍ ሆነለት፡፡



www.ethiopianorthodox.org

፶፪. ምዕመናንን ከአምላከቸው ደም አንድ የሚያደርጋቸው ይህ ካህን እንደም ያለ ነው፡፡ የማይዳሰሰውን የሚዳስስ የማይነካውን የሚነካ ይህ ካህን እንደም ያለ ነው፡፡ ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡

## ምዕራፍ ፲ (ክፍል ፯)

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ማርያም ሆይ አምላካዊውን እንጀራ ላስገኘሽልን ላንቺ መገዛት ይገባል፡፡

፪. ድንግል ሆይ ርኩሰታችንን የሚአነጻውን የወይን ጽዋ ላነቃሽልን ላንቺ መገዛት ይገባል፡፡ ሰማያዊውንም በግ ነባቢውንም መሥዋዕት ለወለድሽልን ላንቺ መገዛት ይገባል፡፡

፫. ድንግል ሆይ ለበረከት የሚሆነውን ረቂቅ ምሥጢር ላስገኘሽልን ላንቺ መገዛት ይገባል፡፡

፬. ድንግል ሆይ የሚታረደውን በሬ እርዱም ለሠርግ ሰዎች የሚሆነውን ለወለድሽልን ላንቺ መገዛት ይገባል፡፡

፭. ሰውን ከመላእክት ጋራ ያስማማሽ ድንግል ሆይ ላንቺ ማገልገል ይገባል፡፡ የሰውንም ልጆች ሁሉ በኪሩቤል ምስጋና እንዲያመሰግኑ ያደረግሻቸው ድንግል ሆይ አንቺን ደጅ መጥናት ይገባል፡፡

## ምዕራፍ ፲፩

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ በልጅሽ በወላጅሽ መታመም መከራም በመቀበሉ የፀብና የክርክርን ግርግዳ አፍርሰሽ የሃይማኖትን መሠረትን ላጸናሽልን ላንቺ ማገልገል ይገባል፡፡

፪. ድንግል ሆይ ባንድ ልጅሽ መስቀል ሰውን ለኃጢአት ከመገዛት ባርነት ነፃ ላወጣሽው ላንቺ መገዛት ይገባል፡፡

፫. ድንግል ሆይ ለማይና ምድርን ላስማማሽ ላንቺ መታጠቅ ይገባል፡፡

፬. የሕይወት መድኃኒት ምንጭ ሆይ የፈውስ መድኃኒት ውሀን ከአንቺ የሚቀዱ ሕመም ቁስለ ሥጋ ቁስለ ነፍስ የለባቸውም፡፡

፭. የሰላም ምንጭ ሆይ የምሕረት ውሀን ካንቺ የሚረኩ የሚጠጡም ለዘለዓለም አይጸሙም፡፡ የሌት ቁር የመዓልት ሐሩር አያገኛቸውም ፡፡ (ዮሐንስ ፬ ፣ ፲፬ ፡፡)

፮. የደኅንነት ምንጭ ሆይ ካንቺ የሚጠጡ ሐዲሳን አትክልት ዋዕየ ፀሐይ አያደርቃቸውም፡፡ ጽድቅ አበበቸውም አይጠወልግም፡፡

፯. የሕይወት ምንጭ ሆይ ካንቺ የሚረጩ ርኩሰተ ሥጋ ርኩሰተ ነፍስ የለባቸውም፡፡

፰. ለዘወትር የማትደርቅ ረብሀ ጥቅም የሚገኝባት የሕይወት መድኃኒት ፈሳሽ አንቺ ነሽ፡፡

፱. ቄስለኞች የሚፈወሱበት የሕይወት ውሀ ነቅዕ አንቺ ነሽ፡፡ ያዘኑትን የሚያረጋጋቸው የፍጹም ደስታ ነቅዕ አንቺ ነሽ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፲. ለዝንጉዎች ዕውቀትን የሚገልጽ የጥበብና የአእምሮ ነቅዕ ፈሳሽ አንቺ ነሽ፡፡ የቅዱሳን መዓዛ የንጹሕ ዕጣን ፈልፈል አንቺ ነሽ፡፡

፲፩. ለዓለም ሀብትን የምታሰጥ የደናግል ገንዘብ አንቺ ነሽ፡፡

፲፪. አቤኔዜር የተባለች የረድኤት ደንጊያ አንቺ ነሽ፡፡ ይህችውም የየቡሳዊው የአረውና አውድማ እግዚአብሔር በውስጧ የዕሴይን ልጅ የዳዊትን መሥዋዕት የተቀበለባት፡፡ ከእግዚአብሔር የታዘዘው መቅሠፍት በራቀ ጊዜ ( ፪ ሳሙኤል ፳፬ ፣ ፲፰ ፣ ፳፭ ፡፡)

፲፫. ለእስራኤል አምላክ ኤልያስ የመሥዋዕት መዓዛ ያሸተተባት የቀርሜሎስ መሠዊያ አንቺ ነሽ፡፡ እሳት ከሰማይ ወረደች መሥዋዕቱንም በላች፡፡ ዕንጨቱንና ደንጊያውንም መሬቱንም ደግሞም በጉድጓድ የነበረውን ውሀ ላሰች፡፡ (፩ኛ ነገ ፲፰ ፣ ፴፰ ፡፡)

## ምዕራፍ ፲፪ ክፍል ፰

፩. ድንግል ሆይ ባማረው በተወደደው ነገር ሁሉ መሰልሁሽ ምስጋናሽን ግን ለመፈጸም አልቻልኩም፡፡

፪. ስለንቺም የተነገረው ፍጹም ምስጋና በምስጋናሽ ባሕር ጥልቅነት፡፡ ዘንድ እንደ መጥለቂያ ጠብታ ነው፡፡

፫. ምሕረት በቀኝሽ በኩል ነው፡፡ ይቅርታም በግራሽ በኩል፡፡ ብርሃንና ፀዳል በፊትሽ ነው፡፡ ረድኤትና መድኃኒ በስተፊትሽ፡፡

፬. የዓለም ሁሉ ክብር የነገሥታትም ብዕላቸው ድንግል ሆይ ነገሥታትና መኳንንት ዓለምም ሁሉ ከእግርሽ በታች ከጫማሽ ወድቀው ይገዛሉ፡፡

፭. የምስጋና ዘውድ በራስሽ ላይ ነው፡፡ የጽድቅ ጋሻም አንቺን ይከባል፡፡ የሃይማኖት አጽር ቅጽርም ይከብብሻል የመንፈስ ቅዱስ ክንፉ ይጋርድሻል፡፡
፮. አዳም ከልጆቹ ጋራ ያመሰግንሻል፡፡ በሱ የተፈረደ መርገመ ሥጋ ባንቺ ጠፍቷልና፡፡ እግዚአብሔር ሔዋንን የረገማት መርገም ባንቺ ተሽሯልና እንዲህ ሲል፡፡

፯. ፃዕርሽን ጋርሽን አበዛለሁ፡፡ ልጆችሽን በፃዕር ትወልጃለሽ፡፡ ከወለድሽም በኋላ ፈቃድሽ ወደ ባልሽ ይሆናል ፣ እርሱም ይገዛሻል፡፡ (ዘፍጥረት ፣ ፫ ፲፯፡፡)

፰. አንቺ ግን ያለ ህማም ወለድሽ እንግዲህ የሚገዛሽ የለም ከኃጥያት ሽክም በታች አልተጠመድሽምና፡፡

፱. ኖኅ ከልጆቹ ጋር ያመሰግንሻል የበረከቱ ቃል ባንቺ ተፈጽሟልና እንዲህ ያለው እግዚአብሔር በሴም ድንኳን ይደር፡፡ (ዘፍጥረት ፣ ፱ ፣ ፳፯ ፡፡)

፲. አብርሃም ከሳራ ጋር ያመሰግንሻል እግዚአብሔር ተስፋ ያስደረገው ባንቺ ተፈጽሟልና እንዲህ ሲል፡፡ ከይስሐቅ ላንተ ብዙ ዘር ይጠራልሃል፡፡ ፲፯ ፣ ፲፱ ፣ ፳፩ ፡፡)

፲፩. ይስሐቅ ከርብቃ ጋር ያመሰግንሻል በያዕቆብ ላይ የሆነው በረከት ባንቺ ተፈጽሟልና፡፡

፲፪. ቡሬኬውም እንዲህ የሚል ነው አሕዛብ ይገዙልሃል፡፡ ወገኖችም ይሰግዱልሃል፡፡ ለወንድምህም ጌታ ሁነው፡፡ (ዘፍጥረት ፣ ፳፯ ፣ ፳፱ ፡፡)

www.ethiopianorthodox.org

፲፫. ይኸውም የትንቢት በረከት ያለ ልጅሽ አልተፈጸመም፡፡

፲፬. ዕብራዊያን ያዕቆብም ከልጁ ከይሁዳ ጋራ ያመሰግንሻል የርሱ በረከት በልጅሽ ተፈጽሟልና እግዚአብሔር ይሁዳን የባረከው እንዲህ ሲል፡፡

፲፭. ይሁዳ ሆይ ወንድሞችህ አንተን ያመሰግናሉ፡፡ እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው፡፡ የአባትህ ልጆች ይሰግዱልሃል፡፡ (ዘፍጥረት ፣ ፵፱ ፣፰ ፡፡)

፲፮. የአንበሳ ግልገል ይሁዳ ልጄ ሆይ ከምርኮ ወጣህ እንደ አንበሳ እንደሴት አንበሳም ተንበረከክ፡፡ ተኛም ያስነሳው ዘንድ ማን ይችላል፡፡ (ቁ.፱)

፲፯. በትር ከይሁዳ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መሐከል አይጠፋም የሰላም ንጉስ እስኪመጣ ድረስ ርርሱም የአሕዛብ መታዘዝ ይሆናል፡፡ (ቁጥር ፲ )

፲፰. አህያይቱን በወይን ግንድ ያህያውንም ግልገል በወይን ሐረግ ያስራል፡፡ ልብሱን በወይን መጎናጸፊያውንም በወይን ዘለላ ያጥባል፡፡ ፲፩ )

፲፱. ዓይኑ ከወይን ይቀላል፡፡ ጥርሱም ከወተት ይነጻል፡፡ (ቁ.፲፪ )

፳. ሙሴ ከእስራኤል ልጆች ሁሉ ጋራ ያመሰግንሻል እግዚአብሔር በሙሴ አሪት ስላንቺ እንዲህ ይላልና፡፡

፳፩. ሰማይ አድምጽ እነግርህማለሁ፡፡ ምድርም ያፌን ነገር ትስማ፡፡ ዘዳግም ፴፪ ፣ ፩ ፡፡

፳፪. ትምህርቴም እንደ ዝናም ትፍሰስ ነገሬም እንደ ጠል እንደ ካፊያም በርሻ ላይ ይውረድ እንደጠፈጠፍም ሳር ይሁን እንግዲህ አንቺን እርሻ ብሎ ጠፋሽ ልጅሽን ደግሞ ጠል አለው፡፡ (ቁ ፪ )

፳፫. ዳዊት ከመዘምራን ጋራ ያመሰግንሽል እንዲህ ሲል መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው፡፡ (መዝሙር ፣ ፹፯ )

፳፬. እግዚአብሔር ከያዕቆብ መኖሪያዎች ሁሉ ይልቅ የጽዮንን ደጆች ይመርጣቸዋል፡፡ (ቁ.፪ )

፳፭. የእግዚአብሔር አገር ሆይ በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል፡፡ (ቁ.፫ )

፳፮. ማኅበረ መላእክት ሁሉ ያመሰግንሻል በንጽህና ስርዓት እርሳቸውን መስለሻልና፡፡

፳፯. ማኅበረ ነቢያት ሁላቸው ያመሰግኑሻል ትንቢታቸው ባንቺ ተፈጽሟልና፡፡

፳፰. የሐዋርያት ማኅበር ያመሰግኑሻል የተወደደ ልጅሽ ወንድም ሆኗቸዋልና፡፡ ለመንግስቱም ወራሾች አድርጓቸዋልና፡፡

፳፱. የበጎ ኅልማሶች ሰማዕታት ያመሰግኑሻል፡፡ የልጅሽ መከራ አንድነት በስጋቸው ተቀብለዋልና፡፡

፴. ደናግል መነኮሳት ያመሰግኙሻል አኗኗራቸውን ለንጽህናሽ አምሳል ብፅዓት አድርገዋልና፡፡

፴፩. ሊቃነ ጳጳሳት ፣ ኤጲስቆጶት ያመሰግኑሻል የልጅሽ እንደበት ስልጣን ባንደበታቸው ተዋህዷልና፡፡

፴፪. ቀሳውስት ያመሰግኑሻል፡፡ ለክህነታቸው መዓርግ ልጅሽ አለቃ ሁኗልና፡፡

፴፫. ስለ በጎ መልእክት የሚፋጠኑ ዲያቆናት ያመሰግኑሻል፡፡ በልጅሽ ገዥነት ምሥጢር አገልጋዮች መላክተኞች ሁነዋልና፡፡

፴፬. አናጉንስጢስ መዘምራን ያመሰግኑሻል ለልጅሽ ምስጋና በቤተ መቅደስ ድምጻቸው እንደ ወርቅ ጸናጽል ይሰማልና፡፡

፴፭. የክርስቲያን ማኅበር ሁሉ ያመሰግኑሻል፡፡ ከልጅሽ ከቀኝ ጎኑ የተገኘውን የጥምቀት ድርብ በፍታ ተጎናጽፈዋልና፡፡

## ምዕራፍ ፲፫

፩. አደፍ ፣ ጉድፍ የሌለብሽ ንጽሕት ሆይ ያለ ኃጢአት ጽሪት ያለ ርኩሰትም ቅድስት ሆይ የድንግልሽ ምስጋና ዕፁብ ድንቅ ነው፡፡

፪. የንጽሕናሽም ውዳሴ የተደነቀ ነው፡፡ ስለዚህም ክብርሽን ፣ ገናንነትሽን ልንናገር ይገባናል፡፡

፫. በላይሽ ያፈረውንም ጸጋ ክብር እንናገር ፣ ዕውቀት ልቡና ያለው ሁሉ ለንግስትነትሽ ይገዛል፡፡

፬. አፍ እንደበት ያለው ሁሉ የቅድስናሽን ኃይል ያመሰግናል፡፡ በቅዱሳን ሁሉ ዘንድ ቅድስት ነሽ፡፡

፭. በተመረጡትም ዘንድ የተመረጥሽ ነሽ ፣ በተመሰገኑትም ላይ ተመሰገንሽ ስምሽም በሁሉ የሰለጠነ ገዥ ነው፡፡

፮. ወደአንቺ የሚገሰግስ የቤትሽንም ደጅ የሚመታ የሚጸፋም የተደነቀ ነው፡፡ የፍቅርሽ ኃይል ያረፈበት የተደነቀ ነው፡፡ የክብርሽን የገናንነትሽን ምስጋና ዘወትር የሚያነብ የተደነቀ ነው፡፡

፯. የስምሽን አጠራር ካፉ የማያርቅ የገናንነትሽንም ነገር ካንደበቱ የማያቋርጥ የተመሰገነ ነው፡፡

፰. በፍጹም ልቡናው የሚከተልሽ በሐሳቡም ሁሉ አንቺን የሚፈልግ የተመሰገነ ነው፡፡

፱. አንችን የተጠጋ እምነቱንም በልጅሽ ያደረገ የተመሰገነ ነው፡፡

፲. የፍቅርሽ መሰረት ከልቦናው የማይነዋወጥ አንቺን ከማሰብም ልቡናው የማይወላውል የተደነቀ ነው፡፡

፲፩. ዘወትር ለምስጋናሽ የሚተጋ ጸሎቱንም በጆሮሽ የሚዘራ የተመሰገነ ነው፡፡

፲፪. የልጅሽ የሞቱን መስቀል ለመሸከም ዘወትር ልቡን የሚያጨክን ይቅርታንም ከድንግልናሽ ነቅዐ የሚቀዳ የተመሰገነ ነው፡፡

፲፫. ያበባውን ሽቱ ከንጽህናሽ መዓዛ የሚቀምስ የተደነቀ ነው፡፡

፲፬. ከልጅሽ የመገዛት ቀምበር በታች ራሱን ዘንበል ያደረገ ያንድ ልጅሽ የወንጌሉን ፍለጋ የተከተለ የተመሰገነ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፭. እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ትእዛዙንም ሊጠብቅ የሚወድ ምስጉን ነው፡፡ (መዝሙር ፻፲፪ ፣ ፩ ፡፡)

፲፮. ዘሩም በምድር ብርቱ ይሆናል የቅኖችም ትውልድ ትባረካለች፡፡ (ቁ ፣ ፪)

፲፯. ሀብትና ባለጸግነት በቤቱ ነው፡፡ ጽድቁም ለዘለዓለም ይኖራል፡፡ (ቁ ፣ ፫)

፲፰. የያዕቆብ አምላክ ረዳቱ የሆነ ተስፋውና ትውክልቱም በእግዚአብሔር በአምላኩ የሆነ የተመሰገነ ነው፡፡ (መዝሙር ፻፵፮ ፣ ፭ ፡፡)

፲፱. እግዚአብሔርን የሚፈሩ በመንገዱም የሚሔዱ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው፡፡ (መዝሙር ፻፳፰ ፣ ፩ ፡፡)

፳. ድንግል ሆይ በጸሎትሽ ረዳትነት የሚታመን ምስጉን ነው፡፡ እኔም ስለዚህ ፍቅርሽን ለመከተል ተጋሁ፡፡

፳፩. በላይሽም ያደረው የሃይማኖት ኃይል ልቡናዬን አሰለጠነው፡፡

፳፪. ሥጋሽን የለበሰ የሕያው እግዚአብሔር ቃል ወዳለበት ወደ ላይ በማሰብ ልቡናየን መጠቀኝ፡፡

፳፫. ከፍጥረት ወገኖች ሁሉ ካንቺ የሚከብር እንደ ሌለ እንግዲህ ፀወቅሁ፡፡

፳፬. ከሕይወት እሳት የተገኘ የሕይወት እሳት ተላከ፡፡ ከምስጋና መብረቅ የተገኘ መብረቅ ወረደ፡፡

፳፭. ከብርሃን ሕጽን የተገኘ ብርሃን ወረደ፡፡ ከባሕርይ አምላክ የተገኘ የባሕርይ አምላክ መጥቶ በላይሽ አደረ፡፡

፳፮. ከምልዓቱ ሳይከፈል በወለደው ቀኝ ሳለ በማኅፀንሽ ተወሰነ፡፡ ሳይወሰን ምልዓቱን ፣ ስፋቱን ፣ ርቀቱን ሳይተው በማኅፀንሽ ተሸከምሽው ፀነስሽውም፡፡

፳፯. አነዋዋሩን የሚወስነው ስፍራ የለምና ፣ ለገዥነቱም ልክ መጠን የለውም በማየትም በማሰብም የወሰኑ ልክ ተመርምሮ አይገኝም፡፡

፳፰. ሥጋዊት ደማዊት ብላቴና ሆይ፡፡ የመለኮት በሆድሽ መፀነስ እንደምን ነው፡፡ እስኪ ንገሪኝ፡፡

፳፱. ከኃይል የተገኘ ኃይል እንዴት በላይሽ አደረ፡፡ በመውረዱ የሰማያት ኃይል አልተነቃነቀምን፡፡ በመምጣቱስ የተራሮች መሠረት አልተነዋወጠምን

፴. የሰማይ ስፋት የምድር መዘርጋት ሊወስኑት የማይችሉት እርሱን እንዴት በመሐከል እጅሽ ያዝሽው

፴፩. የሁለት ሽማግሎች ብላቴና ሆይ የዳዊት ያባትሽ ቤት የመንግሥት ሀብት የጠቀመሽ የለም፡፡ የሰሎሞንም የልጁ ድልብ ብዛት ምንም ምን አልጠቀመሽም፡፡ ከርሳቸውም ገንዘብ ምንም ምን የደረሰሽ የለም፡፡

፴፪. ነገር ግን የነዳያን ብዕል የንጹሓን አክሊል የቅዱሳን ጌጥ የሚሆን የመለኮት ባሕርይ በላይሽ አደረ፡፡ ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነስቶ ተዋሐደ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ፡፡

፵፫. በነቢያት መጻሕፍት ግን ከዳዊት ዘር ከወገኖቹም ነገድ ክርስቶስ እንዲወለድ ተጽፏል፡፡

፵፬. እንኪያ በሄሮድስ ልጅ አላደረ፡፡ ከይሁዳም አለቆች ባንዱ ልጅ፡፡

፵፭. ነገር ግን ከገሊላ ልጆች ለናትነት የምትበቃ አላገኘም፡፡

## ምዕራፍ ፲፬

፩. ስለዚህም አንቺን በትሕትና በድንግልና ተጠብቀሽ የምትኖሪዩቱን ብላቴና ወደደ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሚሆነው አዳራሽ ንጹሑን ሥጋሽን አገኘ፡፡

፪. አካላዊ ቃልም ካንቺ በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል ከሩቅ አገር መጡ (ማቴዎስ ፣ ም ፪ ፣ ቁ ፩)

፫. እንዲህ ሲሉ የተወለደው የይሁዳ ንጉሥ ወዴት ነው፡፡ ኮከቡን በምስራቅ አይተናልና ልንሰግድት መጥተናል፡፡ (ቁ. ፪ ዘኁልቍ ፳፬ ፣ ፲፯፡፡)

፬. ሄሮድስም ይኽን ሰምቶ ደነገጠ ታወከ፡፡ ሕዝቡም ከርሱ ጋራ ደነገጡ ታወኩ (ቁ. ፫ )፡፡

፭. የካህናቱ ሁሉ የሕዝቡንም ጸሐፎች ሰበሰበ ክርስቶስ በወዴት ይወለዳል ብሎ ጠየቃቸው፡፡ (ቁ. ፬ )

፮. እርሳቸውም አሉት በቤተልሔም በይሁዳ ዕፃ እንዲህ በነብይ ተጽፏልና፡፡ (ሚካ ፭ ፣ ፩ ፡፡)

፯. አንችም ቤተ ልሔም የኤፍራታ ምድር ከይሁዳ አለቆች ሁሉ ከቶ አታንሽም ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ ንጉስ ካንቺ ይወጣልና፡፡ (ማቴዎስ ፪ ፣ ፯፡፡)

፰. ከነቢይ ቃል ለወጣ በትንቢት መንፈስ ለተነገረ በጻሐፍትና በሊቃነ ካህናት አፍ ወደ ሄሮድስ ጆሮ ለተሰበከ ለዚህ ምስክርነት አንክሮ ይገባል፡፡

፱. የንጉሱን ልቡና አወከ፡፡ ሰውነቱንም በቅናት አቀለጠ አቃጠለውም (ማቴዎስ ፪-፫ ፡፡)

፲. የተወለደበትንም ጊዜ ዘመን በታያቸው ኮከብ ከሰብአ ሰገል ከተረዳ በኋላ የገሊላን ሕጻናት ግደሉ ብሎ አዘዘ፡፡ (ቁ ፲፯ ፡፡)

፲፩. ከእናቶቻቸው ጡት የተነሳ ምድር እስክትነጣ ድረስ ከሕጻናቱም ደም የተነሳ ምድር እስክትቀላ፡፡

፲፪. የሕጻናቱ የመታረዳቸው የደም ጐርፍ፡፡ የገሊላም ሴቶች የጡታቸው የወተት ጐርፍ ባንድ ሥፍራ ፈሰሰ፡፡

፲፫. ሄሮድስ የማያገኘውን ፈለገ፡፡ ጌታም ወደ ምድረ ግብፅ ሔደ፡፡ በቀሊል ደመና ተጭኖ ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረ፡፡

፲፬. እነሆ እግዚአብሔር ወደ ምድረ ግብፅ ይወርዳል በደመና ተጭኖ (ኢሳይያስ ፲፱ ፣ ፩ ፡፡)

፲፭. እመቤቴ ሆይ ደመና ግን አንቺ ነሽ፡፡ ሄሮድስ በቤቱ ነፋስን ሊዘጋ ወደደ ነፋስን መዝጋት በወዴት ይችላል፡፡

፺፯. ሄሮድስ የፀሐይን ብርሃን በእጁ ሊጨብጥ ወደደ፡፡ የፀሐይን ብርሃን መጨበጥ ወዴት ይችላል፡፡

፺፰. እግዚአብሔር በምስር ምድር እንግዳ ሆነ በጀርባሽ ታዝሎ፡፡

፺፱. እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ ትሑት አገልጋይሽ የምሆን እኔን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ አድኚኝ የልጅሽ የወዳጅሽ ቸርነት በሁላቸን ላይ ይደር አሜን፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## አርጋኖን

## ዘሠሉስ

## ምዕራፍ ፩ ክፍል ፩

፩. እመቤቴ የተመረጥሽ ድንግል ማርያም ሆይ በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ አምላክ ካንቺ ጋራ በመሰደዱ በግብፅ መከራሽ እማልድሻለሁ፡፡

፪. መንገድ በመሄድ የድካምሽ አሳብ በልጅሽ ፊት ይቁም ስለ ኃጢአቴ መማለጃ ይሆን ዘንድ፡፡

፫. በምድረ ግብፅ ያገኘሽ የረኃብና የድምፅ ሐሳብ በበኩር ልጅሽ ፊት ይቁም ስለ ኃጢአቴ ማቃለያ ይሆን ዘንድ፡፡

፬. ካይንሽ የፈሰሰው የዕንባ ጎርፍ በፊትሽ የተንጠባጠበው በልጅሽ በወዳጀሽ ፊትም የወረደው፡፡ አሁንም ደግሞ በልጅሽ በወዳጅሽ ፊት ይቁም ስለ ኃጢአቴ ማዘከሪያ ይሆን ዘንድ፡፡

፭. የሠራሁትን ኃጢአት ባስበው ልቡናዬ እጅግ ደነገጠብኝ፡፡ አእምሮ ሳለኝ አለል ዘለል እያልኩ በጽርዓት መኖሬን ባሰብሁት ጊዜ ልቡናዬ እጅግ ደነገጠ፡፡

፮. የኃጢአቴን ብዛት በተቆጣጠርሁ ጊዜ ልቡናዬ እጅግ ደነገጠ አንድ ሰዓት ስንኳን ኃጢአት ለመስራት አላቋረጥኩም፡፡

፯. በሰውና መላእክት ጉባኤ መሐከል ራቁቴን መቆሜን አሰብሁ፡፡ በዓይነ ልቡናዬ እመለከት ዘንድ ወዲህና ወዲያ ተመላለስሁ፡፡ ምናልባት የሚረዳኝ ባገኝ፡፡ ከዚህ እጅግ የሚያስፈራው ከሠራሁት ኃጢአት ፍዳ የተነሣ ምናልባት የሚዋሰኝ ባገኝ ብዬ፡፡

፰. ነገር ግን በማማለድ እኔን ለማዳን የምትችይውን አንቺን አማላጅ አገኘሁ፡፡ ዘወትርም ከኔ እንዳትርቂ ዐወቅሁ፡፡

፱. እንዲህ በፍቅር ያዝሁሽ በጣቶቼ አይደለም በሃይማኖት ያዝሁሽ በመዳሰስ አይደለም በእደ ሕሊና ያዝሁሽ በእደ ሥጋ አይደለም፡፡

፲. እደ ሕሊናየን ግን የሰው ኃይለኝነት ሊያስተወው አይችልምና፡፡ የሰይፍ ስለትም ሊቆርጠው አይችልም፡፡

፲፩. ልትደገፊኝ ያዝሁሽ ልትጥይኝ ግን አይደለም ወደላይ ከፍ ከፍ ልታደርጊኝ ያዝሁሽ ወደ ታች ልታወርጅኝ ግን አይደለም፡፡

፲፪. ለዘለዓለሙ ያዝሁሽ ለዕድሜ ልክ ብቻ አይደለም፡፡ እናቴ ሆይ ነፍሴ ባንቺ ዘንድ ትክበር ስለቸርነትሽም እመቤቴ ነሽ፡፡ ስለ ፍቅርሽ የታመንሽ ስለ ልጅሽም የመድኃኒት ቀንድ ሆይ አስቢኝ እንደ ወደቅሁም እቀር ዘንድ አትርሺኝ፡፡

## ምዕራፍ ፪ ክፍል ፪

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ እናት ልጅዋን ትረሳለችን የወለደችውንስ አትምርምን፡፡

፪. ምንም እናት ልጅዋን ምንም የሆዷን ፍሬ ባታስብ አንቺ ግን አስቢኝ አትርሺኝ ሁልጊዜም በልብሽ አኑሪኝ በአፍሽ የተጠራሁ በፊትሽም የተቀረጽሁ ልሁን፡፡

፫. ኃጢአቴም እንደ መጋረጃ ሁኖ በኔና በእግዚአብሔር መሐከል ቢጋረድ የጸሎቴንም ማረግ ቢከለክል ነቢዩ ኢሳያስ እንደ ተናገረ እንዲህ ሲል፡፡

፬. እንዲህ ይላል እግዚአብሔር የሰራዊት ጌታ በውኑ ዓይኖቼ አያዩምን? ጆሮየስ አይሰማምን? ነገር ግን ኃጢአታችሁ በኔና በናንተ መሐከል ይቆማል (ኢሳይያስ)

፭. አንቺ ግን እመቤቴ የተመረጥሽ ድንግል ማርያም ሆይ በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የኃጢአቴን መጋረጃ አስወግጅ አርቂው እመቤቴ ሆይ፡፡

፮. ጸሎቴ እንዲያርግ ኃጢአቴንም ለማቃለል ወደልጅሽ ጆሮ እንዲገባ ከኔ ዘንድ ያለ ጸሎት ወደ ልጅሽ ጆሮ ይላክ፡፡ ከርሱም ዘንድ ይቅርታ ወደኔ ይምጣ ከሥጋ ርኩሰት ያነጻኝ ዘንድ ከሥራዬም ፍዳ ያድነኝ፡፡

፯. መሃይምናንነ የምትጋርድ የጽድቅ ጋሻ ድንግል ሆይ፡፡ መናፍቃንንም የምታሸብራቸው ለጸላት ከመሸነፍ አድኚኝ፡፡

፰. ለጸላት መሸነፍ እንደ እሳት ነበልባል ልብ ያቃጥላልና ፊትም እንደ ዋሻ ጨለማ ያጠቁራል ደስ ላለው ሰው ልብ ምልክቱ ብሩህ ፊት ነው፡፡

፱. በመጋደል ጊዜ ፈሪ በመፋጠንም ጊዜ ደካማ አታድርጊኝ፡፡

፲. ድንግል ሆይ የፍቅርሽ ብርሃን እንደ ፀሐይ ብርሃን ዓይነ ልቡናዬን አበራው እንደ ፀሐይ ብርሃን ጧት ሲነጋ እንደሚወጣው፡፡ እንዲሁም የፍቅርሽ ብርሃን ከራሴ ጀምሮ እስከ እግሬ ድረስ ተዘረጋ፡፡

፲፩. የደም ግባትሽ ማዳነቅም በኔ ዘንድ የተደነቀ ሆነ፡፡ ላህይሽም እንደ ሜላት ግምጃ የተወደደ ነው፡፡

፲፪. የዘውድሽም ብርሃን ዕሩይነቱም በሦስት ኅብር እንደ ተቀረጸ ቀስተ ደመና አስተያየቱ ያማረ የተወደደ ነው፡፡

፲፫. ነጫጭንም አበባ እንደሚያብብ እንደ ናርዶስ፡፡ በገነትም እንደሚያቅላላ እንደ ሮማን አበባ በየጫፉም እንደሚያፈራ እንደ ወይን ፍሬ ነው፡፡

፲፬. የሽልማትሽ ጌጥም እጅግ ያማረ የተወደደ በሰውና በመላዕክት ዘንድም የተደነቀ ነው፡፡

## <u>ምዕራፍ ፫ ክፍል ፫</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ሆይ ራሴን ለስምሽ ዘፋኝ አማሪት አደረግሁ፡፡ ልቡናዬም ለድንግልናሽ ምስጋና በማኅሌት ለማገልገል ይወዳል፡፡

፪. ሙሴና የእስራኤል ልጆች ሁሉ የኤርትራን ባሕር በተሻገሩ ጊዜ ለእግዚአብሔር ምስጋና ዘፈኑ አገለገሉ፡፡ እንዲህ ሲሉ ምስጉን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፡፡ (ዘፀአት ፲፭ ፣ ፩፡፡)

www.ethiopianorthodox.org

፫. የአሮን እኅት ማርያም እርሷም ደግሞ ከእስራኤል ልጆች ጋራ ስለ ፈርዖንና ስለ ሠራዊቱ መስጠም፡፡ የወገኖቿም ልጆች ከባሕር በደህና ስለወጡ ዘፈነች እንዲህ ስትል፡፡

፬. የእግዚአብሔር ሥራ ይደነቃል ፈረሱንና የሚቀመጠውን ወደ ባሕር ጣለው፡፡ (ቁ ፣ ፩ ፡ ፡)

፭. ዳዊትም እግዚአብሔርን ስለማመስገን ዘፈነ ከጦር አድኖታልና ከሳኦልም እራራለት፡፡ ከአቤሴሎምም ከልጁ፡፡

፮. አሳፍና የቆሬ ልጆች ለእግዚአብሔር መገዛት ዘፈኑ ኢሳይያስም ስለ ራሳቸው ትካዝ ስብሐተ ፍቁር የወዳጁንም ዘፈን ዘፈነ፡፡ ዲቦራም ስለ ሲሳራ ሞት ዘፈነች፡፡

፯. ሰሎሞንም ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያኑም ዘፈነ፡፡ እኔም ደግሞ ስለ ውዳሴሽ እራሴን ዘፋኝ አማሪት አደረግሁ፡፡ (ቁ ፣ ፩ ፡ ፡)

፰. እግዚአብሔርንም ባመሰገንሁ ጊዜ ባንቺ ለስሙ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በስምሽም ጸሎቴን ለልጅሽ አቀረብሁ፡፡

፱. ላንቺም በዘፈንሁ ጊዜ ለልጅሽ ዘፈንሁ በገናዬም መሰንቆዬም አንቺ ነሽና፡፡

፲. ደስ ብሰኝ ባንቺ ደስ እሰኛለሁ፡፡ ባዝንም ናንቺ እጽናናለሁ፡፡ መከራና ችግርም ቢያገኘኝ ወዳንቺ እጮሃለሁ፡፡

፲፩. ያመፀኛም ምላስ ቢያስከፋኝ ወዳንቺ ፊት እማለላለሁ፡፡

፲፪. ሰወነቴም የወደደችው ነገር ቢኖር አንቺን አለምናለሁ፡፡ በመታመን የሻሁትንና የተመኘሁትንም ባንቺ አገኛለሁ፡፡

፲፫. መታመን ያድናል ሃይማኖትም ያስቀናል መታመን ያነጻል፡፡ ሃይማኖትም ያራቅቃል መታመን ተስፋ ያደርጋል ሃይማኖትም ይሰጣል፡፡ መታመን ይጀምራል ሃይማኖት ይፈጽማል፡፡

፲፬. መታመን ያጋድላል ሃይማኖት ይጋርዳል፡፡ ሃይማኖት ተራራ ያፈልሳል ወደ ደፈረሰው ባሕር ጌታ በወንጌል እንደ ተናገረ እንዲህ ሲል፡፡

፲፭. የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል ሃይማኖት ቢኖራችሁ ይህንን ተራራ ከዚህ ተነስተህ ወዲያ ሂድ ብትሉት ይሔዳል፡፡ (ማቴ ፣ ፲፯ ፣ ፳ ፡ ፡)

፲፮. ይህችን ሾላ ከስርሽ ተነቅለሽ ወደ ባሕር ውደቂ ብትሏት እንደ ተናገራችሁ ይሆናል፡፡

፲፯. ጳውሎስም እንዲህ አለ ለሚያምን ሁሉ ይሆንለታል፡፡ ስለሚጠራጠሩትም ሐዋርያት እንዲህ አለ፡፡ ሁለት ልብ ያለው ሁሉ በመንገዱ ሁሉ የጸና አይደለም፡፡ (ያዕ ፩ ፣ ፰ ፡ ፡)

፲፰. ደግሞ እንዲህ አለ ተጠራጥሮ የሚለምን ነፋስ የሚመታውን የሚመልሰውን የባሕር ሞገድ ይመስላል፡፡ (ቁ ፮ ፡ ፡)

፲፱. ደግሞ የሚጠራጠር ልቡናውም የሚወላውል በአፉ እንጀራ ይዞ የሚሄድ ውሻ ይመስላል፡፡ ሁለተኛውም ውሻ ተከታተለው ሲደነባበሩም ከትልቅ ባሕር ዳር ደረሱ፡፡ ጥላውንም በውሀ ዳር አየ፡፡ እንጀራ ይዞ በውሃ ውስጥ ሌላ ውሻ ያለ መስሎት ያንን ያፋን እንጀራ ትቶ ከውሀው ውስጥ ገባ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፳. ያም የተከተለው ሁለተኛው ውሻ ያንን እንጀራ ይዞ ሄደ፡፡ ያ ግን ከባሕሩ ወጥቶ ያንንም ሁለቱንም አጣ፡፡ ያንንም ይህንንም አላገኘም፡፡

፳፩. እንዲሁም እየተጠራጠረ የሚጸልይ ሁሉ ዋጋውን አያገኝም፡፡ የጸሎቱ ዋጋ ለሌላ ሳይጠራጠር ለሚጸልዩ ይሆናል እንጂ፡፡ (ቁ ፯ ፡፡)

፳፪. ስለዚህም እኔ በጸሎትሽ ለመታመን ተጋሁ፡፡ ድንግል ሆይ የልጅሽ መታመን ከልቦናዬ አይወጣም፡፡ ፍቅርሽም ከልቦናዬ አይናወጥም፡፡

፳፫.አዳም ችግርም ቢያገኘኝ ባንቺ እታመናለሁ፡፡ አንቺ በጸሎትሽ እንድትፈጽሚልኝ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፬</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ በወርቅ ግርግዳ ላይ የተሰራሽ የዕንቁ ጉልላት አንቺ ነሽ፡፡

፪. ለራሴ ጌጥ ቀጸላ ሁኚኝ፡፡ የምስጋናሽ ፍጻሜ ወዳለበት እደርስ ዘንድ በክንፈ ሕሊናዬ ወዳየር ተነጠቅሁ፡፡ ሃሳቤም ልምሾ ሁና ተመለሰች፡፡ ከምስጋናሽ ከእኩሌታው እኩሌታ ሳትደርስ፡፡

፫. ዳግመኛም ውዳሴሽን ወደማወቅ ባሕር ልዋኝ ወደድሁ ወደ ክብርሽ ገናንነት ወደብ እደርስ ዘንድ ደከምኩ ያንዲቱን ማዕበል ሞገድ ያህል ስንኳን አላለፍሁም፡፡

፬. ወደ ጽርሐ አርአያም ጠፈር ለመድረስ የሚቻለው ማነው፡፡ ከምድር በታች ወዳለው ባሕር መሠረትሽ መዋኘት ማን ይችላል፡፡

፭. ድንግል ሆይ ክብርሽን ገናንነትሽን ጠንቅቆ ለመናገር የሚቻለው ማን ነው፡፡ በመሃይማን ዘንድ ስምሽ የጣፈጠ ነው፡፡ ከምስጋናሽ ጋራ በጠሩሽ ጊዜ፡፡

፮. ሃይማኖታቸው በቀና ምዕመናን ሁሉ አፍ ስምሽ ጥዑም ነው፡፡ ከውዳሴሽ ጋራ በጠሩሽ ጊዜ፡፡

፯. በቤተክርስቲያን ሁሉ አፍ ስምሽ የጣፈጠ ነው ከምስጋና ጋራ በጠሩሽ ጊዜ ስምሽ ከወተት ከማር ወለላ የጣፈጠ ነው፡፡

፰. የድንግልናሽን ኃይል የሚሰድብ ያለዘር ያለሩካቤ ፀንሰሽ ያለ ዘር ያለሩካቤ እንደወለድሽ የማያምን ርጉም ነው፡፡

፱. ከርኩሰት ሁሉ ንጽሕት ከኃጢአትም ሁሉ የጸራሽ እንደሆንሽ የማያምን ርጉም ነው፡፡

፲. ካንቺ የተወለደው እግዚአብሔር እንደሆነ የማያምን እርሱንም ከወለድሽ በኋላ በድንግልና እንደኖርሽ የማያምን ርጉም ነው፡፡

፲፩. የማያከብርሽ ለልዕልናሽም የማይሰግድ ለዘለዓለሙ ርጉም ነው፡፡ በፍጹም ልቦናው የማይወድሽ ከትልቅ ሀሳቡም የማያከብርሽ ርጉም ነው፡፡

፲፪. በከንፈሮቹ የማያመሰግንሽ ባንደበቱም የማይመርቅሽ ርጉም ነው፡፡ ለክብርሽ የማይሰግድ ለገናንነትሽ የማይገዛ ዕድል ፈንታው ጽዋ ተርታው ገሃነመ እሳት ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፫. ድንግል ሆይ የሚወዱሽ የተወደዱ ናቸው፡፡ ንግስት ሆይ የሚያከብሩሽ የከበሩ ናቸው፡፡ ንጽሕት ሆይ የሚቀድሱሽ ሁሉ የተቀደሱ ናቸው፡፡ ፍሥሕት ሆይ የሚመርቁሽ የተመረቁ ናቸው፡፡

፳፬. ልዕልት ሆይ የሚያደንቁሽ የተደነቁ ናቸው፡፡ ውድስት ሆይ ለንግሥትነትሽ የሚገዙ ሁሉ የተባረኩ ናቸው፡፡

፳፭. አሁንም ከስንፍና እንቅልፍ እንንቃ፡፡ የልጅሽ የወዳጅሽን ምሥጋና በሚያስቀር በክቡድ እንቅልፍ እንደ በድን አንሁን፡፡

፳፮. አንቺም ደግሞ ቀኝ እጅሽን ዘርጊ እኔን ከመኝታዬ ለማንሣት ከሰው ደም የተጸማ ጸላት ለጸሎት ሊነቁ በወደዱ ጊዜ ባይን ቅንድን ላይ እንቅልፍ ያበዛልና፡፡

፳፯. በማንቀላፋትም ሽፋሽፍትን ይሰብራል፡፡ ምሥጋናንም ስለማስታጎል ይህን ሁሉ ይተናኮላል፡፡ ቢነቁም እንቅልፍ ከዓይን ቢርቅ የዚህን ዓለም ንብረትና ውዳሴ ከንቱ በማሳሰብ ደግሞ ይተናኮላል፡፡

፳፰. ሰይጣን ከቶ እንደ ጸሎት ማስታጎል የሚወደው የለም፡፡ ጸሎት ፍላጻ ነውና ዓይኑን ይወጋዋል፡፡ ከሚጸልዩ ሰው አንደበት እሳት ወጥቶ ሰይጣንን ያቃጥለዋልና፡፡ ሰይጣንም ስለዚህ ከበጎ ሥራ ሁሉ ጸሎትና ትጋትን ይጠላል፡፡

፳፱. ይልቁንም ያንቺን ምስጋና ወሬ ሲሰማ በብስጭት ጥርሱን ያፋጫል የምስጋናሽ ወሬ በርሱ ዘንድ መራጃ ነውና ራሱን ይቆርጠዋል፡፡

፴. ከስምሽ አጠራር የተነሣ መብረቅ በኃይል ሲጮህ እንደ ሰማ ሁሉ ይደነግጣል፡፡ አንቺ ከተወለድሽ ጀምሮ ፈጽሞ ዕረፍት አላገኘም፡፡

፴፩. ባንቺ ታመመ በልጅሽም ተጨነቀ ባንድ ልጅሽ መስቀል ሥቃይ አገኘው፡፡ ከፍጡራን ወገኖች ሁሉ ይልቅ ሰይጣል አንቺን ይጠላል፡፡

፴፪. በግብር አምላካዊ አምላክን ለመውለድ በመፅነስሽ ጊዜ እርሱ በአይሁድ ልቡና ዕንቅፋትን አገባ፡፡ እንዲህ ሲል በዘር በሩካቤ እንደተወለደ ከዩሴፍ እንደሆነ፡፡

፴፫. በአይሁድ ልቡና ቅናትን አሳደረ በልጅሽም ላይ እንዲተባበሩ የግድ አላቸው እንዲሰቅሉትም እሺ በጎ አሰኛቸው፡፡

፴፬. ሰቅለውም ርኩሳን አይሁድ ምራቃቸውን በፊቱ እንዲተፉበት እስኪሞትም ድረስ ስርግርግ ለማለቱ መፃፃውን ከሐሞት ጋራ እንዲያጠጡት አደረጋቸው፡፡

፴፭. ሙቶም ከተቀበረ በኋላ በመቃብሩ ጠባቂዎች እንዲሾሙ አይሁድን ዘበዘባቸው ጠባቂዎች እንደተነሣ በነገራቸው ጊዜ ዳግመኛ ዘበዘባቸው፡፡

፴፮. ለጠባቂዎቹ ወርቅ እንዲሰጧቸው የትንሣኤውን ምስክርነት ያሳብላቸው ዘንድ ሌሊት እኛ ተኝተን ደቀ መዛሙርቱ መጥተው ሠርቀው ወሰዱት እንዲሉ አስተማራቸው፡፡ (ማቴዎስ ፳፰ ፣ ፲፪- ፲፫ )

፴፯. በዕረፍትሽም ጊዜ የአይሁድን አርበኞች በልጅሽ ደቀ መዛሙርት ላይ በጠላትነት አስነሣ በድንሽን ጥለው እስከ ሽሹ ድረስ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ሰይጣን አንቺን ይጠላልና፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# <u>ምዕራፍ ፭ ክፍል ፲፭</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ እንግዲህ በርሱ ላይ አሰልጥኝኝ እራሱን እረግጠው ዘንድ፡፡

፪. በበኩር ልጅሽ መስቀል ፍላፃ እነድፌው ዘንድ አሰልጥኚኝ፡፡ ሰለባ የሌለው ይህን ኀስቋላ እገለው ዘንድ ንግሥት ሆይ አሰልጥኝኝ፡፡

፫. ንግሥት ሆይ ይህን በመለኮት ሰይፍ ራሱን እቆርጠው ዘንድ፡፡ ንግስት ሆይ ይህን ዕቡይ ትዕቢተኛ እሳለቅበት ዘንድ ተይኝ፡፡

፬. የልጅሽ እጅ የጸናው ክንዱም በኔ እጅ ይዞ ይጣለው መንፈሳዊ ረቂቅ ኃይሉም ጥልቀቱም ወደማይታወቅ ርዝመቱም ወደማይገኝ ወደ ገሃነም ገደል ይጣለው፡፡

፭. የሲኦልንም መዝጊያ ይቆልፍበት ይህ ሐሰተኛ ቀማኛ ከውስጧ እንዳይወጣ፡፡

፮. በድንግልናሽ ላይ የስድብ ነገር ስለ ተናገረ ቀናሁ፡፡ መንፈሳዊውንም ፅንስሽን ስላሳበለ ቀናሁ በድንግልና መውለድሽንም ስለሰደበ ቀናሁ፡፡

፯. በናዝራዊው በልጅሽ ላይ የአይሁድን ልቡና ስላከፋበት ቀናሁ፡፡ የዓለም መድኃኒት ርሱን እንዲገድሉ ስላስጨከናቸው ቀናሁ፡፡ ስላንቺም ስድብ ስለ ልጅሽም ቀናሁ፡፡

፰. በመዝሙር እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ የቤትህ ቅናት በልታኛለችና፡፡ የሚላገዱህ መላገድ በላዬ ወደቀ፡፡ (መዝሙር ፹፱ ፣ ፱)

፱. ነቢዩ እንግዲህ አንቺን የእግዚአብሔር ቤት አለሽ፡፡ የሚላገዱህ መላገድ በላዬ ወደቀ ያለውም የአይሁድ ተናግሮት ነው፡፡ ሰይጣን ካስተማራቸው ምቀኝነት የተነሣ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ የተናገሩት ስድብ ነው የዮሴፍ ልጅ ነው ሲሉ፡፡ (ሜቴ ፣ ፲፫ ፣ ፶፭ )

፲. የእግዚአብሔር ሀገር ሆይ እኔ ስላንቺ ደስ እሰኛለሁ ነቢያት ፀሐይን ለመውለድ እንደተዘጋጀች ጎሕ ያዩሽ ነባቢት ኤዶም ሆይ ባንቺ ኃሜትን አደርጋለሁ፡፡

፲፩. ሰሎሞን ወንድምሽ እንደተናገረ እንዲህ ሲል ይህች ማናት እንደ ማለዳ ብርሃን የምትታይ፡፡ (መኃ ፣ ፮ ፣ ፲)

፲፪. ዳግመኛም እርሱ መሸከሚያ ብሎ ጠራሽ ተናግሯልና እንዲህ ሲል፡፡ ሰሎሞን ለራሱ መሸከሚያ አሠራ፡፡ (መሐ ፣ ፫ ፣ ፱)

፲፫. ልጅሽ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰሎሞን ይባላል ሰሎሞን ማለት ፍቅር ሰላም ማለት ነው ጳውሎስ እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ በመስቀሉ ሰላምን አደረገ ድልንም ገደለው፡፡

፲፬. ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን አንቺን ሊያዩ ወደዱ አላዩም ምሳሌሽን እንጂ፡፡ የልጅሽን የመለኮትነቱን ምሥጢር ያየን እኛ ግን በቅድስት ጠረጴዛ ሥጋውንና ደሙን ቁርባኑን ተቀበልን አንድ አካል አንድ አምሳል በመሆናችን የተመሰገንን ነን፡፡

፲፭. የእግዚአብሔር ልጅ ትሕትናው የተደነቀ ነው፡፡ ይህ የተደነቀ ትሕትና እንደምን ያለ ነው፡፡ ለዚህ

www.ethiopianorthodox.org

አንክሮ ይገባል፡፡

፲፮. እንደዚህ ያለ ትሕትና ያሣየው ነው ሥጋውን ቆርሶ ሰጠን፡፡ ንጹሕ ሥጋውን በማዋሐድ ሥጋቸንን ለማንፃት፡፡

፲፯. የመድኃኒቱን ጽዋ ደሙን ሰጠን፡፡ በክቡር ደሙ ደማችንን ለማክበር በደቀ መዛሙርቱ ላይ መንፈስ ቅዱስን በንፍሐት በማሳደሩ ለኛ መንፈስ ቅዱስን ሰጠን፡፡ መንፈስ ቅዱስን በመስጠት ነፍሳችንን ለመቀደስ ከርሱም ጋራ ሊያስተካክለን ወራሾችም ሊያደርገን፡፡

## ምዕራፍ ፮

፩. ኑ እንግዲህ ይህችን ንጽሕት በግ እናክብራት እናግናት የድኅነታችን መሥዋዕት የሚሆነውን በግ ወልዳልናለችና፡፡

፪. ንጹሑን የዝናም ውሃ የተሸከመችልን የብርሃን ደመና እርሷን እናግናት እናትነት ከድንግልና አስተሳብራ የያዘች እርሷን ኑ እናመስግናት፡፡

፫. እስከ ዘለዓለሙ ድረስ ለአብርሃም ልጆች መመኪያ የሆነች እርሷን ኑ ክብሯን ገናንነቷን እንናገር፡፡

፬. ቅድስተ ቅዱሳን የተባለችውን ሁለተኛ ክፍል እርሷን ኑ እናመስግናት በዚች ሕግ በዚህችም ኪዳን አለባት፡፡ ሙሴም በኦሪት የተጻፈውን ለሕዝቡ ከነገረ ወዲያ ድንኳኑንም የሥራቸውንም ዕቃ ሁሉ ንዋየ ቅድሳቱን ይረጫል፡፡ (ዘፀአ ፣ ፳፬ ፣ ፰)

፭. እንዲሁም ልጅሽ ለደቀ መዛሙርቱም የወንጌልን ሕግ ካስተማራቸው በኋላ በዕንጨት መስቀል ላይ ራሱን ሠዋ፡፡ ባምላካዊ ደሙ ፈሳሽነትም መሃይማኑን የተቀቡ አደረጋቸው፡፡

፮. መለኮት የተዋሐደው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በውነት ነው፡፡ ይህ ደም ስላፈሰሰው ወንድሙን እንደሚከስ እንደ አቤል ደም አይደለም፡፡

፯. እግዚአብሔር ቃየልን እንደተናገረው እንዲህ ሲል የወንድምህ የደሙ ቃል ወደኔ ደረሰ፡፡ (ዘፍጥ ፣፬ ፲ )

፰. የሕዝብና የአሕዛቡን ኃጢአት የሚያርቅ ነው እንጂ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ እንደነገራቸው እንዲህ ሲል ኃጢአት በሚሠረይ ገንዘብ ስለ እናንተ የሚፈስ ደሜ ይህ ነው ንሡ ጠጡ፡፡ (ማቴ ፳፮ ፣ ፳፮ ፣ ፳፰ )

፱. ይህ ደም ስለ ወይኑ ቦታ እንደሞተ እንደ ኢይዝራኤላዊው፡፡ እንደ ናቡቴ ደም አይደለም፡፡ (፩ ነገ ፳፩ ፣ ፲፫ )

፲. ለበጎቹ ቤዛ የተሰቀለ የናዝሬቱ ኢየሱስ አምላካዊ ደም ነው እንጂ፡፡ (ዮሐ ፣ ፲ ፣ ፲፩ )

፲፩. ይህ ኃጢአትን ለማራቅ የማይችሉ የአሮን ልጆች እንዲሠዉት ላም ደም አይደለም፡፡ የዓለሙን ኃጢአት የሚሸከም የእግዚአብሔር በግ ንጹሕ ደም ነው እንጂ፡፡ (ዕብራውያን ፲ ፣ ፬ ፣ ፭ )

፲፪. ይህ ደም በቀራንዮ የፈሰሰው ነው፡፡ በአሥራ አንደ ሰዓት ጊዜ የአይሁድ ፋሲካ አለፈ ይህም ደም ዘወትር የሚቀዳው ፈሳሽነቱም እስከ ዘለዓለሙ የማይደርቅ ነው፡፡

፲፫. ይህ ደም የኔ ዋጋ የዕዳዬም ከፋይ ነው፡፡ እኔ በዚህ ደም ተማጥኜአለሁ ዕድል ፈንታዬ ጽዋ ተርታዬ ፍሬ ከሌላቸው ጋራ እንዳይሆን፡፡ ይህም ካንቺ ሰው የሆነው አምላክ ደም የሚረባኝ የሚጠቅመኝ ይሁነኝ፡፡

፲፬. ቅድስት ድንግል ሆይ በክርስቶስ እንድድን በክርስቶስም እንድኖር በክርስቶስም ነፍሳትን ከሚውጡ አባቦች እንድቤዝ አድርጊኝ፡፡

## ምዕራፍ ፺

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ ፍጡራንን ሁሉ ከሚጎዳ ደዌና መከራ አድኝኝ፡፡

፪. በጉጉት በሰጎን ተመስለው ከሚያሳቱ አጋንንት አድኝኝ፡፡

፫. አስማት ከሚጽፉ ጠልሰም ከሚጠለስሙ በዖፍ ከሚያመልኩ በእሳት ከሚያሚርቱ ጠጠር ጠርበው ከሚጥሉ ጠንቋዮች ዕንጨት ጠርበው ደንጊያ አለዝበው ከሚያመልኩ አድኝኝ፡፡

፬. ከዛፍ እግር ከተራራ ሥር ለጣዖት ለአጋንንት ከሚሠዉ፡፡ በፀሐይ በጨረቃ በከዋክብት ከሚያመልኩ በመጻሕፍት ምልክት ከሚጠነቁሉ አድኝኝ፡፡

## ምዕራፍ ፺፩

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ ይህንን ሁሉ ከመሥራት ይህንንም ሁሉ ከሚሠራ አድኝኝ፡፡

፪. እኔ ግን በልጅሽ ልኖር በባሕርይ አባቱም ልድን በመንፈስ ቅዱስም እጅ ልጠበቅ እወዳለሁ፡፡ በሦስትነቱ የሃይማኖት ፈትል ተይዤ ልኖር እፈቅዳለሁ፡፡

፫. የተሸበረ ፈትል ፈጥኖ አይቆረጥምና ሦስቱ ሥላሴን በማመን ደንጊያ መሠረት የታነፀውን የሲኦል አጋንንትን አይችሉትም አይበረታቱበትም (ማቴዎስ ፲፮ ፣ ፲፰ )

፬. እሊህም ደግሞ እንደመጣባቸው የሚገሡ እንዳገኙ የሚጠቅሱ መናፍቃን ናቸው፡፡ ቅድስት ቤተክርስቲያን ትንቢት የተናገረችባቸው እንዲህ ስትል ቀበሮችን አጥምዳችሁ ያዙልን፡፡ ጥቃቅኑንም ቀበሮች የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ወይናችን አብቧልና፡፡ (መሐ ፣ ፪ ፣ ፲፭)

፭. ድንግል ሆይ በሰንካላው ጉዳጎድ ጎዳና ከመሄድ እንድርቅ፡፡ በቀናው ጎዳናም እንድሄድ አድርጊኝ፡፡

፮. ድንግል ሆይ ዶሮ ገላግልቶቿን በክንፎቿ በታች እንድትሠውር በክንፈ ረድኤትሽ ጥላ ሠውሪኝ፡፡

፯. ድንግል ሆይ ያማረ የተወደደ የነቢያት ነገር ተነገረልሽ ያማረ የተወደደ ምስጋናም ስላንቺ ተደረገ፡፡ የአብ ልዑል ክንዱ ከደነሽ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ክንፉ ጋረደሽ አንድ ልጁ ካንቺ ሰው በሆነ ጊዜ፡፡

፰. መልአኩ ገብርኤልም ባበሰረሽ ጊዜ ይህ አካላዊ ቃል ከገብርኤል ብስራት ጋር በሆድሽ ገባ፡፡ በመሐል እጁ የሚሸከም እርሱ ሲሆን ተሸከምሸው፡፡

፱. ሳይሰማ ወዳንቺ መጣ ሳይታይ ወረደ፡፡ ሳይታወቅ ተፀነሰ፡፡ ወንጌላዊ እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ በኩር ልጅዋን እስከ ወለደች ድረስ ዮሴፍ ደንግል ማርያምን አላወቃትም፡፡ (ማቴ ፩ ፣ ፳፭ )( ሉቃስ ፪ ፣ ፯ )

፲. ስለዚህ ነገር የሳቱ የተሰናከሉ ብዙዎች ናቸውና ከወለደች በኋላ ዮሴፍ በግብር ዐወቃት በማለት፡፡ እነዚህንም መናፍቃን የኤጲፋንዮስ መጽሐፍ ፀረ ማርያም ይላቸዋል፡፡

፲፩. እርሳቸውም ለራሳቸው የሐሰት ምክንያት አደረጉ፡፡ መጽሐፍ በተናገረው ቃል እንዲህ ሲል፡፡ አዳም ሔዋንን ዐወቃት ቃየልም ዳግም ሚስቱን ዐወቀ፡፡ (ዘፍጥ ፬ ፣ ፩-፲፯)

፲፪. በነገሥትም መጽሐፍ ደግሞ እንዲህ ይላል አቢሳን ዳዊት አላወቃትም (፩ ነገ ፩ ፣፬)

፲፫. ይህንን ነገር ምክንያት አድርገው ወደ ድንግል መለሱ፡፡ ከወለደች በኋላ ከዮሴፍ ተገናኝች በማለታቸው፡፡

፲፬. ዐወቃት ማለት ግን ወደ ሁለት ነገር ይተረጎማል፡፡ ከማወቅ ወዳለማወቅ ከመገናኘት ወዳለመገናኘት ወንጌላዊ ግን የበሕር ልጅዋን እስከ ወለደች ድረስ ዮሴፍ ድንግልን አላወቃትም ማለቱ አምላክ በሆዷ ስላለ የድንግል መልኳ ይለዋወጣልና ነው፡፡

፲፭. መልኩ በሆዷ በተለዋወጠ ጊዜ ከርሱ ጋር እንደርሱ መልኳ ይለዋወጣል፡፡  እንደ ንጹሕ ብርሌ መልክ በውስጡ ባኖሩበት ጊዜ ውሀ መስሎ እንዲታይ፡፡

፲፮. የወይን ጠጅም ባኖሩበት ጊዜ የወይን ጠጅ መስሎ እንዲታይ በውስጡም ያለ ቀይ ነገር ቢሆን እንዲቀላ፡፡ ቁጽልጽልም ቢሆን እንዲቁለጸለጽ፡፡

፲፯. ድንግልም እንዲሁ የልህዋ መልክ በሆዷ በተለወጠ ጊዜ የርሷ መልክ ከርሱ ጋራ እንደርሱ ይለዋወጣል፡፡ (ቁ ፣ ፲፭)

፲፰. እንደ ሮማን አበባ የምትቀላበት ጊዜ አለ፡፡ እንደ ናርዶስ አበባ የምትነጣበት ጊዜ አለ፡፡ እንደ ጽጌረዳ የምታንጸባርቅበት ጊዜ አለ፡፡ እንደ ገነትም ተክል የምትለመልምበት ጊዜ አለ፡፡

፲፱. ከወለደች በኋላ ግን መልኳ አልተለወጠም፡፡ በመልኩ መለወጥ መልኳን የሚለውጠው ልጅዋ መለኮት ከርሷ ከነሣው ትሰብእት ጋራ ከሆዷ ወጥቷልና፡፡ የልዑል ኃይሉ ሥራም ፍጹም ገናና ነው፡፡ ፍርዱም እውነት ነው፡፡ የስሙ ምስጋናም ብሩክ ልዑል ነው፡፡

## ምዕራፍ ፱  ክፍል ፲፰

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለች የተመረጠች ድንግል ማርያምን ወደዳት አከበራት ከፍ ከፍ አደረጋት፡፡

፪. በሁሉ ላይ አሰለጠናት፡፡ ሁሉን አስገዛላት፡፡ አምላክን በድንግልና የወለደች እርሷም የንጽሕና የቅድስና መሠረት ሆነች፡፡

፫. አቤቱ ሆይ ክብሯን ገናንነቷን በመረዳት አመሰግናት ዘንድ ለልቡናዬ ድምር ዕውቀትን ስጥ፡፡

፬. አቤቱ ሆይ ላንደበቴ ኃይለ ቃሉን ስጥ የማጎፀኗን መክበር የድንግልንዋን ነገር አወራ ዘንድ፡፡

፳፮. እርሷም ደግሞ እኔን ለማዳን የታመነች ናት፡፡ ለድንቁርናዬም የበጎ ምስራች ወሬ ናት፡፡

፳፯. ለእጆቼም የቅድስና አምባር ለእግሮቼም እውነተኛ ጎዳና ላንገቴም ድሪ አሸንክታብ ለራሴም አክሊል ዘውድ ላፌም የጣፈጠ እንጀራ ላፍንጫዬም የሸቱ መዓዛ ለመዋረዴም ከፍታ፡፡ ለሕመሜም ጤና ናት፡፡

፳፰. ድንግል ሆይ ንጽሕናን እንደ መላእክት የለበስሽ እንደ ነቢያትም መንፈስ ቅዱስን የተመላሽ ሁሉንም አቸናፊ በሚሆን በልዑል እግዚአብሔር እጅ የታነፅሽ የመለኮት ማደሪያ ነሽ፡፡

፳፱. የአሕዛብ ብርሃን የነገስታት ኃይል የምድር መሠረት የሰማይ ጽናት የአየር ርቀት የባሕር ጥልቀት የደመና ግዘፍ የዝናማት መታዘዝ፡፡ የፀሐይና የጨረቃ የከዋክብት ፀዳል አንቺ ነሽ፡፡

፴. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ደንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ በሁሉ ተመሰልሽ በሁሉም መሰሉሽ አንቺን ግል የሚመስልሽ የለም፡፡

፴፩. ሰማይ አይተካከልሽም ምድርም የሆድሽን ስፋት ያህል አትሆንም የማትችለውን ችለሽዋልና፡፡ የማትሸከመውንም ተሸከምሽ፡፡

፴፪. ኪሩቤል የልጅሽ ሠረገሎች ናቸው፡፡ ሱራፌልም ከበህር ልጅሽ በታች ወድቀው ይገዛሉ፡፡ ክብር ለከፍታሽ ነው፡፡ ገናንነትም ለጌትነትሽ፡፡

፴፫. ቅድስት ድንግል ሆይ ጉልበታችን ኃይላችን ሞገሳችን ክብራችን ተድላ ደስታችን አንቺ ነሽ ለዘመዶቻችንም መመኪያ ሆንሽ፡፡ የዓለም ሁሉ መድኃኒት ባንቺ ተደረገ፡፡

፴፬. የአምላክም ይቅርታ በሰው ልጆች ላይ ባንቺ ጸና የፍጡር ባሕርይ ከፈጣሪ ጋራ ባንች አንድ አካል አንድ ባሕርይ አንድ ገዥ ሆነ ይህ ስራ እጅግ ድንቅ ነው፡፡

፴፭. ሠሪ ሥራውን መልበስ እጅግ መንክር ነው፡፡ ሠሪውም ሥራውን የለበሰበት ሥርዓት ዕፁብ ነው፡፡ ፈጣሪ ፍጡሩን መልበስ ይህ ትህትና እጅግ የተደነቀ ነው፡፡

፴፮. ድንግል ሆይ አሁንም ወደ ልጅሽ እጮኻለሁ፡፡ እንዲህ ስል ከመላእክት ልዕልና ይልቅ የሰውን መዋረድ የወደድህ ሆይ ስለሠራሁት ኃጢአት አትናቀኝ አትንቀፈኝ፡፡

፴፯. የሰማያውያን መላእክት አንድነት ይልቅ ምድራውያን ፍጥረታትን ለመሳተፍ የወደድህ ሆይ ነውር ነቀፋ ከሌለበት ከመለኮትነትህ ምሥጢር አሳትፈኝ፡፡

፴፰. ከኤሳው መልክ ይልቅ የያዕቆብን የፊቱን ደም ግባት የወደድህ ሆይ አቤቱ ስለ ሠራሁት ኃጢአት እኔን አታርቅ፡፡ እኔ አንተን ለብቻህ በደልሁ ለራሴም ኃጢአት አብዝቼ ሠራሁ፡፡

፴፱. አንተ ንጹሕ አድርገህ ፈጠርከኝ፡፡ እኔ ግን በጠላቴ ምክር በደልሁ አንተ በሃይማኖት በትሩፋት አስጌጥከኝ፡፡ እኔ ግን ኃጢአትን በመውደድ ጌጤን ሽልማቴን ተውሁ፡፡

፵. አቤቱ ሆይ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እሆን ዘንድ እኔን በምግባር በሃይማኖት ለማነጽ ትጋ፡፡ መንቀሳቀስ በሌለበት ኃጢአት በመውደቅ የተጎዳሁ እንዳልሆን፡፡

፵፩. አቤቱ ሆይ እኔን ይቅር ለማለት ትጋ ይቅርታ ካንተ ዘንድ ነውና፡፡ አቤቱ ሆይ ቁስሌ የሚፈወስበትን መድኃኒት አንተ ታውቀዋለህ፡፡ አቤቱ ሆይ ድካሜ የሚበረታበትን ረዳትነት አንተ ታውቀዋለህ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፷፩. አቤቱ ሆይ ሕይወቴ የሚሆንበትን ጥበብ ምክንያት አንተ ታውቀቃለህ፡፡ ሠራተኛ ሥራው የሚከናወንበትን ነገር ያውቃልና፡፡ ሥራ ለሠሪው ጥበብም ለጥበበኛው ይታዘዛል ይከናወናል፡፡

፷፪. አቤቱ ሆይ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሸክላህን አድስ፡፡ አቤቱ ሆይ የእጆችህን ሥራ እንደማይጠፉ አድርግ፡፡

፷፫. አቤቱ ሆይ የወዳጆህ የአብርሃምን የይስሐቅን ኪዳን አስብ፡፡ የመረጥከውም የእሥራኤል ያዕቆብን ኪዳን ሕግህን ለመጠበቅ ከአሕዛብ የለየኸውን በሕግህ ያጸናኸውን በስምህ ያስጠራኸውን፡፡ ለቤተ ርስትም ዕድል ፈንታ ጽዋ ተርታ ያደረግኸውን ያዕቆብን አስብ፡፡

፷፬. አቤቱ ሆይ ካንደበትህ በወጣው ቃል መብራትነትህ ለሕዝብህ ያበራ ዘንድ መሪ ያደረግኸው የታመነ የሙሴን ኪዳን አስብ፡፡

፷፭. በእሥራኤል ልጆች ላይ መሲሕ ሊሆን የቀባኸውን በፊትህም ሞገስ ያገኘውን የባርያህ የዳዊትን ቃል ኪዳን አስብ፡፡

፷፮. የአዳም አባቱ አንተ ስትሆን እናት የሆነችህን የተባረከች ንጽሕት ቅድስት ሙሽራ የወለዱህን የለዚህን ቅዱሳን ሁሉ ኪዳን አስብ፡፡

፷፯. አቤቱ ሆይ ከሰማየ ሰማያት ወርደህ በቅድስት ድንግል ማኅፀን ማደርህን አስብ፡፡ አቤቱ ሆይ በማኅፀኗ ዘጠኝ ወር መወሰንህን አስብ የቀኑ ቁጥር ግን ሁለተ መቶ ሰባ አምስት ቀን ነው፡፡

፷፰. አቤቱ ሆይ ድንግል ስትሆን ከርሷ መወለድህን ንጽሕትም ስትሆን በጡቷ ማደግህን አስብ አቤቱ ሆይ በጎል መጣልህን በጨርቅ መቀቅለልህን አስብ፡፡

፷፱. አቤቱ ሆይ ይህንን ሁሉ አስበህ እኔን ባርያህን ስለ ኃጢአቴ አትናቀኝ አትንቀፈኝ በማዳንህ አርዳኝ በመድኃኒትህም ጋሻ ጋርደኝ፡፡

፸. አቤቱ ሆይ ስለ ወለደችህ ማርያም አማላጅነት ስለ አሳደጉህ ጡቶቿ ስለ ሳሙህ ከንፈሮቿ ስላቀፉህ እጆቿ ስለ ተቀበሉህ ጉልበቶቿ አካልም ይሆንህ ዘንድ ስለ ነሣኸው ነፍስና ሥጋዋ እርዳኝ ጠብቀኝ፡፡

፸፩. አቤቱ ሆይ ስለ ንጽሕት እናትህ ድንግልና እኔን ከርኩሰት አንጻ ትሕትናየንም ምረጥ አቤቱ ስለናትህ ክብርተና ስለ ገናንነቷም፡፡

፸፪. አቤቱ ሆይ ቅዱሳን ሐዋርያትን እንደ ወደድህ እንደመረጥኻቸውም እኔን ደግሞ ውደድ በሰማያዊ ማኅበራቸውም ከርሳቸው ጋራ አንድነት አድርገኝ፡፡

፸፫. ወደ ሠርጋቸውም የተጠራሁ ልሁን፡፡ በዚህ ዓለምም እኔን ባርያህን ከሚቃረነኝ ሁሉ አድነኝ፡፡

፸፬. ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ፡፡ (መዝሙር ፻፴፱ ፣ ፯)

፸፭. ወደ ሰማይም ብወጣ አንተ ከዚያ ነህ፡፡ ምንጣፌንም በሲኦል ባነጥፍ ከዚያም እነሆ አንተ አለህ፡፡ (ቁ ፰)

፸፮. እንደንስር የንጋቱን ክንፎች ንወስድ በባሕር ዳርም ብቀመጥ ከዚያም ደግሞ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ትይዘኛለች፡፡ (ቁ ፣ ፱ ፣ ፲)

፴፮. አቤቱ ከአማልክት አንተን የሚመስል የለም እንደ ሥራህም ሥራ የለም፡፡ (መዝሙር ፹፮ ፣ ፰፡፡)

፴፯. አኗኗርህ የተሠወረ ነው በዓለምም ሁሉ ምሉ ስትሆን ለወደድኸው እንጂ ለሁሉ አትታይም፡፡ ሰማይም ዙፋንህ ነው፡፡ ምድርም የእግርህ መረገጫ ናት፡፡

፴፱. ባሕር ባርያህ ናት፡፡ ነፍሳትም ላንተ ይታዘዛሉ፡፡ ፀሐይ መላክተኛህ ነው፡፡ የጨረቃም መንገድ በቃልህ የተሠራ ነው፡፡ ከዋክብትም በቃልህ የተተከሉ ናቸው፡፡ የዓለምም ሁሉ ስፋት በእጅህ የተያዘ ነው፡፡ (መዝ ፹፰ ፣ ፱፰ ) (ዕንባ ፫ ፣ ፲፩)

፵. ነገር ግን የምትቀመጥባቸው አይደለህም፡፡ በዳርቻቸውም አትወሰንም ለግዛትህም ወሰን ዳርቻ የለውም ለምስጋናህም ስፍር ቁጥር፡፡

፵፩. በኃይልህ ጽኑ ብርቱ ስትሆን የሁለቱ አረጋውያን ልጅ ተሸከመችህ፡፡ ባኗኗርህም የምትፈራ ልዩ ስትሆን ታናሽ ብላቴና ቻለችህ፡፡

፵፪. ባባትህ ቀኝ የተቀመጥህ ስትሆን በታችኛው ዓለም በጭኗ ላይ አድርጋ አቀፈችህ፡፡ ከልዑላን በላይ ልዑል የባሕርይ አምላክ ስትሆን በዚህ ዓለም ከትሑታን ጋራ ተመላለስህ፡፡

፵፫. በሁሉ ዘንድ ብቸኛ ስትሆን በሰው መሐከል ታየህ፡፡ ላምና አህያ ጌታቸው እንደሆንክ አወቁህ፡፡ በትንፋሻቸውም አሟሟቁህ፡፡ እስራኤል ግን አላወቁህም፡፡

፵፬. አምላካቸውም እንደሆንህ ተመራምረው አልተረዱም ከልቦናቸውም አራቁ እንጂ ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረው ነገር በላያቸው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ እንዲህ ያለው፡፡

፵፭. በሬ የገዛውን አወቀ አህያም የጌታውን ጋር እስራኤል ግን አላወቁኝም ወገኖችም አላስተዋሉም፡፡ (ኢሳ ፩ ፣ ፫)

፵፮. ባገራቸው ትንቢት የተነገረላቸው፡፡ በዕብራይስጥ ልሳንም በመስጊዳቸውም የተጻፈላቸው እስራኤል ምንም ባያውቁህ ከዓለም አስቀድሞ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ እኔ አወቅሁ፡፡

፵፯. አቤቱ ሆይ እኔ ባንተ አመንሁ ከዳዊት ዘር ከምትሆን ቅድስት ድንግል መወለድህም ዳግም አወቅሁ፡፡

፵፰. አቤቱ ሆይ ባናዋዋርህ የአብ ልጅ እንደሆንህ አመንሁብህ፡፡ አቤቱ ሆን በመለኮትነትህ የአብ ልጅ በትስብእትህ የሰው ልጅ እንደሆንህ አመንሁብህ፡፡

፵፱. አቤቱ ሆይ ከሕይወት ነቅዕ የተገኘ የሕይወት ነቅዕ እንደሆንህ አመንሁብህ፡፡ ከባሕርይ አምላክ የተገኘህ የባሕርይ አምላክ ከሕይወትም የተገኘህ ሕይወት እንደሆንህ አመንሁብህ፡፡

፶. ከወላዴ ባሕርይ የተገኘህ የባሕርይ ልጅ ሆይ ከብርሃንም የተገኘህ ፀዳል ከዕውቀት ባሕር የተገኘህ ጥበብ እንደሆንህ አመንሁብህ፡፡

፶፩. አቤቱ ሆይ ለወለደህና ለወለደችህ አንድ ልጅ እንደሆንህ አመንሁብህ፡፡ የላይኛው ልደትህ ሌላ ነው ሁለተኛውም ልደትህ ሌላ፡፡ ሰማያዊ ልደትህ ሌላ ነው፡፡ ምድራዊ ልደትህም ሌላ፡፡

፶፪. የፊተኛው ልደትህ ከሕይወትህ እሳት የተገኘ የሕይወት እሳት ነው የኋለኛው ልደትህ ከሴት የተወለደ

www.ethiopianorthodox.org

አካላቃ ቃል የፊተኛው ልደትህ ከኃይል የተገኘ ኃይል ነው፡፡ የኋለኛው ልደትህ የመለኮት ኃይል ነው፡፡

፶፫. የፊተኛውን አሻሁት አላገኘሁትም የኋለኛውን ሳልደርስበት አመሰገንሁት የኋለኛውን በአብራከ ልቡናዩ ሰግጄ እጅ ነሣሁት፡፡

፶፬. የፊተኛው ልደት በኋለኛው ልደት ታወቀ፡፡ የመለኮት ወገን በድንግልና ወገን ተመሰገነ ከድንግል ከተወለድህ ወዲህ ከአብ የመወለድህ ሃይማኖት ተገለጸልን፡፡

፶፭. ስለዚህም ዳዊት እንዲህ አለ እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ፡፡ ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው፡፡ (መዝ ፸፮ ፣ ፩)

፶፮. ይህንን እንግዲህ ከእስራኤል ልጅ ከይሁዳ ወገን አካላዊ ቃል ስለመወለዱ ይናገራል፡፡

፶፯. ከድንግል መወለድህን በሚናገር ትንቢት ከአብ መወለድህ ታወቀ፡፡ አሁንም ባለመጠራጠር ከአብ መወለድህን አመሰግናለሁ፡፡ ከድንግልም መወለድህን አመሰግናለሁ፡፡

፶፰.የድንግል ሆድ በሰማይ ካለው የብርሃን ሠረገላ ሰፋ፡፡ የድንግል ሆድ ከአየር በለጠ ከፍ ከፍ አለ፡፡ በኪሩቤል ዘንድም ተመሰገነ፡፡

፶፱. የድንግል ሆድ የሰማይ ደጅ ሆነ፡፡ ሳይከፈትም የፀሐይ መውጫ መግቢያ ነው፡፡ የድንግል ሆድ በውነት ለጽድቅ ገንዘብ ሣጥን ሆነ፡፡ የድንግል ሆድ ለልዑል እግዚአብሔር ማደሪያ ሆነ፡፡

፷. አሁንም እግዚአብሔርን እናመስግነው እንዲያ እያልን ላንተ ምስጋና ይገባል፡፡ በባሕርይ አባትህም ለአብ ለባህርይ ሕይወትህም ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል፡፡

፷፩. ለተሸከመችህም ገናንነት ለወለደችህም መገዛት ለእናትህም ውዳሴ ለስግደትህም ቅድስና ይገባል፡፡

፷፪. አሁንም ጸሎቴን እንደ ንጹህ ዕጣን በፊትህ ተቀበለኝ ወዳንተም የጮህሁትን የልመናዬን ነገር አድምጥ፡፡ አቤቱ የኃያላን አምላክ ስማኝ የያቆብም አምላክ አድምፀኝ አቤቱ ሃይማኖቴን እይልኝ፡፡ አድምፀኝ አቤቱ ሃይማኖቴን እይልኝ፡፡ አቤቱ ጋሻችን ሆይ ተመልከት ቀብተህ ወዳነገሥከውም እይ፡፡ (መዝሙር ፹፩ ፣ ፷፱)

፷፫. አቤቱ ወዳንተ የለመልሁትን ልመናዬን ስማኝ፡፡ ከጠላቶቼም ፈርሃት ሰውነቴን ጠብቅ፡፡ (መዝ ፣ ፷፬ ፣ ፩)

፷፬. ከክፎች ሸንጎ ከክፉ አድራጊዎች ሁከት ሠውረኝ፡፡ (ቁ.፪)

፷፭. እንደ ሰይፍ መለሳቸውን ከሳሉት መራራውን ነገራቸውን እንደ ቀስት ከገተሩት (ቁ.፫)

፷፮. አምላኬ ሆይ ጩኸቴን ስማ ጸሎቴንም አድምጥ አቤቱ ጸሎቴን ስማ ጩኸቴን አድምጥ ወዳንተ ይድረስ (መዝሙር ፻፪ ፣ ፩ ም ፷፩ ፣ ፩፡፡)

፷፯. በመከራዬም ፊትህን ከኔ አትሠውር ጆሮህንም ወደኔ አዘንብ፡፡ በጠራሁህም ጊዜ ፈጥነህ መልስልኝ፡፡ (ቁ. ፪)

፷፰. አንተን አምናለሁና ማለዳ ምሕረትህን አሰማኝ የምሄድበትን መንገድ አስታውቀኝ፡፡ ነፍሴን ወዳንተ አንስቻለሁና (መዝሙር ፻፵፫ ፣ ፰)

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፳፱. አቤቱ ባንተ ተማፅኛለሁና ከጠላቶቼ እጅ አድነኝ፡፡ በጎ ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ አንተ አምላኬ ነህና በጎ መንፈስህም በቀናችው መንገድ ይምራኝ (ቁ. ፱ ፣ ፲)

፴. አቤቱ ስለ ሰምህ አድነኝ በጽድቅህም ነፍሴን ከመከራ አውጣት፡፡ በጸጋህም ጠላቼን አጥፋቸው፡፡ ነፍሴንም የሚያስጨንቋትን ሁሉ ደምስሳቸው፡፡ እኔ ያንተ ባሪያ ነኝና (ቁ. ፲፩ ፣ ፲፪)

፴፩. ቃሌን አድምፅ አቤቱ አሳቤንም አስተውል የጩኸቴን ቃል አድምፅ፡፡ ንጉሤ አምላኬ ሆይ ወዳንተ እጸልያለሁና፡፡ ማለዳ ድምጼን ትሰማለህ፡፡ (መዝሙር ፭ ፣ ፪)

## <u>ምዕራፍ ፲</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ አንቺ ደግሞ ለጸሎቴ መጨመሪያ የወርቅ ጽንሐሕ ሁኚ ልመናዬን ባንቺ ወደ ልጅሽ ኢየሱስ ክርስቶስ አቀርብ ዘንድ፡፡

፪. ካህን ዕጣኑን ከወርቅ ማዕጠንት እንዲጨምር እንዲሁም ጸሎቴን ከጆሮሽ እጨምራለሁ ካፌ የወጣውንም ቃል ተቀበይው በልቡናሽም ያደረ ይሁን፡፡

፫. የልቡናሽም ትጋት ወደ ልቡናዬ ትጋት ይሁን፡፡ የልቡናሽም አሳብ ወደ ልቡናዬ አሳብ ይሁን፡፡ ልጅሽንም ለምኝው እንዳያሳፍረኝ፡፡ ተስፋም እንዳያስቆርጠኝ፡፡ የልቤንም ግዳጅ እንዲፈጽምልኝ፡፡ ዘወትርም የተመኘሁትን እንዲሰጠኝ፡፡

፬. በመንፈስ ቅዱስ በረከትም ይባርከኝ የእጄንም ሥራ ሁሉ ያቅናልኝ፡፡ በልቡናዬም የሰው መውደድ ያሳድርብኝ፡፡ በሰውም ልቡና እኔን መውደድ ያሳድርበት፡፡

፭. የርሱንም ቸርነት በልቤ የጨምር በመለኮት ጨው የጣፈጥሁ ያድርገኝ፡፡ የጥበብ መብራትንም በልቡናዬ ያብራ፡፡ የዕውቀት መንፈስም ከኔ ላይ አይራቅ፡፡

፮. ይህንን ነገር ከልጅሽ ከወዳጅሽ አሸልኝ ከክርስቲያን ልጆች ጋራ ሁሉ አስማሚኝ፡፡ ልጅሽንም ከሚወዱ ሁሉ ጋራ በፍቅር ባንድነት አኑሪኝ፡፡ ከክፉ ነገር ሁሉ ጠብቂኝ ከጠላቶቼም ወጥመድ ካሸክላው አድኚኝ ለጽድቅ መገዛትን የተገዛሁ አድርጊኝ፡፡

፯. ከኃጢአት ሸክም ነፃ አድርጊኝ ኃጢአትን የሚሠራት ሁሉ የኃጢአት ባሪያዋ ነውና (ሮሜ ፣ ፯ ፣ ፲፯ ፣ ፳)

፰. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ በላዬ ይሰለጥን ዘንድ ሰይጣንን አታሰናብችው፡፡ በምውልበትና በማድርበትም የልጅሽ ሠራዊቶች የሚሆኑ መላእክት ይጎብኙኝ ከጠላት ጦርነት ያድኑኝ ዘንድ፡፡

፱. በልጅሽ መስቀል አጥርነት እጠሪኝ እኔ ባለሁበት ሥፍራ ሁሉ ርኩሳን መናፍስት እንዳይገቡ በቅድስናሽ መጎናጸፊያም ሠውሪኝ በልብስሽ መዓዛ እሻተት ዘንድ፡፡

፲. ከእንቅልፍም በነቃሁ ጊዜ ያለ ስንፍና እንዳመሰግንሽ ጸሎት ለማስታጎል እንቅልፍ በመጣብኝ ጊዜ የልጅሽ የመለኮትነቱ ኃይል ከቅንድቤ ከሽፋሽፍቴም ያርቀው፡፡ እንደበቴም አንቺን ለማመስገን የተጋ የነቃ ይሁን፡፡

፲፮. እግሮቼም በፊትሽ ሳይናወፁ ይቁሙ፡፡ ግዳጄን ካንቺ ዘንድ እስክፈጽም ድረስ ለጸሎቴም እጆቼ የተዘረጉ ይሁኑ ከጌታው ደመወዙን እንደሚቀበል ሰው ሁሉ፡፡

፲፯. ዐሥሩ ጣቶቼም እንደፋና መብራት ይሁኑ ጠላቴን ይወጋው ዘንድ የእሳት ሰይፍም ከአንደበቴ ይውጣ፡፡ የሚቃረነውን ይቆርጠው ዘንድ በጸሎት ሳለሁ በላዬ አሳብ ማብዛትን እንግዲህ ወዲህ አይድገም፡፡

፲፰. የሚወላውልም ልቡና አያምጣብኝ፡፡ አባቶቼ ቅዱሳን መነኮሳት እንዲህ ይላሉና ከእግዚአብሔር ፊት የሚጸልይ ሁሉ የልቡናው ሀሳብ ከቤተክርስቲያን ውጭ ቢሆን ወይም ወደ ሥራው አንድ ልጅ ያለው ከርሱም ሌላ የሌለው ሰውን ይመስላል፡፡

፲፱. እርሱም በእግዚአብሔር ፊት የሠዋው እርሱ ደግሞ ስለ ሥጋዊ ነገር የሚደክም የነፍሱን ነገር ቸል የሚል ይመስላል፡፡

## ምዕራፍ ፲፬

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ልቡናዬን በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት የተቃጠለ የተሟሟቀ አድርጊው፡፡ ከሰይጣን ወገን የሚገኘውን የልቡናዬን መቀዝቀዝ ስንፍናዬንም አርቂው፡፡

፪. ሐሳቤም በመንፈስ ቅዱስ ሙቀት የተሟሟቀ ይሁን ጽጋግና ጨለማም ከኔ ይራቅ ልቤም እንደመብረቅ ብርሃን ይብራ፡፡ እንደሚያዝያም ፀሐይ በኃይል እንደሚታይ ይሁን፡፡

፫. በማናቸውም ነገር ሁሉ ችግረኛ አታድርጊኝ፡፡ እናትም ለልጆቿ እንድትተጋ ለገዳጄ ሁሉ ትጊ ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ እንደ ባሪያ ወደ እመቤቴ እጅ፡፡

፬. ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ ባሮች ወደ ጌቶቻቸው እጅ እንዲያንጋጥጡ፡፡

፭. ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ ልጆች ወደአባቶቻቸው እጅ እንዲያንጋጥጡ ዓይኖቼ ወዳች ያንጋጥጣሉ፡፡ ልጆች ወደ እናቶቻቸው እንዲያንጋጥጡ ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ ሠራዊቱ ወደ ንጉሡ እጅ እንዲያንጋጥጡ፡፡ ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ ሕዝቡ ወደ መኮንኑ እጅ እንዲያንጋጥጡ፡፡

፮. ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ ስላንቺ ልመና የልጅሽ ምሕረት ይወርድልኝ ዘንድ በእስራኤል ልጆች ሠፈር መና እንደ ወረደ፡፡

፯. የመናውም አተያየቱ እንደ ድምብላል ጥቃቅን እንደ አመዳይም ነጭ ነው፡፡ ጣዕሙም እንደማር ወለላ ከቅቤ ጋራ ነው፡፡ (ዘፀአ ፲፯ ፣ ፴፩)

፰. ከልጅሽ ምሕረት ይልቀ ምን ይጣፍጣል፡፡ ክልጅሽ ይቅርታ ንጹሕነት ይልቅ ምን ይነጻል፡፡ የበደለውን እንዳልበደለ፡፡ ያደፈውን እንዳላደፈ፡፡ ኃጥኡንም እንደ ጻድቅ ዘማዊውን እንደ ድንግል ያደርገዋል፡፡

፱. አሁንም ደግሞ ይህ የሚያነጻው ይቅርታው በኔ ላይ ይውረድ፡፡ ርኩሰቴን ያነጻ ዘንድ የልጅሽም የምሕረቱ ዝናም በላዬ ይውረድ የሰውነቴን ርኩሰት ያጽብ ዘንድ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፲፪

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ አንጋጥጬ እንዳላፍር ተስፋ እንዳልቆርጥ የተመኘሁትንም እንዳላጣ አድርጊኝ፡፡

፪. ድንግል ሆይ ለንጽሕና መንፈስ ማደሪያ ለበረከትም አዳራሽ አድርጊኝ፡፡ ለጸሎት ሠረገላ ለምስጋናም መሰላል አድርጊኝ፡፡

፫. ድንግል ሆይ ለመጻሕፍት ነገር ማከማቻ መዝገብ ለሃይማኖት ሽቱም ሙዳይ አድርጊኝ፡፡ ድንግል ሆይ በየዋህነት የተጌጥሁ በትእግሥትም የተከለልሁ አድርጊኝ፡፡

፬. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ እመቤቴ የተመረጥሽ ድንግል ማርያም ሆይ ወዳንቺ የቀረብሁ ወደልጅሽም አንድ የሆንሁ አድርጊኝ፡፡

፭. አሁንም ወዳንቺ እጮሃለሁ፡፡ የወደድሁትን ነገር ታቀኚልኝ ዘንድ የሻሁትንም በአሰብሁትም ሁሉ ታሳምሪልኝ ዘንድ፡፡

፮. በኢያቄም በአባትሽ ወገን የንጉሥ ልጅ ሆይ አመሰግንሻለሁ፡፡ የዳዊት ልጅ ነሽና የሊቀ ካህናት ልጅ ሆይ ውዳሴሽን አቀርባለሁ፡፡ ከእናትሽ ወገን የአሮን ልጅ ነሽና፡፡

፯. ገናንነትሽንም አደንቃለሁ፡፡ የነገድሽን ወገን አመሰግናለሁ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት ተገኝተሻልና፡፡

፰. ስለዚህም የነጎድጓድ ልጅ ነሽ እልሻለሁ ያዕቆብና ዮሐንስን አኔሬጌስ ብሎ እንደጠራቸው ይኸው የነጎድጓድ ልጆች ማለት ነው፡፡ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት ናቸውና፡፡

፱. ስለዚህም የነጎድጓድ ልጆች ተባሉ፡፡ አኔም የነጎድጓድ ልጅ ነሽ አልሁሽ፡፡ የመወለድሽ ድምፅ (ወሬ) እንደ ነጎድጓድ ድምፅ ይሰማልና፡፡

፲. ከሁለቱ ከተቀቡት ነገድ በነቢያት አለቃ በሙሴ እጅ ለክህነት ከተቀባው ከአሮን ቤት፡፡ በሳሙኤል እጅ ለመንግስት ከተቀባው ከዳዊት ዘር፡፡ (፩ ሳሙ ፲፮ ፣ ፲፫) (ዘሌዋ ፰ ፣ ፲፪)

፲፩. ደግሞም ያንበሶች ልጅ ነሽ እልሻለሁ እንደ አንበሳ ግልገል ጩኸት እንደ ሴትም አንበሳ ድምፅ የልደትሽ ወሬ ይሰማልና፡፡ አባቱ ያዕቆብ ይሁዳን ያንበሳ ግልገል ብሎታልና፡፡ (ዘፍጥ ፵፱ ፣ ፱ ፣ ፱)

፲፪. ስለዚህም ያንበሶች ልጅ እልሻለሁ፡፡ ሰሎሞን እንደተናገረ እንዲህ ሲል አንቺ ሙሽራ ከሊባኖስ ጋራ ነይ ከሊባኖስ ጋራ ነይ፡፡ ከአንበሶችም ጉድጓድ ወጥተሽ ነይ፡፡ (መሐ ፣ ፬ ፣ ፰)

፲፫. ከተመረፀ ነገዱ የተነሣ ከሚመካ ወገን የመወለድሽ ወሬ እጅግ ግሩም ነው፡፡

፲፬. ድንግል ሆይ በመልክ በደም ግባት ያማርሽ የተወደድሽ (የተጌጥሽ) ነሽ፡፡ ከእግርሽም እስከ ራስሽ ድረስ ክፋ የለም በነገድም ወገን የተመረጽሽ ነሽ፡፡

፲፭. በመልክና በደም ግባትም ከሁሉ ይልቅ አማርሽ ተወደድሽ በንጽሕናም ተሸለምሽ፡፡ በቅድስናም ተከለልሽ በሁሉም ፍጽምት ነሽ፡፡ (ቁ. ፲፬)

፲፮. አንቺን ለማመስገን ቃሌን ከፍ ከፍ አደርጋለሁ ለውዳሴሽም በኃይል እጮኻለሁ ለዘፈንሽም በእጆቼ

አጨበጭባለሁ ለልልታሽም በእግሮቼ አሸበሽባለሁ፡፡

፲፯. ለክብርሽም መገዛትን እሰጣለሁ፡፡ ስግደትም ለገናንነትሽ፡፡ ከሆድሽም ፍሬ ባፌ እጨምራለሁ የፍሬሽም ደም ለዠሮየ የጣፈጠ ነው፡፡

፲፰. የሽቱሽም መዓዛ ለፍንጫዬ ያማረ የተወደደ ነው፡፡ የድንግልናሽ ምስጋናም ደረቅ ጠጅ እንደጠጣ ልቡናዬን ደስ ያሰኛል ስላንቺ ደስታዬ ምን ያህል ነው ሐሤቴ ስለ ክብርሽ ምንኛ ነው፡፡

፲፱. አነጋገርሽ ያማረ ነው፡፡ ነገርሽም የጣፈጠ ከንፈሮችሽም የኃሤት መፍሰሻ አንደበትሽም የምስጋና ጎርፍ ያለበት ነው፡፡ እጅግ አማርሽ እጅግም ተወደድሽ መልክሽ ምንኛ ውብ ነው፡፡ ውድሽም እንደ ምን ነው፡፡ ፍቅሬ ሆይ በደስታሽ ይህ ቁመትሽ የሰሌን ዛፍ ይመስላል፡፡ (መሐ ፯ ፣ ፯-፰)

፳. የልብስሽም ሽታ እንደ ሽቱ ሽታ ነው፡፡ ያፍንጫሽም መዓዛ እንደ ወይን ጨርቋ ነው፡፡ ያፍሽም አከፋፈት እንደ ቀናንሞስ አበባ ምዑዝ ነው፡፡ ከሊባኖስ ዕንጨት ሁሉ ጋራ፡፡ (መሐ ፣ ፬-፲፬)

፳፩. ሁለንተናሽ ያማረ የተወደደ በመንፈሳዊ ጌጽ የተጌጠ ነው፡፡ የምስጋና መብራት ይከብሻል፡፡ ከመለኮታዊ ብርሃን ጋራ የብርሃን እናት ሆይ የመሢሕ እናት የአምላክ እናት የዓለም መድኃኒት እናት የናዝሬቱ ኢየሱስ እናት ሆይ ከልጅሽ ዘንድ ለምኝልኝ፡፡

፳፪. ለሥጋዬ መበረታታትን ለነፍሴ ዕረፍትን ለልቤ ኃሤትን፡፡ ከዛሬም እስከ ዘለዓለሙ ድረስ ሕይወትን ከልጅሽ ከወዳጅሽ አሰጭኝ፡፡

፳፫. እመቤቴ ሆይ ከሞት ለዘለዓለሙ ታድኚኝ ዘንድ አድኚኝ አልልም፡፡ እንዲህማ አል ዘንድ ለዘለዓለም የሚኖርስ ሞትን የማያይት ማነው፡፡ (መዝሙር ፹፱-፺፰)

፳፬. እኔስ የምለው እንዲህ ነው፡፡ ንስሐ እስክገባ ድረስ እንዲቆይልኝ፡፡ የንስሐ ፍሬንም እስካቀርብለት ቸርነቱንም ደስ እስካሰኝ እንዲጠብቀኝ፡፡

፳፭. እመቤቴ ሆይ አንቺ ጠበቂኝ፡፡ ለዘወትርም ከኔ እንዳትርቂ ነፍስና ሥጋዬን ወዳንቺ አደራ እሰጣለሁ በዕድሜየም ሁሉ ለዘወትር አትተይኝ በዚህ ዓለም ከሚመጣብኝ መከራ ሁሉ ጠብቂኝ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# አርጋኖን
# ዘረቡዕ
# <u>ምዕራፍ ፩</u>

፩. ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሜ እግዚአብሔርን አመግናለሁ፡፡ ስላንቺም፡፡ (ሮሜ ፩-፰)

፪. የውዳሴሽ ወሬ በዓለም ሁሉ ተሰምቷልና በመንፈስ ቅዱስ እንደተናገርሽ እንዲህ ስትይ እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል፡፡ (ሉቃ ፣፩ ፣፵፰)

፫. በውነት ምስጋና ይገባሻል፡፡ የእግዚአብሔር እናቱ ሁነሻልና በውነት መደነቅ ይገባሻል፡፡ ዓለምን ሁሉ በመሐል እጁ የያዘ እርሱን ወልደሻልና በዕውነት ብፅዓን ይገባሻል ለዕውነተኛ ፀሐይ መውጫ ሆነሻልና፡፡

፬. በዕውነት መመስገን ይገባሻል ለማለዳው ኮከብ ምሥራቅ ሆነሻልና በውነት መደነቅ ይገባሻል፡፡ ለጥምቀት ልጆች መመከያ ሆነሻልና፡፡ በውነት ብፅዕና ይገባሻል፡፡ ለሃይማኖት መሠረት ጽናተ ሆነሻልና፡፡

፭. ከኪሩቤል ክብር ገናንነት ላንቺ ይገባል፡፡ ከሱራፌልም ውዳሴ ከመላእክትም እልልታ ከመላእክት አለቆችም ዝማሬ ላንቺ ይገባል፡፡

፮. ከነቢያት ትንቢት ከሐዋርያት ስብከት ላንቺ ይገባል፡፡ ከቅዱሳን ሰማዕታት እናታችን መባል ከመሐይምናንም እመቤታችን መባል ከክርስቲያንም ሁሉ አፍ የመድኃኒታችን ቀንድ መባል ላንቺ ይገባል፡፡

፯. ከመሲሐውያን ነገስታት አፍ ንግሥታችን መባል ከልዑላንም መላእክት በላይ ከፍ ከፍ ማለት ከታችኛችም ፍጡራን ላንቺ መገዛት ይገባል፡፡ እንግዲህ አንቺ ከሰማይ ትበልጫለሽ ከተራሮችም ከፍ ትያለሽ፡፡ ስለ አንቺም እንዲህ እላለሁ ከፀሐይ ብርሃን ከጨረቃም ድምቀት አንቺ ትበልጫለሽ፡፡

፰. ስለ አንቺ እንዲህ እላለሁ፡፡ ከአርዮብ መልክ ከመብረቅም ብርሃን አንቺ ታበሪያለሽ፡፡ ስላንቺ ደግሞ እንዲህ እላለሁ በሰማይ ካሉ ትጉሃን መላእክት ትከብሪያለሽ፡፡ ከመናብርትም ከሥልጣናትም ትቀደሻለሽ፡፡

፱. ስላንቺም እንግዲህ እንዲህ እላለሁ መልኩ አስተያየቱ ልዩ ልዩ ከሚሆን አበባ ፍሬ ትሸቻለሽ፡፡

፲. አሁንም ደግሞ ወደ ልጅሽ እጮሃለሁ፡፡ እንዲህ ስል አቤቱ በምሕረትህ አስበኝ በመስቀል ላይ በምስማር ተቸንክረህ ሳለህ የቀኙን ወንበዴ እንዳሰብከው፡፡

፲፩. አቤቱ በምሕረትህ አስበኝ፡፡ ስለ ንጹሑ አቤል ደም አማላጅነት፡፡ ስለ ሰው መሆንህ ትንቢት ምስክርነት ስለሞቱት ሰማዕታት አማላጅነት፡፡

፲፪. አቤቱ አስበኝ በጸራ ወርቅ ምንጭ ወንጌልህን ለማስተማር ስላፈሰሱ ስለ ጴጥሮስና ጳውሎስ ደም መፍሰስ አማላጅነት፡፡

፲፫. አቤቱ በምሕረትህ አስበኝ፡፡ ባንተ ዘንድ የተወደደው የድንግልናው መዓዛ እንደ ተጣፈጠ ሽቱ፡፡ በካህናቱ ራስ ላይ ስለ ተቀላቀለው ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ አማላጅነት፡፡

፲፬. አቤቱ በቸርነትህ አስበኝ ስለ ሐዋርያትህ ደም ስለ ሥጋዊህ ምስክርነት ስለ ፈሰሰው አማላጅነት አቤቱ በይቅርታህ ብዛት አስበኝ ስለ መዋዕያን ሰማዕታት ደም ስለ ስምህ ምስክርነት አማላጅነት፡፡

፲፭. አቤቱ በይቅርታህ አስበኝ ስለ ደከሙልህ ቡሩካን ጻድቃን ገድል አማላጅነት፡፡ አቤቱ በምሕረትህ አስበኝ ስለ ተመረጹት ደናግል ንጽሕና የድንግልናቸውን ባሕርይ እጅ መንሻ አድረገው ስላቀረቡልህ አማላጅነት፡፡

፲፮. አቤቱ በቸርነትህ አስበኝ ስለ ኪሩቤልና ስለ ሱራፌል፡፡ ስለትጉሃንም መላእክት ማኅበር እርሳቸውም ያለ ርኩሰት ንጹሓን ያለ ሐኬትም መዘምራን፡፡

፲፯. አቤቱ በምሕረትህ አስበኝ አንተን ስለ ወለደች ማርያም ስለ ከበረች ቡርክት ልዕልት የተመረጸች ንጽህት ድንግል አማላጅነት፡፡ ስለ ቅድስናዋ ስለ ድንግልናዋም መዓዛ ከፍጡራንም ሁሉ ይልቅ ስለ ወደድኸው ወዟ ደም ግባቷ፡፡

፲፰. የሕይወት የመድኃኒት መጀመሪያ ናትና፡፡ የንጽሕና የቅድስናም መሠረት የዓለም ሁሉ ጌጥ ፈርጽ የፍጥረትም መመኪያ ዘውድ፡፡ ከዚህም እስከ ሰማይ የምታደርስ መሰላል ናት፡፡

፲፱. ከዚህ ዓለም ጥፋት ገደል ሰዎች ሁሉ የሚሸጋገሩበት ድልድይ መንግሥተ ሰማያት የምንገባባት ደጅ ካመፀኞችም ከወንጀለኞችም ጦርነት ከክፉዎችም ወገኖች ጸብ ክርክር ከሚያባርሩን የምንድንባት አምባ መጠጊያችን ናት፡፡

፳. ከሰይጣን ፍላፃ ከተሳሉትም ጦሮች፡፡ ከወጥመዱም ካሸክላው የምንድንበት ሃይማኖት ቅጥር፡፡ በአበባዋ የምንሻተትባት፡፡ ከፍሬዋም የምንመገብላት ከጫፎቿም በታች የምናርፍባት የገነት ዕንጨት ናት፡፡

፳፩. በክብርና በገናንነቷ፡፡ የምንመካባት ንግሥት በልዕልናዋም ደስ የምሰኝባት ቅዱስ ምሥጢርም የሚያፈራባት መሠዊያ ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ የሚሸትባት፡፡

፳፪. ለእስራኤል ቅዱስ ንጹሕ ምሥጢር የሚሠራባት ቅድስት ጠረጴዛ ከውስጧም ከአፍኣዋም በወርቅ የተለበጠ የሙሴም ኪሩቤል በላይዋ የሚጋርዷት ታቦት፡፡ (ዘፀአ ፣፳፭ ፣ ፲፰)

፳፫. ሳትተከል ውሀ ሳይጠጣ በእስራኤል በትሮች መሐከል ለምልማ አብባ አፍርታ የተገኘች የአሮን በትር (ዘኁል ፲፯ ፣ ፰)

፳፬. ከሲና ምድረ በዳ እስከ ቃዴስ በርኔ የእስራኤል ልጆች፡፡ ለበሉት እንጀራ መሥፈሪያ ከሚሆን የወርቅ ጎመር የተምር ውሀ የተቀዳባት የወርቅ መቅጃ፡፡

፳፭. ድርብ ከተከረረ ከጥጥ ፈትል የተሠራች ድንኳን የአሮን የክህነት ልብስ ሰማያዊ ቀይ ቀለም ከከበበው ከጠለቀው ቀይ ቀለም ግምጃ በዙሪያውም እንደሮማን ፍሬ ያለ የወርቅ ሻኩራ ያለባት፡፡ (ዘፀአ ፳፰ ፣ ፴፬ ፣ ፴፭)

፳፮. በውስጧ ዕጣን የተቀላቀለው ፍህም የተጨመረባት፡፡ የሚያንፀበርቅ ስኂን ቀንዓት የልብን ውሀ በውስጧ ያለባት የወርቅ ማዕጠንት አንቺ ነሽ፡፡

፳፯. ሰባት ማብሪያ ያላት በየሦስቱ መያዣዎች ሰባት መፍሰሻ በራሷ ላይ ለነበሩ ማብሪያ የነበረባት የወርቅ መቅረዝ አንቺ ነሽ (ዘካ ፣ ፬ ፣ ፪)

www.ethiopianorthodox.org

፳፰. በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ ዐሥሩ ቃላት በውስጧ ያሉባት የመሐላ ጽላት አንቺ ነሽ (ዘፀአ ፣፴፩ ፣ ፲፰)

፳፱. በላይዋ የበረከት ጠል የወረደባት የጌዴዎን ብዝት ግምጃ አንቺ ነሽ፡፡ (መሳፍንት፮ ፣ ፴፯ ፣፴፰)

፴. የእግዚአብሔን ምስጋና ዘፈን የሚዘፍንባት የዳዊት መሰንቆ አንቺ ነሽ፡፡ (፪ ሳሙ ፮ ፣ ፲፬)

፴፩. ከንጽሕና ጋራ ሙሽራ ከድንግልና ጋራ እናት ሆይ ከጥፋት እድን ዘንድ ለምኝልኝ፡፡ የዚህ ዓለም ዘመኖች የሚሰጥሙ ማዕበልና ሞገድ ሆነዋልና፡፡

፴፪. የመንፈስ ቅዱስ ክንፍ የሚጋርዳት ያለ ርኩሰት እናት ሆይ፡፡ መመለሴ ወደ ሰንካላው መንገድ ወደ ጉድጓድ ጎዳና እንዳይሆን ልጅሽን ወዳጅኝን ኢየሱስ ክርስቶስን ለምኝልኝ፡፡

## ምዕራፍ ፪

፩. በዕብራይስጥ ማሪያም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ ያለ ዘር ያለ ሩካቤ አካላዊ ቃልን የወለድሽው እሳትንም በሥጋ የወሰንሽ ድንግል እኔን ኃጢአተኛውን አማልጅኝ፡፡ ሥጋችንንም እንደሰም ከሚያቀልጠው ከሥጋዊ ፈቃድ እሳትነት አድኝኝ፡፡

፪. እመቤቴ ድንግል ሆይ የመልክ ቀጸላ የመሃይምናን አክሊል፡፡ የሙሽርነት ጌጽ፡፡ የቅዱሳን ሽልማት ሆይ ከዘመናት ማዕበል ሞገድ አድኝኝ፡፡ በጸሎትሽም ጸጥ እንዲል አድርጊው፡፡

፫. የዓለም ሁሉ መመኪያ ድንግል እናት ሆይ፡፡ ከሚያሰጥመው ካመፀኛ አፍ በደምም ከሰከረች መለስ አድኝኝ፡፡

፬. መንፈሳዊት መርከብ ሆይ፡፡ ድንግልናዊት መፆር ሆይ፡፡ ከክፉ ዘመን መከራ አድኝኝ፡፡

፭. የሁላችን መመኪያ የመድኃኒት ሽቱ ብልቃጥ፡፡ ያለ ርኩሰት ሙሽራ ሆይ ከቀን ወራሪ ከሌሊት ሰባሪ አድኝኝ፡፡

፮. የሕይወት የመድኃኒት ድልድይ የድኅነት መሰላል ሆይ ከዚህ ዓለም ባሕር ማዕበል ሞገድ አድኝኝ፡፡ ከባሕር ጠልቆ ከገደል ወድቆ ከመሞት አድኝኝ፡፡

፯. አሁንም ዓለም ከሚደርስበት አድርሽኝ፡፡ ኋላ ደግሞ በልጅሽ በወዳጅሽ በስተቀኝ አንድቆም አድርጊኝ፡፡

፰. የደናግል መመኪያቸው የቅድስናቸው አክሊል ሆይ እኔን ከኃጥኣን ሁሉ ይልቅ የአረከሱትን አንቺን ከመውደድ በልጅሽ በወዳጅሽ በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ከማመን በቀር ሌላ ትሩፋት የሌለኝን ይቅር በዩኝ ይቅር አሰኝኝ፡፡

፱. ከኔ ከኃጢአቴ ፍዳ የሚበዛ ለሰው የኃጢአት ፍዳ ስድብ ሽሙጥ የለም የመላእክትም የሰውም ቢሆን ከንጽሕና ምስጋና የለም፡፡

## ምዕራፍ ፫

፩. በዕብራይስጥ ማሪያም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ በላዩ የሚመጣውን ዕዳ

በንጽሕናሽ ክፈይኝ፡፡

፪. አምላክን የወለድሽ ቅድስት ድንግል ሆይ የእግዚአብሔርን ልጅ የወለድሽ ንዕድ ክብርት ሆይ እውነተኛ ፀሐይን ያስገኘሽ የተመረጽሽ ድንግል ሆይ ምን ብዬ እጠራሻለሁ በምንስ ምላሴ እመስልሻለሁ፡፡

፫. ኪሩብ የያዘው ዙፋን ነሽን፡፡ ነገር ግን ከርሱ አንቺ ትሻያለሽ፡፡ ኪሩብ ከያዘው ዙፋን የተረባሁት የለም፡፡ ገነት ከመውጣት አላዳነኝም ከሰይጣን ቀንበር በታችም ከመገዛት አልተበዠኝም፡፡

፬. ነገር ግን በላዬ ለሚቀመጥ የእግዚአብሔር ስሙ ይክበር አደፍ ጉድፍ የሌለብሽ ንዕድ ክብርት የብርሃን እናት ሆይ፡፡

፭. ርኩሰት የሌለብሽ ስብሕት የዓለም ሁሉ ጌታ እናት እንግዲህ ምን አልሻለሁ ሰማይን እልሻለሁ፡፡

፮. ነገር ግን ከርሱ አንቺ ትሻያለሽ በስተምስራቅ በኩል ቀድሞ እግዚአብሔር ከተከላት ኤኮም ከተባለች ገነት እንዳልወጣ፡፡ ሰማያት ስለኔ አልለመኑምና፡፡

፯. ከሰማየ ሰማያት ዘምበል ብሎ ወዳንቺ ወርዶ ካንቺ ሰው ሁኖ ማኅተመ ድንግልናሽን ሳይለውጠው ለተወለደ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይግባው ክርስቶስ ስሙም ክቡር ምስጉን ይሁን፡፡

፰. ከተወለደም በኋላ በኅቱም ድንግልና ኖርሽ፡፡ ሥርዓትሽም ከሰው ሥርዓት ልዩ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ያልሆነ እንግዲህም የማይሆን ነው፡፡

፱. የድንግልናሽን ምስጋና መናገር የሚችል ምን አፍ ምን አንደበት ምን አነጋገር ነው፡፡ ምስጋናሽን ለመስማት የሚቻለው ምን ጆሮ ነው፡፡ ከምስጋናሽ ወደብ ከፍጻሜው የሚደርስ ምን ልቡና ምን ሐሳብ ነው፡፡

፲. አንድ ሰዓት ስንኳን የድንግልናዋ መዝጊያ ያለተከፈተ፡፡ ዘለዓለም ተዘግታ የምትኖር ደጅ ሆይ ሕዝቅኤል ያየት የምሥራቅ ደጅ፡፡ ከኃያላን ጌታ በቀር በውስጧ የገባ የለም፡፡ በመግባቱ በመውጣቱ አልተከፈተችም፡፡ (ሕዝቅ ፵፬ ፣ ፩ ፣ ፪)

፲፩. የንጽሕና ፍሬ የምታፈራ ድንግልና አበባ የምታብብ ነባቢት ገነት ሆይ እሷን ለመትከል ውሀም ለማጠጣት የደከመ የለም፡፡

፲፪. የመለኮት ምንጻፍ የተነጸፈባት ንጽሕት አዳራሽ ሆይ፡፡ የንጽሕና ሙሽራ ቤት ርኩሰት የሌለባት የመንፈስ ቅዱስ ሠርግ ቤት፡፡

፲፫. ከዕሴይ ሥር የተገኘች የወይን ሐረግ ከዳዊት ግንድ የበቀለች በትር፡፡ ከርሷም አበባ የወጣ ይኸውም የቅዱሳን መዓዛ ኢየሱስ ክርስቶስ (ኢሳ ፣ ፲፩ ፣፩)

፲፬. ርኩሰትን ለማንጻት ኃጢአትንም ለማፀብ የሚመነጭ የሕይወት ውሀ መቅጃ የክብር አዘቅት ሆይ ለሥላሴ መስገድን ለምዕመናን የምታስተምር የሃይማኖት መሠረት የእምነት መጀመሪያ፡፡

፲፭. ከማይታዩ ረቂቃን መላእክት ከነፋሳት ይልቅ ረቂቅ የሆነ የማይታይ፡፡ በባሕርይ የተሠወረ አካላዊ ቃል ከርሷ የተገለጸ ንጽሕት ሰፊ የተድላ ደስታ መጋረጃ፡፡

፲፮. ሥጋዋን ባይጋርድ ናይታየም ነበር፡፡ ከርሷም የትስብእትን ድርብ በፍታ ባይጎናጸፍ ባልተገለጸም

www.ethiopianorthodox.org

ነበር፡፡

፲፯. ለዘለዓለሙ የማትፈርስ የማትወድቅ ጸንታ የምትኖር አዳራሽ ለዘወትርም አጥረ ቅጥረ የማይፈርስ፡፡ የሥጋዊ ነገር ማዕበል ሞገድ የማይነቀንቃት የሥጋዊ ፈቃድም ነፋስ ኃይል የማያዘነብላት መርከብ፡፡

፲፰. ለአዳምና ለልጆቹ ቤዛ የሚሆነውን የሕይወት መድኃኒት መሥዋዕት የምትሸከም መሠዊያ፡፡

፲፱. እመቤቴ ድንግል ሆይ በብዙ ማናፊያ ካናፋት ከመሥሪያ እሳት ይልቅ የፍቅርሽ እሳትነት በሰውነቴ አዳራሽ ይሟሟቃል ይላላባል እኮን፡፡

፳. ከርሱም ይልቅ የፍቅሬ እሳትነት በሰውነትሽ አዳራሽ የበዛ ትርፍርፍ ያለ ይሁን፡፡ አንቺ ከወደድሽኝ ልጅሽ አይጠላኝምና፡፡

፳፩. ልጅሽም ከወደደኝ በኃይልም ቢሆን በሹመትም በተንኮልም በመላስም በሥራዬም በዘመናይነትም ቢሆን የሚችለኝ የሚቃወመኝ የለም፡፡

፳፪. ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረ እንዲህ ሲል እግዚአብሔር አምላካችን ከኛ ጋራ ከሆነ የሚችለን የለም፡፡

፳፫. ቀድሞ እንደተናገርሁት አሁንም ደግሞ መልሼ እናገራለሁ እንዲህ ስል ኪሩብ የያዘውን ዙፋን የረባኝ የጠቀመኝ የለም ሰማያትም የፈቡኝ የጠቀሙኝ የለም፡፡

፳፬. አንቺ ግን ከሞት ባርነት አዳንሽኝ የአብ በኩር ልጁ ካንቺ ሥጋ በመልበሱ ነው አሁንስ ወደማን እማልዳለሁ ወደማንስ ለሰው ልጆች ሁሉ የጸሎታቸው መውጫ መውረጃ መሰላል ወደምትሆን ወዳንቺ በቀር፡፡

፳፭. ጸሎቴ ባንቺ ትረግ ወደ ሥላሴ መንበር በአየርም ቢሆን በረጅሙም በሰማይ ዳርቻ በእሳት ደመና የተቀላቀለ የብርሃን መጋረጃ የሚያናቅፋት የሚከላክላት አይኑር፡፡

፳፮. ዓለምን እንደ ጽንሐሕ እንደ ዕንቁላል በያዘ በልዑል እግዚአብሔር በዙፋኑ ዙሪያ በሚቆሙ በካህናተ ሰማይ በማዕጠንታቸው ጽንሐሕ ውስጥ የተቀላቀለች ትሁን ኃጢአቴን ያቃጥል፡፡ ቁስለ ኃጢአቴንም የሚያጠግ የፈውስ የምሕረትን ምንጭ ይቅዳልኝ፡፡

፳፯. ስለ ልመናም ካንደበቴ የወጣችው አንዲት ቃል ለግዳጇ የምትረባ የምትጠቅም በጽርዓትም የምትቀር አትሁን፡፡ የፍጥረትንም ሁሉ ጸሎት በሚሰማ በልዑል እግዚአብሔር ፊት ደግሞ የተቃናች ትሁን፡፡

፳፰. ልመናዬም ያለ ዋጋ አትቅር የተመኘችውን ሳታገኝ ራቁቷን አትመለስ ያንቺ ኃይለ ቃል በኔ አንደበት አቸናፊ እግዚአብሔርን ይጥራው፡፡

፳፱. በልቡናዬ ያለውን ግዳጅ ሁሉ ለመፈጸም የልመናዬንም ዋጋ ለመስጠት ሁሉን የሚችል ሁሉን የሚያጽናና መንፈስ ይውረድ፡፡

፴. እንግዲህ ማናቸውን ደጅ እጸፋለሁ ከቤትሽ ደጅ በቀር ይኸውም መሃይምናን የሚጸልዩበት የስምሽ መኖሪያ ነው፡፡ ከቤትሽም በገባሁ ጊዜ ወደ ልጅሽ እጮሃለሁ እንዲህ ስል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፵፩. አቤቱ ሆይ የስምህ መኖሪያ ወደምትሆን ወደዚች ቤት መግባቴን ለሕይወት ለደኅንነት ለሰላም ለደስታ ለጸጋ ለክብር ለባለሟልነት ለሰወ ፍቅር ብሩህ ለመሆን አድርግ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፬</u>

፩. አቤቱ ሆይ የምሕረትህን ደጅ ክፈትልኝ ምንም ስለ ኃጢአቴ የተዘጋ ቢሆን አቤቱ ሆይ የቁጣህን ደጅ ዝጋልኝ ምንም ስለበደሌ የተከፈተ ቢሆን አንተ እንዲህ ብለሀልና፡፡

፪. የሻ ሁሉ ያገኛል የጸፋም ይከፈትለታል፡፡ አቤቱ ይቅርታህን እሻለሁ እንዳገኝ ስጠኝ፡፡ አቤቱ ሆይ የምሕረትህን ደጅ ጸፋሁ እንድገባ ክፈትልኝ (ማቴ ፯ ፣ ፰)

፫. ምንም ቸርነትህን ባስቆጣት ባበሳጫትም መሐሪት ዓይንህ ትመልስልኝ ይቅርታን የተመላች ቀኝህም ትደግፈኝ፡፡

፬. የቁጣህን ጽዋ በላዬ አታፍስስ ለጥፋትም የተዘጋጀውን የኃጥኣንን በትር በላዬ አታንሣ በውነትህ ገሥጸኝ በይቅርታህም ተከራከረኝ እንጂ የቁጣህ በትር ከምሕረትህ አጽቅ ተቆርጣለችና (መዝ ፣ ፻፵፩ ፣ ፫)

፭. አቤቱ የኃጢአቴን ቁጥር አትተሳሰብ የተጻፈውን ፋቀው፡፡ ያልተጻፈውን ደግሞ አታስበው ከትሩፋት ግን ጠቂት ብሰራ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህልም ቢሆን ወይም የምጣድ ብልጭልጭታ ወይም የእሳት ፍንጣሪ ያህል በቸርነትህ አብዛው፡፡

፮. የተጻፈውንም አትደምስሰው ያልተጻፈውንም በማይጠፋው በማይደመሰሰው በቅዱሳን መጽሐፍ ጻሐፈው፡፡

፯. ለኔ የደለበችውንም የዕዳ በደል ደብዳቤ ወደ ምሕረትህ ጥልቅ ባሕር ጣላት ወርውራት፡፡ አቤቱ የይቅርታህም ማዕበል ሞገድ ያስጥማት የስሟም አጠራር ለዘለዓለም እንዳይኖር ጽሕፈቷን አጠብ ሰርዛት፡፡ አቤቱ ቸር ሰው ወዳጅ ለሆን ለአብ ለባሕርይ አባትህ ይቅር ባይ ለመንፈስ ቅዱስ ለባሕርይ ሕይወትህ ላንተ ክብር ምስጋና ይገባል ለዘለዓለሙ በውነት ያለ ሐሰት፡፡

፰. የተድላ ደስታ መፍሰሻ በምትሆን እናትህ በጸሎቷ ለሚያምኑ ጸጋ ክብር ኃይል ባለሟልነት ይገባቸዋል፡፡ የድሆች ልጅ ስትሆን ኪሩባዊውን ሠረገላ መስላ ለተሸከመችህ ለርሷ ጸጋ ክብር ኃያልነት ይገባል፡፡

፱. አሁንም እንግዲህ ቅድስት ድንግልን እናመስግናት እናዳንቃት እንዲህ እያልን፡፡ በየጊዜው ሁሉ ንጽሕት ሆይ በየሰዓቱም አደፍ ጉድፍ የሌለብሽ በመፅነስም ቢሆን በመውለድም ባራስነትም ቢሆን ያደፍሽበት የረከሰሽበት ሰዓት የለም፡፡

፲. በመውለድ ማኅተም ድንግልናዋ ያልተለወጠ እናት ሆይ፡፡ ድንግልናዋም በሥርዓቱ ተጠብቆ የነበረ ብላቴናውን ለማሳደግ ወተት በድንግልና ይፈሳት የነበረች ድንግል፡፡

፲፩. ሳይዘሯት የምታፈራ ንጽሕት እርሻ እርሷም ለቁርባን ያማረ የተወደደ ስንዴ የተሰጠ ሳያጠጧት የለመለመች የወይን ሐረግ ለበዓልም መጠጥ ሊሆን የበረከት ፍሬ ከርሷ የተገኘ፡፡

፲፪. የጌዴዎን ብዝት ግምጃ በድንግል ትመሰላለች ምድር ሁላ በመላዋ ደርቅ ስትሆን እርሷ ብቻዋን በዝናም ካፊያ ርሳ ለምልማ ተገኝታለችና፡፡ (መሳ ፮ ፣ ፴፯ ፣ ፴፰)

www.ethiopianorthodox.org

፲፫. ሴቶች ሁላ ከዚያ ጠል ያልተነካኩ ሲሆኑ ከሰማያዊ አብ ብብት የወረደውን የበረከት ጠል እንደተቀበለች፡፡ ጠሉን ለመቀበል ሌሎቹ ሴቶች ዝግጁ አይደሉምና፡፡

፲፬. ከዝናሙም ካፊያ ምድር ሁላ በመላዋ ለምለም ስትሆን ግምጃዪቱ ደግሞ ደረቅ ሁና ተገኘች (መሳ ፮ ፣ ፴፱ ፣ ፵)

፲፭. ሴቶች ሁላ በተለመደው በወንዶች ዘር ሲፀንሱ ድንግልን የሴቶች ልማድ የወንዶች ዘር አላገኛትምና፡፡

፲፮. ድንግል ግን በሥርዓት ከሴቶች ጋራ አልተባበረችም፡፡ መፀነሷ ልዩ ሆነ መውለዷም ደግሞ ልዩ ነው፡፡

፲፯. የወርቅ ጎሞር በወርቅ ተመሰለች፡፡ እንደ አራሾች ሥርዓት በአውድማ ያልተበራየውን እንጀራ ተሸክማለችና (ዘፀአ ፲፮ ፣ ፴፪ ፣ ፴፫)

፲፰. የአሮን በትር በድንግል ተመሰለች ሳይተክሏት ለምልማ፡፡ ውሀ ሳያጠጧት አብባ ተገኝታለችና (ዘኍልቁ ፲፮ ፣ ፰)

፲፱. ድንግል እነሆ ይህች ነቢዩ ዳዊት ስለርሷ አሰምቶ የተናገረላት እንዲህ ሲል ስሚ ልጄ ጆሮሽንም አዘንብይ፡፡ ሕዝብሽንና ያናትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥም ውበትሽን ወዷልና እርሱ ጌታሽ ነውና፡፡ (መዝ ፵፭ ፣ ፲፩)

፳. ድንግል ይህች ናት ኢሳይያስ ነቢዩ ስለርሷ የጮኸለት፡፡ እንዲህ ሲል እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ትለዋለች፡፡ (ኢሳ ፮ ፣ ፲፬ ማቴ ፩ ፣ ፳፫)

፳፩. ድንግል ይህች ናት ሕዝቅኤል ስለርሷ ትንቢት የተናገረላት እንዲህ ሲል በታላቀ ዕፁብ ድንቅ ማኅተም የታተመ ደጅ በምሥራቅ አየሁ፡፡ ከኃያላን ጌታ በቀር የገባባት የለም እርሱ ግን ወደርሷ ገብቶ ወጣ፡፡ (ሕዝ ፵፬ ፣ ፩ ፣ ፪)

## ምዕራፍ ፫

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለች የተመረጠች ድንግል ማርያም ይህች ናት ነቢያት ያሰቧት ሐዋርያት ያደነቋት የደናግል የሰማዕታት ማኅበር ለርሷ ይገዛሉ፡፡

፪. ድንግል ሆይ በመሃይምናን ሁሉ አንደበት የስምሽ አጠራር እንደምን ይጥማል ድንግል ሆይ የገናንነትሽ ምስጋና እንዴት ያምራል፡፡ ንጽሕት ርግብ ሆይ ከፀሐይ ከጨረቃ ከከዋክብት ብርሃን ይልቅ የሚያምር የመልክሽ ደም ግባት እንዴት ያማረ የተወደደ ነው፡፡

፫. የምስጋናሽስ ዘፈን ማኅሌት ምን ያህል ይወደድ ለሚሰማው እጅግ ያማረ የተስማማ ነው፡፡ መሰንቆ ለጆሮ እንዲያምር እንዲስማማ የሙሽራ ጌጽ ላይን ማር ላፍ ሽቱ ላፍንጫ የወይን ወለላ ለጉረሮ ጸጅ ለልብ ያማረ የተስማማ እንደ ሆነ፡፡ ውዳሴሽም እንዲሁ ያማረ የተስማማ ነው፡፡

፬. ድንግል ሆይ ክብርሽንና ገናንነትሽን መናገር እጅግ ያማረ እጅግም የተወደደ ነው፡፡ ያበባዋም መልክ የማይጠወልግ የማትደርቅ ንጽሕት ተክል ሆይ የማትጠወልግ የሕይወት እንጨት የአሸቷ ፍሬ የማይረግፍ፡፡

፭. የማትሰበር የክህነት በትር የቅዱስ ምሥጢር አገልጋዮች ካህናቱ የሚመረኮዟት የሚጸጉባት

ለምዕመናን ሕንፃ ዘወትር ዝግጁ የሆነች የማትነዋወጽ የሃይማኖት መሠረት፡፡

፮. ብል ነቀዝ የማያበላሻት ሌባ የማይቀርባት መርከብ የውስጧም ዋናተኛ ቀዛፊውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱም በቅዱስ ወንጌሉ ቀዛፊዎች በሐዋርያት ዓለምን ሁሉ ከኃጢአት ማዕበል ሞገድ የሚያሻግር ነው፡፡

፯. የመርከቢቱ ምሰሶ ግን ከሁሉ በላይ የሚሆን አብ ነው፡፡ የባህሩም ጸጥታ መልሕቁ የድንግልና መርከብ እንዳትሰበር የሚመግባት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው፡፡

፰. የሥጋዊ ፈቃድ ሙሽራ ያይደለሽ የመንፈሳዊ ሙሽራ ርግብ ሆይ በመመረጽ ማኅተም የተጌጥሽ የተሸለምሽ ነሽ፡፡ የሐሰት ደንጊያ በሚሆን በኃላፊው ወርቅ ሽልማት ጌጥ አይደለም ሥጋዊውንም ፈቃድ በሚያመጣ ዋጋው በበዛ ዕንቁ አይደለም፡፡

፱. የንጽሕና ቀሚል የምታጠልቅ የብርሃን መጎናጸፊያ የምትጎናጸፍ ንግሥት ቁልፏ ሳይከፈት ከውስጧ የሕይወት ውሀ የተቀዳባት የተቆለፈች የክብር አዘቅት፡፡

፲. በሐዲስ ሥርዓት የሆነው ደጅዋ ሳይከፈት ፍሬዋ የተለቀመ የተዘጋች የተክል ቦታ ገልጾ ሲያነባት የሚችል የሌለ የታተመች መጽሐፍ በአለቆች ላይ አለቃ ለሚሆን በነገሥታትም ላይ ለሚነግሥ መቀመጫ የምትሆኚ ኪሩባዊት ሠረገላ፡፡

፲፩. የመለኮት አትራኖስ የእሳትነቱን ነበልባል የተሸከመች ሥጋዊት ዙፋን የሰማይ ሁለተኛ ሰማይ እውነተኛውን ያራቀ ያስወገደ የቅዱሳን ብርሃን ነው፡፡

፲፪. ዝናማት ያላበቀሉትን አየራት ያላሳደጉትን የሰማዩን እንጀራ ያስገኘች ቤተልሔማዊት መሶብ ሆይ የእሳቱን ነበልባል የተሸከመች ዕፀ ጳጦስ ሆይ አንጨቱ ሳይቃጠል እሳቱ ሳይጠፋ፡፡ (ዘፀአ ፫ ፤ ፪ ፤ ፲፯ ፤ ፳፪)

፲፫. የዚህም ምሳሌ ትርጓሜው ሚጠት ውላጤ ሳይኖርበት ካንቺ የነሣው የወልድ ትስብእት ምሳሌ ነው፡፡ የትንቢት ምንጭ የምስጋና መፍሰሻ፡፡ የደስታና የኃሤት መቅጃ፡፡

፲፬. የነቢያት ጌጻቸው የሐዋርያት አክሊላቸው የደናግል መነኮሳት መመኪያቸው የሰማዕታት እናታቸው፡፡ የመላእክት እኅታቸው፡፡ ከሱራፌል የተወዘወዘች የቅዱስ ምሥጢር ጽንሐሕ፡፡ የኪሩቤል የዕጣናቸው መዓዛ፡፡

፲፭. የማይተኙ የማያንቀላፉ ትጉሃን የሰማይ መላእክት ሁላቸው የሚያመሰግኗት በየነገዳቸውም ለልጅዋ ክብር ጌትነት ገናንነት ይገዛሉ፡፡ መላእክት በሥርዓታቸው፡፡ የመላእክትም አለቆች ባነዋወራቸው፡፡ አጋዕዝት በገናንነታቸው ይገዛሉ፡፡ ሥልጣናት በክብራቸው መናብርት በከፍታቸው ይገዛሉ፡፡ (ዳን ፯ ፤ ፲፬)

፲፮. ኃያላን በየወገናቸው ሊቃናት በሹመታቸው ሱራፌል በምስጋናቸው ኪሩቤል በቅዳሴያቸው ይገዛሉ ወደ ዙፋኑም የቀረቡት የተጠጉትም በክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ ከርሱ የሚወጣው የእሳቱ ኃይል እንዳያቃጥላቸው (ኢሳ ፮ ፤ ፪) (ሕዝቅ ፩ ፤ ፳፫)

፲፯. በዙፋኑ ዙሪያ ከበው የሚቆሙትም ሱራፌል ይጮኻሉ እንዲህ ሲሉ፡፡ አቸናፊ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ ቅሱስ ክቡር ምስጉን ልዩ ነህ ምስጋናህም ምድርን ሁሉ መላ፡፡ (ኢሳ ፮ ፤ ፫)

፲፰. ሳያቋርጡ በምስጋና ይጮኻሉ ምስጋናም በተመላ በሰላም ቃል ያለዚያ አንዱም ላንዱ ሁለተኛውም

ለሌላው ይመልስለታል፡፡

፲፱. ባነዋወር የከበሩ ቅዳሴንም የተመሉ እንስሶች ፊታቸው ዐራት ነው፡፡ ክንፋቸውም ስድስት ነው፡፡ ከእሳት የተሠራውን ዙፋን ተሸክመው ቅድመ ዓለም ለነበረው ኋላም ዓለምን አሳልፎ ለሚኖረው ይሰግዳሉ (ራእይ ፬ ፥ ፰)

፳. እሊህም አለቆቶች የወርቅ ማዕጠንት የያዘ የብርሃን ሞጣሕት የለበሱ ናቸው አክሊላቸውም እንደበረድ ነጭ ነው፡፡ እርሳቸውም ደግሞ በበጉ ፊት ይሰገዳሉ እንዲህ ሲሉ (ራእይ ፬ ፥ ፰)

፳፩. ጌታ ሆይ ምስጋና ክብርም ችሎታም ትቀበል ዘንድ ላንተ ይገባሃል፡፡ (ራእይ ፬ ፥ ፲፩)

፳፪. ዕጣንን የተመላ የወርቅ ጽንሐሕ ይዘው ለመለኮትነቱ እጅ መንሻ ያቀርባሉ ይኸውም የንጹሓን ጸሎት መዓዛ ነው፡፡

፳፫. እመቤቴ ሆይ ባንቺ ጸሎቴ ትረግ በለዚህም ዕጣን ማዕጠንት ትዋሐድ በእስራኤልም ቅዱስ ፊት የተወደደች እርሱም የተቀበላት ትሁን፡፡ በጸሎትሽም መዓዛ ጸሎቴ የጣፈጠች ትሁን ልጅሽ በመቀበል እንዲያሸታት በሉባር ተራራ ያሸተተውን የኖኅን መሥዋዕት እንዳሸተተ፡፡ (ዘፍጥረት ፰ ፥ ፳ ፥ ፳፩)

፳፬. አብርሃም በተራራ ላይ የሠዋውን የሥዋዕት እንደተቀበለ ጸሎቴንም ደግሞ ይቀበል፡፡ ይስሐቅ በአዘቅተ መሐላ ያዕቆብ የሚደን አውራጃ በምትሆን በሎዛ የሠዉትን እንደተቀበለ፡፡ (ዘፍጥ ፳፪ ፥ ፲፫)

## ምዕራፍ ፮

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ የምሕረት ነቅዕ የሚሆን ልጅሽን ለምኝው ኃጢአቴን እንዳይዘከር እንዳያስብ፡፡

፪. በኃጢአት ሁሉ እንደኔ ያለ ሴሰኛ ርሱስ አበሰኛ በደለኛ የለም፡፡ እንደ ልጅሽም ቸር ሰው ወዳጅ ይቅር ባይ ከመዓት የራቀ ምሕረቱ የበዛ እውነተኛ የለም፡፡ (መዝሙር ፹፮ ፥ ፲፭)

፫. የመድኃኒት ብልቃጥ ድንግል ሆይ ጸሎቴ በልጅሽ ፊት የተወደደ ይሁን የሙሴ መሥዋዕት በምድረ በዳ የአሮን መሥዋዕት በምስክሩ ድንኳን የተወደደ እንደ ሆነ፡፡

## ምዕራፍ ፯

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ የሰው ልጆች ሁሉ ጸሎት መመለለሻ የአዳምም ልጆች ሁሉ ምሕላ መቀበያ ንጽሕት የወርቅ መሰላል የአካል ሦስትነት ወዳለበት ወደ ላይ ጸሎቴን አሳርጊ፡፡

፪. በዚያውም ላይ ኃጢአቴን የሚያርቅ ዕዳዬን የሚከፍል ያማረ የተወደደ እግዚአብሔርም በረድኤት የተቀበለው ይሁን፡፡

፫. ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታገባ የመድኃኒት ደጅ ድንግል ሆይ ወደ ልጅሽ ወደ ወዳጅሽ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሠርግ እንድገባ አድርጊኝ፡፡

፬. የክርስቲያን ወገኖች ሁሉ የሚጸጉባት የሃይማኖት በትር ድንግል ሆይ በኃጢአት ተሰናክዬ በመሪር ልቅሶ ላይ ከመውደቅ ደገፊኝ፡፡

፭. የሕይወት ውሀ መቅጃ የክብር አዘቅት ድንግል ሆይ ከሥጋዬ ርሱሰት ንጹሕ አድርጊኝ ያውም የማመንዘር ርኩሰት ነው፡፡

፮. ከሽቱ ሁሉ መዓዛ ያማረ የተወደደ የበረከት አበባ የሚሆን ዐማኑኤልን ያስገኘሽ ነባቢት ገነተ ድንግል ሆይ በሽቱሽ መዓዛ እንድሻተት አድርጊኝ፡፡ በንጽሕናሽ መዓዛም የኃጢአቴን ክፋ ሽታ አርቂልኝ፡፡

፯. በወርቅ ዘርፍ ልብስ የተጎናጸፈች የተሸለመች ንግሥት ሆይ በየጊዜው በየሰዓቱ የንጽሕና ልብስ የቅድስናም መጎናጸፊያ እንደ ልብስ አድርጊኝ፡፡ (መዝ ፵፭ ፣፲፬)

፰. ዓመፀኞች በደለኞች የሚሆኑ አሕዛብ አርበኞች በጦርነት የማይደፈሩ ኃያላን ሠራዊት ሊወጡባት ሊደፋፈሯት የማትቻል የመሃይማናን መጸጊያ አምባ ኮረፍታ ድንግል ሆይ ካልታወቀ ከተሠወረ ከታወቀ ከተገለጸ ጠላት መነሳሳት አድኚኝ፡፡

፱. ካመፀኞች ከበደለኞች ሰዎችም ፀብ ክርክር ሠውሪኝ፡፡ ከመለስ አሉባልታም በጥላሽ በረድኤትሽም ክንፍ ሸፍኚኝ፡፡

፲. የሲኦል አጋንንት የማይበረታቱባት የቤልሆር ሠራዊትም የማያጠፏት በማይከፈል በሦስቱ ቅዱስ ሃይማኖት የወርቅ መሠረት ላይ የተመረሠረተች የማትፈርስ የሕይወት የመድኃኒት ግድግዳ ድንግል ሆይ ለዘለዓለም እውነተኛ ምግብ የሚሆን መና የተከማቸብሽ የወርቅ መሶብ ሆይ፡፡ ጽርሰፎራውን የቁርባኑን መሥዋዕት ልጅሽን እንድቀበል አድርጊኝ፡፡

፲፩. የመንፈስ ቅዱስ መዓዛ የተዋሀደውን የምሥጢሩን ወይን የምትሸከም የወርቅ ጽዋ ድንግል ሆይ ከልጅሽ ደም እንድቀበል የተገባሁ አድርጊኝ፡፡ በመጠጣቱም ቅዱስ በመቀበሉም ንጹሕ ልሁን፡፡

፲፪. ድንግል ሆይ የንጉሥ እናት ንግሥት እመቤቴ የእግዚአብሔር እናት ክብርት የአምላክ እናት ንጽሕት የንጹሕ ባሕርይ እናት ሰማይ የፀሐይ መገኛ ቤተ መንግሥት የመሢሕ እናት ታቦት የሕግ እናት፡፡

፲፫. ድንኳን የነባቢ በግዕ እናት የወይን ሐረግ የሕይወት ፍሬ መገኛ ብዝት ግምጃ የጠል መውረጃ መሠዊያ የሰማያዊ ቁርባን እናት መርከብ የዋነተኞች እናት መቅደስ የካህን እናት ሰፊ መጋረጃ የመለኮታዊ ምሥጢር መኖሪያ፡፡

፲፬. መቅረዝ የብርሃን እናት ንጽሕት ጥጃ የነጭ በሬ እናት ልዕልት በአርያም የሚኖር ልዑል እናት ቡርክት የአኩት እናት ውድስት የምስጉን እናት ምዕዝት የሽቱ እናት የወርቅ ሣፅን የዕንቁ ባሕርይ መገኛ፡፡

፲፭. ጎሞር የመና እናት ኢየሩሳሌም የትንቢት ሀገር መመኪያችን የሐዋርያት እናት ምሥራቅ የሰማያዊ ኮከብ መገኛ፡፡

፲፮. ድንግል ሳላቋርጽ አመሰግንሽ ዘንድ የኪሩቤልን አፍ የሱራፌልን ልሳን ብቀበል በዚህም ምስጋናሽን ለመፈጸም አልችልም፡፡ ልዑሉንም ምሥጢር እናገር ዘንድ እንደ ነቢዩ ሕዝቅኤል የተሠወረውን ምሥጢርም እንደ ዮሐንስ የዕውቀት መጻሕፍትንም ብበላ በዚህም ውዳሴሽን ለመፈጸም አልችልም፡፡

፲፯. የሰሎሞንን ጥበብ ብነሣ የልቡናዬም አፅቅ ቢሰፋ እስከ ባሕር ቢዘረጋም የቃሌም ቡቃያ እስከ ቀላይ ድረስ ቢጠልቅ በዚህ ውዳሴሽን ለመፈጸም አልችልም፡፡

፲፰. መጋቤ ብርሃናት በሚሆን በዑራኤል መልአክ እጅ ዕውቀት የሚገልጥ የእሳት ጽዋን ሱቱኤል የተባለ

www.ethiopianorthodox.org

እዝራ እንደ ጠጣ የመጻፍትን ነገር የሚያናግር የምስጋና ጽዋን ብጠጣ፡፡ በዚህም ቅዳሴሽን ለመፈጸም አልችልም፡፡

፲፱. ድንግል ሆይ ሰውነቴ ሁሉ አንደበት የተመላ ቢሆን ባፅንቶቼም ቁጥር ዕውቀት ቢሰጠኝ የራሴ ፀጉርም ሁሉ መናገር ቢሰጠው በዚህም ውዳሴሽን ለመፈጠም አልችልም፡፡

፳. ሰማይ በስፋቱ ብራና ቢሆን ባሕርም ቀለም ቢሆን ምስጋና የተመላውን ክብርሽን ገናንነትሽን ለመጻፍ በዚህም ምስጋናሽን ለመፈጸም አልችልም፡፡

፳፩. የነቢያትና የሐዋርያት ማኅበር ለመፈጸም የማይችሉት ምስጋናሽን እኔ ድሀው ለመፈጸም እንደምን እችላለሁ፡፡ የጻድቃንና የሰማዕት ማኅበር ለመፈጸም የማይችሉት ውዳሴሽን እኔ ወራዳው ለመፈጸም እንደምን እችላለሁ፡፡

፳፪. የደናግል መነኮሳት ማኅበር ለመፈጸም የማይችሉትን ቅዳሴሽን እኔ ምስኪኑ ለመፈጸም እንደምን እችላለሁ፡፡ አሁን ግን የኃጢአቴ ብዛት ከቁጥር ከስፍር የተረፈ ሁኗልና በልመናሽ አቅልይልኝ፡፡

## ምዕራፍ ፰

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ለጸሎት እጄን ወደ ልጅሽ በዘረጋሁ ጊዜ ስለኔ ለመጸለይ ቅዱሳት እጆችሽን ንጹሓን ጣቶችሽን ወደልጅሽ ዘርጊ ከኔም ጋራ ቁሚ፡፡

፪. በርሷ ያለውን ምኞት ግዳጅዋንም ለማግኘት ልቡናዬ እንድትተጋ እንዲሁ ደግሞ አንችም ግዳጄን ለመስጠት የከበደውንም ጭንቄን ለማቀለል የተጋሽ የነቃሽ ሁኚ፡፡

፫. ከሁሉ ይልቅ እኔ ድሀ ስሆን ከሁሉ ይልቅ ጻድቅ እንደሆንኩ አስቤ ባንቺ ባለጸግነት እመካለሁ፡፡ ከሁሉም ይልቅ ኃጥእ ስሆን ከሁሉ ይልቅ ጻድቅ እንደ ሆንሁ አስቤ በንጽሕናሽ እመካለሁ፡፡

፬. በኔም በጎ ሥራ በትሩፋቴም የመጽደቅ ተስፋ የለኝም፡፡ ባንቺ ጽድቅ በበጎው ሥራሽ እንጂ በራሴም ድካም የመዳን ተስፋ የለኝም ባንቺ እንጂ፡፡

፭. ኃጢአቴን ለመናገር ለምን አፍራለሁ አለመናዘዜስ ለምን ነው የሚከሱኝ ጠላቶቼ የሚመሰክሩብኝም ኃጢአቶቼ ሳሉ እንግዲህ ኃጢአቴን እናገራለሁ የተሰወረውን በሚያይ አፍ የተናገረውን ልቡና የመከረውን መርምሮ በሚያውቅ በልዑል እግዚአብሔር በዓይኖቹ ፊት የተገለጸ ሲሆን እኔ ለምን እሠውረዋለሁ፡፡

፮. እኔም ብሠውረው ኃጢአቴ ሊከሰኝ ይጮኻል፡፡ በደሌን ለማመን እኔ እንግዲህ ለምን ዝም እላለሁ፡፡ የሠራሁትም ክፉ ሥራዬ ያሳጣኛል፡፡ እኔ እንዳልሠራ ለምን እሆናለሁ፡፡ የሚዘልፈኝ ምስክር አልሻም እኔ ለራሴ የራሴን ዘለፋ እነባለሁ እንጂ፡፡

፯. ለምን እሠውረዋለሁ፡፡ የማይሠወርልሽን ስለዚህ እንዲህ እላለሁ፡፡ ስለ ኃጢአቴ ራሴን ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጠላለሁ፡፡ (መዝ ፴፪ ፣ ፬)

፰. ደግሞ እንዲህ አልሁ፡፡ ኃጢአቴ ከራሴ ፀጉር በዝቷልና እንደ ጽኑ ሸክም ከበደኝ፡፡ ከስንፍናዬም የተነሣ ቁስሌ መገለ፡፡ እጅግም ከረፋ ሸተተ፡፡ (መዝ ፴፰ ፣ ፬ ፣ ፭)

፱. ዳግመኛም እንዲህ አልሁ ስፍር ቁጥር የሌላት ክፉ ነገር አግኝታኛለችና ኃጢአቶቼ አገኙን ያዙኝም እኔ ግን ማየት ተሳነኝ፡፡ (መዝ ፵ ፣ ፲፪)

## ምዕራፍ ፱

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ ስለኔ ጸልዩ ለምኝልኝ እኔ ባንቺ ጸሎት አምኛለሁና፡፡

፪. ለልጅሽ ይቅርታ መምጣት እንጋጥጣለሁ ለክብርሽም እሰግዳለሁ፡፡ ለገናንነትሽም እሰግዳለሁ (እገዛለሁ) ላንቺ አገልጋይ የሚሆን የባርነቴ ደብዳቤ በልቤ ሰሌዳ ተጽፏል፡፡ ጽሕፈቱም እንዲህ የሚል ነው፡፡ አምላክን ለወለደች ድንግል በዕብራይስጥ ማሪሃም ለተባለች ለተመረጠች ንዕድ ክብርት ለሆነች ማርያም ባሪያዋ አገልጋይዋ ልጅዋ ወዳጅዋ ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጀው ዕገሌ ነው፡፡

፫. ይህችም ደብዳቤ በልጅሽ በኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ቀለምነት ልቡናዬ ሰሌዳ ሁኖ ተጽፋ ትኑር፡፡ ጽሕፈቷም ለዘለዓለሙ አትፋቅ በመከራም በሞትም በሕይወትም ቢሆን አትደምሰስ፡፡

፬. ለዘለዓለሙ ተጽፋ ትኑር የተሰወረውን የሚያውቅ መንፈስ ቅዱስ ያንብባት የሚያጠፋትም የለም ያለ መለየት በአነዋዋር በተባበሩ አንዱም ሳይበልጥ አንዱ ሳያንስ አንዱ ሳይቀድም አንዱ ወደ ኋላ ሳይቀር ባገዛዝ በአነዋዋር በመልክ አንድ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ታትማለችና፡፡

፭. አኳኋናቸውም አይታውቅም ይህ ከዚህ ነው፡፡ ሁለተኛውም ከዚህ ውስጥ ነው፡፡ ሦስተኛው እንዲህ ያለ ነው አይባባሉም፡፡ ባለመለየት ሲኖሩ ለቀዳማውያንነታቸው ጥንት ለደኃራውያንነታቸው ፍጻሜ የለውም፡፡ ለዘለዓለሙ በውነት ያለ ሐሰት የሚሰማውም ሁሉ ይበል አሜን በውነት ይሁን ይደረግ፡፡

## ምዕራፍ ፲

፩.በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ አንቺ ደግሞ የምሕረት ዓሥራት አድርገሽ ውደጅኝ፡፡ ሰውና መላእክት በተሰበሰቡ ጊዜ፡፡

፪. መባርቅትም በተጨነቁ ጊዜ የበደሉትም የዕዳ በደላቸው ደብዳቤ በተገለጸ ጊዜ የተዳደፉትንም በሚያረክስላቸው ጊዜ፡፡ በተድላ በደስታ ካንቺ ጋራ እንድኖር እንድመላለስ አድርጊኝ፡፡

፫. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ያለ ዋጋ የምሕረት ምጽዋትን ካንቺ ዘንድ እለምናለሁ፡፡

፬. ወንድ ልጅ ካባቱ መልካሙን ስጦታ እንዲለምን፡፡ ሴት ልጅም ከናቷ በጎውን ነገር እንድትለምን ወንድ ባሪያ ከጌታው ሴት ባሪያ ከመቤቷ እንዲለምኑ፡፡ እንዲሁም ከበጎ ሥራ ከትሩፋት ባዶ ስሆን ባንቺ ደግነት የሚገኘውን በጎውን ዋጋ ለማግኘት ነፍሴ ትታመናለች፡፡

፭. የመለኮት ዙፋን ሆይ ከምስጋና ጌታ በቀር ምንም ያልገባባት ንጽሕት አዳራሽ፡፡ እርሱ ግን እደተቆለፈች የገባ፡፡ እንደተዘጋችም የወጣ፡፡ የልጅሽ ሙሽርነት በሸህ ማዕድ ባምሳሐ ደብረ ጽዮን እንድቀመጥ ዝግጁ አድርጊኝ፡፡

፮. የዓሣትን ዘመዶች እርሳቸውም የሦስቱ አስማት የሥላሴ ማኅበር የሚሆኑ የቅዱሳንን ነፍሳት የምትሰበስብ ዘረመትራ ሆይ ማቴ ፲፫ ፤ ፵፯ ፤ ፵፰፡፡

፯. ከሐር ፈትል የተሠራች በውርቅ መርገፍ የተጌጸች የተከፈፈች ጌጿ ፈርጿም ለዓይን የሚያምር ንጽሕት የተድላ ደስታ መጋረጃ ያቸናፊ ልዑል እግዚአብሔርን የበሕር ልጁን የተሸከመች የአሚናዳብ

www.ethiopianorthodox.org

ሠረገላ፡፡

፰. ዓለምን ሁሉ የመላ እርሱን የተሸከመሽ ድንግል ሆይ ሁከትን በተመላ ዘመን ሠረገላ ከሚጫን ከዓለም ኅልፈት ጥፋት እንድድን አድርጊኝ፡፡

፱. የዓለም ሁሉ አርነት ደብዳቤ የተጻፈብሽ የሕይወት መድኃኒት ሰሌዳ ሆይ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት አዕማድ ስሜን ጻፊልኝ፡፡ የሕግና የሥርዓት ነቅዕ የሚሆኑ የነቢያት ማኅበር ድንኳን ከተተከለበት፡፡

፲. የአሕዛብ ብርሃን የዕውራን መሪዎች የሚሆኑ ሐዋርያት የተተከለበት ትስብእት እስከዚህ ድረስ ለለበሰ አምላክ የመከራው ተካፋዮች የሚሆኑ እንደ በግ በሰይፍ የታረዱ እንደ ወርቅ በእሳት የተፈተኑ የሰማዕታት ማኅበር ድንኳን ከተተከለበት፡፡

፲፩. ለንጉሠ ነገሥት እጅ መንሻ የመንፈስ ቅዱስ ድልብ የተባሉ፡፡ ያለ ማቋረጥ በማመስገን ያለ ርኩሰትም በንጽሕና አናዋዋራቸውን ወደ መላእክት ሥርዓት የለወጡ የደናግል የመነኮሳት ማኅበር ድንኳን ከተተከለበት፡፡

፲፪. የሐዲስ ሥርዓት መሥዋዕት መዓዛ የሚሠምርብሽ ንጽሕት ጠረጴዛ ሆይ የኔን ርኩሰትና ዝገት በንጽሕናሽ ወልውይው ሸንግዪልኝ፡፡

፲፫. ጽሕፈታቸው የልዑል እግዚአብሔር ጽሕፈት ሥራቸውም የልዑል እግዚአብሔር የሚሆን የመሐላ ጽላት በወርቅም የተለበጠ ታቦት በውስጧ ያለባት የቅዱሳን ቅድስት የተባለች የሕይወት የመድኃኒት ሁለተኛ ክፍል ሆይ፡፡

፲፬. ለኃጢአቴ ሥርየት ለብዙዎችም ቤዛ ሊሆን እራሱን ያማረ የተወደደ መሥዋዕት የበጎ መዓዛ አድርጎ ያቀረበ የካህናቱ አለቃ ልጅሽ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደገባበት ጽርሐ አርያም መጋረጃ ውስጥ ደግሞ ስሜን ጻፍልኝ፡፡

## ምዕራፍ ፲፩

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ፡፡ በጸሎትሽ የታመንሁ ስሆን ማነን እፈራለሁ፡፡ ከማን ግርማ መፈራት የተነሣ እደነግጻለሁ፡፡

፪. እንግዲህ የሚችለኝ የለም፡፡ ሰማይ መጅ ቢሆን ምድርም ወርጮ ቢሆን እኔንም ለመፍጨት ቢገናኙ የሚያደርጉኝ የለም፡፡

፫. ምድርም ከበታቿ ያለውን የቀላይን ምንጭ ሁሉ ብታመነጭ ቀደሞም በኖኅ ጊዜ እንደ ተደረገ የጥፋት ውሀን ለማውረድ ሰማይ ቢቀደድ በጸሎትሽ አምኜ ሳለሁ የሚጎዱኝ የሚያደርጉኝ የለም፡፡ ዘፍ ፯ ፣ ፩፡፡

፬. በሎጥም ዘመን በሰዶምና በገሞራ ላይ እንደ ዘነመ እሳትና ድኝ ቢዘንብም በልመናሽ አምኜ ሳለሁ የሚያደርገኝ የለም፡፡

፭. ኖኅም በዕንጨት መርከብ ከማየ አይኄ እንደ ዳነ እንዲሁም እኔም በቅድስናሽ መርከብ እድናለሁ፡፡ ዘፍ ፯ ፣ ፲፫፡፡

፮. ሎጥም በቅዱሳን መላእክት እጅ ከወረደው እሳትና ዲኝ እንደ ዳነ እኔ ደግሞ በቅዱሳት እጆችሽ የማይዳሰሰውን እሳት ባቀፉት በዓለም ላይ ከሚመጣው ከወረደውም መቅሠፍት እድናለሁ፡፡ ዘፍ ፲፱ ፣

፳፱፡፡

፯. ረአብ ዘማም በማመኗ ፈትለ ለይ ቀይ ሐር በቤቷ መስኮት ዓሥራ ሰባቱ የከነዓንን ነገሥታት ካጠፉ ከእስራኤል አርበኞች እንደዳነች እኔም እንዲሁ በጸሎትሽ በመታመን ከምትመጣብኝ ከጠላት ጠብ ክርክር እንዳመልጥ የልጅሽ የወዳጅሽን የደሙን ቅላት ምልክት አድርጌ እድናለሁ፡፡ ኢ.ያሱ ፪ ፣ ፳፩፡፡

፰. ቅድስት ድንግል ሆይ ምስጋናሽ ለልቤ መሰንቆ ነው፡፡ የውዳሴሽም ዘፈን ላፌ እንዚራ ነው፡፡ የፊትሽም መልክ ባይኖቼ ፊት የተሳለ ነው፡፡ የስምሽንም አጻራር ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ለምስጋናሽም እሰይ ይላሉ፡፡

፱. የሙዚቃ ድምጽ የዘፋኙን ልቡና እንዲያነቃቃው፡፡ ያዝማሪንም ልቡና የመሰንቆ ጩኸት እንዲያነሣሣው የስምሽ መጠራት እንዲሁ ልቡናዬን ያነቃቃዋል፡፡

፲. ፍቅርሽ በልቡናየ አደረ እንደ ውሀ ባንጀቴ እንደ ቅቤ ባጥንቴ ገባ የውዳሴሽም ማኅሌት ጌጽ ሽልማት ሆነኝ፡፡ ለክብር ለማብራት ጌጽ ሆነኝ፡፡

፲፩. በወርቅ ላይ እንደተለበጠ ዕንቁ በሐር ፈትልም እንደ ተደረደረ ፈርጽ በነገሥታት ራስ ላይም እንደሚያንጸባርቅ ዘውድ፡፡ እንደ ሙሽራም ሽልማት፡፡ እንደ ሙሽራይቱም ጌጽ፡፡

፲፪. ድንግል እናት ሆይ ያለርኩሰት ሙሽራ አደፍ ጉድፍ የሌለባት የሠርግ ቤት በንጽሕና መፅነስሽ ከፍጥረት ሁሉ ልዩ ነው፡፡ መውለድሽም ያለ ርኩሰት ነው፡፡ ሰውነትሽ በማይለወጥ ድንጋሌ ማኅተም ታተሞ ሳለ ነው፡፡

፲፫. የነፋሳት ኃይል ሊጥላት የወንዝ ፈሳሾችም ሊገፏት የማይችሏት ለዘላለሙ ፀንታ የምትኖር አዳራሽ ሆይ ከመገፋት ከመውደቅ አድኝኝ፡፡ የሁከት ዘመን አውሎ ነፋሱን አስነስቶብኛልና፡፡

፲፬. አምሮ ከተሠራ ደርከኖ ከሚባል ግምጃ ጋራ በወርቅ ፈትል የተደረደረች የተከፈፈች ያክንትም ከሚባል ዕንቁ ከፒሶስ ልብስ፡፡ ጰደሬም ከሚባል እፅፍ ድርብ የተሠራች የታላቁ ሊቀ ካህናት የአሮን ልብስ (ዘፀአ ፣ ፳፱ ፣ ፩)

፲፭. በውስጧም የዘይት ዕንጨት የተባሉ የዓሥራ ሁለቱም ነገደ እስራኤል ምሳሌ ዓሥራ ሁለቱ ዕንቁ የተደረደሩባት ያሥራ ሁለቱም አዕናቁ የውነት ትርጓሜአቸው ባስራ ሁለቱ ሐዋርያት የመለኮት ደቀ መዛሙርት ይተረጎማል፡፡

፲፮. ደግሞ በወስጧ እንደ ሮማን ፍሬ ያለ የወርቅ ሻኩራ ያለባት ጸጸዴጤን ልብስ ሻኩራዎቿም የሙሽራይቱ ጌጽ ፈርጽ የተባሉ ቅዱሳን ሰማዕታት ያለ መጥፋት የሚበሩ ፋናዎቿ ናቸው፡፡ (ዘፀአ ፳፱ ፣ ፳)

## <u>ምዕራፍ ፲፪</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ የንጽሕና መጎናጸፊያ እንድጎናጸፍ የሃይማኖት መጨከንን እንድለብስ፡፡ የመመረጽ ድርብ በፍታን እንድከደን፡፡ የሕይወት የመድኃኒት አክሊል እንድቀዳጅ አድርጊኝ፡፡

፪. የልጅሽን ደግሞ የመስቀሉን በትር በመያዝ በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ የተፈራሁ ልሁን፡፡ የሚቃረነውንም ጠላት በልጅሽ በወዳጅሽ በችንዳሮቹ ፍለፃ ልንደፈው፡፡ የመለኮትንም ሰይፍ የታጠቅሁ ልሁን፡፡

፫. የጨለማው መኳንንት መላእክተ ጽልመት እኔን ለመቃወም ለመከራከር እንዳይችሉ የጽድቅ ጋሻን ከግራ ከቀኝ የተጋረድሁ ልሁን፡፡

፬. የንጹሓን ደናግል መመኪያቸው ድንግል ሆይ የኃያላን ሰማዕት እናት ሙሽራ ከመሃይምናን ሁሉ ተድላ ደስታ ንዕድ ክብርት የተዋረዱትን ከፍ ከፍ የምታደርጋቸው፡፡

፭. ብፅዕት የተመረፁት የተድላ ደስታቸው፡፡ ማረፊያ የመሬታውያን ፍጥረታትን ከሰማያውያን መላእክት ጋራ አንድ የምታደርጋቸው ቡርክት በቅዱሳን ሁሉ ዘንድ የተመረጸች ናት በተደነቁት ሁሉ ማኅበር ሹማምንት ዘንድ የተመሰገነች ናት፡፡

፮. የትጉሃን መላእክት ማኅበር ሁላችሁ ወደኔ ኑ ስማችሁ የተጠራ መላዕክተ ገጽ የከበራችሁ የምስጋና መላእክት የተመረጻችሁ የቅዳሴ መላእክት ወደኔ ኑ፡፡

፯. የኃይል መላእክት ጽኑዓን የተልእኮ መላእክት አዛዦች፡፡ የረዳትነት መላእክት አቻናፊዎች የማዳን መላእክት መንፈሳውያን ረቂቃን የምሕረት መላእክት ባላደራዎች ወደኔ ኑ፡፡

፰. የእሳት መላእክት የሚያስፈሩ ግሩማን የነጎድጓድ መላእክት መደንግፃን፡፡ የፀዳል መላእክት ብሩሃን የደመናት መላእክት ረዋድያን፡፡ የነፋሳት መላእክት ኃያላን ወደኔ ኑ፡፡

፱. በፀሐይና በጨረቃ በከዋክብት ላይ የተሾማችሁ መላእክት ባሕሩን የወንዙን ውሀ ሁሉ ምንጩን ለመጠበቅ የተሾማችሁ መላእክት የዕንጨቱን ፍሬ የምድረ በዳውንም ዕንጨት አትክልት አዝርዕትን ለመጠበቅ የተሾማችሁ መላእክት ወደኔ ኑ፡፡

፲. የሚበረውን ሁሉ ዖፍ በውሀ ውስጥና በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውን ሁሉ ለመጠበቅ የተሾማችሁ መላእክት የቌላ የላብ መላእክት፡፡ የበርድና የውርጭ መላእክት፡፡ የበረድና የጉም መላእክት ወደኔ ኑ፡፡

፲፩. የዐውሎ ነፋስና ያመዳይ መላእክት መናብርት ሥልጣናት አጋዕዝት ኃያላት መኳንንት ሊቃናት ባናዋዋር የከበራችሁ አርባብ ወደኔ ኑ፡፡

፲፪. ሰይፍ ጃግሬዎች የሚካኤል ሠራዊት የጌታን ጠላት የምትጋደሉ የገብርኤል ሠራዊት በኃይል የታጠቃችሁ የእሳቱንም ሰይፍ አጽንታችሁ የያዛችሁ ወደኔ ኑ፡፡

፲፫. የእሳት አክሊል ራስ ወርቅ የደፋችሁ የማቸነፍ ጋሻ የያዛችሁ የሩፋኤል ሠራዊት ጋሻ ጃግሬዎች የዑራኤል ሠራዊት የብርሃን መላእክት ልቡና በሚያሽብር በሚያሸሽ ነጋሪት ድምጽ ምስጋና የምታሰሙ ወደኔ ኑ፡፡

፲፬. የሰዳክኤል ሠራዊት የመብረቅ ልብስ የለበሳቸሁ የእሳት ጦር የያዛቸሁ ለጦርነት የተዘጋጃችሁ ሠራዊት የማያቋርጽ ምስጋናን የተመላችሁ የአናንኤል ሠራዊት በየጊዜው በየ ሰዓቱ የቅዱሳንን ጸሎት ለማሳረግ ወደኔ ኑ፡፡

፲፭. ዓይንን የተመሉ ኪሩቤል ለያንዳንዱ ዐራት ገጽ አለው ለያንዳንዱም ክንፉ ስድስት ነው ሌሎች ደግሞ ስምንት ክንፍ ያላቸው ናቸው፡፡ ሠረገላቸውና ክንፋቸውም ዓይን የተመላ ነው፡፡ (ሕዝ ፩ ፣ ፮ ፣ ፲፰)

፲፮. ሱራፌልም ቅዳሴን የተመሉ ናቸው፡፡ ክንፋቸውም ስድስት ነው፡፡ ከርሳቸውም ደግሞ የከበሩ

የተመረጹ ኻያ ዐራት አለቆች አሉ፡፡ ለመለኮት ገናንነት ለጌትነቱም እጅ መንሻ ሊሆን የቅዱሳንን ጸሎት የሚያሳርጉ ናቸው፡፡

፲፯. ከኪሩቤል ባናዋዋር የከበሩ የልዑል እግዚአብሔር ሠረገሎች ወደ ሠራዊት ጌታም የቀረቡ አሉ እርሳቸውም ዐራቱ እንስሶች ናቸው ላንዱ ፊቱ የሰው የሁለተኛው የአንበሳ የሦስተኛው የላም ዐራተኛውም የንስር ነው፡፡ ሕዝቅኤል ነቢዩ እንደተናገረው፡፡ (ሕዝ ፩ ፣ ፲ ፣ ፲፩)

፲፰. ከራሳቸው እስከ ወገባቸው ዐራት ናቸው ከወገባቸው እስከ እግራቸው አንድ ናቸው፡፡ አንዲት ሰዓት ስንኳን ምስጋናውን አያቋርጡም፡፡

፲፱. እንግዲህ የመላእክት ማኅበር ሁላችሁ ወደኔ ትመጡ ዘንድ እናገራለሁ፡፡ አምላክን በወለደች በዕብራስጥ ማሪሃም በተባለች በተመረጸች በተደነቀች ድንግል ማርያም በድንግልናዋ ምስጋና ጊዜ ከእናንተ ጋር አንድ ሁኜ እንዳመሰግን ነው፡፡

፳. ነገር ግን እናንተን ለመጥራት የምደፋፈር በኔ ደግነት አይደለም በጌታችሁ እናት በተመረፀች ድንግል የስሟ መጠራተ ነው እንጂ፡፡

፳፩. የኔን ወራዳነት አታስቡ፡፡ የንግሥታችሁን ልዕልና አስቡ እንጂ የኔን ድኅነት አታስቡ፡፡ የእመቤታችሁን ክብሯን ገናንነቷን አስቡ እንጂ የኔን ኃጢአት አታስቡ፡፡ የአምላካቸሁን እናት ንጽሕናዋን አስቡ እንጂ፡፡

፳፪. የሰማይ መላእክት ትጉሃን ሆይ ኃጥኡ እኔ በደለኛውም፡፡ የመሃይምናን የጸሎታቸው ሙሳይ የምትሆን በዕብራይስጥ ማሪሃም በተባለች በተመረፀች ድንግል ማርያም በከበረ ስሟ በፀለይሁ ጊዜ እናንተም ደግሞ ከኔ ጋር ጸልዩ ልቡናዬ ለፈቀደው ነገር ለግዳጄ ተመካከታቸሁ ትጸልዩልኝ ዘንድ እማለዳቸኋለሁ፡፡ የክብራችሁንም ገናንነት አደንቃለሁ፡፡

፳፫. ካላንተ አንዱም አንዱ ስለ ኃጢአቴ ቸል በማለት ከልመናዬ ፊቱን የሚመልስ አይሁን፡፡ በንጹሕ ልብ በሰፊው አሳብ ለኃጢአቴ ሥርየት ለምኑልኝ እንጂ፡፡

፳፬. በገሃነም ተሠውሮም ቢሆን በኔ የተነሣ ተቃራኒ ጠላት ቢኖር የእሳቱን ሰይፋችሁን ምዘዙ የእሳቱን ጦራችሁን ወርውሩ፡፡ የመብረቁን ቀስታችሁን አሸቡ የነጎድጓዱንም ፍላጻቸሁን ሳቡ ሊቃወመኝ የወደደውን ንደፉት፡፡

፳፭. በሚበርቀው የእሳት ፈረስ ክበቡት ምድርን በሚያነዋውፀው የመብረቅ ሠረገላ ተከተሉት፡፡ ከምታገኘውም ከቁጣችሁ መፈራት የተነሣ የሰማይ ስፋት ይጥበበው፡፡ ከምትከፋውም የጻችሁ መክበድ የተነሣ የምድር ስፋት ይጭነቀው፡፡

፳፮. ከፊታቸሁም ግርማ የተነሣ ተቃራኒ ጸላት ይሸሽ ትዕቢተኛ ኩሩ ይውደቅ፡፡ ልቡናውንም ከፍ ከፍ የሚያደርግ በርሱም መዓርግና ክብር የሚታበይ ይሰበር ይሰባበር፡፡

፳፯. የአባብ መርዝ አልጫ ይሁን ወጥመዱም ይቀደድ፡፡ ሰውንም ከሰው የሚያጣላ ዲዳ ይሁን፡፡ የዓመፀኛም አፍ ይለሆም ሟርተኛ ጠንቋይ ይነቀል፡፡ አስማተኛ ሥራየኛ ይጥፋ፡፡ በሰውም የሚታመን ይረገም እንደ ተጻፈ፡፡

፳፰. በእስራኤል ቅዱስ ግን የሚመካ በያዕቆብም አምላክ የሚያምን በንጽሕት እናቱም ጸሎት የሚጠጋ በደህና ይደር በደህናም ይዋል እስከ ዘለዓለሙ አሜን፡፡

# አርጋኖን
# ዘሐሙስ
## ምዕራፍ ፩

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ መላእክትን ለፈጠረ በኪሩቤል ላይ ለሚቀመጥ እናቱ ለምኝልኝ፡፡

፪. ከሚያሰጥም ባሕር ማዕበልም ሞገድ፡፡ ከከበደ ዓለም ኅልፈት ጥፋት በጸሎትሽ አድኝኝ፡፡

፫. አምላክን የወለድሽ ድንግል ሆይ በላዩ ያደረውን የኃጢአቴን ሸታ አርቂው፡፡ በጸሎትሽም መዓዛ እንደ ኪሩቤል ዕጣን ሽታ እንደ ሱራፌልም ጽንሐሕ ጸሎቴ ደግሞ ያማረ የተወደደ እግዚአብሔርም የተቀበለው ይሁን፡፡

፬. ምስጋናን የተመላሽ ድንግል ሆይ እንዳልወድቅ ከመሰናክል አድኝኝ ደግፊኝ፡፡ ጥልቅቅ የሚያደርግ አእምሮ የሚያሰጥ ወይን መጠጥን እንደጠጣ ልቤ ዕውቀት አጥቷልና፡፡

፭. ሕጉን ትእዛዙን ለመጠበቅ እያሰብሁ ሌሊቱን ሁሉ አደክማለሁ፡፡ ጥቂትም ቆይቶ አናዋዋር የሚለውጥ ሐሳብ ይመጣብኛል፡፡ የዚህን ዓለም ማሠሪያ ከኔ ቁረጭው ሰውነቴ በርሱ ገመድ ተይዟልና ለርሱም ከገዛት ነጻ አድርጊኝ፡፡

፮. ጸጋ ክብርን የተመላሽ ድንግል ሆይ ከመግፋት ከመገፋት አድኝኝ፡፡ ቅድስና የተመላሽ ድንግል ሆይ ከመበደል ሌላውንም ከመበደል አድኝኝ፡፡ ከደም አፍሳሽ አድኝኝ፡፡ እኔም ደግሞ የሌላውን ደም ከማፍሰስ ሠውሪኝ፡፡

፯. የተድላ መፍሰሻ ድንግል ሆይ ከሸንገላ አድኝኝ፡፡ ከሸንጋይም ደግሞ ሠውሪኝ፡፡ የምስጋና መፍሰሻ ድንግል ሆይ ከሸሙጥ ከስድብ ከሚያስሽሚጥጥና ከሚሰድብ ደግሞ ሠውሪኝ፡፡

፰. የባለ ጸግነትና የክብር መፍሰሻ ድንግል ሆይ ሰውን ከሰው ከማጣላት አድኝኝ፡፡ ሰውን ከሰው ከሚያጣላ ሐሰተኛ ደግሞ ሰውሪኝ የሕይወት የመድኃኒት ምንጭ ሆይ ከቂምና ከቅናት አድኝኝ ከቂመኛ ከቀናተኛ ደግሞ አድኝኝ፡፡

፱. የፈውስ መቅጃ የበረከት አዘቅት ድንግል ሆይ ከፀብ ከክርክር አድኝኝ፡፡ ከሚጣላና ከሚከራከር አድኝኝ፡፡ እሳት የሚለብሱ ኪሩቤልና ሱራፌል በመብረቅ ክንፍ የሚጋርዱሽ የንጉሠ ነገሥት ማደሪያ የምትሆን የብርሃን ድንኳን ሆይ፡፡ በሕይወት በመድኃኒት ጋሻ ጋርጅኝ ከአጋንንት ፍላፃ እንድድን፡፡

፲. ይቅር ባይ በሆነ ልጅሽም መጋረጃ ሸፍኝኝ፡፡ ሰወን ከሰው ማጣላትን ከተመላ ከመላስ ነገር እንድሠወር አጥሯ ቅጥሯ የማይፈርስ መሠረቷ የማይናወጽ ለዘለዓለም ጸንታ የምትኖር አዳራሽ ሆይ፡፡ የመሃይምናን መኖሪያ ወደሚሆን ዕድል ፈንታዬን ጽዋ ተርታዬን ገነት መንግሥተ ሰማያትን አድርጊልኝ፡፡

፲፩. ድንግልና አበባን በቅድስናም የበረከት ፍሬን ያፈራች የወይን ቦታ ሆይ፡፡ ንስሐ ፍሬን እንዳፈራ ንጹሑንም መሥዋዕት እጅ መንሻ አድርጌ ለልጅሽ እንዳቀርብ አድርጊልኝ ለበጎ ሥራም የዋህ ልቡና ትሑት ሰብና ስጭኝ፡፡

፲፪. ከምድር እስከ ሰማይ የትምደርስ የወርቅ መሰላል ሆይ የመለኮት አንድነት ሦስትነት ወዳለበት፡፡ የምሕረት ምንጭ ወደሚቀዳበት ጸሎቴን አሳርጊልኝ፡፡ ጽዋ ተርታዬን ዕድል ፈንታዬንም ይቅር መባል

አድርጊልኝ፡፡ ነገር ግን በፍርድ አይደለም ባንቺ በረከት በማቸነፍ ነው እንጂ፡፡

፲፫. የልዑል እግዚአብሔር የበኩር ልጁ የጌትነቱ መሣሪያ የብርሃን መጋረጃ ድንግል ሆይ ከክፉ ዕለት ከጥፋት ሰዓት በቀን ከሚወረወር ጦር በጨለማም ሌሊት ከሚመላለስ ነገር ሠውሪኝ፡፡

፲፬. ከዓውሎ ነፋሰ የተነሣ ምዕመናንን የምታሻግር የመድኃኒት ድልድይ የድኅነት መርከብ ሆይ ከኃጢአት ማዕበል ሞገድ አሻግሪኝ መርከብ ሰውነቴን እንዳያነዋውፀው፡፡

፲፭. የንጹሐን የደናግል መመኪያቸው ንጽሕት ድንግል ሆይ ከኃጢአት ርኩሰት ከማመንዘርም መተዳደፍ ንጹሕ አድርጊኝ የቅዱሳን ሁሉ መመኪያቸው ቅድስት ድንግል ሆይ በልጅሽ ደም ንጹሕ አድርጊኝ፡፡ በበህር ልጅኝ በጎኑ ፈሳሽ የጸዳሁ አድርጊኝ፡፡

፲፮. ደስ ያላቸው የምእመናን ሁሉ መመከያቸው ፍሥሕት ድንግል ሆይ ለዘለዓለም በማያልቀው በልጅሽ ደስታ ደስ አሰኝኝ ያለ ርኩሰት የሠርግ ቤት የመንፈስ ቅዱስ ሙሽራ የመለኮት ዙፋን ድንግል ሆይ፡፡ ልቡናዬን ከምታረክሰው ነፍሴንም ከምትጠብሳት ከሥጋ ፈቃድ ንጹሕ አድርጊኝ፡፡

፲፯. እንደ ባሕር ከጠለቀው ርኩስ ሣቅ ጨዋታ ከክፉውም ከሴሰኝነት ማዕበል ሞገድ የምታሻግር የወርቅ መሰላል ድንግል ሆይ ከዕዳ በደል ረግረግ አሻግሪኝ፡፡

፲፰. ኖኅ ከማየ አይኅ ረግረግ የዳነባት መርከብ ድንግል ሆይ የሰው ሁሉ ልጆች ከሚመጣው መቅሠፍት ፈግረግ አውጭኝ በኃጢአት እንደኔ የረከሰ ሰው የለምና ዘፍጥረት ፯ ፣ ፳፫፡፡

፲፱. በጎ ሥራዬም ሁሉ እንደ ግዳጅ ጨርቅ ነው፡፡ ርኩሰቴም ደግሞ ከደመ ሕርስ ሁሉ አጽፍ ድርብ እንደሚሆን የወለደች ሴት ርኩሰት ሁና እንደምትሰነብት እንደ ሰባቱ ቀር ርኩሰት ያለ ነው፡፡

፳. ለመንጻቴ ማንን እጠራለሁ፡፡ ቁስሌንስ ለመፈወስ ወደ ማን እጮሃለሁ የኃጥአን ዕዳ በደላቸው ንጹሕ መሆና የቁስለኞችም የቁስላቸው መፈወሻ ከምትሆን ካንቺ ሌላ፡፡

፳፩. ከልጅሽ ሌላ ባለመድኃኒት አልሻም፡፡ ከጸሎትሽም ረዳትነት በቀር ደግሞ ኃጢአቴን የሚያስተሠረይልኝ አልፈልግም፡፡ ንጽሕት ሆይ ከርኩሰቴም ከዕዳም በደሌም ሁሉ ንጹሕ አድርጊኝ፡፡ ከሥጋና ከነፍስ ቁስሌም ፈውሽኝ፡፡

፳፪. ለደዌ መድኃኒት ይሹለታል ለቁስልም አቃቁር መልካሙን ቅመም ይፈልጉለታል የኃጢአት ቁስል ግን ያለ ልጅሽ ፈቃድ አይጠግም፡፡

## ምዕራፍ ፪

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ደንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ፡፡ የደናግል መመኪያ የቅዱሳንም ሁሉ የመመረጣቸው አክሊል ኃጢአቴን እንደ ነጭ ሐር ግምጃ ንጹሕ አድርጊው ዕዳ በደሌንም እንደ በረድ ነጭ አድርጊው፡፡

፪. ጸሎቴም ወደ ልጅሽ ፊት ትግባ፡፡ በልጅሽም በወዳጅሽም ጆሮ የተሰማች እርሲም የተቀበላት ትሆን ዘንድ ባንቺ ፊት እማለላለሁ፡፡ ከልጅሽም ዘንድ ለኃጢአቴ ሥርየት እሻለሁ፡፡

፫. በየሰዓቱም በየጊዜውም ለማኅፀንሽ ፍሬ ይቅርታ መምጣት ደጅ እጠናለሁ፡፡ ለጅሽም እንደ በደሌ ቢበቀለኝ እንደ ሥራዬም ቢከፍለኝ አንዲት ሰዓት ለመቆም የተገባሁ ባልሆንኩም ነበር፡፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፬. ነገር ግን የጸሎትሽ ረዳትነት የልጅሽም ይቅርታው በየዕለቱ በየዘመኑ ሁሉ ይከራከርልኛል፡፡ ስለዚህ አልፈራም ምንም ምድር ብትናወጽ ተራሮችም በምድር ላይ ቢናወፁ፡፡

፭. ለጦርነትም በመሣሪያ ለተሰለፈ ከአርበኛ ሰው ግርማ የተነሣ አልደነግጽም፡፡ በኃይል ከሚጮህ አንበሳም ግርማ ደግሞ አልፈራም ልዩ በሆነ ችሎታ አናብስትን ባስገዛ በዳንኤል አምላክ አምኛለሁና፡፡ ዳን ፮ ፣ ፳፡፡

፮. በሚነደውም የእሳት ነበልባል ፊት ከግርማው የተነሣ አልፈራም፡፡ እሳቱን እንደ ጠል አቀዘቀዘው በአናንያ በአዛርያ በሚሳኤል አምላክ አምኛለሁና፡፡ (ዳንኤ ፫ ፣ ፳፮)

፯. በጸሎትሽም ተጠግቻለሁና በማይፈርስ በአድማስ ቁጥር መካከል እንደሚኖሩ ያገር ሰዎች አንቺ ስለኔ ይቅር የምታሰኚ ነሽ፡፡ ለኔ ቁስልና ጉስቁልና የይቅርታ መገኛ ነሽ፡፡

፰. ስምሽን ስጠራ ልቡናውን እንዳያጸናብኝ አውቄ አምኜ ወደ ልጅሽ እጄን እዘረጋለሁ፡፡ ስምሽን በመጥራት ስለምነው ምሕረቱን አያዘገይብኝም ይቅርታውንም ዐውቀዋለሁ፡፡ ከመዓት የራቀ እውነተማ የባሕርይ አምላክ ነውና፡፡

## ምዕራፍ ፫

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ፡፡ የበረከት ጽዋ የሕይወት መቅጃ ከማይደርቀው ከይቅርታው ምንጭ የፈሰሰው የሕይወት ውሀን ቅጅልኝ፡፡

፪. የኃጢአቴ ብዛት ያለ ቁጥር የዕዳ በደሌም ልክ ያለ መጠን ሆነ ከርሱ ደግሞ የልጅሽ ምሕረት ይበዛል፡፡ እንደተጻፈ ለትእዛዝህ ይቅርታ ልክ መጠን የለውም ተብሎ፡፡

፫. ጸጋ ክብርን የተመላሽ ቅድስት ድንግል ሆይ በጸሎትሽ ረዳትነት አምኜ ሳለሁ የማቸነፍ ጥሩር እንድለብስ የመለኮትንም ሰይፍ እንድታጠቅ አውቃለሁ፡፡

፬. እርስ በርሳቸውም ይረዳዳሉ፡፡ የኔ ሃይማኖት ያንቺ ጸሎት የልዑል እግዚአብሔር ማዳን ዳግመኛም የኔ መታመን ያንቺ ልመና የልዑል እግዚአብሔር ይቅርታ እርስ በርሳቸው ይረዳዳሉ፡፡ እኔ ባንቺ አምኜ ሳለሁ ግዳጄን የማግኘቴ ተስፋ አንቺ ስለኔ ተግተሽ መለመንሽ እግዚአብሔርም ቸል ሳይልና ሳይነቅፍ ግዳጄን መስጠቱ እርስ በርሳቸው ይረዳዳሉ፡፡

፭. እኔ በስምሽ እለምናለሁ አንቺም ስለኔ ትማለጃለሽ፡፡ ልጅሽም ስላንቺ የልመናዬን ዋጋ ይሰጠኛል እኔ ለፍቅርሽ ካልተጋሁ አንቺ እኔን ለማዳን አትተጊም፡፡ ልጅሽም እኔን ይቅር ለማለት አይተጋም፡፡

፮. እኔ በስምሽ ግዳጄን ሁሉ ማግኘት እመኛለሁ፡፡ አንቺ ለኔ አማላጅ ነሽ፡፡ ልጅሽም ግዳጄን የሚሰጠኝ ነው፡፡ እኔ የተጸማሁ ነኝ፡፡ አንቺ የወርቅ መጥለቂያ ነሽ፡፡ ልጅሽም የሕይወት ውሀ አዘቅት ነው፡፡

፯. የመለኮትን ዕንቁ ለመግዛት እኔ ነጋዴ ነኝ፡፡ አንቺ የሕይወት መርከብ ነሽ፡፡ ልጅሽም የበጎ ነገር ሁሉ ድልብ በውስጡ ያለበት የትርፍ ሥፍራ ነው፡፡

፰. እኔ ገደሉን ለማለፍ ወደ ብርሃን ሥፍራ ለመድረስ የቸኮልሁ ነኝ፡፡ አንቺ የመድኃኒት ድልድይ ነሽ፡፡ ልጅሽም ለተገፉት መጸጊያ የተድላ ደስታ ሥፍራ ነው፡፡

፱. እኔ የምንፈስ ቅዱስን ሃብት የምፈልግ ድሀ ነኝ፡፡ አንቺ የክብር ሁሉ መከማቻ ነሽ፡፡ ልጅሽም

ለባለሟልነትና ለክብር ለማሞገስ የሸልማት ጌጽ ነው፡፡

፲. እኔ እለምናለሁ አንቺ ጸሎቴን ታሳርጊያለሽ ልጅሽም ኃጢአቴን ያስተሠርያል፡፡ የልቤን ግዳጅ ይሰጠኛል፡፡ እኔ ቁስለኛ ነኝ አንቺ የመድኃኒት ሙዳይ ነሽ፡፡ ልጅሽም ባለ መድኃኒት ነው፡፡

፲፩. እኔ ቁስለ ኃጢአቴ የሸተተ፡፡ የቅዱሳንንም መዓዛ ሽቱ የሻ ነኝ፡፡ አንቺ ያማረ የተወደደ ሽቱ ብልቃጥ ነሽ፡፡ ልጅሽም ከሽቱ ሁሉ ይልቅ ያማረ የተወደደ የመለኮት ቅቤ ነው፡፡

፲፪. እኔ የታረዝሁ የብርሃን ልብስ የምሻ ነኝ፡፡ አንቺ የሸማኔ ዕቃ ነሽ ልጅሽም የማያልቅ የማያረጅ የሃይማኖት ልብስ ነው፡፡

፲፫. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ፡፡ ሁልጊዜ በዓይነ ልቡናዬ አይሻለሁ በሃሳቤም በየሥፍራው ሁሉ አገኝሻለሁ በተኛሁ ጊዜ እኔን ለመጠበቅ የነቃሽ ነሽ፡፡ ከመኝታዬም ስነቃ እኔን ለማንሳት የተዘጋጀሽ ነሽ፡፡

፲፬. ስቀመጥም እኔን ለመምከር ትደርሻለሽ፡፡ በቆምሁም ጊዜ በቀኜ ትቆሚያለሽ በተናገርሁም ጊዜ አንደበቴን ለማጣፈጥ ታከናውኛለሽ፡፡ በዝምታዬም ጊዜ ለመጠበቄ ማሞገሻ ነሽ ኃሤትም ባደረግሁ ጊዜ ተድላ ደስታ ነሽ፡፡

፲፭. ባዘንሁም በተቈረቈርሁ ጊዜ የኃዘኔ መጽናኛ ነሽ፡፡ ባለቀስሁም ጊዜ የልቅሶዬ መተዊያ ነሽ፡፡ በዘፈንሁ ጊዜ ለእጄ እንደ መሰንቆ ለጣቶቼም እንደ በገና ነሽ፡፡

፲፮. በተራብሁም ጊዜ ለሆዴ ትመግቢኛለሽ በተጸማሁም ጊዜ እኔን ለማርካት የሕይወት ውሀን የተመላሽ ነሽ፡፡ የተፍገምገምሁም ጊዜ እኔን ለመደገፍ እጅሽን ትዘረጊያለሽ፡፡ በወደቅሁም ጊዜ እጅሽን ዘርግተሽ ታነሺኛለሽ፡፡

፲፯. ተባሕትዎም በያዝሁ ጊዜ እኔን ለመጎብኘት አታቋርጭም፡፡ በማኅበር መሐከል ወደኔ ትደርሻለሽ በደከምሁም ጊዜ ድካሜን ታበረቻለሽ፡፡ በታመምሁም ጊዜ ሥጋዬን ከሞት ታድኛለሽ፡፡ በተቸገርሁም ጊዜ ከችግሬ ታድኝኛለሽ፡፡

፲፰. በተጨነቅሁም ጊዜ ጭንቄን ታርቂያለሽ፡፡ በቆሰልሁም ጊዜ ቁስሌን ታጠጊልኛለሽ፡፡ በርኩሰቴም ጊዜ ንጹሕ ታደርጊኛለሽ፡፡ በበደልሁም ጊዜ ኃጢአቴን ታቃልያለሽ፡፡ በደኸየሁም ጊዜ ለድኅነቴ ባለጸግነት ሀብት ነሽ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፬</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ አንቺን የማላስብበት ጊዜ የለም፡፡ የማላይሽ ጊዜ የለም፡፡ በዓይነ ልቡናዬ የማልመለከትሽ ጊዜ የለም፡፡

፪. ፍቅርሽም በልቤ እንደተጻፈ እንዲሁ ደግሞ ፍቅሬ በልብሽ ይጻፍ ባንቺ ዘንድ እየበዛ እየተባዛ እጽፍ ድርብ ይሁን፡፡

፫. የመለኮት ማደሪያ ድንግል ሆይ የመንፈስ ቅዱስ ታቦት የተመሰገነውን የድንግልናሽን ነገር ምን እናገራለሁ፡፡ ምን አወራለሁ የአርያም እኅት የምትሆኚ ሁለተኛ ሰማይ ድንግል ሆይ ስለቅድስናኝ ኃይል ምን እላለሁ ምን እናገራለሁ፡፡

፬. ክብርሽን ገናንነትሽን ከማሰብ የተነሣ ልቡናዬ ልምሾ ሁኗልና፡፡ የድንግልናሽንም ምስጋና ከመናገር

የተነሣ አንደበቴ ደከመ ፍቅርሽን ክብርሽን ለመናገር እሽ በጎ ያሰኛል፡፡ አንደበቴ ግን ይደክማል፡፡

፭. ውዳሴሽንም ለመናገር ነፍሴ በጭንቅ ትተጋለች ሥጋዬ ግን ይደክማል፡፡ የሥጋዬ ባሕርይ ደካማ ነውና ግብሩም ስንፍና ነው፡፡

፮. ለሚጋደሉ ሁሉ አክሊላቸው ድንግል ሆይ የመሃይምናን የሃይማኖታቸው ቀፀላ የቅዱሳን ሽልማት የነቢያት ልጃቸው የሐዋርያት እናታቸው የሰማዕታት መመኪያቸው፡፡ የደናግል የመነኮሳት ጌፃቸው፡፡

፯. የዓለም ሁሉ ክብር ድንግል ሆይ ለክብርሽ ለገናንነትሽ እንደ ምን ያለ ምስጋና እንዴትስ ያለ መገዛት ይገባል፡፡ እንደ ምን ያለ ውዳሴ እንዴትስ ያለ ልዕልና ይገባል፡፡

፰. የሁለተኛው አዳም ማደሪያ ነባቢት ገነት ድንግል ሆይ ከገብርኤል ጋራ እንደ ገብርኤል አመሰግንሻለሁ፡፡ እንዲህ ስል ጸጋ ክብርን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል፡፡

፱. ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና፡፡ ባዳራሽ ድንኳንም የምትኖሪ የሕግ ታቦት ሆይ፡፡ ደስ ይበልሽ፡፡ የሕይወት ውሀ መቅጃ የክብር አዘቅት ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲. በንጉሡ በቀኝ የምትቀመጥ ንግሥት ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡ በወርቅ ልብስ የተሸለመች ያጌጸች ሙሽራ ሆይ ደስ ይበልሽ ያለ ዘር ያለ ሩካቤ የወለድሽ እናት ሆይ ደስታ ይገባሻል፡፡ የታላቁ ንጉሥ ማደሪያ አዳራሽ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲፩. ከዓውሎ ነፋስ የተነሣ የማትታወክ በሥላሴ ቀዛፊነት ምእመናንን የምታሻግር መርከብ ሆይ ደስታ ይገባሻል፡፡ የበረከት ፍሬ የምታፈራ ከርሷም የምስጋና ፍሬ የተገኘባት የወይን ሐረግ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲፪. የመለኮት የዕንቁ ባሕርይ ሣፅን የሃይማኖት ሙዳይ ሽቱ ሆይ ደስታ ይገባሻል፡፡ የሊቀ ካህናት ማደሪያ የብርሃን ድንኳን ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡ ከይሁዳ ቤት የተገኘች የመንግሥት ሽቱ ብልቃጥ ከሌዊ ቤት የበቀለች የክህነት ቀንድ በእስራኤልም የመድኃኒት ቀንድ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲፫. በአምላካዊ ምሥጢር ደም የተረጨች በወርቅ ፈትል የተዘረጋች ንጽሕት ሰፊ መጋረጃ ሆይ ደስታ ይገባሻል፡፡ ጎኖቿ በወርቅ ቁጽልጽል ክንፎቿም በብር የተሠሩ ርግብ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲፬. የቅዱሳን ምግብ የሚሆን የቁርባኑ እንጀራ የተጨመረባት የወርቅ መሶብ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡ የምሥጢሩን ወይን የምትሸከም የወርቅ ጽዋ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲፭. የልዑል እግዚአብሔር ንዋየ ቅድሳት የተሸከምሽ መሠዊያ ሆይ ደስታ ይገባሻል፡፡ በልዑል እግዚአብሔር ፊት የተወደደውን በጎውን መዓዛ የተሸከምሽ የወርቅ ማዕድ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲፮. የመለኮትን ፍም የተሸከምሽ የወርቅ ማዕጠንት ሆይ ደስታ ይገባሻል፡፡ እውነተኛ ፀሐይን ያስገኘሽ ሰማይ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡ ሁሉን የተሸከምሽ የአሚናዳብ ሠረገላ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲፯. ለእግዚአብሔር ያማረ (የተመረጸ) ያማረ የተወደደ የምሥጢር ሥርዓት የሚሠራበት የወርቅ ጠረጴዛ ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡ የምሕረት ዝናምን የምትሸከም ቀሊል ደመና ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲፰. ነፍስ ለተዋሐደው ፍጥረት ሁሉ ምግብ የሚሆነውን የመሥዋዕት ስንዴ የምታፈራ ንጽሕት እርሻ ሆይ ደስ ይበልሽ የሕይወት ውሀ የምታመነጭ የክብር አዘቅት ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡ የሚያስፈራውን የእሳቱን ነበልባል የተሸከምሽ ዕፀ ጳጦስ ሆይ የደመናት ዝናም ያላጠጧት የኢሳይያስ የተጸማች ምድር

www.ethiopianorthodox.org

ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡ ነውር ነቀፋ የሌለብሽ ንጽሕት ጥኛ ሆይ ወተትና ማር የምታፈስ የእግዚአብሔር ሀገር የምትሆን ሁለተኛ ኢየሩሳሌም ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡

፲፱. እስራኤል በተባለ ያዕቆብ አፍ የሰማይ ደጅ የተባለች ቤቴል የነቢያት ሀገር ቤተልሔም ሆይ የልዑል አምላክ የሥጋዊው ሰፍራ መስገጃ መጸለያ ኃጢአት ማስተሰረያ ሆይ ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል፡፡

## ምዕራፍ ፯

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ ያላንቺ እንዴት ያለ ፈውስ እንደምን ያለ ይቅርታ ተደረገ፡፡ አንቺ ሳትወለጅስ እንደምን ያለ ረዳትነት ተደረገ፡፡

፪. አቤል በቃየን እጅ በግፍ ሞተ ደሙ ለማንም ለማን አልጠቀመም የሆድሽ ፍሬ ግን ደሙ አዳምንና ልጆቹን አዳናቸው፡፡ (ዘፍጥ ፬ ፣ ፰)

፫. ከአዳም ሰባተኛ የሚሆን ሄኖክ እግዚአብሔርን አገለለው ከሞት በፊት ተሠወረ አልተገኘም እግዚአብሔር ሠውሮታልና ነገር ግን በጽድቁ ለራሱ ዳነ እንጂ የርሱን ደግነት ጽድቁም ለሌሎቹ አልጠቀማቸውም፡፡ (ዘፍጥ ፭ ፣ ፳፬)

፬. የድንግልናሽ ቡቃያ ግን በቸርነቱ ሞትን በሥጋ ቀመሰ ሙታንንም (በሥጋ) በመለኮቱ አዳናቸው፡፡

፭. ኖኅ በእግዚአብሔር ፊት ባለሟልነትን አገኘ ከሚስቱና ከልጆቹም ጋራ ከማየ አይኅ ዳነ ሌሎቹን ግን ከማየ አይኅ አላዳነም፡፡ (ዘፍጥ ፯ ፣ ፳፫)

፮. ልጅሽ ግን በመስቀሉ ሕዝንባ አሕዛብን አዳነ፡፡

፯. አብርሃም ለእግዚአብሔር የታመነ ሁኖ ተገኘ፡፡ የምድርና የሰማይ ኪዳንም ተሠራለት የብዙዎች ሕዝብ አባት ተባለ በርሱም ልጆችና በሌሎቹ አሕዛብ ከሐከል መለዮ ሊሆን የግዝረት ምልክት ተሰጠው እርሱ ለእግዚአብሔር የተመረጸ ሕዝብ ነውና ይህንን ሁሉ ክብር ተቀብሎ ሳለ ስንኳን ሌላውን ራሱን ስንኳን ከሲኦል ለመርዳተ አልተቻለም፡፡ የባህር ልጅሽ ግን በሞቱ በዙን አዳነ፡፡ (ዘፍጥ ፲፭ ፣ ፮ ) (ም ፳፩ ፣ ፬)

፰. ንጹሕ ይስሐቅ የእግዚአብሔር ወዳጅ ተባለ አባቱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበው፡፡ ቤዛውንም ንጹሑን የበግ ጠቦት አወረደለት፡፡ ይስሐቅ በበግ ደም ዳነ እንጂ ሌሎችን አላዳነም፡፡ (ዘፍጥ ፳፪ ፣ ፲ ፣ ፲፫)

፱. ልጅሽ ግን እንደተወደደ በግ ሁኖ በደሙ ፈሳሽነት ዓለሙን ሁሉ አዳነ፡፡

፲. እስራኤል የተባለ ያዕቆብ ለዓለም ሁሉ ጌታ ዓሥራት ተነሣ፡፡ ኅሬ በመባልም ከአሕዛብ መሐከል ተለየ በአምላኩ ስምም ተጠራ፡፡ (ዘፍጥ ፴፪ ፣ ፳፰)

፲፩. ከምድር እስከ ሰማይ የምትደርስ የወርቅ መሰላል እግዚአብሔር ተቀምጦባት የእግዚአብሔር መላእክት ወደዚያች መሰላል ሲወጡ ሲወርዱ አየ፡፡ (ዘፍጥ ፳፰ ፣ ፲፪)

፲፪. ያዕቆብ ስንኳን አያት እንጂ ወደዚያች መሰላል ለመውጣት አልተቻለውም፡፡ አንቺ ግን ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ መውጫ ሆንሽን፡፡ ባንቺም ወደ እግዚአብሔር የቀረብን ሆን በጽርሐ አርያም ለመኖር፡፡

፲፫. ሙሴ ከእስራኤል ልጆች ሁሉ ይልቅ ከፍ ከፍ አለ ከእግዚአብሔር ጋራ ፊት ለፊት ተያየ አፍ ላፍም ተነጋገረ፡፡ በደመናውም ዓምድ መሐከል አለፈ፡፡ ወደ እሳቱም ዓምድ መሐከል ገባ፡፡ በእግዚአብሔርም ፊት ቆመ ብርሃኑንም አየ፡፡ ራሱን ለማዳን ሕዝቡን ከሞት ለማዳን አልተቻለውም፡፡ (ዘፀአ ፲፫ ፣ ፩) ፳፩ ፣ ፳፪) ፳፬ ፣ ፲፰)

፲፬. ስላንቺና ስለ ልጅሽ ግን ሙሴ የተባገረው ረድኤትና መድኃኒታችን ባንቺ ተደረገ፡፡

፲፭. የእስራኤል ወገኖች ከሰማይ የወረደውን እንጀራ በሉ ውህም ከደንጊያ ጠጡ የእግዚአብሔርም ከመና ጋረዳቸው እሳት የተዋሀደውም የብርሃን ዓምድ መራቸው፡፡ (ዘፀአ ፲፫ ፣ ፳፩ ፣ ፳፪ ፣ ፲፮ ፣ ፴፭)

፲፮. እርሳቸውም ደግሞ ራሳቸውን ከሞት አላዳኑም ከርሳቸውም ብዙዎች በምድረ በዳ ወደቁ፡፡ ልጅሽ ግን ብዙዎችን ከሕዝቡ ወደርሱ ማረከ የዘለዓለም ሕይወትንም ከፈለቸው፡፡

፲፯. ታላቁ ሊቀ ካህናት አሮን የእግዚአብሔርም አገልጋይ ለአምላኩ ስጦታ ተሰጠ ለፈጣሪውም ዕድል ፈንታ ሆነ፡፡

፲፰. ከወንድሞቹ ከሌዋውያን ይልድ ክብሩ ልዩ ነው ለደብተራ ኦሪትም ተዘጋሀ በቅድሳት ልብስ ተሸለመ በዕንቁ የተሠራ የወርቅ ልብስ አጌጸ የወርቅ አክሊል ተቀዳጀ፡፡ (ዘፀአ ፳፰ ፣ ፴፬ ፣ ፴፭)

፲፱. በልብሱም ዘርፍ የወርቅ ሻኩራ አለበት፡፡ የእግሩም አረማመድ ከሩቅ ይሰማል፡፡ የሌዊም ልጆች በሽልማታቸው ተሸልመው ሲታዩ በመሐከላቸው ይታያል፡፡ በብሩሃን ከዋክብት መሐከል ያጥቢያ ኮከብ ደምቆ እንዲታይ፡፡ (ዘፀአ ፳፰ ፣ ፴፭)

፳. አስቀድሞም ስለራሱ ይሠዋል በኋላ ግን ስለሕዝቡ ይሠዋል፡፡ ወደ ሕዝቡም በሆር ተራራ ተጨመረ ሊኖር ሞት አላሰለጠነውምና፡፡ (ዘሌዋ ፲፮ ፣ ፮)

፳፩. ልጅሽ ግን በፈቃዱ ራሱን በዕንጨት መስቀል ላይ ሠዋ በደሙ ፈሳሽነትም መሃይምናንን ዋጀ (አዳነ)

፳፪. ካባቶቻችን ዘንድ የነበረች ደብተራ ኦሪት በወርቅ የተለበጠ ታቦትም በውስጡ ያለባት የሕግ ትእዛዝ ጽላትም ተቀመጠባት፡፡ ከጽላቲቱም በላይ ከኪሩብ ሥዕል ጋራ የወርቅ ጉልላት አለ የእግዚአብሔር መኅብኛ ነው፡፡

፳፫. በውስጧም መና ያለባት መሶበ ወርቅ የበቀለችም የክህነት በትር ከኮሬብ ደንጊያ ንጹሕ ውሀ የሚቀዳባት የወርቅ እንስራ የወርቅ ማዕድ በኤላም በኩል በወርቅ ማዕጠንት በፊቷ የእግዚአብሔርም መሠዊያ በማዕድ ጎን፡፡

፳፬. ሰባተ ማብሪያ ሰባት አዕፁቅ ያሏት የወርቅ መቅረዝ ድንኳኒቱም የእግዚአብሔርን ምስጋና ተመላች፡፡ በዓምደ እሳት ብርሃንም ተሸለመች፡፡ በውስጧም የሚኖሩን ከሞት አላዳነቻቸውም የሕግ ታቦትም አልረባትም፡፡

፳፭. መሶበ ወርቅ አልጠቀመችም መናም የሚበሉትን ከሞት አላዳናቸውም የኮሬብ ደንጊያ ውሀም የሚጠጡትን የክህነት በትርም የሚመረጎዟትን ማዕድም በጎውን መዓዛ የሚያቀርቡ፡፡

፳፮. ማዕጠንትም ለካህናቱ መሠዊያይቱ ለሚሠውት መቅረዝም ለሚያበሩባት የደብተራ ኦሪት ነዋየ ቅድሳት አምሳል መርገፍ ነው፡፡ ያንቺም አርአያ ነው፡፡ መድኃኒታችን ግን አንቺና ልጅሽ ናችሁ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፯. የነዌ ልጅ ኢያሱ የእግዚአብሔርን መንፈስ ተመላ ሙሴ እጁን በላዩ ጭኖበታልና የእግዚአብሔር ረድኤት ኃይልም በላዩ አደረ ፀሐይን በገባዖን በኲል አቆመ ጨረቃይቱንም በኤላም ቈላ፡፡ (ዘዳግ ፴፬ ፣ ፱)

፳፰. ስመ ጥር የሆኑትን ነገሥታት አዋረደ ኃይለኞችን አርበኞችን አጠፋ፡፡ የኤናቅንም ልጆች ምድር ለእስራኤል ከፈለ የመንግሥተ ሰማያት ክፍል ግን አልተቻለውም ለራሱም ለሌሎችም ቢሆን፡፡ (ኢያ ፲፪ ፣ ፯)

፳፱. ልጅሽ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ያባቱን መንግሥት ለወገኖቹ ከፈለ፡፡

፴. ሳሙኤል ታላቁ ነቢይ የዔሊ ምትክ ሊቀ ካህናት ለእስራኤል ተነሣ ከምስክሩ ድንኳን የሸቱ ብልቃጥ ነገሥታትን የሚቀባ ሆነ ምድራውያን ነገሥታትን ሊቀባ ሥልጣን ተሰጠው መንግሥተ ሰማያትን ለመቀባት ግን አልተሰጠውም፡፡ (፩ ሳሙ ፲ ፣ ፲፭ ፣ ፩ ፣ ፴)
ልጅሽ ግን መሃይምናንን በመለኮቱ ቅብ ቀባቸው ለመንግሥተ ሰማያትም ዝግጁ አደረጋቸው፡፡

፴፩. ከትንሽነቱ ጀምሮ የአምላኩን ምስጋና የሚዘምር የዕሤይ ልጅ ዳዊት ገና ታናሽ ሳለ ከወንድሞቹ ይልቅ እርሱ ለመንግሥት ቅብ ተመረጸ ቀኙም ጠላት የሚያጠቃ ሆነ፡፡ (፩ ሳሙ ፲፯ ፣ ፲፫)

፴፪. የእጆቹ ክንድ ሥር እንደ ብረት ቀስት ጸና ጻቶቹም ጦርነት የተማሩ ሆኑ፡፡ በእስራኤል ላይ የታጀረ ጎልያድንም በወንጭፍ ደንጊያ ጣለው፡፡ ራሱንም በገዛ ሰይፉ ቆረጠው፡፡ (፩ ሳሙ ፲፯ ፣ ፶ ፣ ፶፩)

፴፫. ስለዚህ ዘፋኞች ተቀበሉት እንዲህ ሲሉ፡፡ ሳኦል ሺህ ገደለ ዳዊት ግን እልፍ ገደለ፡፡ ለጨኛውም ለሳኦል ልጅ ሜልኮል ማጫ ከኢሎፍሊ ቆላፋን ወገን መቶ ሰለባ አገባ (፩ ሳሙኤል ፲፰ ፣ ፯)

፴፬. በፈጣሪውም ስም የታመነ ነውና ከንፈሮቹም የእግዚአብሔርን ምስጋና ተመሉ ካንደበቱም የምስጋና ጎርፍ ፈሰሰ በሰማይና በምድር ያሉ ፍጥረታትም በርሱ ቃል ያመሰግናሉ፡፡ እርሱም ካባቶቹ ጋራ አንቀላፋ ሞተ ነፍሱንም ከሞት አላዳናትም፡፡

፴፭. ከዳዊት ዘር የመጣ ልጅሽ ግን ከአቤል ጀምረው እስከዚያ ጊዜ ድረስ የተሰበሰቡትን ነፍሳት ከሲኦል አዳነ (ማረከ ፡፡)

፴፮. ሰሎሞን ዐሥራ ሁለት ዓመት ሲሆነው ለእስራኤል ነገሠ፡፡ እንደ ባሕር አሸዋ በሰማይም ረቦ እንደሚታይ ጉም ጥበቡ ሰፋ፡፡ ከአሕዛብም ነገሥታት ጋራ እጅ መንሣሣትን ለራሱ አደረገ፡፡ ከሕዝባቸውም እጅ ተነሣሣ፡፡ በዘመኑም የወርቅ ብዛት እንደ ደንጊያ የሚያማምረውም ልብስ ብዛት እንደ ቅጠል ሆነ፡፡ (፩ ነገ ፪ ፣ ፲፪) (፪ ዜና ፩ ፣ ፲፭)

፴፯. የእግዚአብሔርን ቤት ባልተወቀረ ደንጊያ አነፀ፡፡ በሴትፋሩሄም ወርቅ ለበጠው፡፡ የጢሮስም ንጉሥ ኪራም በዋንዛና በዝግባ ረዳው የሳባ ነገሥታትም በጽድ ዕንጨት አረዱት፡፡ (፪ ዜና ፫ ፣ ፭ ፣ ፯) (፩ ነገ ፱ ፣ ፲፪)

፴፰. የሰሌን ግንድና በቅንጭብ እንጨት በደጁ ሠራ በቅድስተ ቅዱሳን ኪሩቤል አሳለ በመቅደሱም አኩል የብረት አዕማድ አቆመ፡፡ ስማቸውንም በለዝ ያቁም ብሎ ጠራቸው፡፡ የመቅደሲቱን ሥራ ላይን የሚያምር ለልብ የሚያስደንቅ አደረገ፡፡

፴፱. ባሥራ ሁለቱ የወርቅ አንበሶች የተሠራ ዝሆን ጥርስ አትራኖስ አደረገለት፡፡ የዝሆን ጥርስ ሰሌዳውን ንጹሑን ወርቅ ቀባው ለምስማኩም ዐራት የወርቅ ላም አደረገ በመንበሩ ባራት ወገን አኖረው፡፡

፺. በሁለት በሁለቱ ላሞች ይተያያሉ የመንግሥቱም ግርማ የተደነቀ ሆነ፡፡ ሕዝቡም እርሱን ለመስማት ከምድር ዳርቻ ይመጣሉ፡፡

፺፩. እርሱ ግን በአሕዛብ ነገሥታት ልጆች አመነዘረ በሴቶችም ፍቅር ፈጣሪውን በደለ በአምላካቸውም በኋላ አስከተሉት፡፡ (፩ ነገ ፲፩ ፣ ፫ ፣ ፬)

፺፪. ልጅሽ ግን አመንዝሮችን ወደ ንጽሕና መለሳቸው የሃይማኖት የድንግልና ልብስን አለበሳቸው የሚያመልኩትን ወደ ባሕርይ አባቱ ወደ ልዑል እግዚአብሔር መለሳቸው፡፡

፺፫. ቴስብያዊ ኤልያስ ለአምላኩ ቀናተኛ ሆነ፡፡ እስከ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ድረስ ዝናም እንዳይዘንም ሰማይን ለጎመ እርሱ በደግነቱ በእሳት ሠረገላ ተቀምጦ ብሔረሕያዋን ተሻገረ፡፡ ሌላውን ግን ከርሱ ጋራ ሊያሻግር አልተቻለውም፡፡ (፩ ነገ ፲፯ ፣ ፩ ፣ ፪ ፣ ፲፩)

፺፬. ልጅሽ ግን መሃይምናንን ከሞት ወደ ሕይወት ካለማወቅ ወደ ማወቅ አሻገራቸው፡፡

፺፭. ኤልሳዕ የመምህሩ የኤልያስን ዕፅፍ ድርብ መንፈስ ቅዱስ ተቀበለ፡፡ በመጠምጠምያውም መትቶ የዮርዳኖስን ባሕር ከፈለ የመጥረቢያውንም ብረት በውሀ ላይ አንሳፈፈው ብዙውንም ተአምራት አደረገ፡፡ (፪ ነገ ፪ ፣ ፲፭)

፺፮. ሙት አነሣ በግዮን ውሀም ለምፃሙን ንዕማንን አነፃው፡፡ የሚያመክነውንም ውሀ ምረት በጼው አጣፈጠ የመከኑት የዚያ አገር ሴቶች እንዲወልዱ ርኩሰትን ለማንጻት ግን የነፍስንም ምረት ለማጣፈጥ አልተቻውም፡፡ (፪ ነገ ፳ ፣ ፳፩)

፺፯. ልጅሽ ግን የሥጋ ለምጻሞችን አነጻቸው የበደሉትን የነፍሳቸውን ምረት በመለኮቱ ጨውነት አጣፈጠ፡፡ ውሀውን አጣፈጠ ወይን አደረገው፡፡ (ማቴ ፮ ፣ ፪ ፣ ፫) (ዮሐ ፪ ፣ ፮ ፣ ፱)

፺፰. ኢሳይያስ ከእስራኤል ነቢያት ሁሉ ይልቅ ነገሩ የበለጠ ሆነ የይሁዳም ነቢያት አለቃ ሆነ፡፡ ሐሳቡም እስከ ቀላይ ድረስ ጥልቅ ሆነ፡፡ እስከ ሰማይም ከፍ ከፍ አለ ረቂቁን ምሥጢር ተመለከተ፡፡

፺፱. የአምላክንም ከድንግል ሰው መሆን ካምስት መቶ ዘመን አስቀደሞ እንደሚያይ ሁሉ አይቶ ጮኸ እንዲህ ሲል እነኋት ድንግል ትጸንሳለች፡፡ ልጅም ትወልዳለች፡፡ እንግዲህ በትንቢት መንፈስ አየ እንጂ በዓይነ ሥጋ አላየም፡፡ (ኢሳ ፯ ፣ ፲፬)

፻. ነገር ግን ቃል ካንቺ በመወለዱ የዓለም ሁሉ ሕይወተ ሆነ፡፡

፻፩. የኬልቅዩ ልጅ ካህኑ ኤርምያስ ነገሩ የጣፈጠ የወልድ ዋህድን መምጣት የሚያስብ ስለ ኢየሩሳሌም አለቀሰ በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር እጅ ልጆቿ በተማረኩ ጊዜ ራሱንና ሕዝቡን ከመማረክ ለማዳን አልተቻለም ሰቆቃው ኤርምያስ (፩ ፣ ፲፮ ፣ ፲፯)

፻፪. ልጅሽ ግን የጽዮንን ምርኮ መለሰ፡፡ የሲኦልንም ምርኮ በረበረ፡፡ ሙሴ እንደተናገረ እስራኤል የተደነቅህ ነህ እንዳንተ የእግዚአብሔር ሕዝብ ማነው መቁረጥህ በሰይፍ ሆነ፡፡ ይህ የትንቢት ተስፋ ያለ ልጅሽ አልተፈጸመም የእስራኤል ተስፋ በርሱ ላይ ዐርፏልና፡፡

፻፫. ሱቱኤል የተባለ ዕዝራ የእስራኤል ልጆች ከተማረኩ የጽዮን ሀገር ከወደቀች በሠላሳ ዓመት ለጽዮን ያለቅስላት ጀመረ፡፡ አሪትም ስለጠፋች መራራ ልቅሶ ሲያለቅስ ሌዋውያንም ስለተማረኩ ሲያለቅስ እንደ ፀሐይ እግር ፊቷ ሲያንጸባርቅ ታየችው፡፡ (ዕዝ ፲ ፣ ፩)

፶፬. በቃሏም አመላለስ የተነሣ ተራሮች ተነዋወጡ የሚከባትን የምስጋና ብርሃን ባየ ጊዜ ዕዝራ ተጽናናባት፡፡

፶፭. ድንግል ሆይ ዕዝራ ጽላሎትሽን አየ፡፡ የመልክሽን ብርሃን ግን አላየም ፀዳሉን አየ ፀሐዩን አላየም መብራቱን አየ የፋናውን ፀዳል አላየም፡፡ እውነተኛው የጽድቅ ብርሃን ባንቺ ሆነ፡፡ ጨለማን ያራቀ የቅዱሳን ፀሐይ ካንቺ ተገኘ፡፡

፶፮. ያማቴ ልጅ ዮናስ ያገሪቱን ጥፋት ለነነዌ ሰዎች ሊያስተምር በታዘዘ ጊዜ ከእግዚአብሔር ፊት ኮበለለ ታጣ፡፡ ወደ ተርሴስም አገር ሊሄድ በባሕር ከሚሄዱ ጋራ ወደ መርከብ ወጣ፡፡ (ዮና ፩ ፣ ፫)

፶፯. እግዚአብሔርም የሚያስፈራራውን ማዕበል አስነስቶ ወደ ባሕር ጣለው፡፡ እግዚአብሔር ታላቁን አንበሪ ዮናስን እንዲውጠው አዘዘ፡፡ ዮናስም በአንበሪ ሆድ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት አደረ፡፡ አንበሪውም በነነዌ አውራጃ በባሕር ዳርቻ ጣለው፡፡

፶፰. ዮናስም ለነነዌ ሰዎች አስተማራቸው በማስተማሩም ከምድራዊ መቅሠፍት ዳኑ ከሰማያዊ መቅሠፍት ግን አልዳኑም፡፡ (ዮና ፫ ፣ ፬)

፶፱. ልጅሽ ግን ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አደረ ለተማረኩትም ነፃ መሆንን ሰበከላቸው፡፡ ከሲኦልም እጅ አዳናቸው፡፡ ከሞትም ተበዣቸው፡፡ (ማቴ ፲፪ ፣ ፵)

፷. የሐዳ ልጅ ታላቁ ካህን ዘካርያስ የበራክዩ፡፡ በየካቲት ወር ሰባት ማብሪያ ያላት የወርቅ መቅረዝ አየ ከወዲያና ከወዲህ በቀኝና በግራ የዘይት አዕፁቅ ያላት፡፡ በመንፈስ መታየትም የሙሽራይቱን የሥራዋን አስተያየት አየ፡፡ (ዘካ ፬ ፣ ፪ ፣ ፫)

፷፩. ምሳሌ ስላየ አደነቀ በገሃድ አይደለም ዘካርያስም ያየው የመቅረዚቱ ብርሃን ለነቢዩ ብቻ እንጂ ለሌላ አላበራም በላይሽ ያደረው የመለኮት ብርሃን ግን ከሰው ላይ ጨለማን አርቆ በዓለም ሁሉ ጽንፍ እስከ ጽንፍ አበራ፡፡

፷፪. የቡዝ ልጅ ሕዝቅኤል በባቢሎን አገር ለእስራኤል ቤት ጉበኛ ተባለ፡፡ በኮበር ወንዝም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን በኪሩቤል ሠረገላ ላይ አየው፡፡ የመላእክትን ሥርዓት አየ፡፡ (ሕዝ ፩ ፣ ፩፮)

፷፫. የትጉሃንን ምስጢር አስተዋለ ወገኖቻቸውንም ሰማ የሠረገላቸውንም መንኮራኩር ባራት ወገን የሆነውን ፊታቸውን፡፡ ስድስት የሆነውን ክንፋቸውን የማይቆጠረውንም ያይናቸውን ብዛት እንዳየም ተናገረ፡፡ (ሕዝ ፩ ፣ ፭ ፣ ፮)

፷፬. ይህንን እየፈራ እየተንቀጠቀጠ አየ፡፡ ከነሱ አንዱን ስንኳን ሊዳስሰው ሊቀርበው አልተቻለውም እርሱ እንዲህ እንዳለ ለመጠየቅ (አልረባኋቸውም) አልቀረብኋቸውም፡፡

፷፭. አንቺን ግን ባናዋዋር የከበሩ ባስተያየት የተፈሩ ኪሩቤል የሚንቀጠቀጡላት እርሱን በሆድሽ ተሸከምሺው ሱራፌልም ወደ ዙፋኑ ለመቅረብ የማይደፋፈሩትን በክንድሽ አቀፍሽው በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ እርሱንም በጀርባሽ አዘልሽው፡፡

፷፮. የዳኮር ልጅ ዕንባቆብም የልጅሽን የመውረዱን ድምፅ ሰማ በልቡናውም እንዲህ ሲል ፈራ፡፡ እንደምን ያለ ሥፍራ ይችለዋል ሲል ነው፡፡ በተደነቀ ትሕትናም ሥራውን ያየው በጨርቅ ተጠቅሎ በጎል ተጥሎ ነው፡፡

፹፯. የዳኮር ልጅ ዕንባቆም በሁለቱም እንስሶች መሐከል አይቶት አደነቀ ዘመኑም እንዲቀርብ ዐወቀ ጊዜውም እንዲደርስ አስተዋለ፡፡ (ዕንባ ፫ ፣ ፪)

፹፰. ይህም መንፈስን የተመላ ነቢይ በሐሳቡ ፈራ በመንፈሱም አደነቀ፡፡ አንቺ ግን ዓለምን ሁሉ የመላ እርሱን ወሰንሽው፡፡

፹፱. ብልጣሶር የተባለ ዳንኤል በንጽሕና አደገ፡፡ በመንፈስ ጎለመሰ በውቀትም ከፍ ከፍ አለ፡፡ የተሰወረውንም የሕልም ትርጓሜ ዐወቀ፡፡ በንጉሡ ግድግዳ በተሠወረች እጅ የተጻፈውን ጽሕፈት ያለ ምልክት አነበበ፡፡ ማኒ ቴቄል ፋሬስ ብሎ ነው ይህንን ለንጉሡ ተረጎመለት፡፡ (ዳን ፪ ፣ ፲፮)

፺. ማኒ መንግሥትህን እግዚአብሔር ሰፈራት ቴቄል በሚዛን መዘናት ጎድላ ተገኘች፡፡ ፋሬስ ካንተ ተነሥታ ለሌላ ተሰጠች ብሎ ተረጎመለት፡፡ (ዳን ፭ ፣ ፳፭ ፣ ፳፮ ፣ ፳፯ ፣ ፳፰)

፺፩. ዘመኑም ያልተቆጠረ የሆነውን ደግሞ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየው የራሱም ፀጉር እንደ በረድ ነጭ ነበር፡፡ የእሳት ወንዝ ከፊቱ ይፈስ ነበር፡፡ አእላፍ መለእክትም ከበውት ይቆማሉ፡፡ (ዳን ፯ ፣ ፲፫)

፺፪. ነቢዩ ይህንን ባየ ጊዜ መታገሥ ተሳነው፡፡ አንቺ ግን ዘመኑ ያልተወሰነ የሆነ እርሱን ብቻ ያየሺው አይደለም በማኅፀንሽ ወሰንሽው እንጂ በክንድሽም አቀፍሽው በጀርባሽም አዘልሽው፡፡ በጡትሽም አሳደግሽው፡፡

፺፫. የይሁዳ ንጉሥ ልጆች አናንያ አዛርያ ሚሳኤል የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ታላቅ ጣዖት ባቆመ ጊዜ በፍጻሜው ለጣዖት ሥራ በዓል አደረገ አዋጅም ነገረ እንዲህ ሲል፡፡ (ዳን ፫ ፣ ፬)

፺፬. የነጋሪት ድምጽ በተሰማ ጊዜ የመለከትና የእምቢልታ የበገና የዛጉፍ የዘፋኞች ድምፅ ሰምቶ ንጉሡ ለጣዖት ያልሰገደ ቢኖር ቤቱ ይበርበር ገንዘቡ ይወረስ በራሱ ሞት ይፈረድበት፡፡ (ዳን ፫ ፣ ፮)

፺፭. እለዚህም የይሁዳ ንጉሥ ልጆች ይህንን ሰምተው የንጉሡን ትእዛዝ እምቢ አሉ፡፡ እንዲህ ሲሉ ንጉሥ ሆይ አምላክህን አናመልክም ለሠራኸው ምስል አንሰግድም፡፡ (ዳን ፫ ፣ ፲፰)

፺፮. ንጉሡም ተቆጣ የፊቱም አስተያየት ተለወጠ፡፡ የባቢሎን ሰዎች በዲኝና በጨው ባሩድ በዶሮ ማር ባያያዙት በነደደው እሳት ምድጃ ጣሏቸው ብሎ አዘዘ፡፡ (ዳን ፫ ፣ ፲፱)

፺፯. ከዚያም ጣሏቸው ከነበልባሉም የተነሣ አልተቃጠሉም እሳቱም አልቆነጠጣቸውም ከራሳቸውም ፀጉር አንዲቱ ስንኳን አልጠፋችም በፍጥረት ሁሉ ምስጋና የምስጋናን ጌታ ከዚያ ሆነው አመሰገኑት፡፡ (ዳን ፫ ፣ ፳፯)

፺፰. በደግነታቸው ለራሳቸው ከእሳት ዳኑ እንጂ ሌሎችን አላዳኑም፡፡ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ጣዖትን አላጠፉትም፡፡

፺፱. ልጅሽ ግን በመጣ ጊዜ ጣዖታትን ሁሉ አጠፋ ኢሳይያስ እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ ቤል ወደቀ ዳጎንም ተቀጠቀጠ፡፡ በሲኦል የነበሩትን አወጣቸው፡፡ እሊህንም ልጆች ሌሎችን ነቢያት ደግሞ በመዝሙር እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ (ኢሳ ፷፮ ፣ ፩)

፻. እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ ያን ጊዜ አፋችን ደስታን ተመላ አንደበታችንም ኃሤትን አደረገ፡፡ (መዝሙር ፻፳፮ ፣ ፩ ፣ ፪)

፻፩. እንዲህ ደግሞ አለ ምርኮ ማርከን ወደ አርያም ወጣህ ጸጋህንም ለሰው ልጆች ሰጠህ፡፡ (መዝሙር

፳፰ ፣ ፲፰)

፹፪. ከይሁዳ ነገሥታት ልጆች አንዱ ዘሩባቤል ከዳዊት ወገን የበቀለ ቡሩክ አፅቅ በንጉሡ በዳርዮስ ቤት ከሚኖሩ ልጆች ጋራ በጥበብና በምሳሌ ክርክር አደረገ በንጉሱም ፊት ፍርድ አኖሩ፡፡

፹፫. በምሳሌው ያቸነፈ የወርቅ ልሻን ባንገቱ ሊያሠራ የራስ ወርቅም በራሱ ሊደፋ ንጉሡም በሚቀመጠው ሠረገላ ሊቀመጥ፡፡ ንጉሡም በሚጠጣበት የወርቅ ጽዋ ሊጠጣ በወርቅ አልጋም ሊተኛ የንጉሡ ልጅ ሊባል ነው፡፡

፹፬. ይህንን ምሳሌያቸውን ንጉሡ ዳርዮስ በነቃ ጊዜ ተናገሩ ንጉሡም ፍርዱን ለዘሩባቤል መለሰ፡፡ ዘሩባቤልንም ምን ላድርግልህ ከኔስ እንደምን ያለ ሀብት ትሻለህ አለው፡፡

፹፭. ዘሩባቤልም ለንጉሡ መለሰ እንዲህ ሲል የእግዚአብሔር ሀገር ኢየሩሳሌም ብትሠራ እወዳለሁ የእስራኤልም ወገን ምርኮኞች ወዳገራቸው ይመለሱ፡፡

፹፮. ንጉሡም ነገሩን ወደደለት እንዳሰበው አደረገለት፡፡ የተመኘውን አገኘ ናቡከደናፆርና ያዛዦቹ አለቃ ናቡዛርዳን ያፈረሱትን የእግዚአብሔርን ቤት ሠራ፡፡ ሥራዋም የአምላክ ቤት በዓርባ ስድስት ዓመት አለቀ፡፡

፹፯. ነገር ግን ልዑል አምላክ የሰው እጅ በሠራው ቤት የሚያድር አይደለም እንዲህ ብሏልና፡፡ ሰማይ ዙፋኔ ነው፡፡ ምድርም ለእግሬ መሔጃ ናት፡፡ እንግዲህ ለማደሪያዬ የምትሠሩልኝ ቤት እንደ ምን ያለ ነው የማረፊያዬስ ሥፍራ ምንድነው፡፡

## ምዕራፍ ፯

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ የእግዚአብሔር ግን ማደሪያ አንቺ ነሽ በምድር ላይ የተሠራሽ፡፡ በሰማይ የተቋፀርሽ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ የተዘረጋሽ ከባሕርም እስከ ባሕር ከምድር ዳር እስከ ምድር ዳር የሰፋሽ፡፡

፪. ማነው ካባቶቻችን የምትገዛቸው ሕግ ሳትኖር ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ለእግዚአብሔር ያገለገሉ ከሙሴም እስከ መንገድ ጠራጊው ዮሐንስ ዘመን በኦሪት ሕግ የተገዙ፡፡ ከኦሪትም ቀምበር በታች የተገዙ ከሲኦል ራሱን ለማዳን የቻለ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ፡፡

፫. ልጅሽ ግን በርሳቸው አርአያ በመጣ ጊዜ የማይጠፋ ሊያደርገው የሚጠፋውን ሥጋ ለበሰ መጽሐፍን ሁሉ በኃጢአት ብረት ዘግቶ ተወው የሙሴ ኦሪት እንዲህ ትላለችና፡፡

፬. በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የማይሠራ ሁሉ የማይፈጽምም የተረገመ ይሁን ስለዚህም ነገር ነቢያት ሁሉ በሲኦል ደጅ ተዘጉ፡፡ የኦሪትም ቃል መዝጊያ ሆነችባቸው፡፡ (ዘዳግም ፳፯ ፣ ፳፮)

፭. ልጅሽ ግን ይህንን መቆለፊያውን ሊሰብር በኦሪት ማሠሪያ የታሠረውንም ደጅ ሊከፍት መጣ፡፡ ዘርም ምክንያት ሳይሆነው ካንቺ ሰው ሆነ፡፡ ማኅተመ ድንግልናሽም ሳይለወጥ ተወለደ፡፡

፮. ወደ ኦሪትም እርግማን ገባ፡፡ የኦሪትንም መርገም ሊሽር በዕንጨት ላይ ተሰቀለ እንዲህ ትላለችና በዕንጨት የተሰቀለ ሁሉ ርጉም ነው፡፡ (ዘዳግም ፳፩ ፣ ፳፫)

፯. ስለዚህም የኦሪት መርገም ተሻረ፡፡ የኃጢአትም ማሠሪያ ተፈታ፡፡ ዳዊት በመዝሙር እንደተናገረ

ዕንዲህ ሲል፡፡ ማሠሪያቸውን ከኛ እንቆርጣለን፡፡ (መዝሙር ፪ ፣ ፫)

፰. የሲኦልንም መዝጊያ ሰበረ፡፡ መቆለፊያውንም ቀጠቀጠ፡፡ በመዝሙር እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ የእግዚአብሔር ምሕረቱን ተናገሩ ጽድቁንም ለሰው ልጆች፡፡ የብረቱን መዝጊያ ሰብሯልና የብረቱንም መቆለፊያ ቀጥቅጧልና፡፡ (መዝ ፻፮ ፣ ፲፭ ፣ ፲፮)

፱. ከነቢያትም ለፍጥረት ሁሉ መድኃኒት ሊሆን የቻለ የለም፡፡ ዳዊትም እንዲህ አለ ዓይኖቼን ወደ ተራራ አነሣሁ፡፡ መረዳቴ ከወዴት ይምጣ፡፡ ዳዊት እንዲህ ማለቱ ከነቢያት ረዳት ሲሻ ነው፡፡ ከርሳቸው ውስጥ ከሲኦል የሚያድነኝ እንዳለ ብሎ፡፡ (መዝሙር ፻፳፩ ፣ ፩)

፲. ከእግዚአብሔር ልጅ በቀር የሚያድነው እንደሌለ ባወቀ ጊዜ በትንቢት ጮኸ እንዲህ ሲል መረዳቴስ ሰማይና ምድርን ከፈጠረ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው አለ፡፡ (መዝሙር ፻፳፩ ፣ ፪)

፲፩. ክርስቶስም ከዘሮቹ ልጅ በሥጋ እንዲወለድ ባወቀ ጊዜ ደግሞ አሰምቶ ተናገረ፡፡ እንዲህ ሲል እግዚአብሔርን ዘወትር አየዋለሁ፡፡ ሁልጊዜም በፊቴ ነውና፡፡ እንዳልታወክ በቀኜ ነውና ስለዚህም ልቡናዬን ደስ አለው አፌም ኃሤትን አደረገ በተስፋው ደግሞ ሥጋዬ አደረ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፡፡ ለጻድቅህም ጥፋትን ያይ ዘንድ አትሰጠውም፡፡ (መዝሙር ፲፮ ፣ ፰ ፣ ፲፩)

፲፪. የእግዚአብሔር ልጆች የቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ማኅበር እንግዲህ ይህችን ንጽሕት ሙሽራ የወለዱልንን ኢያቄምንና ሐናን እናድንቃቸው የማትነቀፍ የእስራኤል ድንግል የተባረከችይቱም ፍሬ የተፈራችባት የሩካቢያቸው ንጽሕት ቀን እንደምን ያለች ናት፡፡

፲፫. ከይሁዳ ወገን የምትሆነውን ንጽሕት ርግብ ለመፅነስሽ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነው የመገናኘታቸው ቀን እንደምን ቅድስት ናት፡፡ የንጉሥ አዳራሽ የምትሆን የርሷ መሠረት የተመሠረተባት ዕለት እንደምን ደስ ያለች ናት፡፡

፲፬. ኑ በሕያው እግዚአብሔር ደስ ይበለን፡፡ ከባርያው ከዳዊት ወገን የመድኃኒታችንን ቀንድ ላነሣልን ለያዕቆብ አምላክ ይባቤ እናቅርብ በትንቢት መንፈስ ተስፋ እንዳስደረገው እንዲህ ሲል በዚህም ለዳዊት ቀንድ አበቅላለሁ፡፡ ለመሲሑም መብራት አዘጋጃለሁ፡፡ (ሉቃ ፩ ፣ ፷፱)

፲፭. ዳግመኛም በዳዊት መዝሙር እንዲህ አለ፡፡ እግዚአብሔር ለዳዊት በውነት ማለ አይጸጸትም በዙፋንህ ከሆድህ ፍሬ አስቀምጣለሁ ብሏልና፡፡ (መዝሙር ፻፴፪ ፣ ፲፩)

፲፮. ኢሳይያስ እንዲህ አለ ከዕሤይ ሥር በትር ትወጣለች፡፡ ከግንዱም አበባ ይወጣል በላዩም የእግዚአብሔር መንፈስ ያርፍበታል፡፡ (ኢሳ ፲፩ ፣ ፩ ፣ ፪)

፲፯. ይኸውም ትንቢት በጽዮን የተነገረው በኢየሩሳሌም የተሰበከው በነቢያት አንደበት የተሰማው በሌዋውያን እጅ በዕብራይስጥ ልሳን የተጻፈው ሊፈጸም የክህነት በትር በቀለችልን፡፡

፲፰. የመንግሥትና የኃይል የሕይወትና የመድኃኒት የሃይማኖት የንጽሕና የቅድስና በትር የኃይል የመዊዕ በትር በቀለችልን፡፡ ከነቢዩ ዳዊት ጋራም እናመስግን እንዲህ ስንል፡፡

፲፱. አሕዛብ ሁላችሁ በእጃቸሁ አጨብጭቡ፡፡ በደስታም ቃል ለእግዚአብሔር እልል በሉ፡፡ ስሙንም አመስግኑ፡፡ ለጌትነቱም ምስጋና አቅርቡ፡፡ (መዝ ፵፯ ፣ ፩ ፣ ፷፮ ፣ ፩)

፳. የእስራኤል ንጉሥ በእስራኤል ልጅ አደረ የዳዊት አምላክ ከዳዊት ልጅ ሥጋ ለበሰ፡፡ የዕብራውያን ጌታ በዕብራውያን ልጅ ማኅፀን ተወሰነ፡፡ ለአብርሃምም የዕብራይስጥ ልሳን ያስተማረው ከቀድሞም

ያልሰማውን ልሳን እንዲናገር አፉን ጆሮውን የከተለት ከዕብራዊት ድንግል ተወለደ፡፡

፳፩. በድንግልና ወተት አደገ፡፡ ጥቂት ጥቂት እያለ አደገ፡፡ የሕፃናትንም ሥርዓት እንዳያጎድል አፉን የሚፈታበት ዘመን እስኪፈጸም ጥቂት ጥቂት እያለ በዕብራይስጥ ልሳን ሲናገር ኖረ፡፡ (ሉቃስ ፪ ፣ ፵) (ዕብራውያን ፪ ፣ ፲፯)

፳፪. ለሙሴ በዕብራይስጥ ልሳን በጻቶቹ የተጻፉትን ዐሥሩን ቃላት በደንጊያ ሰሌዳ የተጻፈውን የሰጠው አሮሕ የዕብራይስጥ ፊደል ለመማር ከመምህር እግር በታች ተቀመጠ፡፡ (ዘፀአ ፴፩ ፣ ፲፰)

፳፫. የባቢሎን አውራጃ በምትሆን ሰናዖርም የፍጥረትን ሁሉ ቋንቋ የበተነ እርሱ የአሕዛብን ልሳን እንደማያውቅ ሁሉ እናቱ በተፈጠረችበት ልሳን በዕብራይስጥ ልሳን ሲናገር ኖረ፡፡ (ዘፍጥ ፲፩ ፣ ፯-፱)

፳፬. ጆሮ እርሱን ከመስማት የተነሣ የሚለመልምበት ይህ ነገረ ዕፁብ ድንቅ ነው፡፡ ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡ ልቡናም መርምሮ የማያገኘው ይህ ምክር ዕፁብ ድንቅ ነው፡፡ ከማየቱም የተነሣ ዓይን የማትጸግበው የአምላክ ሥጋዌ እጅግ መንክር ነው፡፡ ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡ ነቢዩ ዳዊት እንደተናገረ እንዲህ ሲል ከሰው ልጆች ሁሉ ላህዩ ያምራል፡፡ (መዝ ፵፭ ፣፪)

፳፭. መላእክት ሊያዩት የሚመኙት ሱራፌል ለማየት የሚያስጎመጃቸው እርሱ መልኩ ያምራል ብሎ የተነገረለት እስራኤል ያላገኘው ምንድር ነው፡፡ ሳሬስ ያጣው ምን አለ፡፡

፳፮. የምድርና የሰማይ ኪዳን ተሠራለት፡፡ እርሱም ለብቻው የነገድ መመኪያ ሆነ ደብረ ሲና የእንግድነቱ ተራራ ነው፡፡ ኢየሩሳሌም ለርሱ ርስት ጉልት ናት፡፡ የኤርትራም ባሕር ለእግሩ መተላለፊያ ልትሆን ከሦስት ተከፈለች፡፡ (ዘፀአ ፲፬ ፣ ፲፰)

፳፯. የተኪዝ ውሀም ከላይ እስከታች ተከፍሎ ሸሸ የአምላክ ፈቃድ እርሱን ለያሻግር ወደ የደመናው ዓምድ ሊመራው በቀን ይመላለሳል፡፡ የእሳቱም መቀነት ብርሃን ሌሊት ያበራለታል ለምግቡም የሰማይ እንጀራ ይዘንምለታል፡፡ (ዘፀአ ፲፫ ፣ ፳፪ ፣ (፲፮ ፣ ፲፭)

፳፰. መልአከ ገጽም በፊቱ ይመላለሳል፡፡ ጽኑዓኑ የኃይል መላእክት የድንኳኑን ዙሪያ ይከቡታል ነቢያት የርሱ ናቸው፡፡ ሐዋርያትም የራሱ ናቸው፡፡ የሕግ ታቦት የርሱ ናት፡፡ የማኅሌትም መዝሙር ከርሱ ዘንድ ነው፡፡

፳፱. ኦሪት የርሱ ናት ወንጌልም ከርሱ ዘንድ ናት እንደተጻፈ እንዲህ ሲል፡፡ ሕግ ከጽዮን ይወጣልና የእግዚአብሔር ቃልም ከኢየሩሳሌም፡፡

፴. ሕግ ከጽዮን ይወጣል የተባለው የኦሪት መጨመሪያ በሚሆን በወርቅ በተለበጠው ታቦት ውስጥ የሚጠብቀው የመሐላ ጽላት ሕግ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ከኢየሩሳሌም የተባለ ንጹሕ የእግዚአብሔር ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱ ነው፡፡ ከኢየሩሳሌም ሰዎች ወገን የዕብራውያን ልጅ ናትና እንደተጻፈ እንዲህ ሲል፡፡

፴፩. የኢየሩሳሌም ልጅ ደስ ይበልሽ የጽዮንም ልጅ ኃሤት አድርጊ፡፡ የጽዮን ልጅ በማለቱ የሐዋርያትን ቤተሰብ ቤተክርስቲያንን ይጠራታል የእስራኤልን አምላክ ማደሪያ ጽዮንን እናት አድርጎ የሐዲሱ ሕግ ከብሉይ ተገኝቷልና፡፡ (ዘካ ፱ ፣ ፱)

፴፪. ኢየሩሳሌም ሆይ ኃሤት አድርጊ በማለቱ ደግሞ ቅድስት ድንግልን ይጠራል ከይሁዳ ወገን የኢየሩሳሌም ልጅ ናትና፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፷፫. ስለዚህ እስራኤልን እናመስግነው በእግዚአብሔር ስጦታ የተሸለመ ሁኗልና ባለሟልነትን ከቅድስት ደንግል ተቀበለ በቅዱሳን ነቢያት ራስ ላይ የምታንጸባርቅ የወርቅ አክሊል ይህች ናት፡፡ ጌጿም በዕንቁ ፈርጽ የተሠራ ነው፡፡

፷፬. በተመረጹ ሐዋርያት ራስ ላይ የምታበራ የብርሃን አክሊል ይህች ናት፡፡ የልጅዋን ጠላቶች በሚጋደሉ ቅዱሳን ሰማዕታት ራስ ላይ የምታበራ የመዊዕ አክሊል ይህች ናት በኃጢአት ዕድፍ የክህነታቸውን ልብስ ባላሳደፉ ለማገልገልም በተሾሙ ካህናት ራስ ላይ የምታንጸባርቅ ዋጋዋ የበዛ የዕቁ አክሊል ይህች ናት፡፡

፷፭. በመላእክት ሥርዓት ሰውነታቸውን ንጹሕ አድርገው በጠበቁ በደናግል ራስ ላይ የምትብለጨለጭ የንጽሕና አክሊል ይህች ናት፡፡ ሰማያዊውንም ሙሽርነት ወደው የዚህን ዓለም ሠርግ በናቁት መነኮሳት ራስ ላይ እንደ ፀሐይ የምታበራ የቅድስና አክሊል ይህች ናት፡፡

፷፮. የዚህ ዓለም ርኩሰት ያላገኛት የሙሽርነት አክሊል ይህች ናት፡፡ የኃሣር ያይደለች የክብር አክሊል ይህች ናት፡፡ ለርጉማን የማትገባቸው የበረከት አክሊል ይህች ናት፡፡

፷፯. የዓለም መድኃኒት በሚሆን ልጅዋ ስም ላልተጠቀሙት የምታደርሳቸው የመሃይምናን ጌጽ የምትሆን የጽድቅ አክሊል ይህች ናት የመለኮት የዕንቁ ሣፅን ለነዳያንም ሀብት ባለጸግነት የምትሆን የወርቅ ሙዳይ ይህች ናት፡፡

፷፰. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ እመቤቴ ማርያም ሆይ መሰንቆ ልቡናዬን ፍቅርሽን አነሣሣው የትንቢት መንፈስ ሆዴን አወከው ሰውነቴም ከምስጋናሽ መታገስ ተሳናት፡፡

፷፱. ልቡናዬም አንደበቴን ዘበዘበችው ምስጋና የመላውን ክብርሽንም እንዲናገር የግድ አለችው፡፡ በከንፈሮቼም የመንፈስ ቅዱስ ትንፋሽ ተሰማ፡፡

፸. የእስራኤል ነቢያት የትንቢት መሰንቆ በመተባበር ዜማ እየመቱ ይጮኻሉ፡፡ የልጅሽ ምስጋና አቀንቃኝ ለዘፈን ወደርሱ ይጥቀሰኝ ስለአንችም የሚጮሁትን የትንቢት መሰንቆች የመቃኘታቸውን ድምጽ ያሰማማልኝ፡፡

፸፩. የሚናገረውም የነጋሪት ድምጽ ይኸውም የመለኮት ወንጌል እርሱ ደግሞ የቃልን ሰው መሆን የበህር ልጅሽም ካንቺ መወለዱን ይነገረኝ ጳውሎስ አዋጅ ነጋሪው እንደተወለደ ይሰብክልኛል እንዲህ ሲል፡፡ ከሴት ተወለደ በኦሪት የነበሩትን ሊወዳጃቸው ሊያበዛቸውም በዐራት ሥራ ሠራ፡፡

፸፪. ዳግመኛም ጌታ መወለዱ ከዳዊት ዘር እንደሆነ ተናገረ እንዲህ ሲል በሮሜ መልእክቱ ጳውሎስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ ሐዋርያውም የተባለ ወንጌልንም ለማስተማር የተለየ ስለተወለደው ልጁ በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለመጣው አስቀድሞ በነቢያት ተስፋ ያስደረገውን (አሜን)፡፡ (ሮሜ ፩ ፣ ፩ ፣ ፲፪ ፣ ፫)

www.ethiopianorthodox.org

# አርጋኖን
# ዘዓርብ
# <u>ምዕራፍ ፩</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ከነቢያት ማኅበር ሁሉ ጋራ ወደኔ ነዪ፡፡ ካንደበታቸው የወጣውን የምስጋናሽ ኃይለ ቃል ልብ ታስደርጊልኝ ዘንድ፡፡

፪. ድንግል ሆይ የቃልን ካንቺ ሰው መሆን ሥጋ መልበሱንም ጽንፍ እስከ ጽንፍ አስተማሩ፡፡ በልጅሽም ዕርፈ መስቀል የአሕዛብን ምድር ካረሱ የቃሉንም ድልብ በምድር ሁሉ ከዘሩ ሐዋርያት ጋራ ወደኔ ነዪ፡፡

፫. ድንግል ሆይ በሥጋቸው የልጅሽን መከራ ከተሸከሙ የሰማዕትነታቸውን ደም ከተቀቡ ሰማዕት እርሳቸው ሁለት ልዳን ያለው ሰይፍ የሚታጠቁ ድል የሚነሱ የንጉሥ ሠራዊት ናቸው፡፡ ከርሳቸው ማኅበር ጋራ ደግሞ በረድኤት ወደኔ ነዪ፡፡

፬. ድንግል ሆይ በማመንዘር እድፍ ልብሳቸውን ካሳደፉ፡፡ ለመንፈስም ማደሪያ ከሆኑ ንጹሐን ደናግል ማኅበር ጋራ ወደኔ ነዪ፡፡

፭. ድንግል ሆይ ስለመንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን ጃንደረባ ካደረጉ ፍጹማን መነኮሳት ማኅበር ጋራ ወደኔ ነዪ፡፡

፮. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ፡፡ በየጊዜው በየሰዓቱ ምስጋናና ቅዳሴን ከማያቋርጹ ከትጉሃን መላእክት ማኅበር ጋራ ወደኔ ነዪ፡፡ ድንግል ሆይ ከቅድስት ቤተክርስቲያን ማኅበር ከምዕመናን ሁሉ ጋራ ወደኔ ነዪ፡፡

፯. ድንግል ሆይ ከቅዱሳን ሁሉ ማኅበር ጋራ ወደኔ ልትመጭ እወዳለሁ ይልቁንም ከዚህ ከማኅሌታዊው አባትሽ ከዳዊት ጋራ ብትመጭ እፈቅዳለሁ፡፡ በተቃጠለ ፍቅር ስላንቺ ይጮህልና እንዲህ ሲል፡፡

፰. በጽዮን ለሚያድር እግዚአብሔር ምስጋና አቅርቡ ሥራውንም ለአሕዛብ ንገሯቸው ዳግመኛም ዳዊት እንዲህ አለ ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ፡፡ እንዳትታወክም እግዚአብሔር በመካከሏ ነው፡፡ (መዝ ፱ ፣ ፲፩) (፵፯ ፣ ፬ ፣ ፭)

፱. ዳግመኛም ዳዊት እንዲህ አለ፡፡ ጽዮንን ክበቡ፡፡ በዙሪያዋም ተመላለሱ፡፡ በቤቷም ተናገሩ፡፡ በብርታቷም ልባችሁን እኑሩ፡፡ ታላላቁንም ቤቶቿን ለሚመጣው ትነግሩ ዘንድ አስቡ፡፡ (መዝ ፵፰ ፣ ፲፪ ፣ ፲፫)

፲. በቅድስት ድንግል ምን ያህል የከበደ ሥርዓት ሸክም ተሠራ፡፡ በቅድስት ኦሪት ላይ ቅዱስ ወንጌል፡፡ በቅዱሳን ነቢያት ላይ ቅዱሳን ሐዋርያት በብሉይ ኪዳን ላይ ሐዲስ ኪዳን፡፡ ለእስራኤልም በተሰጠው የፍርድ መጽሐፍ ላይ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የቀኖና መጽሐፍ ስለዚህም እንዲህ አለ፡፡

፲፩. ሸክሟንም ትካፈላላችሁ ለሚመጣው ትውልድ ትነግሩ ዘንድ ባለጊዜ ደግሞ ስለ ጥምቀት ልጆች በሥጋ ስለማይመኩ የእግዚአብሔር ልጆች ሊሆኑ ሥልጣን ስለ ሰጣቸው ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከሰው ፈቃድ ከሥጋዊ ፍትወት ከሥጋዊ ከደማዊ ስላይደሉ ይናገራሉ፡፡ (ዮሐ ፩ ፣ ፲፪ ፣ ፲፫)

፲፪. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ፡፡ አምላክን በሥጋ የወለድሽ ከትንሽነቴ ጀምሮ ተስፋዬ አለኝታዬ አምባዬ መጸጊያዬ ጉልበቴ የመድኃኒቴ ሸቱ ብልቃጥ

www.ethiopianorthodox.org

የመመኪያየ አክሊል ክብሬ ገናንነቴ የራሴ ከፍ ከፍ ማያ ሆይ፡፡ በክርስቲያን ሥርዓት ጠብቂኝ፡፡

፲፫. በክርስቲያን ሃይማኖት አጽኚኝ ክርስቲያን አድርጊኝ፡፡ ክርስቲያን ልባል ምስጋና በክበበ ትስብእት በመንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ ክርስቲያን ሁኜ ልገኝ፡፡

፲፬. የኃጢአቴን ሥሯን ከኔ ላይ ንቀይልኝ ጫፎቿ በሥጋዬ ላይ እንዳይረዝሙ፡፡ ከልቡናዬም የሥጋዊን ፈቃድ ግንድ ቁረጭ እሾክ አሜከላ በላዬ እንዳይበቅል፡፡ ነፍሴንም የምታስጨንቃትን ወደ ጥፋትም የምታደርሰሽን የዚህን ዓለም ማማር ፈቃአ አአአአ አጥፊልኝ እንድጎዳም አትተዪኝ፡፡

## ምዕራፍ ፪

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ የቤልሖር መንፈስ እንዲገዛኝ አትጣይኝ፡፡ ከቀምበሩም በታች እንዳልጸመድ አድርጊኝ፡፡

፪. የሚያጣላ የሚያስት መንፈስ እርሱ ነውና፡፡ ለጊዜው ኃጢአትን ያማረ የተወደደ አስመስሎ ያሳያል ሥጋዊውንም ፈቃድ ለልቡና ያከናወናል መራራውን የጣፈጠ ጨለማውን ብርሃን ያደርጋል፡፡ ኃጢአትን ሠርቶ ከፈጸሚት በኋላ ግን እርሱ አስከድሞ ይከሳል፡፡ የሠሩትንም ከልዑል እግዚአብሔር ፊት ያጣላቸዋል፡፡

፫. እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ ይህንን መስተዋድይ እፈራዋለሁ ይከሰኛል ብዬ የዚህን የማሳት መንፈስ ፈቃድ እንዳልሠራ አድኚኝ፡፡ ኃጢአትም ሳያሠራኝ አስቀድሞ አድኚኝ፡፡ ሳያጣላኝም ከልዑል ፊት ኃጢአቴን አስተሥርዩልኝ፡፡

፬. ቢያጣላኝም በሰማይ የሚኖር ተስፋ አለኝ ሥጋሽን የለበሰ ወልድ በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ የሚጣላልኝ የሚከራከርልኝ አለና፡፡ ነገር ግን ፍቅርሽን በልቡናዬ ለጨመረ አቸናፊ እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው ስሙም ምስጉን ብሩክ ይሁን፡፡ (ማር ፲፯ ፣ ፲፱ ሉቃ ፩ ፣ ፳፰ ፣ መዝ ፵፩ ፣ ፲፫)

፭. ወይን ከውሀ እንዲቀላቀል አንዱም ክንዱ ሊለይ እንዳይቻል እንዲሁም ደግሞ ፍቅርሽ ከልቡናዬ ልቡናዬም ከፍቅርሽ ተዋሐደ፡፡ የጣጢአቴ ቁስል የነፍሴም መግል ያለንቺ ጸሎት እንዳይድን ልዑል እግዚአብሔር ያውቃልና፡፡ ኃጢአት እንዲበልጥ ተረዳ ንጽሕናሽ ደግሞ ከቅዱሳን ሁሉ ንጽሕና እንዲበልጥ እንዲበዛ ዐወቀ፡፡ ስለዚህም ፍቅርሽን በልቡናዬ ጨመረ ጽኑ ቁስል ያለ ጽኑ ዕፁብ ድንቅ መድኃኒት እንዳይጠግ ያውቃልና፡፡

፮. የእግዚአብሔር የጥበብ ርቀት ምን ይረቅ ምን ይጠልቅ፡፡ ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡ ደግነቱንና ይቅርታውንስ ማን ይናገራል፡፡ በኃጢአት ቁስለኞች ፊት መድኃኒት አዘጋጀ፡፡ ተቀብተው በርሱ እንዲድኑ ነው፡፡

፯. በኃጢአት በቆሰሉት ፊት የሕይወት የመድኃኒት ሽቱ አዘጋጀ፡፡ በርሱ ተሻተው ከመከርፋት እንዲድኑ ነው፡፡ የሕይወትም ወሀ አዘቅትን አመለከተ ወደርሷ ሂደው በርሷም የመነጨ የንጽሕና ውሀ ተረጭተው ታጽበው እንዲድኑ፡፡

፰. የምድር ኃጥኣን ሁላችሁ ወደ ቅድስት ድንግል ኑ፡፡ በርሷ ስጦታ ጻድቃን ትሆኑ ዘንድ ልብሳችሁ ያደፈ ሁላችሁ ወደዚች ቅድስት ምንጭ ኑ፡፡ የይቅርታ ውሀ ወደምትፈስ ልብሳችሁንም በልጅዋ ደም እጠቡ፡፡ ለሰማያዊ ሙሽርነት ዝግጁ ትሆኑ ዘንድ፡፡

፲. ድውያነ ሥጋ ሁላችሁ ወደ ድንግል ኑ በጸሎቷ ኃይል እንድትፈወሱ የዕውቀት ድሆች ሁላችሁ ኑ፡፡

የዕውቀት ምንጭን ከሷ ትቀዱ ዘንድ፡፡ ያማረ የተወደደውን የጥበብ ምክር ያገኙ ዘንድ፡፡

፲፩. ድንግል ሆይ የኔን አመንዝራነቴን እናገራለሁ ያነቺን ንጽሕና የልጅሽን ቸርነት አወራለሁ፡፡ ድንግል ሆይ የኔን ስሕተት ያንቺን ማማለድ የልጅሽንም መታገስ እናገራለሁ፡፡ ድንግል ሆይ የኔን ስንፍና ያንቺን ምክር የልጅሽንም ይቅርታ እናገራለሁ፡፡

፲፪. ድንግል ሆይ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያቸንፈኝ በኔ ላይ ይመኛል (ይሻል) ይቅርታ የሚያደርግልኝ ልጅሽን ለምኝው በኔ ላይ እንዳያሰለጥነው፡፡ ጸሎቴም በሚቃረን ፊት በአርበኛ እጅ እንደ ፍላፃ በኃይልም እንደሚወጋ ጦር የጎን አጥንትም እንደሚሰብር እንደሚያቆስልም ይሁን፡፡

፲፫. ደግመኛም እንደ ሰይፍ የሚቆርጥ እንደ እንደ ጠገራ የሚሰነጥቅ ይሁን ጠላቴም ይህንን አይቶ ይሸሽ ከኔ ጋራ ለመቃረን እንግዲህ አድባም ተንኮሉ ይጥፋ መንገኑም አልጫ ይሁን፡፡ የኃይሉም ብርታት ልምሾ ይሁን የሚጸናናበትም ተስፋ አያግኝ፡፡

፲፬. መሃይምናን በጥላዋ የሚያድፉባት ታላቂቱ የዘይት ዛፍ ድንግል ሆይ የትንቢት ዝናም የምትጠጭ የሰማይ ደመና ብርሃን የሚጋርድሽ በቤተ መቅደስ ያደግሽ አስቀደሞም ልጹል እግዚአብሔር የተከለሽ ከእስራኤል ወገን የምትሆኚ ቡርክት ፍሬ ሆይ፡፡

፲፭. ቡሩክ ፍሬ ይኸውም ጌታቸን ኢየሱስ ክርስቶስ ካንቺ የተገኘ በላህዩም መሻከራቸውን ለማለዘብ ከርሱ የመለኮትነት ቅቤ የሚፈሰው እርሱ ካንቺ የተገኘ ድንግል ሆይ አንቺ ደግሞ የኃጢአቴን መሻከር በልጅሽ መለኮትነት ቅቤ አለዝቢልኝ በርሱ ላህይ ደም ግባቴን እንዳገኝ፡፡

## ምዕራፍ ፫

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ያለ ዘር ያለ ሩካቤ አካላዊ ቃልን የወለድሽ ንብ ከማር መፈጠሪያ ከሰፈፍ ውስጥ እንዲወለድ የንብ ልጅ ዕጩ ከሰፈፍ ውስጥ በንቡ ዜማ ጩኸት ነውና፡፡

፪. ማርም ደግሞ ከሰፈፍ ይቀዳል የክርስቶስም ካንቺ መወለድ እንዲሁ ነው፡፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንዲህ ብሏልና፡፡ ጸጋ ክብርን የተመላሽ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል፡፡ ከእግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ አንደ አካል አንደ ባሕርይ ሁኗልና፡፡ (ሉቃ ፩ ፣ ፳፰)

፫. ከሴቶችም ሁሉ የተባረክሽ ነሽ ከእግዚአብሼር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና፡፡ እነሆም ልጅ ትወልጃለሽ፡፡ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፡፡ (ኢሳ ፯ ፣ ፲፬ ፣ ሉቃ ፩ ፣ ፴፩)

፬. አንቺ ደግሞ እንዲህ አልሽው ወንድ ሳላውቅ እንደምን ይሆንልኛል፡፡ መልአኩም እንዲህ አለሽ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በላይሽ ይመጣል፡፡ የልዑል ኃይሉ ይጋርድሻል፡፡ በገብርኤልም አንደበት የአብ ቃል በጆሮሽ ተሰማ፡፡ (ሉቃ ፩ ፣ ፴፭) (ማቴ ፩ ፣ ፲፰ ፣ ፳)

፭. ስለዚህም በሰፈፍ ተመሰልሽ፡፡ ቃልን በመስማት ፀንሰሻልና፡፡ ስለ ንብ ክንፍም የመንፈሰ ቅዱስ ክንፍ ጋረደሽ ንብም አበባውን ሰብስቦ ስለሚሠራው ማር ከቅዱሳን ነቢያት ቃል አበበ የተቀሰመው ትንቢት የማር ወለ በላይሽ ፈሰሰ፡፡

፮. ቃል ካንቺ እንደ ንብ መወለዱንም ዳዊት መስሎ ተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ እኔ ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም እንደ እርሱ አድርጎ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ሲናገር ነው፡፡ (መዝ ፳፪ ፣ ፮)

፯. በሚሽልቱት ፊት የማይናገረውን ነባቢ በግ በሕማሙም ጊዜ በወጉት ፊት አፉን ያልከፈተውን የወለድሽልን ድንግል ሆይ ለምኝልን ልጅሽ በደሙ ይዋጀን፡፡ እኔ እንዳልጎዳ በልጅሽ ፊት የተናቅሁ እንዳልሆን ለሰይጣንም የተሰጠሁ ለአጋንንት የተገዛሁ እንዳልሆን የመስቴማ ሠራዊት በላዬ እንዳይመኩ የቤልሖርም መናፍስት እንዳይሳለቁብኝ (ኢሳ ፶፫ ፣ ፯)

፰. የኔን መውደቅ የሚወዱ ሁሉ እርሳቸው የወደቁ ይሁኑ፡፡ ጉስቁልናዬንም የሚወዱ ሁሉ እርሳቸው የጎሰቆሉ ይሁኑ፡፡ እኔ ባሪያሽ ግን ከፍ ከፍ ልበል፡፡ እርሳቸም ይፈሩ ይጎሳቆሉ፡፡ ለርሳቸው ችግር መናቅ ይምጣባቸው፡፡

፱. ለኔ ክብር ባለጸግነት ይሁን፡፡ ለርሳቸው ማፈር ፊት ማጥቆር ለኔ ከፍታ ባለሟልነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለርሳቸው አበር ቸነፈር እግል ማጣት፡፡ ለኔ ጽጋብ መወደድ ተድላ ደስታ ይሁን፡፡

፲. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ የእግዚአብሔር የመቅደሱ ተራራ በእስራኤል ልጆች ፊት እንደ እሳት ነበልባል ሲነድ በላይዋ ሲበራ የታየባት ደብሩ ይወሳል፡፡ ብርሃንም እንደ መጋረጃ ይከበዋል፡፡ (ዘፀ ፲፱ ፣ ፲፰)

፲፩. ሙሴ ይናገራል እግዚአብሔርም ይመልስለታል፡፡ የእስራኤል አምላክ የምስጋና ብርሃን በላይዋ የታየባት ድንኳን እግዚአብሔር ከሰወ ጋራ ያደረባት አንቺ ነሽ፡፡ (ዘፀ ፲፱ ፣ ፲፱)

፲፪. ያዕቆብ የእግዚአብሔር ሠራዊት ያደሩባትን አይቶ ከዚያውም ሐውልት ያቆመባት ዘይት ያፈሰሰባት ሎዛ አንቺ ነሽ፡፡ (ዘፍጥ ፣ ፳፰ ፣ ፲ ፣ ፲፱)

፲፫. እግዚአብሔር ላባቶቻችን ተስፋ ያስደረጋት ምድረ ርስት የተመሰገነች የተወደደች ጽጎቿ ብረት የሆኑ ከተራሮቿም ብረት የሚያከማቹባት አንቺ ነሽ፡፡ (ዘሌዋ ፳ ፣ ፳፬)

፲፬. የእስራኤል ልጆች ከውስጧ ፍሬ የቆረጡባት የቆላ የወይን ሐረግ በባጢቀፎ የተሸከሙላት አንቺ ነሽ ይኸውም የድንግልናሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ (ዘኁል ፲፫ ፣ ፳፫)

፲፭. የእግዚአብሔር እግሮች የቆሙባት የኮሬብ ቦታ አንቺ ነሽ ከዚያም አለት ደንጊያ አለ፡፡ የጣፈጠ ውሀ ዐሥራ ሁለት ምንጭ የሚፈስበት ሕዝቡም ለጽማቸው የሚጠጡት ሲሄዱም ከርሳቸው ጋራ የሚሄድ ደንጊያው ግን ክርስቶስ ነው፡፡ (ዘፀአ ፲፯ ፣ ፮)

፲፮. ኢሎፍሊ የወረደች የእስራኤል አምላክ ታቦት በዚያም ዳጎንን የጣለችው፡፡ በጣዖት የሚያመልኩትንም የቀሠፈቻቸው፡፡ በወጣችም ጊዜ ከዛጦን ሰዎች ካሳዋን የተቀበለች የእስራኤል አምላክ ታቦት አንቺ ነሽ፡፡ ከካሳዋም ጋራ እምቦሳ ባላቸው ላሞች ላይ ጭነው ለኳት፡፡

፲፯. የእግዚአብሔርን ታቦት የወርቁንም አይጥና የእበጣቸውን የወርቅ ምሳሌ በሣፅን አድርገው በሠረገላ ላይ ጫኑት፡፡ (ሳሙ ፩ ፣ ፮ ፣ ፲ ፣ ፲፩)
፲፰. ሰሎሞን ያሠራት ቤተ መቅደስ በጉልላትም ያስጌጣት ቤቱንም ዕንጨቱንም መድረኩንም ናሱንም በወርቅ ለበጠው በውስጧም ሥዕለ ኪሩብ አሳለ፡፡ ቁመቱ ሀያ ክንድ ነው፡፡ ክንፉ ዐሥራ አምስት ክንድ ነው፡፡ ባንዱ ናሱን ይነካ ነበር፡፡ የሁለተኛውም ክንፉ ወደላይ የተዘረጋ ነበር፡፡ እንዲሁም ሁለተማው በወዲያና በወዲያ ነው፡፡ ክንፋቸውም በቅርስተ ቅዱሳኑ ቤት ላይ ይነካካ ነበር፡፡ (፩ ነገ ፮ ፣ ፳ ፣ ፴)

፲፱. ለካህናትና ለመንግሥት የተሠራች፡፡ ከካህናትና ከንጉሥ በቀር ማንም የማይቀባት ማንም በእጁ ያልቀመማት ዕፍረት ሽቱ አንቺ ነሽ ይህችንም ማንም እንዳይቀባት እግዚአብሔር ከለከለ እንዲህ ሲል እንዲህ ያለውን ሽቱ የተቀባ ቢኖር ሞት ይፈረድበት፡፡ (ዘፀአ ፴ ፣ ፴፩ ፣ ፴፪ ፣ ፴፫)

ዕረፍት ሽቱ አንቺ ነሽ፡፡ ሥጋሽንም የተቀባው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ክርስቶስ ማለት ቅቡዕ ማለት ነውና ቄርሎስ እንደተረጎመው (ዳን ፱ ፣ ፳፬)

፷. የምስክሩን ድንኳን ቅቤ ማንም እንዳይቀባው እግዚአብሔር እንደከለከለ ከንጉሡና ከሊቀ ካህናቱ በቀር ማንም እንዳያገኘው፡፡ እንዲሁ ደግሞ በኅቱም ድንግልና መወለድ ከአብ ቃል በቀር የተከለከለ ነው፡፡ ንጹሐ ክህነት ፍጹም መንግሥት የርሱ ብቻ ነውና፡፡

፷፩. የትንቢት መንፈስ የተመለች ከሳኦል ቤት የራቀች፡፡ ወደ ዳዊት ቤት ያረፈች የሳሙኤል የሽቱ ብልቃጥ አንቺ አካላዊ ቃል ከሱ ዘር ሰው ሁኗልና፡፡ (፩ ሳሙ ፲፮ ፣ ፲፫)

፷፪. ርኩሰት የሌለብሽ ሙሽራ ሆይ ዕዳ በደልም የሌለብሽ ንግሥት አንቺን እማልዳለሁ በገናንነትሽም እማፀናለሁ ያሥራ ሁለት ዓመት ታናሽ ብላቴና ስትሆኚ ሰማይና ምድር የማይወስኑትን በወሰነው ሆድሽ እማፀናለሁ፡፡

፷፫. ዓለምን ሁሉ የመላ እርሱንም ዘጠኝ ወር ካምስት ቀን በተሸከመው ማኅፀንሽ እማፀናለሁ፡፡ በመውለድም ማኅተሙ ባልተለወጠ የድንግልናሽ ኃይል ሥጋ የለበሰውን ፍጥረት ሁሉ የሚያሳድገውን እርሱን ባሳደገ ጡትሽ ወተት እማለድሻለሁ፡፡

፷፬. ፈረሶቹዋን የሚያደላድል የሕይወት እሳት ሠረገላውንም የእሳት ነበልባል አደረገ እርሱን ባቀፉት ጉልበቶችሽ፡፡ የማይዳሰሰውን እሳት ያለ ጉጠት በዳሰሱት ቅዱሳት እጆችሽ እማልዳለሁ፡፡

፷፭. ከገሊላው ንጉሥ ከሄሮድስ ፊት ከልጅሽ ከወዳጅሽ ጋራ ስትሸሺ መንገድ በመሄድ በደከሙት ቡሩካት እግሮችሽ በአዳም በፊቱ የሕይወት መንፈስ ያሳደረበት እርሱን በሳሙት ከንፈሮችሽ እማልድሻለሁ፡፡ (ዘፍጥ ፪ ፣ ፯)

፷፮. ልጅሽን ወስደው እንዳይገሉት ከሄሮድስ ሠራዊት ፈርተሽ ስለ ልጅሽ መራራ ልቅሶ ባለቀሱ ዓይኖችሽ እናቴ እማማ በማለት በታናሽ ብላቴና አንደበት፡፡ (በሕፃን አንደበት) ሲያጫውትሽ የሚጣፍጠውን ነገሩን በሰሙት ጆሮችሽ እማልዳለሁ፡፡

፷፯. የንጹሕ ድንግልናሽ አበባ የሚሆነውን የአብ የበህር ልጅ የልብሱን ሽታ ያፋንም መዓዛ ባሸተተው አፍንጫሽ ከሽቱ ሁሉ የሚበልጠውንም የሰውነቱን መዓዛ ባሸተተው ከጽጌረዳም በሚቀላው ፊትሽ እማልዳለሁ፡፡

፷፰. እንደ ብርሌም በጠራው መልክሽ ብርሃኑ እንደ መላ እንደ ፀሐይ በሚያበራው ያማረ የተወደደ ሽቱ የፈሰሰበት ፊትሽ አንጥረኛ የሠራው የወርቅ ዘንግ በሚመስለው አንገትሽ እማፀናለሁ፡፡ (መሐ ፮ ፣ ፲)

፷፱. በተከፈከፈው ፀጉርሽ ጥቁረቱም የሐር ነዶ በሚመስለው የኪሩቤልም ክንፍ በሚጋርደው እንደ ሉል እንደ በረድ በሚነጣው ወተትም የፈሰሰበት በሚመስለው ጥርስሽ፡፡ እንደ ሰሌን እንደ ዝግባ በሚመስለው ቁመትሽ እማልዳለሁ፡፡

፸. በቅድስናሽ ልብስ በድንግልናሽ መጎናጸፊያ የወይን ሐረግ በተሳበበት ወርቅ በተጠለፈበት ባባትሽ በዳዊት ወገን የእስራኤል ደናግል እንዲህ ይለብሳሉና አባቶችሽ ባለበሱሽ ልብስ እማፀናለሁ፡፡

፸፩. ከሽቱ ሁሉ በሚበልጥ በልብስሽ ሽታ፡፡ ከምድረ በዳ አበባ ይልቅ ዕፁብ ድንቅ ሽታ በሚሸት ባፍሽ ትንፋሽ፡፡ ከማር ወለላም በሚጣፍጠው አፍሽ ለዓለም ሁሉ ፈብ ጥቅም የሆንሽቱን የተባረክሽቱን ፍሬ አንቺን ባፈሩ ባባትሽ በኢያቄም ጉልበት በእናትሽም በሐና ማኅፀን እማልዳለሁ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፴፪. በከደነሽ በእግዚአብሔር ጥላ የልጁም ማደሪያ ትሆኚ ዘንድ ባፀናሽ በጋረደሽም በመንፈስ ቅዱስ ክንፍ የወልድ ማደሪያ ልትሆኚ ባነጻሽ ባለመለወጥ ባለመመለስ ቃል ካንቺ በመወለዱ እማልዳለሁ፡፡ (ሉቃ ፩ ፣ ፴፭)

፴፫. የድንግልናሽ ማሠሪያ ሳይቆረጽ ካንቺ በመወለዱ በኋል በመጣሉ በጨርቅ በመጠቅለሉ በጎንሽ እርሱን በተሸከምሽበት በጀርባሽ ባዘልሽበት እስከ ጉልምስና በሰው መጠን ለመሆን እስከ ደረሰ ድረስ ጥቂት ጥቂት እያለ በማደጉ እማልዳለሁ፡፡

፴፬. በዘካርያስ ልጅ በዮሐንስ እጅ በመጠመቁ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ በመሰከረለት በአብ በነጭ ርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ በተቀመጠበት መንፈስ ቅዱስ እማፀናለሁ፡፡ (ማቴ ፫ ፣ ፲፮ - ፲፯) (ኢሳ ፵፪ ፣ ፩)

፴፭. ወይናቸው አልቆ ነበርና ወይን የላቸውም ባልሽው ጊዜ ውሀውን ወይን ባደረገው ከርሱም በወጣው ኃይል አጋንንትን ባራቀበት ድውያንን ደዌያቸው ልዩ ልዩ የሆነውን ባዳነበት እማፀናለሁ፡፡ እንዲሁም እኔ ሕይወትን ከእርሱ እሻለሁ፡፡ በደዌ ኃጢአት ተጨንቄአለሁና፡፡ (ማቴ ፬ ፣ ፳፬) (ዮሐ ፪ ፣ ፫ ፣ ፰)

፴፮. ዘለምጽን ዳን ፈቅጃለሁ ንጻ ብሎ ባነጻው በእርሱ ኃይል እማፀናለሁ፡፡ እኔ ደግሞ ከርሱ ዘንድ ከነፍሴና ከሥጋዬ ርኩሰት መንጻትን እሻለሁ፡፡ መጻጉዕን በቤተ ሳይዳ መጠመቂያ በተገናኘው ጊዜ ባዳነው ኃይል እማፀናለሁ፡፡ እኔም እንዲሁ ከሱ ዘንድ በጎ ሥራን ለመሥራት በመድከም ልምሾ የሆነውን ልቡናዬ እንክስና ያረታልኝ ዘንድ እፈቅዳለሁ፡፡ (ማቴ ፰ ፣ ፫) (ዮሐ ፭ ፣ ፲፭)

፴፯. የዕውራንን ዓይን ባበራበት ኃይል እማፀናለሁ፡፡ እኔም ደግሞ እውነተኛውን የጽድቅ ብርሃንን እንዳይ በኃጢአት የጨለመውን ዓይነ ልቡናዬን ያበራልኝ ዘንድ እፈቅዳለሁ፡፡ (ማቴ ፱ ፣ ፳፯-፴)

፴፰. ለብዙዎች ቤዛ በኃጥአን እጅ እንደ ሌባ በመያዙ እንደ ሌባም እጅ እግሩን በመታሠሩ እማፀናለሁ፡፡ እኔ ከኃጢአት ማሠሪያ እፈታ ዘንድ ከርሱ እሻለሁ፡፡ (ማቴ ፳፯ ፣ ፪)

፴፱. በሊቀ ካህናቱም እንደ ባሪያ በጥፊ መመታቱ በጭፍሮችም እጅ በጲላጦስ ፊት በመገረፉ እማፀናለሁ፡፡ እኔም ከርሱ ዘንድ እሻለሁ፡፡ ከወዲህና ከወዲህኛው መቅሠፍት እድን ዘንድ ነው፡፡ (ዮሐ ፲፰ ፣ ፳፪)

፵. በእግሮቹና በእጆቹ መቸንከር እማፀናለሁ፡፡ እኔም ደግሞ እጆቼን ከቅሚያ እግሮቼንም ከመሰናከል ያድንልሽ ዘንድ እሻለሁ፡፡

፵፩. በመስቀል ላይ ራሱን ዘንበል አድርጎ ወዳንቺና ወደ ዮሐንስ በመመልከቱ ዮሐንስን የነጎድጓድ ልጅ አደራ በማለቱ እንዲህ ሲል፡፡ አንተ ሆር እርሷ እናትህ ናት፡፡ አንቺ ሆይ እርሱ ልጅሽ ነው፡፡ እኔም ከርሱ እሻለሁ ባንቺ አደራ ይሰጠሽ ዘንድ እንዲህ ሲል ልጅሽ በደሙ የዋጀው ባሪያ ነው፡፡ እኔንም እንዲህ ይለኝ ዘንድ ከናትህ ከሔዋን ባሕርይ የተገኘች እናትህ እመቤት ናት፡፡ (ዮሐ ፲፱ ፣ ፳፮ ፣ ፴)

፵፪. ከርቤ የተቀላቀለውን መጻጻ ከሐሞት ጋራ በጠጣው አፉ እማፀናለሁ፡፡ ለኔም ደግሞ ጥበብ የሚያናግረውን ዕውቀት የሚገልጸውን ንጽሕና ቅድስና የሚያስተምረውን የደስታና የኃሤት ጽዋ ያጠጣኝ ዘንድ ከርሱ እፈቅዳለሁ፡፡ (መዝ ፷፱ ፣ ፳፩) (ማቴ ፳፯ ፣ ፵፰) (ዮሐ ፲፱ ፣ ፳፰)

፵፫. ነፍሱን ከሥጋው በመለየቷ ነፍሱም የጻድቃን ነፍስ ነፃ ለማውጣት ወደ ሲኦል በመውረዱ እማፀናለሁ፡፡ እኔንም ከኃጢአት ቀምበር ነፃ ያደርገኝ ዘንድ ከርሱ ዘንድ እሻለሁ፡፡ (ዮሐ ፣፲፱ ፣፴)

፵፬. በድርብ በፍታ ተጠቅሎ ከመቃብር ውስጥ ገብቶ ሳይንቀሳቀስ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት

በተቀመጠ ሥጋው እማፀናለሁ፡፡ እኔም ለመውጣት ከማይቻል መዝጊያ ከተቆለፈ ከሲኦል ጉድጓድ እድን ዘንድ እፈቅዳለሁ፡፡ (ማቴ ፳፭ ፣ ፵፩-፵፮)

፵፭. ዓለምን ሁሉ በሚያድን ትንሣኤው እማፀናለሁ፡፡ እኔንም ከመውደቅ ያነሣኝ ዘንድ ከመቀጥቀጥ ልምሾም ከመሆን ያድነኝ ዘንድ እፈቅዳለሁ፡፡

፵፮. ትጉሃን መላእክተ ሰማይ እያመሰገኑት ወደ ሰማይ በማረጉ በአባቱም በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በመቀመጡ እማፀናለሁ፡፡ ለኔም ደግሞ በቀኝ መቆምን ቅዱሳንም በሚገቡበት ስፍራ ሰማያዊ ርስትን ይከፍለኝ ዘንድ ከርሱ ዘንድ እፈቅዳለሁ፡፡ (ማር ፲፮ ፣ ፲፱)

፵፯. ያልተገባሁም በመሆኔ ከልጅሽ ከወዳጅሽ ሠርግ የተለየሁ እንዳልሆን ባንቺ እማፀናለሁ፡፡ ወደ ልጅሽ ሠርግ በዓልም ለመግባት ዝግጁ አድርጊኝ፡፡ ይህንንም በመመኘቴ በፍርድ ይገባኛል ብዬ አይደለም፡፡ ባንቺ ጸሎት የልጅሽንም ምሕረቱን ተሰፋ በማድረግ ነው እንጂ፡፡

፵፰. ለኃጢአቴ አለቅስላታለሁ አዝንማለሁ፡፡ የተሰጠኝን የሙሽርነት ልብስ የኸውም የጥምቀት ድርብ በፍታ እርሱን ስላሳደፍኩ፡፡ ለኃጢአቴ አለቅስላታለሁ፡፡ ፈጣሪየን ስለበደልሁ ብዙ ጊዜ ስላመነዘርኩ ስለኔም የተሠራውን ሕግ ስላጎደልኩ፡፡ ትእዛዝ መጠበቅም ከኔ ዘንድ ስለ ጠፋ አዝናለሁ፡፡

፵፱. ለኃጢአቴ አለቅስላታለሁ ኃሣርን ኀስቁልናን ስለ አለበሰችኝ ደስ መሰኘትን ያይደለ ፊት ማጥቆርን እንደ ልብስ ስለ አደረገችልኝ፡፡ አዝናለሁ ወዮልኝ ወዮታ አለብኝ ሕጉን ትእዛዙን ስለ አልጠበቅሁ ኋላም ንስሐ ስለ አልገባሁ፡፡

፶. ወዮልኝ የሠርግ ልብስ ስላልለበስሁ ወደ ሠርግ ማን ያስገባኛል፡፡ የንጉሡንም መክሊት ስለ አላተረፍኩ ወዮልኝ እፅፍ ድርብ ስለ አልሆነው መክሊቱ ጌታዬ በተቆጣጠረኝ ጊዜ ምን እመልሳለሁ፡፡

፶፩. የመብራት ቅቤን ስለ አላዘጋጀሁ ወዮልኝ የሙሽራው ቤት ደጅ ይዘጋብኛል ብዬ አዝናለሁ እፈራለሁ በሠርጉ ቤት ሰዎች ሥረዓት አልተዘጋጀሁምና እስኪመሽ ድረስ በጽርዓት ስለ ቆየሁ ወዮልኝ ከነገህ እስከ ሠርክ ላገለገሉት ጌታዬ ዋጋቸውን በሰጣቸው ጊዜ ኃፍረት በኔ ነው፡፡ ከጌታዬ ወይን ስፍራ አላገለገልሁምና፡፡

፶፪. ካባቴ የተሰጠኝን ገንዘብ አለል ዘለል በማለቴ ለተቸገርሁ ለኔ ወዮልኝ፡፡ እንደ ኀስቋላውም ልጅ ከሩቅ አገር ሔዶ እርያ ከሚመገበው ዐሠር ቆሞ ሲመገብ እንደ ወደደው ሆንሁ፡፡ (ሉቃ ፲፭ ፣ ፲፩-፲፮)

፶፫. ለኔ የተሰጠኝን መልክ ትቼ ለኔ ያልሆነውን ጥቁረት ለተቀበልሁ ለኔ ወዮልኝ፡፡ የሰውነቴን ርኩሰት አጽብበት ነቅዓ አንብዕ ለሌለኝ ኃጢአቴም የሚሠረይበት የንስሐ ትጋት ለሌለኝ ለኔ ወዮልኝ ነገር ግን ነፍሴ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትፈቅዳለች ሥጋዊ ፈቃድ ያቸንፋታል እንጂ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፬</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ በጎውን ሥራ ለመሥራት የሚያበረታታውን የቅድስና መንፈስ ይልክልኝ ዘንድ ልጅሽን ለምኝልኝ፡፡

፪. ይኸውም የኃይል መንፈስ ከኪሩቤል ሠረገላ ላይ ይዝለል፡፡ የብርሃኑንም ድንኳን ይገለጽ የእሳቱንም መጋረጃ ይጠቅልል፡፡ የሰማዩን ደጅ ከፍቶ ከጽርሐ አርአያም ወርዶ በራሴ ላይ ይቀመጥ፡፡

፫. ነፍሴን አንጽቶ ሥጋዬን ቀድሶ ለርሱ ማደሪያ ያድርገኝ፡፡ ልቡናዬም እግዚአብሔርን ደስ

ከሚያሰኘው ነገር ሁሉ ማናቸውንም ለመሥራት ቢፈቅድ ይህ የጰራቅሊጦስ የጽድቅ መንፈስ ወደርሱ ይማርከኝ፡፡

፬. የስሕተቱን መንፈስ በላዬ አያሰልጥነው አንዲት ሰዓት ስንኳን ነኔ ላይ ያርፍ ዘንድ አይተወው ለበጎ ነገር የሚያበረታታ ይህ የቅድስና መንፈስ ግን በልቡናዬ ይዋሐድ ለዘወትርም ከኔ አይለይ፡፡

፭. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ አንቺ ደግሞ ስለ ኃጢአቴ ሥርየት የተጋሽ ሁኚ በኃጢአቴም ቁስል የልጅሽን መድኃኒት ጨምሪ ከልጅሽም ጎን በፈሰሰው የመረጨት ውህ ርኩሰቴን እጸቢው ዝገቴንም ወልውዪው፡፡

፮. ማኅተሜንም የአምላካዊ ምሥጢሩንም ደም አድርጊልኝ ከልጅሽም ዓሥራት አድርገሽ ውሰጅኝ በጅሽ የተጨበጥሁ በእግርሽ የተረገጥሁ እድል ፈንታሽ እሆን ዘንድ የሰውም ሠራተኛ ወዳልሠራው ወደ ሰማያዊ ሠርግ ቤት እንድገባ ዝግጁ አድርጊኝ፡፡

፯. የኔን ደግሞ እድል ፈንታዬን ጽዋ ተርታዬን የሚያንጸባርቀውን የብርሃን አክሊል አበባ የፈነዳነትን አረግ የተሳበበትን የሃይማኖት መጎናፀፊያ አድረጊልኝ፡፡

፰. በሠርግ ቤትሽም ተሸልሜ ልገኝ፡፡ ለልጅሽም ሠርግ ተሸልሜ ልታይ፡፡ በቅዱሳን ጉባዔ መሀከልም ደስ ብሎኝ ልኑር፡፡ ዋጋዬም ከርሳቸው ያነሰች የጎደለች አትሁን፡፡

፱. ዋጋውን ግን በራሴ ትሩፋት አልሻም መመስገንም በኔ በጎ ሥራ አልፈልግም ዋጋዬ ያንቺ ዋጋ ምስጋናዬም ያንቺ ምስጋና ነው እንጂ እኔ በጸሎትሽ ዋጋ ልቀበል እፈቅዳለሁ በኃጥእት ነፍሴ ላይም የጽድቅሽን ምስጋና ልሸከም፡፡ መጽደቅ በሃይማኖት ትሩፋትን ፈጽሞ ሳይሠሩ መጽደቅ በልጅሽ ፈቃድ ነውና፡፡

፲. ዳዊት በመዝሙር እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ ኃጢአታቸው የተሠረየላቸው እዳ በደላቸውንም እግዚአብሔር ያልቆጠረባቸው የተመሰገኑ ናቸው፡፡ ኃጢአቱንም እግዚአብሔር ያልቆጠረበት የተደነቀ ነው፡፡ (መዝሙር ፴፪ ፣ ፩)

፲፩. እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለው፡፡ እኔ የሰውን ኃጢአት ያባቱን በልጁ በልጅ ልጁ እስከ ሦስት እስከ አራት ትውልድ ድረስ እመራመራለሁ ኃጢአተኛውንም ንጹሕ አላደርገውም የማርሁትን እምረዋለሁ የወደድሁትንም ይቅር እለዋለሁ፡፡ ዘኁልቁ ፲፬ ፣ ፲፰

፲፪. ስለዚህም የጥበብ ነቅዕ የሚሆን ጳውሎስ  እንዲህ አለ እንግዲህ ምሕረቱን እዩ መጨከኑንም ተመልከቱ የወደደውን ይምራል ያልወደደውንም ያስጨንቃል፡፡

፲፫. እኔም ደግሞ ስለዚህ ጸሎትሽን በመታመን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በድንግልናሽም ከኃጢአት መዳነን እፈቅዳለሁ፡፡ ነገር ግን አንቺ ለምኚልኝ ዕድል ፋንታዬ ይቅር ካላቸው ጋራ ይሁን እንጂ ካስጨነቃቸው ጋራ እንዳይሆን አማልጅኝ፡፡

፲፬. ይህንንም ተስፋ አድርጌ ቸር ይቅር ባይ ወደሆነው ልጅሽ እጮኻለሁ፡፡ እንዲህ ስል ይቅርታህና ቸርነትህን ጽድቅህም ዘወትር ያግኙኝ፡፡ ደግሞ እንዲህ እላለሁ፡፡ ስለ ቸርነትህና ስለ ፍርድህ እቀኛለሁ፡፡ ላንተም አቤቱ ዝማሬ አቀርባለሁ፡፡ (መዝ ፶ ፣ ፲፩)

፲፭. ደግሞ እንዲህ እላለሁ፡፡ አቤቱ ለዘለዓለም ቸርነትህን አመሰግናለሁ ጽድቅህን በአፌ ለልጅ ልጂ እናገራለሁ፡፡ (መዝሙር ፹፱ ፣ ፩)

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፲፮. ዳግመኛም እንዲህ እላለሁ አቤቱ አንተ ቸር ይቅር ባይ ነህና ይቅርታህም አንተን ለሚጠሩ ሁሉ ብዙ ነው፡፡ ደግሞም እንዲህ እላለሁ ምሕረትህን እታመነዋለሁ በጎ ሥራህ በቅዱሳን ፊት መልካም ነውና፡፡ (መዝ ፺፪ ፣ ፱)

፲፯.የርሳቸው ግን በገድላቸው ነው የኔ ደግሞ በናትህ ጸሎት ነው የርሳቸው በድካማቸው ነው፡፡ የኔ ግን በናትህ ድካም በመራቧ በመጸማቷ ስለ አገኛትም መከራ ካንተም ጋራ በምድረ ግብጽ በተሰደደች ጊዜ ስለደረሰባት ችግር ነው፡፡

፲፰. እርሳቸው በትጋታቸው ነው እኔ ግን አንተን በተሸከመች ቅድስት ድንግል ልመና ባማለጅነቷም ነው፡፡ እርሳቸው በርሳቸው ንጽሕና ነው፡፡ እኔ ግን በዕብራይስጥ ማሪሃም በተባለች የኃጢአትም ቀምበር ባልተጫነባት ንጽሕት ጥጃ በተባለች ድንግል ማርያም በንጽህናዋ በቅድስናዋ ነው፡፡

፲፱. የኃጢአቴ ሸክም ሚዛን መክበዱ ከሰማይና ከምድር ክብደት ይበረታል፡፡ ከርሱ ደግሞ የምሕረትህ ሚዛን ይደፋል፡፡ አቤቱ ኃጢአቴ ከሰማይ ኮከብ ከባሕር አሸዋ ይበዛል፡፡ ከርሱም ደግሞ ቸርነትህ ይበዛል፡፡

፳. አቤቱ ሆይ በኔ ያደረችውን ኃጢአት ቸርነትህ ያቸንፋት፡፡ ይቅርታህም ከበደሌ ይበርታ የምሕረትህም ዝናም የዕዳ በደሌን ደብዳቤ ይደምስሰው፡፡ የማዳንህም ቃይል በኔ ላይ ይገለጽ፡፡

፳፩. ለቤተ መቅደስህ ተክል ያደረግኸኝ፡፡ አቤቱ ሆይ የውጭ ተክል አታርገኝ፡፡ የጽድቅ ተክል አድርገኝ፡፡ የኃጢአት አይደለም፡፡ የዕውነት ተክል አድርገኝ የሐሰት አይደለም የፍቅር ተክል አድርገኝ የጽል አይደለም፡፡

፳፪. የበረከት ተክል አድርገኝ የመርገም አይደለም የክብር ተክል አድርገኝ የኃሣር የጎስቁልና አይደለም የሕይወት ተክል አድርገኝ የጥፋት አይደለም፡፡ ያንተ ተክል አድርገኝ የሰይጣን አይደለም የቅዱሳን ቅድስት የክል በነቢያት ትንቢት ካፊያ የምለመልም አድርገኝ፡፡

፳፫. የመጻሕፍት መጀመሪያ የምትሆን ኦሪት ደመና የምትጋርደኝ፡፡ ከቅዱስ ወንጌል ፈሳሽ የምጠጣ ከጎንህ ከፈሰሰው ደም የምረካ ልሁን፡፡ በናትህ በድንግል ጸሎት የሃይማኖት አበባ ላብብ፡፡ የጽድቅ ፍሬን ላፍራ ከቅዱሳንህ ሐዋርያትም ከቃላቸው ፍሬ የተነሣ እስከ ዘለዓለሙ ድረስ የተባረከ የወይን ቦታ ልባል የጽድቅን ፍሬ የሚያስቀረውንም የኃጢአት እሾህ ጠምዝዘው ከደጁም አሜከላውን አረሙንም ሙጃውንም ንቀለው፡፡ አቤቱ ከኔም አርቀው ሥርዓትህን የሚሠሩትን ያበባቸውን ፍጻሜ እንዳፈራ አድርገኝ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፳</u>

፩. በዕብራይስጥ መሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ጌጤ ሽልማቴ ሆይ ክብሬ ገናንነቴ ለችግሬ ሀብት ባለጸግነት ለልምሾነቴም ብርታት ነሽ፡፡

፪. የክብሬ አክሊል የወገኖቼ መመኪያ ሆይ በፍቅርሽ ወጥመድ በመውደድሽም አሽክላ ሰወነቴ የተያዘ ነው፡፡ በብረከ ልቡናዬ ላንቺ እሰግዳለሁ በፍጹም ልቡናዬም ወደአንቺ እጮሃለሁ በችግሬ ጊዜ በፊትሽ እማለላለሁ፡፡

፫. ለሆድሽም ፍሬ ይቅርታ መውረድ ዓይኖቼ ይንጋጥጣሉ፡፡ አንቺንም ለማመስገን አንደበቴ ይቸኩላል ለውዳሴሽም ከንፈሮቼ ደስ ይሰኛሉ ለዘፈንሽም የቃሌ አመላለስ ያማረ የተወደደ ነው እጆቼም በመተባበር ያጨበጭባሉ፡፡

፬. እግሮቼም በፈቃዳቸው ያሸበሽባሉ፡፡ ሕዋሳቴም ሁሉ ላንቺ ይገዛሉ ፍቅርሽ በልቡናዬ ውስጥ በቅሏልና ሥሩም እስከ መሔጃዬ ወጥቷልና፡፡ ጫፉም እስከ ራሴ ድረስ ረዘመ የምስጋናሽም አበባ በአፌ ውስጥ ነው፡፡

፭. አሁንም ስለኔ ለምኚልኝ ከዚህ ዓለም ሁሉ ጥፋት ከመከራውም ሁሉ በጎውን ሥራም ከሚቃወመውም የሰይጣን ወጥመድ እድን ዘንድ የሚያስጸይፈውንም ነገር ሁሉ ከኔ አርቂው፡፡

፮. ለበጎ ሥራና ለትሩፋትም የነቃሁ አድርጊኝ ለጸሎትም የተጋሁ፡፡ ጸላትም ስንፍናውን በላዩ ባፈሰሰው ጊዜ የልጅሽ የመለኮትነቱ ፍቅር ያንቃኝ፡፡ ለምስጋናውም የተጋሁ ያድርገኝ ቸርነቱንም ያለማቋረጽ ላመስግን፡፡

፯. አንቺም ደግሞ ስለ ኃጢአቴ ቸል አትበይኝ የከንፈሮቼንም የምልጃ ቃል አንቺ እሺ በጎ ብለሽ ልጅሽን እሺ በጎ አሰኚልኝ፡፡ የግድ በዪው እመቤቴ ሆይ የከንፈሮቼን ጸሎት እንዲቀበል፡፡

፰. ጸሎቴም በጭንጫ ላይ እንደተዘራች ዘር ሳትበቅል ሳታብብ ሳታፈራ እንዳትቀር አትሁን፡፡ ካቸናፊ እግዚአብሔር ጆሮ ገብታ የልቤንም ግዳጅ ከርሱ ዘንድ ፈጽማ ትመለስ፡፡ ምኞቴንም በማግኘት ደስ ታሰኘኝ፡፡

## ምዕራፍ ፯

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ከጸሎትሽ ረዳትነት በቀር ሊረዳኝ የሚችል እንደሌለ ዐወቅሁ፡፡ ከልመናሽም በቀር የሚያድን እንደሌለ ያለበኩርሽም የሚበጀሽ እንደሌለ ዐወቅሁ፡፡

፪. ድንግል ሆይ ከምልጃሽ በቀር ሊጠብቀኝ የሚችል እንደሌለ ዐወቅሁ ያለ ማኅጸንሽም ፍሬ ሊራራልኝ የሚችል እንደሌለ ይህንንም ዐውቄ ወዳንቺ ተጠቃሁ በልጅሽም አመልሁ እርሱንም አመለክሁ ቸርነቱንም ተስፋ አደረግሁ፡፡

፫. በዚህ ሳለሁም ብበድል ይቅር ይበለኝ ብሰናከልም በርሱ ልደገፍ ብወድቅም ልነሣ ወደጨለማም ብሄድ እግዚአብሔር ያብራልኝ እሱ ለሕይወቴ የታመነ ነውና፡፡ (መዝ ፳፯ ፣ ፩)

፬. እግዚአብሔር ረዳቴ ነው የምስጋናዬም ዘመን ነው፡፡ ድንግል ሆይ ባንቺ ተጠግቼ የልጅሽንም ቸርነቱን አምኜ ሳለሁ የብረት ጥሩር እንደለበሰ አርበኛ ደንጊያም እንዳያገኘው በራሱ ላይ የመድኃኒት የሕይወት ጋሻ እንደመከተ ነኝ፡፡

፭. ድንግል ሆይ በጦርነት ጊዜ መመከቻ ጋሻዬ ነሽ በፀብ ክርክርም ጊዜ መሠወሪያዬ በጉባዔም መሐከል ግርማ ሞገሴ በጸላትም አገር የመድሃኒት አምባ ኮረብታ ነሽ፡፡ የመለኮትን ዕንቁ የምትሸከሚ የወርቅ ሣጽኔ ነሽ፡፡

፮. ለሰማያዊ ሠርግ የሚረባ የሚጠቅመውን የክብር ገንዘብ ለመግዛት በየደሴቱ ሁሉ የምሻገርብሽ መርከብ ድንግል ሆይ ውዳሴሽን ለመናገር አፌን ክፈች በውስጡም የልጅሽን የወዳጅሽን ምስጋና ሙዪው፡፡

፯. ከቅንድቤም የስንፍናውን ዕንቅልፍ ካይኖቼም የከበደውን መኝታ ሥጋ የለበሰውን ፍጥረት ሁሉ ነፈስ የተዋሐደውን ሁሉ መንቀሳቀስ እንደማይችል የሚያደርገውን አርቂልኝ የዚህንም ዓለም አለል ዘለል ማለት አርቂልኝ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፰. ብተኛም እንቅልፌ ልክ መጠን ያለው ይሁን ያንቺም ምስጋና የማስታጉል አያድርገኝ በመኝታዬም ደግሞ ጠብቂኝ ርኩሳን መናፍስት እንዳይሰለጥኑብኝ በክፉ ሕልምም እንዳይጣሉኝ ጠብቂኝ፡፡

፱. ከነቃሁም በኋላ የዚህ ዓለም ሥጋዊ ፈቃድ ልቡናዬን ጨልጦ እንዳይወስደው ጠብቂኝ፡፡ የሰውን ጉልምስና እንደ ሪያ የተሰበደበደ በሚያደርገው በዝሙት ምክንያት ቢሆን፡፡

፲. በፍቅረ ነዋይም በተድላ በደስታም ቢሆን በሚያስት ባለጸግነትም ይኸውም የኃጢአት እሾህ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያንቀው አጫንቆም የሚይዘው ያፈራም ዘንድ የማይተወው በርሱ ምክንያት ቢሆን እንዳያታልለኝ ጠብቂኝ፡፡ (ማቴ ፲፫ ፣ ፳፪) (፩ ጢሞ ፮ ፣ ፱)

፲፩. የልጅሽ የባሕርይ ሕይወቱ የጽድቅ መንፈስ ጰራቅሊጦስ ግን በሥጋዬና በነፍሴ የሚበራ ይሁን ለሰይጣንም ወደኔ የሚገባበት ምክንያት አይስጠው፡፡

፲፪. በከንፈርም ከነገር ጋራ ቢሆን በሐሜትም ቢሆን በአፍም ቢሆን በጥርስም ከሣቅ ከጨዋታና ከተድላ ደስታ ጋራ ባይንም ከማየት ከማመንዝርም ጋራ በጆሮም ነገረ ዘርቅ የሐሰት ነገር ከመስማት ጋራ ቢሆን፡፡

፲፫. በልቡናም ካመፅና ከሽንገላ ጋራ ባሳብም ከቂምና ከቅንዓት ጋራ ቢሆን በእጅም ከቅሚያ ጋራ በእግርም ደም ለማፈሰስ ከመሮጽ ጋራ ቢሆን፡፡

፲፬. ባፍንጫም የሴቶችን ሽቱ ሽታ ከማሽተት ይኸውም የጎልማሶችን ለቡና የሚማርክ በሰውነት ባህርይም በሚሆን በሥጋዊ ፈቃድ በሰውነት እሳት ከሚያፈስ ምኞት ጋርም ቢሆን፡፡ ይህ የስሕተት መንፈስ እኔን ወደርሱ የሚነግልበት ምክንያት አያግኝ፡፡

፲፭. የልጅሽ መንፈስ ግን ማደሪያ ያድርገኝ በውስጤም ይግባ በላዬም ይረፍ አንቺንም ለማመስገን ዝግጁዎች ይሆኑ ዘንድ ከንፈሮቼን ይቀድሳቸው ድንግል ሆይ ከኃጥእ ሰው ምስጋና ለምኔ ነው አትበዩ ንጽሕናሽን የኔ ርኩሰት አያረክሰውምና፡፡

፲፮. ማመንዘሬም ቅድስናሽን አያረክሰውም አያስነቅፈውም ድንግልናሽም ስለ ማመንዘሬ በርኩሰቴ የሚሆንብኝ እዳ በደል የሚከፍለኝ ይሁን ድኩም በጽኑ እንዲድን ኃጥእ በጸሎትሽ ይጸድቃልና፡፡

## ምዕራፍ ፰

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ለምስጋናሽ አፌን በከፈትኩ ጊዜ ከልጅሽ ከወዳጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ በረድኤት ወደኔ ነዪ፡፡

፪. እኔ በለመንሁ ጊዜ አንቺ አማላጅ ልጅሽ ደግሞ ኃጢአቴን ያቅልል፡፡ እኔም በጸለይሁ ጊዜ አንቺ ለኔ ሥረየት ለምኚ ልጅሽ ደግሞ ይቅር ይበለሽ፡፡ ለመለመንም እኔ ልጅሽ ለምኝ ልጅሽም ስላንቺ ልመናዬን ይቀበል፡፡

፫. ድንግል ሆይ የሱራፌል የዕጣ ናቸው ጽንሐሕ የኪሩቤልም የምስጋና መቅጃ የወርቅ መጥለቂያ የትጉሃን የሰማይ መላእክት ሁሉ የቅዳሴያቸው ነቅዕ፡፡ የማይተኙትም የውዳሴያቸው ፈልፈል ምንጭ፡፡

፬. ድንግል ሆይ ያልበደሉት የድንግልናቸው መመኪያ ያላደፉትም የንጽሕናቸው አክሊል ድንግል ሆይየሚጋደሉት የመታገሣቸው ዋጋ የመድኃኒታችንንም የመስቀሉን ቀምበር ለሚሸከሙ የቅድስናቸው አስብ፡፡

፭. ድንግል ሆይ ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ መስታወት ያዩሽ የትንቢት ኃይል የልዑል እግዚአብሔርን ወንጌል ያስተማሩ ሐዋርያት ምስጋና ወሬ፡፡

፮. ድንግል ሆይ የእግዚአብሔር እጅ የተከለሽ የገነት ዛፍ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያሳበባት የአብም ጥላ ከፍሬ ያደረሳት፡፡

፯. ኪሩቤል በክንፍ የሚጋርዱሽ በታቦት ላይ የምትሆኝ ምስሃል ድንግል ሆይ የጥበብ መነፈስ በተመሉ ባስልኤልና ኤልያብ እጅ የተሠራሽ፡፡ (ዘፀአ ፴፩ ፣ ፪ ፣ ፫ ፣ ፮)

፰. ጠልን የተመላሽ የዮኤሳ ልጅ የጌድዎን መንቀል፡፡ እንደ እሳትም የምትሆኚ የኔርዮ ልጅ የምስጋና ጽዋ ድንግል ሆይ በማኑሔም ልጅ እጅ ከአንበሳ አፍ የተቀዳሽ ማር ወለላ ድንግል በራሱም ፀጉር የነበርሽ ኃይል፡፡ (መሳ፮ ፣ ፴፰ ፣ ፲፩ ፣ ፰ ፣ ፱)

፱. የአካዝ ልጅ የዕድሜው መጨመሪያ ደንግል ሆይ ለምልክትም ፀሐይ እስከ ዐሥሩ መዓረግ የተመለሰብሽ ዳግም የልጁ የኃጢአቱ ማስተስረያ ያውም ልጁን ለጣዖት በሠዋ ጊዜ፡፡ (፪ ዜና ፴፪ ፣ ጽ፱) (፪ ነገ ፳ ፣ ፲፩ ፣) (ኢሳ ፴፰ ፣ ፯ ፣ ፰)

፲. የቀዓት ልጆች የክህነታቸው ልብስ ድንግል ሆይ የቆሬም ልጆች መዝፈኛ የማመስገኛ ዕቃ ድንግል የሌዋውያንም የመሥሪያቸው ዕቃ ደም መርጫ ዕብራውያንን የመራሽ ሥረጉት ደመና፡፡ (ዘኁል ፬ ፣ ፲፭ ፣ ፱ ፣ ፳፩ ፣ ፲፱ ፣ ፲፰)

፲፩. ድንግል ሆይ የትንቢት ቡቃያ የኢየሩሳሌም የይሁዳ ቡቃያ ቤተልሔማዊት የገሊላ ልጅ የእስራኤል ድንግል፡፡

፲፪. ድንግል ሆይ የያዕቆብ ልጅ በሥጋ የአሕዛብ የሀብት መመኪያ ድንግል ሆይ በመወለድ የዳዊት ልጅ በሃይማኖት የአሕዛብ እናተ ድንግል በአምልኮታቸው የሚመኩ ወገኖች አክሊላቸው በወገን ለሚመኩ ወገኖች ልጃቸው፡፡

፲፫. ድንግል ሆይ የእስራኤል ቤት ተክል የይሁዳ ቡቃያ ከዳዊት ግንድ የወይን ሐረግ ለምልመሽ አብበሽ የተገኘሽ እኛም ደግሞ በድንግልናሽ አበባ ተሻተን ከንጽሕናሽም ፍሬ በላን፡፡

፲፬. በጥላሽ ዐረፍን እንግዲህ ግን ባንቺ እንድንድን ዐወቅን፡፡ በልጅሽ በወዳጅሽም በሥጋውና በደሙ ቁርባን እንድናለን በኦሪት እንዲህ የሚል ተጽፏልና የመሥዋዕቱ ደም ሁሉ የነካው ቅዱስ ነው፡፡

፲፭. እኛም ደግሞ በልጅሽ ደም ተቀደስን በበኩርሽም በጎኑ ፈሳሽ ንጹሓን ሆንን ድንግል ሆይ አንቺ እጅሽን በራሴ ላይ ጫኝ ቀኝሽንም በመሀከል ራሴ ላይ አኑሪው፡፡

፲፮. ቁርባኔም በፊትሽ በልጅሽም በዐማኑኤል ፊት ያማረ የተወደደ ልጅሽ የተቀበለው ይሁን በባሕርይ አባቱም በአብ ባሕርይ በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈሰ ቅዱስ ፊት ያማረ የተወደደ ኃጢአቴን የሚያቃልል ዕዳ በደሌንም የሚደመስስ ለደከሙትም ሸክማቸው ለከበደ ብርታተ ዕረፍትም ይሁን፡፡

፲፯. ድንግል ሆይ ለነገሥታት ክብር ጌትነት ገናንነት ለመሃይናን ብርሃን የክብር አዘቅት የበረከት ምንጭ ሆይ ስለኔ ወደ ልጅሽ ማልጅ በሰማይ በምድር በረከት እንዲባርከኝ፡፡

፲፰. በነቢያትና በሐዋርያት በረከት በቅዱሳንም ሁሉ በረከት እንዲባርከኝ ከልጅሽ በረከት እሻለሁ፡፡ ያዕቆብ ዮሴፈን ልጁን እንደባረከው እንዲህ ሲል በተስማሙት በተራሮች በኮረብቶች በረከት በልዑል እግዚአብሔር መላእክት በረከት በጡት በማኅፀን በረከት ባባትህ በፀናችው እናትህ በረከት፡፡

፺፱. እኔም ደግሞ ከልጅሽ አንደበት ፈጽሜ በረከት እሻለሁ፡፡ እርሱ የባረከውን ሊረግም የሚችል የለምና የቢኦር ልጅ ባላቅም እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡

፻. ባላቅ የሶፎ ልጅ ከመስጴጦምያ ጸራኝ እንዲህ አለኝ ና የያዕቆብን ዘር እርገምልኝ እስራኤልን ስደባቸው አለኝ፡፡ ምን እሰድባለሁ እግዚአብሔር ያልሰደበውን ምንስ እረግማለሁ እግዚአብሔር ያልረገመውን ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል፡፡ (ዘኍ ፳፫ ፣ ፯ ፣ ፰)

፻፩. በተራሮች ራስ አደርገዋለሁና በከረፍቶችም አስተውለዋለሁና እነሆ ለብቻው የሚያድር ሕዝብ ነው ከአሕዛብም ጋራ አይቆጠርም እግዚአብሔርም አምላኩ ከርሱ ነው፡፡ (ዘኍል ፳፫ ፣ ፱)

፻፪. እስራኤል ለእግዚአብሔር እንደተለየ ለዓለም ሁሉ ንጉሥ ዓሥራት እንደተነሣ እንዲሁ ደግሞ እኔን ለልጅሽ የተለየሁ አድርጊኝ ለአምልኮቱም ዕድል ፈንታ ልሁን አንቺም ዓሥራት አደርገሽ ውሰጅኝ ለምስጋናሽም አገልጋይ ልሁን ባሪያሽም ልባል፡፡

፻፫. ባርነቴን ላንቺ በመስጠት ስሜን እንደጻፍሁ እንዲሁም የሰጠሁሽን የባርነቴን ደብዳቤ ጻፊ፡፡ ልጅሽ በደሙ የዋጀኝ እኔን እንድጎዳ አትጣይኝ ልጅሽንም እንዲህ በይ፡፡

፻፬. ይህንን ጎስቋላ ባሪያ በክቡር ደምህ የገዛኸውን ስለ በደሉ ስለ ጉስቁልናው አትናቀው፡፡ ገንዘቡን በወርቁ የገዛውን ለመጽላት የሚችል የለምና፡፡

፻፭. ልጄ ሆይ በደምህ የገዛኸውን ኃጢአተኛውን ባሪያህን እንግዲህ እንዴት ትንቀዋለህ አይደለም ይህንን ፍዳ አታድርግ ከባሪያህም ጋራ ወደ ክርክር አትግባ፡፡ ሕያዊት ነፍስ ያለችው ሁሉ ባንተ ፊት እውነተኛ አይደለምና፡፡

፻፮. ልጄ ሆይ የኃጢአቱን ቁጽር አታስብ እንደበደሉም አታድርግበት ስለ ኃጢአቱም አትበቀለው በሰውነቱም ቢበድል በገቢርም በሐልዮም ቢሆን ስለ ፍዳ እኔ ጸሎትን ማማለድን እከፍላለሁ ይቅርታህ ያባትህም ቸርነት የመንፈስ ቅዱስም ምሕረት በዘመኑ ሁሉ ባርያህን ይጎብኘው ይርዳው ለዘለዓለም በውነት ያለ ሐሰት፡፡ አሜን፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# አርጋኖን ዘቀዳሚት

## ምዕራፍ ፩

፩. የዳዊት ልጅ ድንግል ሆይ ላንቺ እገዛለሁ ላንቺም ከእግርሽ በታች እሰግዳለሁ በፊትሽም እማለላለሁ፡፡ የይቅርታ ብላቴና ሆይ ለልጅሽ መንግሥት እገዛለሁ፡፡

፪. የምሕረት ብላቴና ሆይ የአርሞንኤም ጠል በጽዮን ተራሮች ላይ እንዲወርድ፡፡ እንዲሁም ደግሞ የልጅሽ የቸርነቱ ጠል በላዬ ይውረድ ከሰውነቴም የኃጢአቴን ርኩሰት ይጸብ፡፡ (መዝ ፻፴፫ ፣ ፫)

፫. አጽንቴንም ያለምልመኝ የሥጋዬንም አዳራሽ ይቀድስ የሽቶሽም መዓዛ በላዬ ይዋሀድ እንደ አሮን የክህነቱ ሽቱ በጽሕሙ ላይ እንደወረደ እስከ ልብሱም ዘርፍ እንደደረሰ (መዝ ፻፴፫ ፣ ፪)

፬. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ የለጅሽን ጭፍሮች ሰይፍ ጃግገሬዎቹን ሹሚልኝ ትጉሃን ሠራዊትም ደጁን ይክበቡ፡፡

፭. የአኤናዎንም የክንዱ ኃይል ረዳት ይሁነኝ የተቃራኒ ፀብ ክርክር እንዳያቸንፈኝ በጦር ስለት የሚወጋ በሠረገላውም የሚመካ በፈረሠኞች ሰልፍ ኃይለኛውንም ምሽግ የሚመሽግ ጸላት እንዳያቸንፈኝ፡፡

፮. ሥጋ የለበሰ ሁሉ መመኪያ ድንግል ሆይ ነፍስ የተዋሀዳቸው ፍጥረት ሁሉ አክሊል የዓለም ሁሉ ቤዛ ነፍሴን ከክፉ ነገር ወደ ገሃነምም ከምትወስድ የጥፋት መንገድ አድኛት፡፡

፯. ሳትዘራ ስንዴ ያፈራች ዝናምም ሳይዘንምባት የወይን ፍሬ ያስገኘች ማረሻ ያልዞረባት እርሻ ድንግል ሆይ የኦሪትና የነቢያት ቃል ዝናምን አጠጭኝ በሐዋርያት ወንጌል ቃል ፈሳሽነትም ሐዲስና ብሉይን እንዳፈራ አድርጊኝ፡፡

፰. የኃይል መንፈስ የተመሉትን የተደነቁ የተመረጹትን ሐዋርያት ዋጋ እንድቀበል አድረጊኝ ልቡና የሚገልጽ ዕውቀት የሚያበዛወን መንፈስ የተመሉ ሐዋርያትን ዕሤት እንድቀበል ማለቴ ግን በኔ ገድል በትሩፋቴ አይደለም ባነቺ ደግነት በንጽሕናሽም ነው እንጂ፡፡

፱. በጸሎትሽም ረዳትነት ይህንን ላገኝ እወዳለሁ ድንግል ሆይ በሃይማኖት ጭንጫ ላይ የተመሠረተች መሠረት የማትፈርስ የነፋሳት ኃይል የጎርፍ ፈሳሽ የዝናምም ወጀብ የማይበረታባት አጥር ቅጽር ሆይ እኔን ከጥፋት ጎርፍ በዓመፀኞችና በበደለኞች ላይ ከምትመጣው የመቅሠፍት ኃይል አድኝኝ፡፡

፲. የመለኮት አዳራሽ ድንግል ሆይ የሰማይ ሠራዊት ዖታ ያደረብሽ ንጽሕት ሆይ፡፡ ኅብሩ ልዩ ልዩ በሚሆን ብርሃን በተጌጸ የቅዱሳን አዳራሽ ውስጥ መኖርን ክፈዪኝ፡፡

፲፩. ከቤት ሕንፃ በላይ የታነጽሽ ሰገነት ድንግል ሆይ ወደ አርያም ከፍ ከፍ እንድል በልጅሽም በምስጋናወ አዳራሽ ውስጥ የተሠወረውን ምሥጢር መርምሬ ለማወቅ ወደ ሰማይ ዳርቻ ከፍ ከፍ እንድል ወደ ላይ እንድመሰጥ አድርጊኝ፡፡

፲፪. ለዘለዓለሙ የማትገፊ የማትፈርሽ አምባ ድንግል ሆይ ባንቺ የተጠጉትም ከሚቃረናቸው ጠላት ፀብ ክርክር አድኚኝ፡፡

፲፫. የትንቢት አዝመራ ድንግል ሆይ የቤተክርስቲያን ለውዝ ገውዝ በጨረቃ ጊዜ የምታፈራ የወይን ፍሬ አበባ የሚሻተትብሽ ፍሬውም የሚከማችብሽ ጽድቅ ፍሬን እንዳፈራ የወንጌል ቡቃያ አድርጊኝ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፬. መስገጃ መማለጃ የኃጢአት ማስተስረያ የምትሆኝ የምሥጢር ታቦት ድንግል ሆይ ወደ ልጅሽ ወደ ወዳጅሽ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአቴነ አስተሰርይልኝ፡፡ ድንግል ሆይ የተገፉት መሸሻ የሚያጥሩት አጥር ቅጽር የመዋዕያን ሰማዕታት አክሊል፡፡

፲፭. ገድላቸውንም ለፈጸሙት ብፁዓን የጻድቃን ዋጋቸው የኃጥአዘን ዕረፍታቸው የከሙት ጉልበት የነዳያን ሀብት የንጹሐን መመኪያ ያደፉትም ከርኩሰታቸው የሚነጹብኝ ያዘኑትም የሚጽናኑብሽ ደስ ያላቸው የተድላ ደስታቸው ፍጻሜ፡፡

፲፮. የመዓስባን ረዳት የደናግል ትዕግሥት በፍጹማን መነኮሳት በሰውነታቸው ውስጥ የምታበሪ ዕንቁ በየተራራው በየዋሻው በየጎደጎደው ምድር በሚኖሩ ቅዱሳን ዋጋ ባሕታውያንን የምትጎበኝ ርግብ ከገዳማውያን ጋራ የምትኖር መንፈሳዊት ዖፍ፡፡

፲፯. በሃይማኖት የሚጋደሉት ጋሻ ጦር የሚዘፍኑት መሰንቆ የዘፈን ዕቃ የልዑል እግዚአብሔር የምስጋና ኃይል የአየራት ምጥቀታቸው የሰማያት ልዕልናቸው፡፡ የምድር መሠረት የቀለያት ጥልቀት የሚያዝያ ፀሐይ ብርሃን፡፡

፲፰. የጨረቃና የከዋክብት የነ አርዮብ ብርሃን ፀዳላቸው መልካቸው የምድረ በዳም አበቦች ፀዳል የገነት አበባ መልክ በውስጣቸውም የተዋሀድሽ መዓዛ ድንግል ሆይ ላፍንጫ የሚከረፋው የኃጢአት ክፉ ሽታ ወደ ሰማይ እነዳይወጣ በሃይማኖት ሽቱ አጣፍጭኝ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፪</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ወዳንቺ አለምናለሁ የጸሎት ሙዳይ ሆይ ምልጃ ጽንሓሕ የጥምቀት ልጆች የዕጣናቸው መወዝወዣ ጸሎቴን ሥጋ የለበሰውን ፍጥረት ጸሎት ወደሚሰማው ወደ ልዑል እግዚአብሔር ዙፋን ፊት አድርሽው፡፡

፪. ጸሎቴም ባንቺ ስም እንደ ንጹሕ ዕጣን ሽታ ነውር ነቀፋም እንደሌለበት መሥዋዕት መዓዛ የተወደደ ይሁን እግዚአብሔርም የወደደውን ምክር እንዳስብ አድርጊኝ፡፡

፫. ከክፉም ዓመፅ መንገድ ሁሉ እንድቀር የቅዱሳንንም የጽድቃቸውን ፍለጋ እንድከተል፡፡ ከንጹሐንም በጎች እርሳቸውም ጻድቃን ክርሳቸው ጋራ እንድቆጽር አድርጊኝ፡፡

፬. ለበጎ ስራም እንድተጋ ተግቼም ለመፈጸም ሥልጣንን እንዳገኝ ሠርቼም እድፈጽመው፡፡ የማያረጅ የማይጠፋውንም የጽድቅ አክሊል እንድቀበል፡፡ በገድልም ፅኑዓን ከሆኑት ማኅበር ጋራ አንድነት እንድሆን አድርጊኝ፡፡

፭. ንጽሕት ሆይ ከሥጋና ከነፍሴ ርኩሰት ንጹሕ አድርጊኝ፡፡ የረከሰውን ለማንፃት ልጅሽ ይችላል ዳዊት በመዝሙር እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡

፮. በሂሶጵ እርጨኝ እፀበኝ ከበረድም ይልቅ እነፃለሁ ከነፍስና ከሥጋዬም ቁስል ፈውሺኝ፡፡ የባለ መድኃኒት እናት ሆይ፡፡ የታመመውንና የቆሰለውን ለመፈወስ ልጅሽ ይችላል፡፡ ዳዊት በመዝሙር እንደተናገረ እንዲህ ሲል (መዝ ፶፩ ፣ ፯)

፯. ማረኝ አቤቱ ድውይ ነኝና ፈውሰኝ አቤቱ አጽንቶቼ ታውከዋልና የሠራሁት ኃጢአቴነም ባሰብሁት ጊዜ ነፍሴ ደነገፀች ልቤም ታወከች ከራሴ እግሬ ድረስ ሰግጥጥ ሰግጥጥ አለኝ እንዲህ ስል (መዝ ፮ ፣ ፪ ፣ ፫)

www.ethiopianorthodox.org

፰. ሊወቃቀሱት ከማይቻል ከዚህ ዘለፋ ከዚህም ፀብ ክርክር አንደበትም በማሳመርም ቢሆን ተናግሮ ለመዳን ከማይቻል በዚህም እንዳልድን ዐወቅሁ፡፡ እርሱ እግዚአብሔር ይመረምረኛልና በርሱ ዘንድ ሐሰት አይጠቅምም፡፡

፱. በርሱም ፊት የሐሰት ምስክር አይቆምም ነፍሴንም እንግዲህ እንዲህ እላት ጀመርሁ፡፡ ነፍሴ ሆይ ይህ ነገር አይረባሽም አይጠቅምሽም በፍርድ ቀንም የሐሰት ምክንያት አያድንሽም፡፡

፲. በፊቱም ሐሰት መናገር አይቻልም እውነተኛ ዳኛ ነውና፡፡ ነፍሴ ሆይ የፍርድ ቀን ነገር መውጫ አንደበት በማቀልጠፍ በፀብ በክርክርም እንዳይሆን እወቂ፡፡

፲፩. ነፍሴ ሆይ የልዑል ፍርዱ በማማለጃ በጉቦ እንዳይሆን ዕወቂ ነፍስ ሆይ በመንግሥተ ሰማያት ደጅ ምድራዊ ባለጸግነት አይረባምና አይጠቅምም ዕወቂ፡፡ በፊቱም ማድላትና ፊት መንሳት የለም ባለጸጋውን ስለ ሀብቱ ብዛት አያፍረውም፡፡

፲፪. ነፍስ ሆይ ዋጋው የበዛ ዕንቁ በርሱ ዘንድ እንዳይወደድ ዕወቂ፡፡ ምንም የሚያበራ የህንደኬ ዕንቁ ቢሆን ቁጽልጽልም የዓረብ ወርቅ ቢሆን አይረባም በጎ ሥራ ብቻ እንጂ፡፡ የዋህ መንፈስ የበጎ ሥራ እንጂ፡፡

፲፫. ነፍስ ሆይ አደባባዩ የሚያስጨንቅ ጉባዔው ጽፍቅ መኮንኑ እውነተኛ ሠራዊቱም የሚያስፈሩ እንደሆኑ ዕወቂ፡፡ ነፍስ ሆይ ማዕበል ሞገዱ የሚፈላ የእሳት ባሕር ለኃጥኣን እንደተዘጋጀ ዕወቂ፡፡ ለመግባት የተከፈተ ነው ለመውጣት ግን አይቻልም በጨለማ ቁልፍ የተቆለፈ ነውና፡፡

፲፬. ነፍስ ሆይ በእሳት አለንጋ መገረፍ ለኃጥኣን የተገባ እንደሆነ ዕወቂ፡፡ ኩነኔውም የሚያስፈራ ነው፡፡ እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማያንቀላፋ ነው፡፡ የሚገርፉትም አይሰንፉም ከመግረፍ አያቋርጹም የሚያስጨንቁትም አያርፉም አያንቀላፉም፡፡

፲፭. ነፍስ ሆይ ጨለማ የለበሱ የገሃነም ሠራዊት መላእክተ ጽልመት ይቆዩሻል ፊታቸውም የሚያስፈራ ነው፡፡ ከርሳቸውም ፊታቸው የአንበሳ የሆኑ አሉ፡፡ ፊታቸውም የእባብ ፊት የሆነ ከርሳቸው ውስጥ አሉ፡፡ ከርሳቸውም ፊታቸው የጓጉንቸር ፊት የሆኑ አሉ ዓይናቸውም እንደሚነደው እሳት ነው፡፡ ጥርሳቸውም በማናፊያ እንዳናፋት ከእሳትም ውስጥ እንደወጣ ብረት ችንካር ነው፡፡

፲፮. ነፍስ ሆይ ከልዑል ፍርድ በክርክር መውጫ ማምለጫ እንደሌለሽ ዕወቂ፡፡ የፍጥረቱንም ሁሉ ገዥ ልታሳብይው አትችዪም ኃጢአት ሳትሠሪ አስቀድሞ እርሱ ያውቃል ስትበድዪም መርምሮ ያውቃል፡፡

፲፯. የዕዳ በደልሽም ደብዳቤ በፈቃዱ ተጽፏል ስላንቺ ደግሞ ምስክር አይሻም ሥራሽም ይመሰክርብሻል የዕዳ በደልሽም ደብዳቤ አንቺው ባፍሽ ታነቢዋለሽ ከሠራሽው ሁሉ የሚሠወርልሽ የለም፡፡

፲፰. ነፍሴ ሆይ የምትድኝበትን እኔ እነግርሻለሁ ከዚህ ሁሉ ይልቅ ወደ ቅድስት ድንግል ጩሂ እንዲህም በይ የብርሃን እናት ሆይ፡፡ በልጅሽ ፊት በደልሁ ኃጢአቴን አስተስርይልኝ፡፡

፲፱. በኃጢአት የቆሰለውንም ሥጋየን ፈውሽው የቆሰለውንም ሰውነቴን ለመዳሰስ እጅሽን ዘርጊ ደዌ ሥጋ ከሚሆን ኃጢአት እንድድን ከኃጢአትም ደዌ ሁሉ ጤነኛ እንድሆን፡፡

፳. ስለዚህም አንቺን እሻለሁ ከሲኦልም እኔን ለማዳን እንድትቺይ ዐውቄ የቤትሽን ደጅ መታሁ ሙሽራ ሆይ እንድገባ ክፈችልኝ የሙሽርነት ቤትሽንም እንዳይ ድንኳንሽንም ዞርሁ መሥዋዕትም ሠዋሁ፡፡

፳፩. ነገር ግን ከሰቡት መንጎች የእንስሳ መሥዋዕት የምሠዋልሽ አይደለም የምሥጋና መሥዋዕት እሠዋልሻለሁ እንጂ ለልጅሽ ቸርነት ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

፳፪. ከከንፈሮቼም ፍሬ ንጹሑን ቁርባን አሳርጋለሁ እንዲህ ያለው መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያማረ የተወደደ ነውና ዳዊት በመዝሙር እንደናገረ እንዲህ ሲል ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት ሠዋ ጸሎትህንም ለልዑል ስጠው በመከራህ ቀን ትጠራኛለህ አድንሃለሁ ታመሰግነኛለህ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፫</u>

፩. በዕብራይስጥ መሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ከአናብስት ጉድጓድ የወጣሽ ሙሽራ ከአናምርትም ተራሮች ከነገሥታትም አዳራሽ የወጣሽ (ቁመትሽ የሰሌን ዛፍ ነው፡፡ (መሐ ፬ ፣ ፰)

፪. ቁመትሽ የሰሌን ዛፍ ነው አንገትሽ ሠራተኛ እንደሠራው የወርቅ ዘንግ ነው፡፡ ዓይኖችሽ እንደ አጥቢያ ኮከብ፡፡ ጉንጮችሽ ከኢያሪኮ ባሕር ዳር እንደተለቀመ በባ ናቸው፡፡ ጥርሶችሽም በወተት የታጠቡ እንደ ዕንቁ ያበሩ ናቸው፡፡ (መሐ ፬ ፣ ፪ ፣ ፯ ፣ ፯ ፣ ፭ ፣ ፰)

፫. ያነጋገርሽም ጣዕሙ እንደ ወይን እሸት ነው፡፡ ያፍሽም መዓዛ እንደ አፈው ሽታ ነው፡፡ የልብሶችሽም ሽታ የሽቱ ዕንጨት እንደታጠነ ነው፡፡ ሙሽራ ሆይ ሰውነትሽ ሁሉ ያማረ የተወደደ ነው ምንም ምን ነውር ነቀፋ የሌለብሽ፡፡ (መሐ ፬ ፣ ፯)

፬. መልክሽ ደም ግባትሽ ያምራል፡፡ ጡቶችሽም ግራ ቀኝ እንደሚነቁ እንደ ሁለት ምንጮች ናቸው፡፡ ከርሳቸውም ደግሞ ሥጋ የለበሰውን ፍጥረት ሁሉ የሚመግብ ክርስቶስን ለማሳደግ ድንግልናዊ ወተት ይፈስ ነበር፡፡ (መሐ ፬ ፣ ፩)

፭. እንዲህ ያለ ወሬ የሰማ ማነው በቤተልሔም ዕፁብ ድንቅ ወሬ ተሰማ ያልታየ ታየ፡፡ ዕፁብ ደንቅ ነገር በኤፍራታ ተደረገ የማይገለጽም የተሠወረ ምሥጢር በገሊላ የተሠወረ ተገለጸ፡፡

፮. ዘመኑ ያልተቆጠረለት ጥቂት ጥቂት እያለ አደገ፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ለራሱ አዲስ ልደትን አደረገ እሳት በሴት ማኅፀን ተወሰነ፡፡ በድንግል ብላቴና ሆድ ብሩህ መብረቅ ተቻለ፡፡ (ዳን ፯ ፣ ፱ ፣ ፲፫)

፯. ከተወለደም በኋላ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም ሦስቱን ደጅ ያልከፈተ የአብን ልጅ ጥበቡን አደንቃለሁ፡፡ ያለመለወጥ በኅቱም ድንግልና በመወለዱ የመቃብሩን ደጅ ሳይከፍት ተዘግቶ ሣለ ተነሥቶ በመውጣቱ፡፡

፰. የቤቱም ደጅ ተዘግቶ ሳለ ደቀመዛሙርቱ ተሰብስበው ወዳሉበት ገባ፡፡ ሳይከፈትም ወጣ፡፡ ስለዚህም ሦስት ደጆች ልቤ አደነቀች፡፡ ስለ ሁለቱ ምክንያት አገኘሁ የመቃብሩን ደጅ የሚመስለው ነገር አለ፡፡ (ዮሐ ፳ ፣ ፲፱ ፣ ፳፯)

፱. ብልጣሶር የተባለ ዳንኤልን ባንበሶች ጉድጓድ ውስጥ በጣሉት ጊዜ ጉድጓዱን በታላቅ መዝጊያ ዘጉት ዳንኤልም በረኀብ እንደተጨነቀ ልዑል እግዚአብሔር ባየ ጊዜ መልአኩን ወደ ነቢዩ ዕንባቆም ላከ፡፡ (ዳን ፮ ፣ ፲፯ ፣ ፲፯)

፲. በራሱም ፀጉት አንስቶ ተሸከመሞ ወስዶ ዳንኤል ወዳለበት ጉድጓድ አገባው፡፡ ዳንኤልና ዕንባቆም እንጀራውንና ንፍሮውን በልተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡ ዕንባቆምም ደጁ ተዘግቶ ሳለ ወጣ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፩. ስለቤቱም ደጅ የሚመስል ነገር አለ በግብረ ሐዋርያት እንደተጻፈ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ወርዶ ጴጥሮስን ከግዞት ቤት እንዳወጣው ተጽፏል፡፡

፲፪. ጴጥሮስንም ካወጣው በኋላ ደጁ ተቆልፎ ዘበኞቹ በሁሉ ወገን ይጠብቁ ነበሩ፡፡ (የሐዋ. ሥ ፲፪ ፣ ፮)

፲፫. ለነዚህ ለሁለቱ ደጆች ለቅዱሳን የተደረገውን ምክንያት አገኘሁ ስለ ድንግልናሽ ደጅ እጠናለሁ ግን ምክንያት አላገኘሁም፡፡ ሴት በድንግልና ወለደች ሲሉ አልሰማሁም ከወለደችም በኋላ በደንግልና የኖረች አላየሁም፡፡

፲፬. ይህ ነገር ምን ይረቅ ምን ይጠልቅ ለዚህ አንክሮ ይገባል፡፡ በሕያው እግዚአብሔር ጥበብ የተሠራው ይህ ምሥጢር ዕፁብ ድንቅ ነው፡፡ ቅደመ ዓለም የተወለደው መወለድ ከብቻው አባት ነው፡፡ በኋለኛው ዘመን ደግሞ ከብቻዋ ቅድስት ድንግል ነው፡፡

፲፭. የእግዚአብሔር ሥራ ምን ይረቅ ምን ይጠልቅ፡፡ የእስራኤልም ቅዱስ ጥበቡ እጅግ የረቀቀ ነው ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከአዜብም እስከ መስዕ፡፡ ከምድር ዳር እስከ ምርድ ዳር አየ በምድር ላይ ወደሚኖሩት ሁሉ ላይ ተመለከተ፡፡

፲፮. እንደ ያዕቆብ ያለ አላገኘሁም እርሱንም መረፀው፡፡ ልቡናውም በእስራኤል ላይ አረፈ ፍቅሩም ወደ ዳዊት ቤት ሆነ፡፡ እንደተጻፈ እንዲህ ሲል ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ወገኖች ዕድል ፈንታ ጽዋ ተርታ ሆነ፡፡ (ዘዳግም ፴፪ ፣ ፱)

፲፯. ዳግመኛም ወደ ያዕቆብ ከተማ ተመለከተ፡፡ ከሮቤል ነገድ ጀምሮ እስከ ብንያም ነገድ ድረስ አየ፡፡ ልቡናውም በይሁዳ ነገድ ላይ ዐረፈ ፈቃዱም ለዳዊት ቤት ሆነ እንደተጻፈ እንዲህ ሲል፡፡

፲፰. የጽዮንን ተራራ የወደደ መቅደሱን በአርያም ሠራ ለዘለዓለምም በምድር ላይ ሠራት፡፡ ዳዊትንም ባሪያውን መረጸው የዳዊትንም ቤት አይቶ ተመልክቶ እንግዲህ ቅድስት ድንግልን አገኛት መልኳንም ወደደው፡፡ (መዝ ፸፰ - ፸)

፲፱. ላህላይዋንም መረጸ መዓዛዋንም ፈቀደ፡፡ ከአዳምም ወገኖች ሁሉ ይልቅ አማረችው ደስ አሰኘችው፡፡ ዳዊት በመዝሙር እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ ልጄ ሆይ ስሚ ጆሮሽንም ዘንበል አድርገሽ አድምጭ ወገኖችሽን ያባትሽን ቤት እርሺ ንጉሥ መልክሽን ደም ግባትሽን ወዷልና፡፡ (መዝ ፵፭ ፣ ፲ ፣ ፲፩)

፳. የሁሉ ጌታ ከኪሩቤል ጋራ ወንድማማች ሊሆን ሱራፌልንም ሊመስላቸው ለትጉሃን የሰማይ መላእክትም ቤዛ ሊሆን፡፡ እሳታውያንንም ሊሳተፋቸው አልወደደም መሬታውያንን ሊመስላቸው ወደደ እንጂ፡፡ ጳውሎስ እንደተናገረ እንዲህ ሲል፡፡ መላእክትን የተቀበለ አይደለም የአብርሃምን ዘር ከፍ ከፍ አደረገ እንጂ ወንድሞቹንም ሊመስላቸው ወደደ፡፡

## ምዕራፍ ፴

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ምን ያህል ክብር ተሰጠሽ የያዕቆብ ልጅ ምን ያህልስ ጸጋ ተቀበልሽ፡፡ የእስራኤል ልጅ ሆይ ምን ያህልስ ምስጋና ከበበሽ የይሁዳ ልጅ ሆይ ምን ያህል ባለሟልነት አገኘሽ፡፡

፪. እነሆ ከኪሩቤል ትበልጫለሽ ከሱራፌልም ከፍ ከፍ ትያለሽ ከትጉሃን የሰማይ መላእክትም ሁሉ በመዓረግ አንቺ ትበልጫለሽ የድንግልናሽም ምስጋና ለዘወትር አይፈጸምም፡፡

፫. በዓለም ሁሉ ትመሰገኛለሽ በየዘመኑም ሁሉ ትወደሻለሽ፡፡ በየጊዜው ንጽሕት ነሽ፡፡ በየስፍራው ሁሉ ቅድስት ነሽ፡፡ የአንደበቱም ሁሉ ቡረክት ነሽ ከላህይሽም የሚያምር የለም፡፡ የንጋትም ውጋጋን ቢሆን፡፡

፬. ከቁመትሽም የሚያምር የለም ሰሌንም ቢሆን የሊባኖስ ዛፍም ቢሆን፡፡ ከጥርሶችሽ የሚነጣ የለም፡፡ ወተትም ቢሆን በረድም ቢሆን፡፡ ከዓይንሽም ፀዳል የሚበራ የለም፡፡ በሰማይ ፊት ለፊት የሚያበራ የወርቅ ዘውድም ቢሆን፡፡

፭. ካፍንጫሽም ዕፁብ የሚሸት የለም፡፡ ከልብስሽም ሽታ የሚበልጥ የለም፡፡ ከልበኔም ቢሆን ሐንክሶም ቢሆን፡፡ አስጳዳቶስም ናርዱም ቢሆን፡፡ ዋጋውም የበዛ ሌላ ሽቱ ቢሆን፡፡

፮. ሰውነትሽ ሁሉ ያማረ የተወደደ ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተጋረደ ነው፡፡ ገላግልቶቿን በክንፎቿ የምትታቀፍ ንጽሕት ርግብ ሆይ፡፡ ክብርሽን ገናንነትሽን እናገር ዘንድ ፍቅርሽ ያነቃቃኛል፡፡ ወለላውን ማር ለመቅዳት ለምን እሰንፋለሁ፡፡ ለሚበላው የጣፈጠ ነው፡፡ ወተቱንስ ለመቅዳት ለምን እሰንፋለሁ፡፡ ለሚጠጣው ያማረ የተወደደ ነውና፡፡

፯. የትንቢቱን አበባ ለማሽተት ለምን እሰንፋለሁ፡፡ የመዓዛው ሽታ ላፍንጫ ያማረ ነውና፡፡ የሃይማኖት ሽቱ ለማጣፈጥ ለምን እሰንፋለሁ፡፡ እርሱን በመንካት እጆቼ ይሸተታሉና፡፡ የቅድስት ድንግል በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለችውን የማርያምን አምላክን የወለደችውን የርሷን ምስጋና ለመናገር ለምን እሰንፋለሁ፡፡

፰. ምስጋናዋ ከማር ወለላ ይጥማልና፡፡ ከወተትም ያማረ የተወደደ ነውና፡፡ ከአበባም ሁሉ ያምራል፡፡ ከጣፈጠም ሽቱ ይሸታል፡፡ ፀዓዳ ርግብ ሆይ ምስጋናሽን እናገራለሁ፡፡ ወደ ልጅሽም እጮኻለሁ፡፡ እንዲህ ስል አፌን ምስጋናህን ምላ ምስጋናህን እንዳመሰግን፡፡ (መዝ ፸፩ ፣ ፰)

፱. የወለድችህንም ንጽሕት ድንግል ምስጋና እንድናገር የልጅሽንም መንፈስ ተመልቼ የድንግልናሽን ምስጋና መሰንቆ እመታለሁ፡፡ የተፈራሽ ድንግል ሆይ ልዕልናሽን አደንቃለሁ፡፡

## ምዕራፍ ፳

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ የወርቅ ዘርፍ ባለው መጎናጸፊያ የተጎናጸፍሽ ንግሥት ሆይ ላንቺ እገዛለሁ፡፡ (መዝ ፵፭ ፣ ፲፫)

፪. ስኂንና ሜዓ ስሌሖት በውስጧ የተጨመረባት ሙዳይ ሆይ እገዛልሻለሁ፡፡ ዕውነተኛ ፀሐይን የወለድሽ የአማልክት አምላክ እናት ሆይ እገዛልሻለሁ፡፡

፫. በጥጃ የምትመሰል በፋራን ተራራ እርሷም የትንቢት መፍሰሻ ናት፡፡ የርሷ ምሳሌ ድንግል ሆይ አንቺን አገለግላለሁ፡፡ መላእክት በውስጧ የሚያገለግሉባት የመለኮት ማደሪያ ጽርሐ አርአያም ሆይ እገዛልሻለሁ፡፡

፬. በወርቅ መሠረት ላይ የተመሠረተች በሕንደኬ ደንጊያ የታነጸች፡፡ በሶፎርና በአጳርግዮን ዕንቁ ደንጊያ የተጌጸች ደጆቿም ባሥራ ሁለቱ አዕናቁ የተጸለፈላት ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም በደጅዋ የቆሙባት ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ሆይ ላንቺ እገዛለሁ የባቢሎን አውራጃ በሚሆን በኮቦር ወንዝ ሕዝቅኤል ያያት የብርሃን ሠረገላ ሆይ እገዛልሻለሁ፡፡ (ሕዝ ፩ ፣ ፲፰)

፭. ንጉሡ ዖዝያን በሞተ ዓመት ነቢዩ ኢሳይያስ ያያት ረጅም መንበር ሆይ እገዛልሻለሁ፡፡ የምሕረት መቅጃ የወርቅ መጥለቂያ ሆይ እገዛልሻለሁ፡፡ ጸጋ ክብርን የተመላሽ ድንግል ሆይ ምስጋና የተመላሽ

ድንግል ሆይ እገዛልሻለሁ፡፡ (ኢሳ ፷ ፣ ፲፬)

፮. ሀብትን ባለጸግነትን የተመላሽ ድንግል ሆይ ላንቺ እገዛለሁ፡፡ ከግርሽም በታች እሰግዳለሁ፡፡ የልቤንም ቀፊት ላንቺ አዘነብላለሁ፡፡ ራሴንም ላንቺ አዋርዳለሁ፡፡ ኃጢአቴን ለመክሰስ በፊትሽ እቆማለሁ፡፡ የዕዳ በደሌንም ደብዳቤ በፊትሽ አነባለሁ፡፡

፯. በልጅሽም ዘንድ ራሴን አጣላለሁ፡፡ የኃጢአቴ ሕንጻ ቁመቱ እስከ አርያም ደረሰ የበደሌ ስፋቱም እስከ ዓለም ዳርቻ ነው፡፡

፰. ድንግል ሆይ የኃጢአቴን አጽር ቅጽር ታፈርሽልኝ ዘንድ እታመንሻለሁ፡፡ ድንግል ሆይ የዕዳ በደሌን ደበዳቤ በጅሽ ትቀጅው ዘንድ እታመንሻለሁ፡፡ ድንግል ሆይ በንጽሕና ውሀ ሰውነቴን ታጽቢኝ ዘንድ እታመንሻለሁ፡፡

፱. ድንግል ሆይ በመከራዬና በጭንቀቴ ጊዜ እንዳትጥይኝ ድንግል ሆይ እታመንሻለሁ፡፡ ለጸላቶቼ አሳልፈሽ እንዳትሰጭኝ በጸላቶቼም እጅ እንዳትጥይኝ ድንግል እታመንሻለሁ፡፡ የሚጥለኝን እንድትጥይው የሚቃረነኝንም እንድትቃረኒው፡፡

፲. ድንግል ሆይ እታመንሻለሁ፡፡ የሚበረታታብኝን ልምሾ ታደርገው ዘንድ የሚቃወመኝንም ትቃወሚው ዘንድ ድንግል ሆይ እታመንሻለሁ፡፡ ስወጣ ስገባም እንድትከተይኝ ስቀመጥና ስነሣም እንድትጠብቂኝ፡፡

፲፩. ጠንካራዪቱን አምባ መጸጊያ አንቺን የታመንሽቱን ጋሻ እታመንሻለሁ፡፡ አንቺን ተጠጋሁ ነፍሴንም ነፊትሽ እጥላለሁ፡፡ አንቺን ተጠጋሁ፡፡ ራሴንም በጅሽ ሰጠሁ፡፡ ከንፈሮቼንም ለምስጋናሽ መሣሪያ አደረግሁ፡፡

፲፪. የሚቃረነኝ ጸላቴ እንዳያገኘኝ የሰይጣንም ፈረሶች ሠረገላ እንዳይደርስብኝ አንቺን ተጠጋሁ፡፡ ባንቺም አመንሁ ከመስቴማ ሠራዊት ከመከበብ ከርኩሳንም መናፍስት ወጥመድ እንድድን አንቺን ተጠጋሁ፡፡

፲፫. የመለአክተ ጽልመት ፍላፃ እንዳይነድፈኝ ካመፀኞችም ጦር እንድድን ልዩ ከሆነ ሰይፍም እንድድን አንቺን ተጠጋሁ፡፡ የጽድቅንም መንገድ ከሚቃወሙ ሰዎች ወጥመድ እንድድን አንቺን ተጠጋሁ፡፡ አንቺን አመንሁ እኔን አገልጋይሽን አድኝኝ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

# አርጋኖን ዘእሁድ

## ምዕራፍ ፩

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ እጄን ወደልጅሽ እዘረጋለሁ፡፡ ወደሱም እጮኻለሁ እንዲህ ስል ከችግርና ከመከራ ሁሉ ታደነኝ ዘንድ ከመቅደስህ ከጽርሐ አርያም ውረድ በረድኤትም ወደኔ ና፡፡

፪. አቤቱ ሆይ ከምታስጨንቅ መቅሠፍት ትንሣኤም ከሌለው መውደቅ መጽናናትም ከሌለው ኀዘን ታድነኝ ዘንድ ከተሰናዳው ማደሪያህ ውረድ፡፡ (መዝ ፻፵፬ ፣ ፭)

፫. አቤቱ ሆይ ከሚሰብር አንበሳ ከሚነጥቅ ተኩላ ታድነኝ ዘንድ ከሰማይ ውረድ፡፡ አቤቱ ሆይ ባንተ ዘንድ የመንገድ ድካም የለምና ሰማይ መንበርህ ነው፡፡ ምድርም የእግርህ መሄጃ ናት፡፡ (ኢሳ ፷፮ ፣ ፩)

፬. አቤቱ ሆይ እኔን ለማዳን ውረድ ለማጥፋት ግን አይደለም፡፡ አቤቱ ለይቅርታዬ ውረድ ለመቅሠፍት አይደለም፡፡ አቤቱ ሆይ ለማስመር ውረድ ለማክፋት አይደለም፡፡

፭. ያንተ የሕይወትህ መንፈስ ቅዱስ የአባትህም መንፈስ ከቀማኛ ለማዳን የሚችል እርሱ ደግሞ በረድኤት ወደኔ ይምጣ፡፡ ያንተ መንፈስ የወለደህ የባሕርይ አባትህ ክብርቱ እጅ ለማዳን የሚችል መንፈስ ወደኔ ይምጣ፡፡

፮. ከሚከራከር መበዝበዝ የሚችል ያንተ የላከህም የአባትህ መንፈስ የተሠወረውን ሀሳብህን የሚያውቅ የአባትህንም የተሠወረውን ሀሳብህን የሚያውቅ የአባትህንም የተሠወረውን ሀሳብ የሚያውቅ ያባትህን የሕሊናውን ሀሳብ የሚመረምር መንፈስ ይምጣ፡፡ አንተ የወደድኸው አባትህንም ደስ የሚያሰኘውን ሥራ ልብ እንዲያስደርገኝ፡፡

፯. የአንተን ምሥጢር የባሕርይ አባትህን ምሥጢር የሚያውቅ መንፈስ ይምጣ፡፡ ያንተን ትእዛዝ ከአንተ ጋራ ትክክል የሆነውንም አባትህን ትእዛዝ ለመሥራት እንዲያበረታታኝ አብን ካንተና ከመንፈስ ቅዱስ በቀር በባሕርይ የሚያውቀው የለምና፡፡ (ዮሐ ፮ ፣ ፵፮)

፰. መንፈስ ቅዱስንም ካንተና ካባትህ በቀር የሚያውቀው የለም፡፡ ለአብ ካንተና ከመንፈስ ቅዱስ የተሠወረ ምክር የለም አብ ስለወለደህ ካንተ ቅድሚያ የለውም አንተም ከርሱ ስለተወለድህ ከርሱ ወደኋላ አትሆንም መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ነው፡፡ (ዮሐ ፩ ፣ ፩ ፣ ጢሞ ፩ ፣ ፮ ፣ ፲፮)

፱. አብ እንዴት እንደወለደህ የሚያውቅ የለም፡፡ አንተም ከርሱ እንዴት እንደተወለድህ የሚያውቅ የለም ከመንፈስ ቅዱስ በቀር ላንተም ለርሱም ሌላ መንፈስ ቅዱስ የለምና ያንተ መንፈስ የርሱ መንፈስ አንድ ነው እንጂ፡፡ ዮሐ ፲፯ ፣ ፲- ፳፬፡፡

፲. ለደቀ መዛሙርትህ ተስፋ እንዳስደረግኻቸው እንዲህ ስትል ከአብ ይወጣል ከኔ ይነሣል መንፈስ ቅዱስ ከአብ ዘንድ የለም እንዳንል ከአብ ይወጣል አልህ ከወልድ ዘንድ መንፈሰ ቅዱስ የለም እንዳንል በከበሩ ደቀ መዛሙርትህ ፊት በንፍሐት አሳድርኸው እንዲህ ስትል መንፈስ ቅዱስን ንሡ ተቀበሉ፡፡ ዮሐ ፲፮ ፣ ፲፭ ፣ ፳ ፣ ፳፪፡፡

፲፩. መንፈስ ቅዱስ በፍጹም አካሉ የለም እንዳንል ደግሞ ለሐዋርያትህ ሁለተኛ የሚሆን መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስን እልክላችኋለሁ አልካቸው መንፈስ ቅዱስ በፍጹም አካሉ እንዳለ በአብና በወልድ ህልው እንደሆነ በዚሁ ዐወቅን፡፡ (ዮሐ ፲፯ ፣ ፯)

፲፪. የመንፈስ ቅዱስ አካል ወደ አብና ወደ ወልድ የሚከፈል አይደለም በፍጹም አካሉ ለብቻው አንድ አካል ሁኖ ሳለ በአብና በወልድ ህልው ሁኖ ይኖራል እንጂ፡፡

፲፫. በነቢያት አድሮ ትንቢት ያናገረ እርሱ ነው በሐዋርያት ላይ ወረደ እርሱ ነው ሰማዕታትን ያጸና ከሳቱ ከስለቱ ጨምከነው እንዲገቡ ያደረጋቸው እርሱ ነው ንጹሐን ደናግልን ያበረታቸው፡፡

፲፬. ሥጋዊ ደማዊ ፈቃዳቸውን ጾራቸውንም አጥፍተው በሥጋቸው የመላእክትን ትጋት ገንዘብ ያደረጉ የተመረጹ መነኮሳትን ያጸና ትዕግሥትንም የሰጣቸው እርሱ ነው በየተራራ በየዋሻው በየጸፈቀው ዱሩ በየጎደጎው ምድር የሚዞሩ ባሕታውያንን መሪ የሆናቸው ገዳማውያንንም የሚጎበኛቸው የታሠሩትንም ስለ ክርስቶስ ፈቅርም የተጨነቁትን የሚያረጋጋቸው እርሱ ነው፡፡

፲፭. በፀብ ክርክር ጊዜ የረድኤት መንፈስ ነው በገድል ጊዜ የኃይል በጦርነትም ጊዜ የማቾነፍ በድንግልናም ጊዜ የንጽሕና መንፈሰ ነው፡፡ በመሬታውያንም አንደበት የሚናገር የምሥጋና መንፈስ ነው፡፡ ርኩሳንንም የሚያነፃ ከመሃይምናንም ጋራ የሚኖር የባለሟልነትና የጸጋ ክብር መንፈስ ነው፡፡

፲፮. ዕውቀት ለሌላቸው ዕውቀት የሚገልጽ የቸርነት ዕድል ፈንታ ሁሉ ከርሱ የሚገኝበት፡፡ በጎ ስጥውታውም ሁሉ ፍጹሙም ጽዋ ተርታ ከርሱ የሚገኝበት መንፈስ ነው፡፡

፲፯. የበጎ ዕድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የሚሆን እግዚአብሔር ብዙ ስጥወታ ከብዙች መናፍስት የሚቀዳ አይደለም ካንድ መንፈስ ነው እንጂ የክፉ ዕድል ፈንታ ግን የሚገኝ ከሰይጣን ነው፡፡

፲፰. እንዳትበድል ድንግልን ከናቷ ሆድ ጀምሮ የጠበቃት መንፈስ ቅዱስ እንዳትረክስም ያነጻት ለወልድ ዋህድም ማደሪያ ያደረጋት እርሱ ነው፡፡ አብ ወደዳት ወልድ ከርሷ ሥጋ ለበሰ መንፈስ ቅዱስ ጋረዳት፡፡

## <u>ምዕራፍ ፪</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለች የተመረጠች ድንግል ማርያምን ኑ እናመስግናት፡፡ የክርስቲያን ማኅበር ሁላችሁ ኑ እናዳንቃት የመሃይምናን ማኅበር ሁላቸሁ አምላክን የወለደች ድንግልን እናመስግናት፡፡

፪. በክርስቶስ የተመሰላቸሁ የደናግል የመነኮሳት ማኅበር ሁላችሁ ኑ የዚችን ርኩሰት የሌለባት ንጽሕት ሙሽራ ክብሯን ገናንነቷን እንናገር በነገሥታት አደባባይ የተሰበሰባችሁ ኑ የዚችን ባነዋወር ከከበሩ ሁሉ የምትበልጠውን ንግሥት የሚከባትን ክብር ምስጋና ታዩ ትመለከቱ ዘንድ፡፡

፫. የሰማያት ክብር ከሰማዮችም በላይ ያሉ ሰማያት ከፍታ የኪሩቤልና የሱራፌል መላእክትም ማኅበር ሁሉ ክብር መዓረግ ከራሷ ፀጉር አንዲቱን ስንኳን አያህሉም፡፡ ዳግመኛም የነገሥታት ክብር ጌትነት ገናንነት የአሕዛብ ብልጽግና በዓለም ሁሉ በምድርም ሁሉ የሚኖሩ ቅዱሳን ሁሉ ባለሟልነት የእግሮቿን ጫማ ያህል አይሆንም፡፡

፬. ለቅድስት ድንግል ምን ያህል ጸጋ ክብር ተሰጣት የማያመሰግናትስ ፍጥረት እንደምን ያለ ነው ክብሯንስ የማይናገር ምን አንደበት ነው፡፡ የማይቀድሳትስ ምን አፍ ነው፡፡ ለክብሯስ የማይገዛ እንደምን ያለ ሰውነት ነው፡፡

፭. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ በሰማይ የሚኖሩትን የኪሩቤልና የሱራፌልን ወገኖች በሰማይ ዳርቻ የሚኖሩትን የመላእክትን ሠራዊት ወገኖች አሰብሁ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፮. ላባቶቻችንም ለአዳምና ለአቤል ለሴትና ለሄኖስ ለልዑል እግዚአብሔርም ላገለገሉ ለሄኖክና ለኖኅ የተሰጣቸውን ጸጋ ክብር አሰብሁ፡፡ የአብርሃምንም ባለሟልነት የይስሐቅንም ወዳጅነት የያዕቆብንም መመረጽ የእግዚአብሔር ወገን መባሉንም አሰብሁ፡፡ (ዘፍጥ ፭ ፣ ፳፪ ፣ ፮ ፣ ፱) (መዝ ፻፭ ፣ ፱ ፣ ፲)

፯. የሚሴና የአሮንን የኢያሱንም ክብር አሰብሁ፡፡ የባርቅና የዲቦራን የጌዴዎንንም የዮፍታሔን የሶምሶንና የኤግሎምን የመሳፍንትንም ሁሉ ማቸነፍ አሰብሁ፡፡ የሳሙኤልንም ክህነት መዓረግ አሰብሁ፡፡

፰. የዳዊትን የሰሎሞንን የይሁዳን የእስራኤልን ነገሥራት ሁሉ መንግሥት ሀብት ጌትነትና ገናንነትንም አሰብሁ፡፡ የነቢያትን መመረጽ የሐዋርያትንም ጸጋ ክብር አሰብሁ የሰማዕታትን የመጋደላቸውንም ዋጋ የደናግል የመነኮሳት የትዕግሥታቸውን አሳብ አሰብሁ፡፡ እንዳንቺ ያለ አላገኘሁም፡፡

፱. ቅድስት ድንግል ሆይ በልዑል ዘንድ ባለሟልነትን ያገኘ የእግዚአብሔርም ጸጋ ክብር በላዩ የበዛለት እንዳንቺ የለም ጸጋው ክብሩ ባንቺ ላይ እንደበዛ እንዲሁም ደግሞ ቸርነቱ በኔ ላይ ይብዛ፡፡

፲. ወደ ልጅሽም በጸለይሁ ጊዜ ብቻዬን የምዘነጋ አልሁን አንቺም ከኔ ጋር ሁኚ እንጂ በቀኜም ሁነሽ ካፌ የወጣውን ነገር አቃኝልኝ በሚያስፈራ መኮንን ፊት አማላጅ ያለው ሰው የተደነቀ ነውና፡፡

፲፩. የፍቅርሽም ፍላፃ ልቤን ይንደፈው ለዘለዓለሙ አይነቀል፡፡ የስምሽም መጠራት ከሦከር ከማር ወለላ ላፌ የጣፈጠ ነው የድንግልናሽም ምስጋና ላንደበቴ አልጫ መሆን የሚያጣፍጥ ጨው፡፡ የውዳሴሽም ነገር በሄደሁበት አገር ሁሉ ማመስገኛ መሰንቆ በገና ሆነኝ የገናንነትሽም መናገር መዝፈኛ ሙዚቃ ሆነኝ፡፡

## <u>ምዕራፍ ፫</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ አሁንም ጸሎቴን በፊትኝ አሰፋለሁ ስለኃጢአኤም አለቅሳለሁ ወደ ልጅሽም እጮሃለሁ እንዲህ ስል አቤቱ በደልሁ በሰማይም በፊትህም ደግሞ፡፡

፪. እንግዲህ ወዲህ ልጅህ ልባል አይገባኝም ከባሮችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እንጂ ከመቅደስህ ውስጥ ገብቼ ከምዕመናን ጋራ ልጸልይ አይገባኝም ከንዑሳን ክርስቲያን ጋራ በውጪ ሁኜ እጸልያለሁ እንጂ፡፡

፫. መንፈሳዊውን እርድ ለማየት ከአቤልም መሥዋዕት የሚበልጠውን ደም ነባቢውንም መሥዋዕት ለመመልከት በቅዱስ መሠዊያህ ፊት ለፊት ወደሚቆሙበት በወረደ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ የክንፈሮቹ ጥላ እንዲነካኝ በቤትሽ ጥላ እቆማለሁ እንጂ፡፡

፬. የመለኮትን ፍም እፈራለሁ ለመብላትም አልደፍርም እርሱን ለመቀበል የበቃሁ አይደለሁምና በእሳት ጉጠት እንጂ ሱራፊ ሊዳስሰው የማይችለውን የመለኮትን ፍም እፈራለሁ ነቢዩን ያስፈራውን የመለኮትንም ፍም እፈራለሁ ነቢዩ እንዲህ ብሏልና ከንፈሬ ርኩስ ነውና ከንፈራቸውም ርኩስ በሆነው አሕዛብ መሐከል አለሁ፡፡ (ኢሳ ፮ ፣ ፭)

፭. ሱራፌልም እንዲህ አለው እነሆ ከንፈሮችህን አስነካሁህ ከኃጢአትም ያነፃሃል፡፡ (ኢሳ ፮ ፣ ፯)

፮. ድንግል ሆይ ልጅሽ የጎሰቆለውን ብላቴና እንደተቀበለ እኔንም ደግሞ ይቀበለኝ ዘንድ እወዳለሁ፡፡ ልጅሽ ቸር ይቅር ባይ ርኅሩኅ ነውና፡፡ (ሉቃስ ፲፭ ፣ ፲፱-፲፮)

፯. የተራበ ሆድ ለምግብ እንዲቸኩል ክርስቶስ ደግሞ ይቅር ለማለት ይቸኩላል፡፡

፰. ይህንንም ማለቴ ለጥምቀት ልጆች በፍጹም ንስሐ በተቃጠለም የእግዚአብሔር ፍቅር ለተመለሱት ነው ላልተመለሱት ግን ይቅርታ የላቸውም፡፡

፱. ድንግል ሆይ የልጅሽ የሥጋው መታረጃ የደሙ መቅጃ ወደሚሆን መጋረጃ ውስጥ ያስገባኝ ዘንድ እታመናለሁ ድንግል ሆይ የምስሚር ጠረጴዛ ወደተዘጋጀበት በላዩም የመለኮት ማዕድ የሚሆን የሰማይ እንጀራ በተሠራበት ስፍራ ያስቀምጠኝ ዘንድ እታመናለሁ በጌታችን፡፡
የምሥጢሩ ጽዋዕ ከመለኮት ትስብእት ጎን የመነጨው አምላካዊ ወይን ወደተመለበት ያስቀምጠኝ ዘንድ እታመናለሁ፡፡

፲. ድንግል ሆይ ነፍስና ሥጋን ባንድነት የሚፈውሰውን ቅዱስ ምሥጢር ያሳትፈኝ ዘንድ እታመናለሁ ድንግል ሆይ መለኮታዊውን ቁርባን ሥጋው ደሙን ለመቀበል እንዲያበቃኝ ደጅ እጸናለሁ፡፡

፲፩. በተቀበልሁትም ጊዜ ለወቀሳ ለመፈራረጃ አይሁንብኝ ለነፍሴና ለሥጋዬ መድኃኒት ይሁነኝ እንጂ ድንግል ሆይ እድል ፈንታዬ ጽዋ ተርታዬም የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ ዕንቋችሁንም በዕሪያዎች ፊት አታኑሩ ከተባለባቸው ጋር አይሁን ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ ሞት አያገኘውም ቢሞትም ይድናል ለዘለዓለምም ይኖራል ተብሎ ከተነገረላቸው ጋራ እንዲሆን ደጅ እጸናለሁ፡፡ (ማቴ ፯ ፣ ፮)

፲፪. ድንግል ሆይ የሠርግ ልብስ ይኸውም የቅዱሳን ጽድቅ መጎናጸፊያ እርሱን ደግሞ ስለ ለበስሁ ከበጎ ሙሽርነት የተለየሁ እንዳልሆን ደጅ እጸናለሁ፡፡

፲፫. ድንግል ሆይ ደስ ያላቸው አዕላፍ መለአክት ወደሚኖሩባት በሚያንጸባርቀውም ብርሃን የተሸለመች ታቦት ዘዶር በመሐከላቸው ወደምትሆንበት የብርሃን ድንኳን እንድገባ ደጅ እጠናለሁ፡፡

፲፬. ድንግል ሆይ መላእክት ለመጎብኘት ወደሚመኟት ከመታየቷም የተነሣ ዓይን ወደማትጸግባት እርሷንም ለማየት ልቡና ወደሚመስጥባት ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ማደርን ደጅ እጸናለሁ፡፡

## ምዕራፍ ፬

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ በኃጥኣን እጅ ከመውደቅ አድኝኝ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ስንኳን እጅግ ያስፈራል ይሁን እንጂ በሰው እጅ ከመውደቅ በእግዚአብሔር እጅ ብወድቅ ይሻለኛል፡፡

፪. ቁጣው ብዙ እንደሆነ ምሕረቱ ብዙ ነወና እርሱ መሐሪ ነው፡፡ ቁጣውንም በትዕግስት መመለስ ያበዛል በመቅሠፍቱም ሁሉ አያቃጥልም (መዝ ፸፰ ፣ ፴፰)

፫. ድንግል ሆይ ከዓመፅ ከሸንገላ አድኝኝ፡፡ በልቡናው ሸንጋይ ሰው የእግዚአብሔርን ምሕረት አያይምና ድንግል ሆይ ከመታበይ ልቡናን ከማደንደን አድኝኝ፡፡ ልበ ደንዳና ሰው እግዚአብሔርን ይቃወማልና፡፡ ድንግል ሆይ ከርኩሰት ሁሉ ከሥጋም መተዳደፍ ከማመንዘርም አድኝኝ የሚያመነዝር የውሻ ደምና ደሙንም ለሰይጣን የሚሠዋ ይመስላልና፡፡

፬. ድንግል ሆይ ነፍስ ከመግደል ደም ከማፍሰስ አድኝኝ፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏልና የሰው ደም ያፈሰሰ ሁሉ ደሙ ይፍሰስ ስለዚያ ስለፈሰሰው ደም ሰውን በኔ አምሳል ፈጥሬዋለሁና፡፡ (ዘፀአ ፳፩ ፣ ፲፬)

www.ethiopianorthodox.org

፭. ደግሞ እንዲህ አለ፡፡ በፀብ መሣሪያ የገደለ ሁሉ ስለሞተው ሰው ቤዛ ይሙት፡፡ (ዘኁል ፴፭ ፣ ፲፮)

፮. ድንግል ሆይ ሐሰተኛ ከመሆን ሰውንም ከሰው ከማጣላት አድኝኝ፡፡ ዳዊት እንዲህ ብሏልና፡፡ ሐሰት የዓመፅ ሁሉ ራስ ነው፡፡ ድንግል ሆይ ከመሰሰን ኃጢአት አድኝኝ በነገሥት መጽሐፍ እንዲህ የሚል ተጽፏልና፡፡ (መዝ ፳፮ ፣ ፲፪) (ዘፀአ ፳ ፣ ፲፮)

፯. ሴሰኝነት ታላቅ ኃጢአት ነውና፡፡ ድንግል ሆይ ከነገረ ዘርቅ ዋዛ ፈዛዛውን ከንቱውንም ነገር ሁሉ ከመናገር ሠውሪኝ በወንጌል እንዲህ ይላልና ዋዛ ፈዛዛውን ከንቱውንም ነገር የሚናገር ሁሉ ኃጥእ ተብሎ ይፈረድበታል፡፡ ከነገርህም የተነሣ ትጸድቃለህና ከነገርህም የተነሣ ትኮነናለህ፡፡ (ዘፀአ ፳ ፣ ፲፬) (ማቴ ፲፪ ፣ ፴፮)

፰. ድንግል ሆይ ከሐዋርያት ትምህርት ከመውጣት ከማፋለስ አድኝኝ ልጅሽ እንዲህ ብሏቸዋልና እናንተን የሰማ እኔን የሰማ ነው፡፡ እናንተን እምቢ ያለ እኔን እምቢ ያለ ነው፡፡ የላከኝንም እምቢ አለ፡፡ (ማቴ ፲ ፣ ፵ ም ፲፰ ፣ ፭ ሉቃ ፲ ፣ ፲፮)

፱. ጳውሎስ ደግሞ እንዲህ አለ እናንተስ የኛን መንገድ ተከተሉ እኛም ካስተማርናቸሁ ትምህርት ሌላ ያስተማራችሁ ቢኖር የሰማይ መላክ ቢሆን ውጉዝ ይሁን፡፡ (ገላ ፩ ፣ ፰)

፲. ደግሞ እንዲህ አለ እኛ ካስተማርናችሁ ሌላ ትምህርት ብትማሩ የተወገዛችሁ ሁኑ፡፡ (ገላትያ ፩ ፣ ፱)

## <u>ምዕራፍ ፭</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ እመቤቴ ማርያም ሆይ በሃይማኖት መሣሪያ ሸልሚኝ የልጅሽን ማኅተም ይዤ የተፈራሁ ልሁን ባሪያውም ልባል ጭፍራውም ልሁን፡፡

፪. የመስቀሉን ማመን ጋሻ ልመክት በመስቀሉም ኃይል ልሸለም፡፡ ድንግል ሆይ በጦርነት የሚያቸንፍ ድል የሚነሣ አርበኛ አድርጊኝ በንጉሡም ምስጋና የሚያገኝ ልሁን መሣሪያ ይዞ በጦርነት ጊዜ የሚፈራ ስለፈሪነቱም የሚነቀፈ ስለተቸነፈም የሚዋረድ አታድርጊኝ፡፡

፫. ድንግል ሆይ የማሸንፍ አድርጊኝ የምቸነፍ አይደለም፡፡ ጻድቅ አድርጊኝ ኃጥእ አይደለም ብፁዕ አድርጊኝ ሸንጋይ አይደለም፡፡

፬. የዋህ አድርጊኝ ጠማማ አይደለም፡፡ ቀና አድርጊኝ ተንኮለኛ አይደለም ቸር አድርጊኝ ንፉግ አይደለም ለክብር አድርጊኝ ለኃሣር አይደለም ለሠርግ ቤት አድርጊኝ ለልቅሶ አይደለም ለደስታ አድርጊኝ ለኃዘን አይደለም፡፡

፭. የሠርግ ልብስ ለመልበስ አድርጊኝ ጨርቅ ለመታጠቅ አይደለም፡፡ በገድል ዋጋ የሚወስዱትን ብታድኝ ግን ስለርሳቸው አይደነቅም ዋጋቸውን በድካማቸው ተቀዳጅተው ወስደዋልና፡፡ የሚደነቅ ግን የኔ የኃጥኡ ከክርስቲያንም ሁሉ ይልቅ የበደልሁት ጸሎትሽን በመታመን የጽድቅ አክሊል የደረሰኝ እንደሆነ ነው፡፡

## <u>ምዕራፍ ፮</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ይህ የተደነቀ ነው፡፡ በሁሉም ዘንድ መንክር ነው፡፡ በአምላክ ዘንድ ግን አይደነቅም፡፡

፪. በሰው ልጆች ዘንድ የተደነቀ ነው፡፡ ምሕረቱ እንደ ባሕር በሆነው ዘንድ ግን አይደነቅም በፍጡር ዘንድ ድንቅ ነው በፈጣሪ ዘንድ ግን አይደነቅም፡፡

፫. ድንግል ሆይ የኔ ምሕረት በልጅሽ ዘንድ ስላንቺ አይደነቅም ስለ ስምሽም የኔ ይቅር መባል በልጅሽ ዘንድ አይደነቅም ስለ ጸሎትሽም የኔን ኃጢአት ማቀለል በልጅሽ ዘንድ አይደነቅም፡፡

፬. ስለ ልመናሽም የኔን ዕዳ በደል ማቅለል በልጅሽ ዘንድ አይደነቅም ባንቺ እታመናለሁ፡፡ በዚህ ዓለም ከፀብ ከክርክር ከሞት ታድኝኝ ዘንድ በሚመጣውም ዓለም ማዕበል ሞገድ ከሚፈላው የእሳት ባሕር ታድኝኝ ዘንድ፡፡

፭. ድንግል ሆይ እታመንሻለሁ ከተሠወረው መከራ በግልጽም ከሚመጣብኝ ጥፋት ሁሉ በዚህ ዓለም እንድታድኝኝ በሚመጣውም ዓለም ከገሃነመ እሳት ጥርስ ማፋጨት ጽኑ ልቅሶም ካለበት ከሚያስጨንቅ መቅሠፍት ትሠውሪኝ ዘንድ እኔም ባንቺ አማላጅነት በልጅሽም ምሕረት የታመንሁ ነኝ፡፡ በፈረሰኞች ሰልፍ በሠረገላም መንኮራኩር የምታመን አይደለሁም፡፡ ባንቺና በልጅሽ ብቻ እታመናለሁ እንጂ፡፡

፮. ሰይፍ በማስለት ፍላፃ በማትባት ጦር በመወርወር ቀስት በመገተር የምታመን አይደለሁም በጸሎትሽ ረዳትነት በልጅሽ ብርታት እታመናለሁ እንጂ፡፡

፯. በመዝሙር እንደተባለ በቀስቴ የምታመን አይደለም ጦሬም አላዳነኝም ከቀኝ ከፊትህ ብርሃን በቀር ደግሞ እንዲህ አለ የፈረስ ኃይል አይፈቅድም፡፡ በሰው ጭንም ደስ አይለውም እግዚአብሔርን በሚፈሩትና ቸርነቱን ደጅ በሚጸኑ ደስ ይለዋል እንጂ፡፡ ነፍሴ በእግዚአብሔር ታመነች ከጧት እስከ ሌሊት እስራኤል በእግዚአብሔር ታመን፡፡ መዝ ፻፴፩ ፣ ፫ ፣ ፻፵፮ ፣ ፲፩ ፣ ፲፪፡፡

## ምዕራፍ ፮

፩. ትውክልቴን ማልማትና ማጥፋት መግደልና ማዳን በማይችሉ አማልክት ከአምላኮችም ልዩ በሆኑ ጣዖታት ያላደረገብኝ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፡፡

፪. የአሕዛብ የወርቅና የብር አማልክት በሰው እጅ የተሠሩ ናቸው አፍ አላቸው አይናገሩም እንጂ ዓይን አላቸው አያዩም፡፡ ጆሮ አላቸው አይሰሙም አፍንጫ አላቸው አያሸቱም እጅ አላቸው አይዳስሱም እግር አላቸው አይሔዱም በጉረሮቸውም አይናገሩም ባፋቸውም ትንፋሽ የለም የሠሯቸውም የሚያምኑባቸውም እንደርሳቸው ይሁኑ፡፡ (መዝ ፻፲፭ ፣ ፬ ፣ ፰)

፫. ሰማይን የሰማያትን ሰማይ በውስጣቸው ያሉትንም ሁሉ የሚያመልክ ርጉም ነው፡፡ ምድርንም በውስጧ የሚኖሩትን ሁሉ ባሕሩን ወንዙን ምንጩንም ሁሉ በውስጣቸው ያሉትንም ሁሉ የሚያመልክ ርጉም ነው፡፡ (ዘሌዋ ፳፮ ፣ ፩)

፬. እሳቱን ነፋሱን ብርሃኑን ጨለውውን ከርሳቸውም የተፈጠሩትን ሁሉ ፀሐይ ጨረቃን የሰማይንም ክዋክብት ሁሉ ደመናትን በአየርም ያለውን ሁሉ ይህንን ሁሉ የሚያመልክ የሚሰግድላቸውም እግዚአብሔርን ብቻ ከሚያመልክ በቀር የተረገመ ርጉም ይሁን፡፡

፭. ድንግል ሆይ እኔ ግን ልጅሽን በማምለክ በባሕርይ አባቱም በአብ በባሕርይ ሕይወቱም በመንፈስ ቅዱስ አምኜ ደስ እሰኛለሁ ለሦስትነቱ አንድ ስግደት እየሰገድሁ እመካበታለሁ እንዲህ ስል፡፡

፮. አምላኬ ነው አመሰግነዋለሁ ያባቶቼም አምላክ ነው አከብረዋለሁ አገነዋለሁ ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ፡፡ እግዚአብሔር ፀብ ክርክርን ይሰብራል፡፡ ስሙም እግዚአብሔር ነው፡፡ ደግሞ እንዲህ

እላለሁ (ዘፀአት ፲፰ ፣ ፪ ፣ ፫)

፯. እንደ አምላካችን ያለ ታላቅ አምላክ ማነው፡፡ ይህንንም የመለኮት ሰይፍ ተቀብዬ የሰይጣንን ራሱን አቆርጠዋለሁ፡፡ ይህንንም የሃይማኖት በትር ተመርኩዤ የአባቡን (የዲያብሎስን) ራሱን እቀጠቅጠዋለሁ፡፡

፰. የምስጋናውንም ጽዋ ከጽርሐ አርአያም ቀድቼ ከቤትሽ አፈሳለሁ፡፡ ከትንቢት ቃል ጋራ እንዲህ እላለሁ፡፡ ከሞት ደጅ ከፍ ከፍ የሚያደርገኝ በጽዮን ልጅ ደጅ ምስጋናውን ሁሉ እናገር ዘንድ፡፡

፱. ዳግመኛም እንዲህ እላለሁ፡፡ በጽዮን ምስጋና ላንተ ይገባል በኢየሩሳሌም ጸሎት ላንተ ነው፡፡

## <u>ምዕራፍ ፰</u>

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ከነቢያት አንደበት ምን ያህል ምስጋና ተቀዳብሽ ለእግዚአብሔር ምን ያህል ቁርባን ባንቺ ተሰጠ፡፡ ከመሃይምናንስ ሁሉ አንደበት ምን ያህል ጸሎት ባንቺ ስም አማላጅነት ተላከ፡፡

፪. ድንግል ሆይ የጸባዖት እግዚአብሔር እናት ድንግል ሆይ የእስራኤል አምላክ የእግዚአብሔር እናት ለምኝልኝ እግዚአብሔርን በለመንሁት ነገር ሁሉ ዋጋዬን ያጣሁ ተስፋ የቆረጽሁ እንዳልሆን፡፡

፫. በተቃጠለ ፍቅርም እንደ ፀራሁሽ አንቺ ደግሞ በተቃጠለ አሳብ ልቡናዬ ስለ አሰበው ነገር ለምኚልኝ፡፡ ግዳጄን አቅኝልኝ፡፡ የአዳምና የአቤልን የሴትና የሄኖስ በረከት የሌሎችም አባቶች ሁሉ በረከት እንዲያርፍብኝ፡፡

፬. የሄኖክና የኖኅ የሴምም የተመረፁትም በረከት የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብ የእግዚአብሔርም የገነት ዕንጨቶች የተባሉ ሁሉ በረከት የእግዚአብሔርም ሕዝብ የተባሉት የዘሮቻቸው በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፭. የሙሴና የአሮን የኢያሱም በረከት የከበሩትም መሳፍንት ሁሉ በረከት የሄኖክና የኤልያስ የዕዝራ በብሔረ ሕያዋንም ያሉት በረከት የዳዊትና የሰሎሞን የሲራክና የኢዮብ የጠቢባንም በረከት የኢሳይያስና የኤርምያስ የሕዝቅኤል የነቢያትም ሁሉ በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፮. የጴጥሮስና የጳውሎስ የሐዋርያትም ሁሉ በረከት የመጥምቁ ዮሐንስ የወንጌላዊውም ዮሐንስ የንጹሓን ደናግልም ሁሉ በረከት የእስጢፋኖስና የቅዱስ ጊዮርጊስ የፋሲለደስና የዮስጦስ፡፡ የምሥራቃዊው ቴዎድሮስና የሠራዊት አለቃ ቴዎድሮስ የገላውዴዎስ የፊቅጦር በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፯. የአባ ኪሮስና የአባ ኪሩኮስ የአባ በርሱማና የአባ ብሶይ የአባ አሞኒም የአባ አሳይና የአባ አርሳኒ በረከት የአባ ለትጹንና የአባ አቡናፍር የመክሲሞስና የደማቴዎስ በረከት የእስክንድርያው መቃርስና የሶሪያው መቃርስ በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፰. የበኪሞስና የዮሐንስ ያባ ዳንኤልና የአባ ኤዎስጣቴዎስ የአቡነ ተክለሃይማኖትና የአባ መድኃኒነ እግዚእ የሳሙኤል የዋልድባው በረከት የአባ አረጋዊና የሃሌ ሉያ ደብር አባ ሳሙኤል በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፱. የአባ አሌፍና የአባ ጽሕማ የአባ አፍፂና የአባ ገሪማ የአባ ጉባና የአባ ይምዓታ የአባ ሊቃኖስና የአባ ጰንጠሌዎን የአባ ጰንጹልዮንና የአባ መጣዕ በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኚልኝ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፲. የቀልሞን ደብር የአባ ሳሙኤል በየዋሻውም ያሉት ሁሉ ቅዱሳን በረከት የአባ ዮሐኒና የቅዱስ አባ ጊዮርጊስ በረከት እንዲያርፍብኝ አምኝልኝ፡፡

፲፩. የፀሥራ አራቱ እልፍ ካራት ሽህ ሄሮድስ ያስፈጃቸው ሕጻናት በረከት የመርምህናምና የአርባዓ ሐራ ሰማይ በረከት የሰማዕታተ ናግራን በረከት እንዲያርፍብኝ አምኝልኝ፡፡

## ምዕራፍ ፱

፩. በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ የዮሐንስ አፈወርቅና የቅዱስ ቄርቆስ በረከት የሳዊሮስና የኤጲፋንዮስ የባስልዮስና የጎርጎርዮስ የሊቃነ ጳጳሳትና የጳጳሳት የሴጲስ ቆጶሳትና የቀሳውስት ሃይማኖታቸውም የቀና መምህራን ሁሉ በረከት የዲያቆናት በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፪. የጻድቃን የሰማዕታት በረከት የደናግል የመነኮሳት በረከት የሕፃናቱ የሽማግሎቹ በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ የሚካኤልና የገብርኤል የሱራፌልና የኪሩቤል የዑራኤልና የሩፋኤል የሳቁኤልም በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፫. የሱርያልና የፋኑኤል የራጉኤልና የአፍኒን የሰማይም መላእክት ሁሉ በረከት የ፬ቱ እንስሳ የ፳፬ ካህናተ ሰማይ በረከት የመላእክትም ማህበር ሁሉ በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፬. የሔዋን በረከት የሣራና የርብቃ በረከት የኤልሳቤጥ በረከት የሶፍያ የአርሴማ የበርባራ የዳናና የዲቦራ የአስቴርና የዮዲት የሰሎሜና የማርያም መግደላዊት የማርያም እንተ ዕፍረት በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፭. የአርሶንያና የጽራግያ በረከት የጤቅላ ሐዋርያትንም ያገለገሉ ሴቶች ሁሉ በረከት የንግሥት ሶፍያ የሦስቱ ልጆቿም የጲስና ያላጲስ የአጋጲስ በረከት እንዲያርፍብኝ ለምኝልኝ፡፡

፮. የጣጡስና የዕንባብሬና የዮልያናም የኦሪናና የመሪና የኢየሉጣና የቴክላ ያገለገሉ ደናግል ሁሉ በረከት የሁለቱ ሰንበታት የቅድስት ቤተክርስቲያን በረከት የሥጋውና ደሙ በረከት የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ በረከት ያንቺም በረከት ባገልጋይሽ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላይ ይኑር ለዘለዓለም በውነት ያለ ሐሰት ይሁን አሜን፡፡

www.ethiopianorthodox.org